# እሪበል የጎንደር ትውልድ!

## ከአማረ አፈለ ብሻው

P.O.BOX 492 SEATTLE.WA 98111.U.S.A.

መጋቢት 12 ቀን 2007 ዓም

### ማውጫ!

## ክፍል አንድ

ምዕራፍ 1 መታሰቢያ፤ምስጋና ገጽ 2-3
ምዕራፍ 2 ፈር አስጨባጭ ገጽ 4-9
ምዕራፍ 3 አጭር የኢትዮጵያ ታሪክ ገጽ 10-12
ምዕራፍ 4 ሕገ-ልቦና የኢትዮጵያ የሃይማኖት ቅርስ ነው ገጽ 1-16
ምዕራፍ 5 ወያኔና አቶ ነጋ ጌጤ 1983 ዓም ግንኙነት ገጽ 17-19
ምዕራፍ 6 የኢትዮጵያ ነገሥታ ጣዖት አላመለኩም ገጽ 20-22
ምዕራፍ 7 ቅማንት ጎንደሬ እንጂ ከትግራይ የመጣ አይደለም፤ገጽ 23-24
ምዕራፍ 8 የቅማንት ሕዝብ ክርስትናን በግድ አልተጠቀም፤ገጽ 25-32

## ክፍል ሁለት

ምዕራፍ 1 ትግራይ የተወለዱ ኢትዮጵያን በ1761 አፈረሱ ገጽ 33-35
ምዕራፍ 2 ኢትዮጵያን ለመገንባት የተደረገው ጥረት ገጽ 36-37
ምዕራፍ 3 ትግራይ የተወለዱ ኢትዮጵያን በ1983 አፈረሱ ገጽ 38-45
ምዕራፍ 4 ወያኔ እንደራስ ስሁል ቤተ ክርስቲያሰንን አደማ ገጽ 46-48
ምዕራፍ 5 ትግራይ የተወለዱ ለሥልጣን ሲሉ አገር ሸጡ ገጽ 49-52
ምዕራፍ 6 ወያኔ ሆዳም ስደተኛን በጥቅም ያዘው ገጽ 53-56
ምዕራፍ 7 ወያኔ ስደተኛ ቤተ ክርስቲያን ሊያፈርስ ነው ገጽ 57-60
ምዕራፍ 8 ኢሳ 12፤11“የትዕቢተኞችንም ኩራት እሽራለሁ”ገጽ 61-68

## ክፍል ሦስት

ምዕራፍ 1 አቶ ነጋ ጌጤ የወያኔ መጠቀሚያ ሁነዋል ገጽ 69-70
ምዕራፍ 2 ወያኔ በጎንደር ላይ የፈጸመው አረመኔነት ገጽ 71-76
ምዕራፍ 3 ቅማንትና አማራን ለመለያየት የተደረገው ጥረት ገጽ 77-81
ምዕራፍ 4 ጎንደሬው የመጣውን ሁሉ በጋራ አሳልፎታል ገጽ 82-87
ምዕራፍ 5 ወያኔ ቅማንት የለም ብሎ ካደ! ገጽ 88-93
ምዕራፍ 6 ምሳ26፤22“የጆሮ ጠቢ ቃል እንደጣፋጭ መብል ነው”ገጽ 94-97
ምዕራፍ 7 ጎንደሬ አትበገር ለወያኔ ገጽ 98-101

# ክፍል አንድ

## ምዕራፍ 1

## መታሰቢያ

ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሮሜ መልዕክቱ 15፤5“በአንድ ልብ ሆናችሁ በአንድ አፍ እግዚአብሔርን እርሱም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ታከብሩ ዘንድ የትዕግሥትና የመጽናናት አምላክ እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ ፈቃድ እርስ በርሳችሁ በአንድ አሳብ መሆንን ይስጣችሁ”ባለው መሠረት ለአንድ ዓላማ የቆማችሁ ሁሉ የእግዚአብሔር በረከት አይለያችሁና እሪበል የጎንደር ትውልድ የምትለው መጽሐፍ መታሰቢያነቷ፤ቅድሚያ ለኢትዮጵያ አንድነት ለተዋደቁ ኢትዮጵያውያን፤እንዲሁም ደግሞ በወያኔ ለተገደሉ፤ቁጥራቸው ላልታወቀው ኢትዮጵያውያን በሙሉ፤አብሰም በአማራነታቸው ለተገደሉት፤በጎንደር ክፍለ ሀገር በወገራ አውራጃና በወልቃይት ጠገዴ፤በሰሜን አውራጃ በጠለምት በወሎ ክፍለ ሀገር በራያና አላማጣ በአሸንጌና በሌሎች ወረዳዎች ትግራይ ናችሁ ሲባሉ ትግራይ አይደለነም በማለታቸው ለተፈጁት ሁሉ!

በሰኔ 1983 ዓም ወያኔ ሦስት የቅማንት ልጆችን ይዞ ቅስቀሳ መጀመሩን የሰሙ አዛውንቶች“ በንብ ግዜ ዝምብ ይናከሳል፤የኢትዮጵያ ሁኔታ ችግር ላይ በወደቀበት ሰዓት እኛን ተባባሪ ለማድረግ የታሰበው ሴራ ነው!ከወገኖቻችን ጋር አትከፋፍሉን” ሳሉና ለጎንደር ሕዝብ አንድነት ጥረት ሳደረጉ እነርሱ ከዚህ ዓለም በመለየታቸው ምክንያት የፈሩት አልቀረም:: ቢሆንም ግን መልካም ስም ከመቃብር በላይ ነውና ለብዙ የቅማንት አባቶች ሞረሾች::

ሌላው አሁን ወያኔ ባሴረው ሴራ ቅማንት የለም በማለቱ ምክንያት መብል ለማስከበር ተብሎ የተወሰኑት ጥቂት የቅማንት ተወላጆች የራስን ማስተዳደር ጥያቄ ሲያነሱ ብዙሐኑ የቅማንት ሕዝብ ትክክል አይደለም ሲሉ ብዙዎቹ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ተጋጭተዋል:: ከአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በውጭ አገር በስደት የሚገኙት የቅማንት ልጆች ከአገር ቤት ያለው ጥያቄ ትክክል አይደለም ብለው ለተነሱትና ወገኖቻቸውን ጎንደሮችን ሰብስብ አድርገው“ የጎንደር ሕብረት”ድርጅት ለፈጠሩት ለቅማትን ልጆች፤በመቀጠልም ሌሎች ጎንደሮች እሪታውን ሰምተው ለተሰበሰቡት ሁሉ፤ የምትደክሙት ድካም የጎንደር ሕዝብ አንድነት እንዲኖረው ስላሰባችሁ ነው::
መክብብ 4፤9“ድካማቸው መልካም ዋጋ አለውና፤አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል፤ቢወድቁ አንዱ ሁለተኛውን ያነሣዋልና አንዱ ብቻውን ሆኖ በወደቀ ጊዜ ግን የሚያነሣው ሁለተኛ የለውምና ዎዮለት”የሚለውን በማያዝ እሪ በል ጎንደር ብለው ላሰባሰቡ ሁሉ፤እንዲሁም ከዚህ ዓለም ለተለየው ለአቶ ደረጀ ብርሌ፤ ይች እሪበል የጎንደር ትውልድ የምትለውን መጽሐፍ መታሰቢያ ስሰጣችሁ ከፍ ባለ አክብሮት ነው::

# ምስግና!

መጽሐፈ ሲራክ 12፤2"ለውነተኛ ሰው ሥራ ዋጋህን፤ ታገኛለህ፤በሱ ዘንድ ባታገኘው በፈጣሪው ዘንድ ዋጋህን ታገኛለህ" ባለው መሠረት ቅዱስ መጽሐፍ ለእውነት የቆመ ሁሉ ዋጋ አለው:: በኢትዮጵያ በገጠሪቱ ሀገራችን ሰው ችግር ሲደርስበት "እሪ"ይላል:: እሪታው ድረሱልኝ!ሕይዎቴ አደጋ ላይ ነው ማለት ነው:: ስለዚህ እሪታውን የሰማው ሁሉ ጩኸት ወደሚሰማበት ቦታ ይነጉዳል፤ የተፈጠረውን ችግር መገላገል ከሆነ ይገለግላል ዘራፊ ሽፍታ ከሆነ ሽፍታውን ያባርራል:: ሁሉንም ሕዝቡ አብሮ በጋራ ይወጠዋል:: ይህ ጥሪ ባህላዊና አገራዊ ጥሪ ነው:: ወያኔ ጎንደርን ከዚህ በፊት እንደዘረፈው ሁሉ አሁንም ሊዘርፍና በሕዝቡ ላይ እሳቱን ለማንደድ እያቀጣጠለው ይገኛል::

ወያኔ ለዘመናት አብሮ የኖረውን ሕዝብ አንዱን ነገድ ከአንዱ ነገድ ጋር ሲያጣላ መኖሩ ይታወቃል:: በጎንደር ክፍለ ሀገር ብዙ ነገዶች ይኖራሉ:: ከነዚህም መካከል አንዱ የቅማንት ነገድ ነው:: የቅማንትን ነገድ ወያኔ በሰኔ 1983 ዓም ጀምሮ በፈለገው መንገድ ሊያደራጅ ሞክሮ አልተሳካለትም:: ያሰበው ስላልተሳካለት ተበሳጭቶ "ቅማንት የሚባል ብሔረሰብ የለም" ብሎ ሲክድ ተወላጆች" ቅማንትማ አለ" ብለው መደራጀት ሲጀምሩ አንቀጽ 39ኝ ተቀበሉ ሲባል ቀስ በቀስ" የቅማንት ብሔረሰብ የማንነትና የራስ አስተዳደር" ብለው ሲነሱ ወያኔ ከልቡ ተደሰተ:: ይህ የቅማንት የራስ አስተዳደር መለየት ለጎንደር ሆነ ለቅማንት ሕዝብ አይጠቅም ብለው የቅማንት ልጆች ተነሱ:: በዚህ ምክንያት "እሪ በል ጎንደር" ብለው የክፍለ ሀገሩን ተወላጆች ጥሪ አቀረቡ::

ጥሪውን የተቀበሉ የጎንደር ክፍለ ሀገር ተወላጆች በ7ቱ አውራጃ በ32ቱ ወረዳ በ119 ምክትል ወረዳ እሪታውን ሰምተው የተቀጣጠለውን እሳት ለማጥፋት ዘራፊውን ለማሳፈር ለተሰባሰቡት ሁሉ አመሰግናለሁ:: ሌላው ይህን መጽሐፍ እንድጽፍ ያበረታቱኝን የጎንደር ክፍለ ሀገር ተወላጆች ከእጁ ያልገባውን ሠነድ በመላክ ምክር በመለገስ የተባበራችሁኝን ከልብ አመሰግናለሁ:: ጎንደር የሚኖሩ ባልንጀሮቼ ጎንደር ውስጥ የሚፈጠረውን ዘግበው የሚልኩልኝን የቅማንት ልጆች ወንድሞቼን አመሰግናለሁ:: ከዚህ መጽሔፍ ስም ጠቅሼ ማመስገን አልፈለኩም ነበር:: ነገር ግን አቶ ጌታቸው ረዳ፤ከፍ ያለ ድጋፍ ስላደረጉልኝ ከልብ አመሰግናቸዋለሁ::

# ምዕራፍ 2

## ፈር አስጨባጭ!

ሕዳር 27 ቀን 2007 ዓም ቅዳሜ፤ከስራ ስወጣ ስልኬ ብዙ መልዕክት ተቀብሏል መልዕክቱን አዳምጬ ወደ ጹሑፍ መቀበያው ጣቴን ስልከው የማውቀውና የማላውቀው ስልክ የጹሑፍ መልዕክት አገኘሁ:: ጎንደርን አስመልክቶ በቴሌ ኮንፍረንስ ስብሰባ እንድትገቡ የሚል:: ሕዳር 28 ቀን 2007 ዓም እሁድ ስራ ስለሆኑኩኝ የምሳ ሰዓቴን ተጠቅሜ ለግማሽ ሰዓት ከቴሌ ኮንፍረንሱ ስብሰባ ገብቼ አዳምጫለሁ:: ምሳሌ 15፤4“ፈዋሽ ምላስ የሕይዎት ዛፍ ነው”ባለው መሠረት በአቶ በየነ አስማረ የቀረበውን ፈዋሽ ዘገባ ሪፖርት አድምጬ ሳልጨርሰው የስራ ሰዓቴ በመድረሱ እንጀራ ሆነና ስራ ገባሁ:: ስራው አልተሰራኝም በጣም ተሰማኝ ግን ደግሞ ክርስቲያን ተስፋ አይቆርጥም አልኩኝ:: ምክንያቱም የአቶ በየነ አስማረን ዘገባ ሪፖርት ያቀረበ የቅማንት ልጅ የቁርጥ ቀን መኖሩን በመስማቴ::

ከስራ ስወጣ ስልኬን ሳየው ብዙ መዕክት ይዟል:: መልዕክቱ መጣጥፍ አዘጋጅ የሚል ነበር:: ሌላው ወዳጄ የአሪት አማኝ ከተላቪብ እስራኤል ሰኞ ሕዳር 29 ቀን 2007 ዓም ስልክ ሲመታ ስራ ላይ ነበርኩኝ:: እርሱ ሲያጣኝ የድምጻዊ ፋሲል ደመወዝን ዜማ ከስልኬ ላይ ቀድቶት አገኘሁት:: ያም “እነሱ ምን ያርጉ ከኛ ሰው ሲታጣ” የሚለውን ዘፈን:: ማክሰኞ ሕዳር 30 ቀን 2007 ዓም ስልክ ስመታለት “ምነው ጎንደር በኛ ግዜ ስትከፋፈል ዝም ይባላል” ብሎ ያለቅስ ጀመር:: ይህ የአሪት አማኝ ፈላሻ ወንድሜ የአይከል ከተማ ልጅ በመሆኑ የሚያውቀውን ብዙ ብዙ ታሪክ ነገረኝ ሌላው ዋሽንግተን ዲሲ የሚኖር አዛውንት ታህሳስ 2 ቀን 2007 ዓም ስልክ መትተው መጣጥፍ አዘጋጅ አሉኝ::

ይህ በዚህ እንዳለ ታህሳስ 10 ቀን 2007 ዓም ከጎንደር ባልንጀሮቼ ደጋግመው ስልክ ደውሎ መዝጋት ጀመሩ:: ኢትዮጵያ ያለ ሰው ደውሎ ከዘጋ አንተው ደውልልኝ ማለታቸው ነው የተለመደ ፊሊፐ:: እኔም ስለማውቀው ወደነሱ ደወልኩኝ:: የቅማንት ልጆች ባልንጀሮቼ በአሁኑ ሰዓት ጎንደር ላይ እየተደረገ ያለውን ስልኩ እንዳይጠለፍ በጥንቃቄ አስረዱኝ:: ቃሉም “ለምን እስካሁን ዝም አልክ? ደብዳቤ ጻፍልን፤እኛም ችግር ላይ ነን፤የምንነግድበት ገንዘብ እጥረት አለብንና ችግራችን ዘርዝረን እንጽፋለን”የሚል ነበር:: ከዚህ በፊት የምንግባባበት ቋንቋችን በመሆኑ ተረድቶኛል:: እነሱም ቃል በገቡት መሠረት ከመጀመርያው ጀምሮ አጠናቅረው ላኩልኝ:: ደብዳቤያቸው ክፍል ሦስት ምዕራፍ ሁለት በአጭር ቀርቦአል ይነበባል::

ከዚህ በመቀጠል አሜሪካን ያሉ የቅማንት ባልንጀሮቼ ታህሳስ 15 ቀን 2007 ዓም ስልክ ደውለው መጣጥፍ አዘጋጅ አሉኝ:: እኔም “ጋኖች አለቁና ምንቸቶች

ጋን ሆኑ" ይላሉ አባቶቻችን። ሌሎች ብዙ ብዙ የጎንደር ምሁራን ሊቆች ዝም አሉና እኔ ጻፍ ስባል ጎንደር ባድማ ሆነ እንዴ?አልኩኝ። ትንቢተ ኢሳያስ 1፤21“ ፍርድ ሞልቶባት የነበረ የታመነችይቱ ከተማ እንዴት ጋለሞታ ሆነች፤ ጻድቅ አድሮባት ነበር፤አሁን ግን ገዳዮች አሉ”ባለው መሠረት ጎንደር ልትጠፋ የተቃረበች ክፍለ ሀገር ሆነች ብዬ አዘንኩኝ። ምክንያቱም ነገሥታቷ እምነት ያላቸው ጻድቃንና ደግ ነበሩ። ከነዚህም መካከል ንጉሠ ነገሥት 1ኛው አጤ ኢያሱና ጻድቁ ዮሐንስ ተጠቃሽ ናቸው።

ወዴት ሄዶ ኖሯል ሰሞነኛው ቄሱ
ታቦት ተሸከመ ዘውዱን ትቶ ኢያሱ
የተሸከመውን የአባቱን ቅስና
ገለጠው ኢያሱ ታቦት አነሣና
አየነው ኢያሱን ደብረ ብርሃን ቆሞ
ከኪሩቤል ጋራ ሦስቱን ተሸክሞ
ሰውነቱን ትቶ መልአክ ሆነ ደግሞ
ሥላሴን ቢሸከም ኢያሱ ገነነ
ላራቱ ኪሩቤል አምስተኛ ሆነ

ተብሎ ተገጥሞላቸው የነበሩ ነገሥታት የተወለዱበት ጎንደር፤የነአጤ ፋሲል፤ የነአጤ በካፋና 2ኛ ኢያሱ አገር፤የጻድቁ አጤ ዮሐንስ፤የአጤ ቴዎድሮስ አገር እንዲህ በሰው ደኸየች?የሊቅ ዶ/ር አየለ ዓለሙ አገር፤የነአለቃ ገብረሃና አገር፤ ሆነ ባድማ?ያም ሆነ ይህ ሰሚና አንባቢ ካለ ብዬ ይህን እሪበል የጎንደር ትውልድ ያልኩትን መጽሐፍ አዘጋጀሁ። ምሳሌ 9፤8“ፌዘኛን አትገሥጽ እንዳይጠላህ፤ጠቢብን ገሥጽ ይወድድሃማል” ይላል ቅዱስ መጽሐፍ፤ ይህ እሪ በል የጎንደር ትውልድ ብዬ የጻፍኩት መጽሐፍ ትግሣጽና የምክር የታሪክ ነው። በነገራችን ላይ እሪበል የጎንደር ትውልድ ብዬ መጻፍ ስጀምር ተጨንቄ ነበር። ምክንያቱም ወላጆቻችን ጎንደሮች ማስቀደም ያለብን ኢትዮጵያን መሆኑን አስተምረውናል።

እንደኔ በገጠር ከእድሜ ጠገብ አዛውንቶች ጋር ካደጋችሁ በክፍለ ሀገር ብቻ መጠራት ውርደት መሆኑን ትረዱ ይሆናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ይህን መጽሐፍ ልጽፍ ስል ትዝ ያሉኝ አያቴ እማሆይ የሹሜ ወርቄ ወልደተሌ ያሪድ፤ ናቸው። ከአራት ዓመቴ እስከ አስራ ሁለት አመቴ ያሳደጉኝ አያቴ ስለሆኑ እርሳቸው የጋቱኝ የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፍቅርና የኢትዮጵያን ፍቅር ስለሆነ እሪበል የጎንደር ትውልድ የሚለውን ለመጻፍ ጀምሬ ውስጤን ሰላም ነሳው። ከአእምሮዬ ጋር በክርክር ሰንብቼ ሳልወድ በግድ መጽሐፍ ለመጻፍ ወሰንኩኝ።

ይህ መጽሐፍ መጀመርያ ስጀምረው በራሪ ወረቀት ማለትም ከ1-4ገጽ የሆነ ነበር። ከጀመርኩት በኋላ ዳጎስ ያለ መጣጥፍ 64 ገጽ በታች እንዲሆን ነበር። ነገር ግን ወያኔ በጎንደር ሕዝብ ላይ ያደረሰውን ገበና መዘርዘር ስጀምር እንኳን በመጣጥፍ በአንድ መጽሐፍ የሚገለጽ አይደለም። ምክንያቱም ወያኔ አንዱን ነገድ ከአንዱ ነገድ አንዱን ሃይማኖት ከአንዱ ሃይማኖት ጋር እንዲላተም አድርጎታል። በነገራችን ላይ ወያኔ በጎንደር ሕዝብ ላይ ብቻ በድሏል ማለት

አይደለም:: ወያኔ ሲነሳ ጀምሮ ደም ማፍሰስ የጀመረው ትግራይ ነው:: ከዚያም በጎንደርና በወሎ፤በሸዋና በጎጃም ደም አፍስሶ መላ ኢትዮጵያን ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም ሲይዝ ደም ያላፈሰሰበት ክፍለ ሀገርና ነገድ አለ ሊባል አይችልም:: በሁሉም ክፍለ ሀገርና በሁሉም ነገድ ላይ ደም ያላፈሰሰበት ቦታ የለም:: ይህ እሪበል የጎንደር ትውልድ ብዬ ያዘጋጀሁት መጽሐፍ የተጻፈበት በሁለት ምክንያት ነው::

1ኛ ለኢትዮጵያ ውድቀትና ለኢትዮጵያ ሕዝብ መከፋፈል ጥርጊያ መንገድ የከፈተው ወያኔ በመሆኑ፤የእርሱን እኩይ ተግባር ለማጋለጥ!ሲሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሚያውቀው የተለየ አዲስ ታሪክ ለማቅረብ ባይሆንም እንኳ ይህ መጽሐፍ የወያኔን ተንኮል ይገልጻል:: ወያኔ በሌሎች ክፍለ ሀገራት ውስጥ ያሉትን ነገዶች ነካክቶ በያካባቢያቸው ችግር እንዲፈጥሩ ያደርጋል:: ትግራይ ውስጥ ግን የነገድ ችግር ሲፈጠር አላየሁም:: አሁን ወያኔ ትግራይ ውስጥ አንድ ወጥ የሆነ ነገድ ያለ አስመስሎ ይሰብካል:: የዛሬ 39 ዓመት ላይ የጻፈው ማኒፌስቶ ግን በትግራይ ክፍለ ሀገር ውስጥ ብዙ ነገዶች መኖራቸውን ነው::

<u>የሕወሓት ማኒፌስቶ</u> 1968 ዓም "ይህ መጽሔት የትግራይ ሕዝብ ሀቀኛ ልጅ የሆነው የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭ ድርጅት (ተ.ኃ.ህ/ት)መግለጫና የትግል መመርያ ነው:: የትግራይ ሕዝብ ማለት በትግራይ ውስጥ የሚኖሩትንና በተለያዩ ምክንያት ከትግራይ መሬት ውጭ የሚኖሩትንና ሕዝቦች በሙሉ ያጠቃለለ ነው:: (ትግርኛ ተናጋሪዎች አፋር (ጠልጣል)አገው፤ሳሆ፤ኩናማ፤ወዘተ "ይላል:: ትግራይ ውስጥ ራሱ ወያኔ በየካቲት 1968 ዓም የመሰከረው ከላይ የተጠቀሱት ነገዶች ትግራይ ውስጥ መኖራቸውን ነው:: አሁን ግን የሚሰብክልን አንድ ወጥ መሆናቸውን ነው:: ትግራይ ውስጥ ይህን ያህል ነገድ ሲኖር ሁሉም አንድ መሆናቸውን አስመልክቶ ያላዝናል:: በሌሎች ክፍለ ሀገራት ግን በያንዳንዱ ትናንሽ ነገድ ሳይቀር እንዲደራጁ ምክር ይሰጣል:: ይህን ሌሎች የነገድ ደጋፊዎች እንድትረዱት ያስፈልጋል::

2ኛ የቅማንት አርቀ አሳቢ አዛውንቶች በሰኔ 1983 ዓም "በንብ ግዜ ዝምብ ይናከሳል:: አሁን ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ አስጊ ስለሆነ አርፋችሁ ተቀመጡ ፤ከወገኖቻችን ጋር አትከፋፍሉን" እንዳሉት ወያኔ ባቀደው ጎዳና ተሀዶ ከሚገኘው ጥቅም ጉዳቱ ይበልጣል!አሁንም በጥንቃቄ ይያዝ ለማለት ነው:: ከዚህ በመቀጠል የችግሩ መንስኤ የሆነው የአቶ ነጋ ጌጤን መጽሐፍ ስህተት ያልኩትን የተወሰኑትን ነጥቦች ጠቅሼ እተቻለሁ::

ወያኔ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ሕዝብ አብሶም፤በአማራውና በጎንደር ወልቃይት ሕዝብ የፈጸመው ወንጀል በዓለም ሕግ ፊት ያስከስሰው ነበር፤ምሁር የለም እንጂ ምሁርማ ቢኖር፤ወያኔ በዘር ማጥፋት ምክንያት መከሰስ ይገባ ነበር፤ግን ምሁራን የሉም:: አብሶም የአማራ ምሁራን የተፈጠሩበትን ሕዝብ ረስተዋል:: እኔ እንደሌሎች ምሁራን ጠባብ ይሁኑ ማለቴ አይደለም:: ግን ደግሞ በያካባቢያቸው የሚደርሰውን ጥፋት ማጋለጥ አለባቸው ብዬ አምናለሁ የአማራ ምሁራን ሆኑ የጎንደር ምሁራን የአቶ አባንግ ሚቶን ያህል አልታገሉም:: አቶ

አባንግ ሚቶ ለሕዝብ ቁመዋል:: ከእርሳቸው ምን ተማራችሁ?አጤ ቴዎድሮስ ፤ገብርየን፤ገለሞን፤እንግዳን ይዘው 30 ሽፍታ ገርፈዋል:: እውነታቸውን ነው" መማር እንደ አካልዬ አተካከስ እንደገብርዬ" ያሉት ለካስ ሌላው ዝባዝንኪ ስለሆነባቸው ነበር:: እኔም ለሕዝብ መቆም እንደ አባንግ ሜቶ ወንጌል መስበክ እንደ አባ ወልደትንሣኤ አያልነህ፤እውነት መናገር እንደ ገብረ መድኅን አርአያ ነው ብያለሁ::

ምሁራንማ ቀዝቃዛ ውሃ ተደፋባቸው? ከምሁራት ከያንያት ልቀዋል:: ምሁራት ዝም ሲሉ ነው ከላይ እንደጠቀስኩት ወዳጆቼ ወደኔ የመጡት:: የወልቃይት ሕዝብ ደም ፈሷል:: አሁንም እየባሰው እንጂ እየተሻለ አልመጣም:: በመስከረም 2007 ዓም ሲያርሱት የከረመውን ሰሊጥ ተቀምተዋል:: ከሞት የተረፉት አካባቢውን እንዲለቁ እየተደረገ ነው:: በስደት አገር በሄዱበት እየተገደሉ ናቸው:: ይህ የዘር ማጥፋት ዘመቻ ሲደረግ የሚያውቁትን እንኳ ለመናገር የማይፈቅዱ የታሪክ ተወቃሽ ብዙ አሉ:: በዚህ ዓለም ከፉው ነገር በታሪክ ተወቃሽ መሆን ነው:: ለጥቅም ብሎ በታሪክ ከመወቀስ አምላክ ያድናችሁ:: ክርስቲያን የሆናችሁ መጽሐፍ ቅዱስን ስታነቡ በከሀዲነት ከሚከሰሱት ግንባር ቀደም ይሁዳ ነው:: ይሁዳ ለጥቅም ብሎ ጌታውን በ30 ብር የሸጠ በመሆኑ እነሆ ዛሬ ድረስ በከሀዲነት ይጠቀሳል::

<u>ጥላ መጽሔት</u> የካቲት 2004 ዓም ገጽ 13 "የታሪክ ተወቃሽ ሆኖ ለትውልድ የማይሽር ጠባሣን መተው የሀሊና እዳ ነውና እዳ ያለባችሁ ለመክፈል ልትጥሩ ይገባል"ይላል መጽሔቱ:: ወያኔ ሁነው ሲያገለግሉ የነበሩ አቶ ገብረ መድህን አርአያ አሁን የግል እዳቸውን እየተወጡ ነው:: በእኛ በጎንደር ክፍለ ሀገር ለትውልድ እዳ ከሆኑት መካከል አቶ ነጋ ጌጤ አንዱ ናቸው:: የዚህ መጽሐፍ ዓላማው እርሳቸውን በግል ለመውቀስ ሳይሆን ጽፈው የተውት መጽሐፍ መርዘኛ ስለሆነ ስተች የእርሳቸው ደጋፊ የቅማንትን ሕዝብ እንደመቃወም አድርጋችሁ እንደማትወስዱት ተስፋ አደርጋለሁ::

አቶ ነጋ ጌጤንና የቅማንት ሕዝብ ለይተን ማየት አለብን:: በያንዳንዱ ነገድ ሳይሆን አንዲት እናት ከምትወልዳቸው ልጆች መካከል አንድ ሐቀኛ ሌላው እንኳን ለሕዝብ ሊሆን ቀርቶ የእናቱን ልጅ ወንድሙን ከሌሎች ጋር ሁኖ የሚያደማ ሞልቷል:: ለአንባቢ የምገልጸው ነገር ቢኖር አቶ ነጋ፤የቅማንትን ሕዝብ ቀርቶ ልጆቻቸውን አይወክሉም:: ሲወቀሱ እርሳቸውን ብቻ ናቸው የሚወቀሱት:: እርሳቸው ወያኔ "በል"ያላቸውን ያሉ መሆናቸውን ከሰኔ 1983 ዓም ጀምሮ ያለው ተግባራቸው ምስክር ነው:: እኔ በምፈጽመው መወቀስ ያለብኝ እኔ እንጂ ነገዴ ወይም ክፍለ ሀገሬ፤አልያም ደግሞ የተወለድኩበት ወረዳ፤ቀበሌ ወላጆቼ ሌሎች ቤተሰቦቼ መወቀስ የለባቸውም:: ቅድሚያ ይህን ጠንቅቀን ማወቅ አለብን::

ወያኔ የትግራይን ሕዝብ አይወክልም:: የትግራይ ሕዝብና ወያኔ በእኔ ብቻ ሳይሆን በብዙ ሚልዮን ኢትዮጵያውያን እምነት አንድ አይደሉም:: በእርግጥ የጥቅም ተቋዳሽ እንኳን ወያኔዎች ሌሎች ነገዶች ሁሉ በአሁኑ ሰዓት

ጸጉራቸው ይቆማል፤ሆዳቸው አምላካቸው በመሆኑ ነው:: አነግ ተሳስቷል ስንል አንዳንድ የኦሮሞ ልጆች ኦሮሞን የሰደብን አስመስለው ይመለከቱታል:: ለምሳሌ ዘሬን አሳምሬ የማውቀው እኔ ነኝ ግን አሁን አማራ ነህ ተብዬአለሁ:: ብአዴን ቢሰደብ አይከፋኝም:: ምክንያቱም ብአዴን የአማራ ሕዝብ ጥቅም የሚያስጠብቅ ሳይሆን የወያኔ ሎሌ ነው:: እኔ ብቻ ሳልሆን ሌሎች ብዙ የአማራ ተወላጆች የዚህ ዓይነት አመለካከት አለን:: ስለዚህ ወያኔ ሲወቀስ የትግራይ ሕዝብ አልተወቀሰም፤አነግ ሲወቀስ የኦሮሞ ሕዝብ አልተወቀሰም፤ ብአዴን ቢወቀስ የአማራ ሕዝብ አልተወቀሰም::

አቶ ነጋ ሆኑ አሁን "በቅማንት ብሔረሰብ የማንነትና የራስ አስተዳደር" የጠየቁት የቅማንት ነገድ ተወቀሰ ማለት አይደለም:: ሌሎችም እንዲሁ ናቸው የዚህ መጽሐፍ መነሻው የቅማንትን ሕዝብ ከወገኑ ጋር ለመለየት ብቻ ሳይሆን መሠረታዊ የሆነውን የቅማንት ማንነት በአቶ ነጋ ጌጤ መጽሐፍ ተደፍሯል:: ኢትዮጵያን ታሪክ ያዛባ በመሆኑ እኔ በማስረጃ መልስ እሰጣለሁ:: አንድ የተዛባ ታሪክ በወቅቱ መልስ መሰጠት ነበረበት:: ተንቆ ዝም የሚባል ከሆነ ውሎ አድሮ ታሪክ ይሆናል:: ለምሳሌ 3 መጽሐፍን ታሪክ ልጥቀስላችሁ:: አንድ አፍሪካን አሜሪካን ጸሐፊ ኢትዮጵያ ሕደው ስለ ጉራጌ ባህል መጽሐፍ ጽፈዋል:: ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ አንዱን የጉራጌ ነገድ ታሪክ አበላሽተው ጽፈዋል:: የተጻፈው ትክክል አይደለም ያሉት ተወላጆቹ ቅድሚያ ጸሐፊውን በአካል አግኝተው በራሱ እንዲያርመው ጠይቀው ሳይሳካላቸው ይቀራል::

ከዚህ በኋላ የተጻፈውን ጹሑፍ ተችተው ጽፈዋል:: ይህን ያደረጉት ታሪኩ ትክክል ሁኖ ባለማግኘታቸው ነው:: ሀተታውን ለማንበብ ዓለማየሁ ነሪ ውርጋሶ ኸሰት የባህልና የታሪክ መሠረት አንደኛ መጽሐፍ ተባለውን ይመልከቱ:: መምህር ገብረ ኪዳን ደስታ የትግራይ ሕዝብና የትምኪተኞች ሴራ ከትናንት እስከ ዛሬ የሚል መጽሐፍ ጽፈው የትግራይን ልጆች ከአማራው ትውልድ ጋር የሚያቃርን ጻፉ:: በዚህ ሰዓት ለትግራይ ትውልድ መርዝ መሆኑን የተረዱ አቶ ጌታቸው ረዳ ይድረስ ለጎጠኛ መምህር በሚል መጽሐፍ ጽፈው ታዳጊው የትግራይ ትውልድ ከአማራው ኢትዮጵያውያን ጋር እንዳይለያይ መክረዋል::

ወ/ሮ ሰናይት ኃይሌ <u>ጀግንነት ቢወረስ</u> በተባለ መጽሐፋቸው ገጽ 96 "የቅማንት ሕዝብ እንደማንኛውም አንዳንድ የኢትዮጵያ ክፍል ካለማወቅ የተነሳ ለጠላት አድሮ ነበር"ሲሉ ጽፈው ስለነበር በተወሰኑ ባንዶች ምክንያት ጠቅላላ የቅማንት ማህበረሰብ እኩል ስለተቼ ኮሎኔል አስናቀ እንግዳ ሸክም የማይከብደው ሕዝብ በተባለው መጽሐፍ ከገጽ 138-149 መልስ ጽፈዋል:: አቶ ነጋ ጌጤ የቅማንት ሕዝብ ታሪክ የሚል በ1993 ዓም ሲጽፉ ስህተቱን አልተቸነም:: ያም ሆነ ይህ ጎንደር ክፍለ ሀገር ብዙ ነገዶች አለንበት:: እኔም ሆንኩኝ ሌሎች ጎንደሮች የምናምነው አንድነታችን ነው:: ፍቅርና መግባባቱን ስመሰክር በዓይኔ አይቼ አብሬ ተቀምጬ በልቼ እንጂ ሰምቼ አይደለም:: ያን ሁሉ ነገድ በአንድ ጎንደሬነቱ፤አርቀ በማሰቡ እንጂ በልዩነት አላምንበትም:: የነገዱ ባህልና ማንነት መከበር እንዳለበት እምነቴ ነው:: ቆሮንጦስ 10፤31"እንግዲህ የምትበሉ ወይም

የምትጠጡ ብትሆኑ ወይም ማናቸውን ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት"ይላል:: ስለዚህ ለጎንደር ሕዝብ ክብር ለአገር ወዳድነቱ ለአንድነቱ ክብር ይሆን ዘንድ እምነቴ ነው::

ይህ እሪበል የጎንደር ትውልድ የተባለው መጽሐፉ ሦስት ክፍል 23 ምዕራፍ አለው:: በያንዳንዱ ምዕራፍ የታሪክ ጥቅስ ተወስዶበት የተጻፈ ሲሆን ጥቅስ ያልተወሰደበት ምዕራፍ ቢኖር ክፍል ሦስት ምዕራፍ ሁለት ብቻ ነው:: ምክንያቱም የታሪክ አጻጻፍን ለማሳየት ሲባል ነው:: ሌሎች ምዕራፎች ግን ሠነድ ተጠቅሶባቸው የተጻፉ ናቸው:: ለመጽሐፉ ጥቅስ ስወስድ ከብዙ ጹሁፍ ነው:: መጽሐፍት፤መጣጥፍና ከጋዜጣ፤መጽሔትና መግለጫ፤ደብዳቤና የምስል ድምጽ ቴሌቭዥንና የንፋስ ድምጽ ሬዲዮን በድረገጽ ከወጡት ጹሁፎች ሰብስብ አድርጌ ጽፌአለሁ:: ለምሳሌ ከ1-4ገጽ በራሪ ወረቀት ሲሆን፤ከ5-64 ገጽ መጣጥፍ ነው:: ከ65 ገጽ በላይ ከሆነ መጽሐፍ ይባላል:: ጥቅስ እስካልተወሰደ ድረስ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ነው::

አንድን መጽሐፉ የጸሐፊውን ስም ከጠቀስኩ በኋላ የመጽሐፉን ርዕስ ጽፌ አሰምርበታለሁ:: ከዚያም ገጹን ጽፌ የጥቅስ ምልክት ከከፈትኩኝ በኋላ መውሰድ ያለብኝን እወስድና የጥቅስ ምልክቱን እዘጋለሁ:: ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱስ <u>ትንቢተ ኢሳይያስ</u> 51፤11 "እነሆ እሳት የምታነድዱ የእሳትንም ወላፈን የምትታጠቁ ሁላችሁ በእሳታችሁ ነበልባል ባነደዳችሁትም ወላፈን ሂዱ ይህ ከእጄ ይሆንባችኋል"ይላል:: ለዚህ መጽሐፍ ጥቅስ ስወስድ በዚህ ዓይነት ጽፌ ነው:: አንድ መጽሐፍ ከተለያዩ ምዕራፎች ሊጠቀስ ይችላል:: አንዴ የጸሐፊው ስም ከተጠቀሰ በኋላ ሁለተኛ የመጽሐፉ ርዕስ እንጅ የጸሐፊው ስም አልጠቅስም:: መጽሐፉን ብቻ ስጠቅስ አይሰመርበትም:: የጸሐፉውን ማዕረግ በተመለከተ ጹሑፉ በወጣበት ማዕረግ ተጠቅሜ ጽፌአለሁ::

የመጀመርያው ወደ ቆሮ ሰዎች 13፤4 "ፍቅር ያስታግሣል፤ፍቅር ያስተዛዝናል፤ ፍቅር አያቀናናም፤ፍቅር አያስመካም፤ፍቅር አያስታብይም፤ብቻዬን ይድላኝ አያሰኝም፤አያበሳጭም፤ክፉ ነገርን አያሳስብም፤ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፅ ደስ አይለውም፤ሁሉን ይታገሳል፤ሁሉን ያምናል፤ሁሉን ተስፋ ያደርጋል በሁሉ ይጸናል"ይላል::

ይች እሪበል የጎንደር ትውልድ ብዬ የጻፍኳት መጽሐፍ በችኮላ ስለተለቀቀ የቃላት አርፍተ ነገር አለመስተካከልና የፊደል ግድፈት አለበት:: ውድ አንባቢያን እያቃናችሁ ታነቡት ዘንድ እጠይቃለሁ:: "አንድ ሰው አስቦ አንድ በሬ ስቦ" አይሳካም:: አንድ ሰው ጽፎት አንድ ሰው አርሞት የወጣ በመሆኑ ጥራት ይጎድለዋል:: በሥነ ጹሁፍ ጉድለቱ ይቅርታ እጠይቃለሁ::

መልካም ንባብ ይሁንላችሁ
አማረ አፈለ ብሻው

# ምዕራፍ 3

## አጭር የኢትዮጵያ ታሪክ

ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ ጀምሮ ኢትዮጵያ አለች:: ይች ኢትዮጵያ የሰው ልጅ የተፈጠረባት አገር ስትሆን ያለ መታደል ሁኖ ታሪካችን የተበላሸው በውጭ አገር ጸሐፊያን ምክንያት ነው:: በእርግጥ ኢትዮጵያውያን ጸሐፊዎች ቁጥራቸው ይነስ እንጂ ቀደም ጀምሮ የሰው ዘር የተፈጠረው ኢትዮጵያ መሆኑን ከመግለጽ አልተቆጠቡም:: የነዚህ ዓናሳ ጸሐፊያን እውነተኝነት የሰው ልጅ በኢትዮጵያ መገኘቱ ነው:: ዓለም በጎርፍ ሲጥለቀለቅ ከሞት የተረፈው ኖህ ነው:: ቅዱስ ኖህ ከሞት ሲተርፍና ከመርከብ የወጣው በኢትዮጵያ መሆኑን የተለያዩ የታሪክ መጻሕፍት ጽፈዋል::

1ኛ መምሕር ፍስሐ ጽዮን ካሳ መርኖ አድምና ግዕዝ
2ኛ ፍስሐ ያዜ ካሣ የኢትዮጵያ የ5 ሺ ዓመት ታሪክ ከኖሕ እስከ ኢሕአዴግ
3ኛ ያሪድ ግርማ ኃይሌ የጎንደር ታሪክ ከኢትዮጵያ ታሪክ አንጻር
4ኛ ነጋ ጌጤ የቅማንት ሕዝብ ታሪክ
ከዚህ በላይ የጠቀስኳቸው መጻሕፍት ብቻ አይደሉም ብዙ መጻሕፍት ናቸው:: የሰው ዘር ከኢትዮጵያ ወደ ሌላው ዓለም ሄደ እንጂ ከሌላው ዓለም ተፈጥሮ ወደ ኢትዮጵያ አልመጣም:: ይህን በሚለመከት ብዛት ያላቸው መጻሕፍት መዝግቦ ማሳየት ይቻላል:: የኢትዮጵያን ሕዝብ ሰላም የነሳው "ይህ ነገድ ከዚህ የመጣ ነው" የሚባለው ትረካ ነው:: በመሰረቱ በከብት እርባታ ይሁን በሌላ ምክንያት የሰው ልጆች ከኢትዮጵያ ወደ ኤስያ መሄዳቸው ግልጽ ነው:: ኀብራውያን ከኢትዮጵያ ወደ ግብጽ የሄዱ መሆኑ በታሪክ ሲገለጽ ምናልባት ኢትዮጵያውያን ይደነግጡ ይሆናል::

ዶ/ር ሀብተማርያም አሰፋ <u>የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባሕሎች</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 43 "ሕብራውያን ከኢትዮጵያ ተሰደው ወደ ግብጽ ከሄዱ በኋላ በግብጽ በባርነት ቀንበር ገብተው ሲገደሉ የነበሩ ናቸው"ሲሉ ጽፈዋል:: የዱሮ የሀገራችን ደራሲያን ሰመቲክ ቋንቋ ከእስራኤል ወደ ኢትዮጵያ የመጣ ነው ሲሉ የጻፉት ታሪክ ነበር:: የወቅቱ የታሪክ ጸሐፊያን ደግሞ ይህን አይቀበሉም::

ዶ/ር ላጵሶ ጌ.ድሌቦ <u>የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት</u> ታሪክ በተባለ መጽሐፋቸው ገጽ 19 "የሰው ዘር ምንጭ መነሻ የሆነው ልዩ ምድር የኢትዮጵያ የአዋሽ-ኦሞ ወንዞች ክልል ነው"ይሉና ገጽ 23 "ሴማዊ ሕዝብና ቋንቋ በጥንታዊ አረቢያ ከመገኘቱ በፊት በአፍሪካ ቀንድ ቢያንስ የሁለት ሺህ ዓመታት ቅድሚያ ነበረው:: በሌላ አካባቢ ዘመናዊ የሊንጉዊስቲክስ ሳይንስ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ብሔረሰቦች መካከል የነበረውንና ያለውን ጥንታዊ ታሪካዊና ባሕላዊ አንድነት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብና ሥልጣኔ ምንጩና መሠረቱ የአፍሪካ ምድር መሆኑን ጨምሮ በትክክል የሚያስተምረን

የምርምር ዘዴና ጥበብ ነው”ሲሉ ጽፈዋል:: ሰሙቲክ ቋንቋ በአረቢያ ወይም በኢየሩሳሌም ከመገኘቱ በፊት በኢትዮጵያ እንደነበር የውጭ አገር ጸሐፊዎች አረጋግጠዋል::

Martin Bernal BLACK ATHENA በተባለው መጽሐፋቸው Volum 1 and 2 ሰመቲክ ቋንቋ መነሻው አፍርካ ኢትዮጵያ ጣና ተነስቶ ወደ እስራኤል የሄደ መሆኑን ካርታው ያሳያል:: የሰው ልጆች ከኢትዮጵያ ከወጡ በኋላ ተመልሰው መጥተዋል:: እነዚህ በተለያየ ምክንያት ወጥተው የተመለሱት ኢትዮጵያውያን እንደመጤ ሊያስቆጥራቸው ችሏል:: ለምሳሌ ከ1967 ዓም ወዲህ በብዛት ኢትዮጵያውያን ተሰደናል:: የኔ ሆኑ የሌሎች ኢትዮጵያውያን ልጆች ቢመለሱ መጤ ናቸው:: ቀደም ሲል ተጽፎ ያገኘነው ይህ ነገድ ከዚህ መጣ የተባለው በዚህ ምክንያት ነው:: ያም ሆነ ይህ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ነው::

ከ80 በላይ ያሉት ነገድ አንዱን ነገድ ካንዱ ለመለየት የሚደረገው ጥረት ከእውነት የራቀ ነው:: እነዚህ የተለያየን ነን የምንለው ሁሉ አልገባን ብሎ እንጂ አንድ ነን:: ወደ ስልጣን የሚመጡት ግለሰቦች ያዘጋጁት ሴራ ካልሆነ በቀር የ80 ነገድ አንዳንድ ምስል ፎቶ በአንድ ብናስቀምጥ ፎቶ አይቶ ነገዱን የሚልይ የለም:: ምክንያቱም ሁላችን አንድ ነን:: ቋንቋና ባህል ካልሆነ በቀር አንዱን ነገድ ካንዱ ነገድ ሊለይ አይቻልም:: በመልክ ልዩነት አላቸው የምንላቸው ኩሻዊ ነገድ ብለን ልንጠራ የምንችለው የጎንደርን ግሙዞች፤ የጎጃምን ሻንቅሎችና ጋንቤሎች፤ሐመሮች ሙሉ በሙሉ የኩሽ ዘር ናቸው:: ሌሎች ነገዶች ግን ተደባልቀዋል::

አንዳንድ የኦሮሞ ምሁራን ከአማራ ጋር መዋለዳቸውን ቁምጥና መስሎ ይታያቸዋል:: አንዳንዶችማ አማራው ለኦሮሞው ካሳ መክፈል አለበት ብለው አፋቸውን ሞልተው የሚከራከሩ ተምረው ያልተመራመሩ አሉ:: ካሳ ይከፈል ከተባለ አማራው ሳይሆን ካሳ መክፈል ያለበት ኦሮሞው ነበር:: ምክንያቱም በ16ኛው ክፍለ ዘመን ከቦረና ተነስቶ መላ ኢትዮጵያን አስገብሮ የያዘ ነው:: ኢትዮጵያን ለማጥፋት በመታሰቡ ምክንያት አንዱን ነገድ ከአንዱ ነገድ ጋር ማለያየቱ እንደሚጠቅም ስለታሰበ እነሆ እየሰሩበት ይገኛል:: ወያኔ አማራው ጨቋኝ ነው ብሎ ያምናል:: ለመሆኑ አማራው ጨቋኝ ነበር እንዴ? ከኢትዮጵያ መልክዓ ምድር ከመሀል በመሆኑ ሌሎችን ነገዶች አስተባብሮ ዳር ደንበር በማስጠበቁ የውጭ ወራሪዎችን በማሳፈሩ ወራሪዎች ከሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ከነገድ አማራን ለማጥፋት አሲረዋል:: ለዚህም የኛዎችን ወንድሞች ወደ ሀገራቸው ወስደው የፈጠራ ታሪክ አስተምረው ለቀቁአቸው:: ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ የተማሩትን በተግባር አዋሉ::

ዶ/ር ላጲሶ ጌ ድሌቦ <u>የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና</u> መሣሪያዎች በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 12“አውሮፓውያኑ የፈጠራ ታሪካቸውን አስተማሩን፤የነፃ ትምህርት እድል ሰጡን:: እኛም ያስተማሩንን አጠናን:: ያንን ለሌሎችም ማስተማር ጀመርን”ሲሉ መስክረዋል:: እነዚህ ምሁራን ያስተማሩት ነገር ሌላው ደግሞ በብዕር ስም መጻፍ ነው:: በብዕር ስም መጻፍ የሚፈልገው

ሰው እርሱ ስላላመነበት ነው:: በዚህ ምክንያት አሁን የሚጠሉትን ነገድ ሆነ ሰው በብርዕስ ስም እየጻፉ መሳደብ ተጀምሯል:: በዚህ ባለንበት በምድረ ኤሌክትሮኒስ መልዕክቶች ማሰራጫ ዘዴዎች ተጠቅመው የስድብ ናዳ የሚያወርዱ ግለሰቦች በጣም በዝተዋል::

አንዴ አንዱን ወዳጄ ምሁር "ምነው አንድ በል እንጂ"ስላቸው "ወንድሜ ዝናብ የመታው ብርድ አይፈራም ይባላል"ሌሎች ይወጡት እኔ በዚህ በብዕር ስም ከሚጽፍ ጋጥ ወጥ ጋር አታካሮ አልገባም" አሉኝ:: ምሁሩ በአንድ በኩል እውነታቸውን ነው:: አንዴ መሬት ይክበዳቸውና ርዕሰ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ አስረሱ ተሰማ" አበበ እባላለሁ" ብለው ጥያቄ ሲጠይቁ ተይዘዋል:: ወያኔዎች በዚህ መንገድ የሰው ክብር ስለሚዳፈሩ ላለመሰደብ ፈርተው መሆናቸውን ተረድቻለሁ:: አሁንማ ወያኔዎች ብቻ ሳይሆኑ ወያኔ የመለመላቸው ወዶገባዎች ከማንኛውም ነገድ ያሉ የስድብ ናዳ የሚያዘንቡ ሞልተዋል:: ያም ሆነ ይህ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ነው::

ኤርመያስ 13፤23"በውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዝንጉርጉርነቱን ይለውጥ ዘንድ ይቻላልን?" የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በኢትዮጵያ ቅልቅል ሕዝብ መኖሩን ሲገልጽልን ነው:: ከኢትዮጵያ ክፍለ ሀገራት መካከል አንዱ ጎንደር ነው:: ጎንደር ክፍለ ሀገር ልክ እንደ ኢትዮጵያ ሁሉ ዝንጉርጉር፤ ድብልቅ ነገድ አለን:: ለምሳሌ አማራና ቅማንት፤አገውና ግሙዝ፤ወይጦና ጋፋት ሌላም ሌላ ጎሳዎች ስንኖር እኔ እንደሚገባኝ ቋንቋ ያላቸው አማራ፤ አገው፤ግሙዝ ናቸው:: አንድ ወንድሜ የቅማንት ልጅ እንዲህ ብለውኛል::

<u>አቶ ሞረሽ "የቅማትን</u> ቋንቋ ከ1940ቹ በኋላ የተወለዱት ልጆች አይናገሩትም:: የቅማንት ቋንቋ የሃይማኖቱ ካህናት ናቸው በብዛት የሚናገሩት:: ልክ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህናቱ ግዕዝን እንደሚጠቀሙት ማለት ነው:: ለምሳሌ ግዕዝ በአዋጅ ወይም ተጽእኖ ተደርጎበት ሳይሆን እየደከመ የመጣው ተጠቃሚው ካህናቱ ብቻ ስለሆኑ ነው:: አሁን ካህናቱ ቤተ ክርስቲያን በአማርኛ ቋንቋ መገልገል ሲጀምሩ ግዕዙ መጥፋት የሌለበት ቋንቋ እየጠፋ ነው:: ቅማንተኛ እንዲሁ በመሆኑ አዲሱ ትውልድ መናገሩን ትቶታል" ሲሉ ነግረውኛል:: እኔም ለሁለት ሳምን በገንበራ በኩል እዳይት ማጠቢያ ለሁለት ሳምንት ስቀመጥ ሲነገር አልሰማሁም:: ምናልባት በጭልጋ አውራጃ ይነገር እንደሆነ እንጃ!ያም ሆነ ይህ በክፍለ ሀገሩ ሌሎች ነገዶች አሉ:: እነሱም እንዲሁ ቋንቋቸው ጠፍቶ አማርኛ ይናገራሉ::
የወገራ አውራጃ ወልቃይት ጠገዴ፤ሰሜን አውራጃ የጠለምት አማሮች በጉርብትና ለምደውት ትግርኛ ቋንቋ ይናገራሉ:: ያማለት የትግራይ ሰዎች ናቸው ማለት አይደለም:: ታች አርማጭሆ አወሳኝ ውስጥ ያሉ አማሮች አርብኛ ቋንቋ ይናገራሉ ያ ማለት ሱዳን ናቸው ማለት አይደለም:: ከጎንደር ይልቅ የሚቀርባቸው ሱዳን ነው:: የአሁኑን አላውቅም እንጂ ሱዳኖች መቀር እጣን ሊሰበስቡ የሚከርሙት ከኢትዮጵያ መሬት ላይ ነው:: ምክንያቱም ደንበር አስከባሪ መንግሥት በ1969 ዓም ጀምሮ በአካባቢው አልነበረም::

# ምዕራፍ 4

## ሕገ ልቦና የኢትዮጵያ የሃይማኖት ቅርስ ነው

ሕገ ልቦና ለሕገ ኦሪት መንገድ ጠራጊ ሲሆን ሕገ ኦሪት ለሕገ ወንጌል ድልድይ ነው:: ሕገ ልቦና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት ሲሆን ኦሪት መጽሐፍ ይዞ ሲመጣ የአማኙ ቁጥር ቀንሷል:: እንዲሁም ሕገ ክርስትና ሲሰበክ ሕገ ልቦና ሆነ ሕገ ኦሪት ተዳክሟል:: ይህ ታሪካችን ሲሆን የመጀመርያውን ሃይማኖት ጠብቀው ያቆዩት በጎንደር ክፍለ ሀገር፤በጎንደር ዙርያ አውራጃና በጭልጋ አውራጃ የሚኖሩ ቅማንቶች ናቸው:: ሕገ ልቦና እስከ ከ982 ዓመተ ዓለም ኢትዮጵያውያንን አስተሳስሮ ይዞ የነበረ ብሔራዊ ሃይማኖት ነበር::

አለቃ አያሌው ታምሩ <u>ኢትዮጵያ በሦስቱ ሕግጋት</u> በተባለው መጸሐፋቸው ገጽ 84 "ኢትዮጵያ በህገ ልቡና የጥንታዊ አባቷ የኖኅን ዐሠረፍኖት በማቆየቷ በህገ ኦሪትም ቀዳማዊ እምነቷን በትምህርት አኅልምሳ ዕውቀቷን አድሳ ትኖር ዘንድ ከመርገም ወጥታ ወደ በረከት ገብታ በኪዳነ ኖህ ላይ ኪዳነ መልከጼዴቅን" ጨምራ ሲሉ ጽፈዋል::

ቀሲስ ዘመነ አቡሐይ ደስታ <u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ</u> ቤተ ክርስቲያን አጭር ታሪክ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 5 "ጥንታዊያን የኢትዮጵያ ሕዝቦች የካም ዘሮች ከመሆናቸው አንጻር ሲታይ ምንም እንኳን በጥቂት ጎሣዎች ዘንድ የተወሰነ ይሁን እንጂ የአብርሃምን የቃል ኪዳን ሕግ ጠብቆ በአንድ አምላክ ማመን የተለመደ እንደነበር ብዙ ኢትዮጵያውያን ይስማማሉ"ሲሉ ጽፈዋል:: አንዳንድ ሰዎች ሕገ ልቦና የአብርሃም እምነት ነው ይላሉ:: ይህ የሆነበት አብርሃም የተጻፈ የእምነት መጽሐፍ አልነበረውም::

ቀሲስ ከፍያለው መራሂ የ<u>ቤተ ክርስቲያን አስተዋጽኦ</u> በተባለው መጽሐፋቸው መቅድም "ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ናት ስንል ጥንት በሕገ አበው በሕገ ልቡና ቅድመ ልደት ክርስቶስ በሕገ ኦሪት፤ድህረ ልደት ክርስቶስ በሕገ ወንጌል"ሲሉ ጽፈዋል::

ዘመድኩን በቀለ <u>ቅዱሳን መካናት በኢትዮጵያ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 3" ኢትዮጵያ ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምራ በሕገ ልቦና በመቀጠልም በሕገ ኦሪት እግዚአብሔርን ስታመልክ የኖረች ሐገር መሆኗ የሚታወቅ ነው"ሲሉ ጽፈዋል::

ነጋ ጌጤ <u>የቅማንት ሕዝብ ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 85 "ሕገ-ልቦና ሃይማኖት ለሕገ ሙሴና ለሕገ-ክርስትና ወላጅ አባት ነው ቢባል ከዕውነት የራቀ አይደለም"ሲሉ ጽፈዋል:: ሌሎችንም መጻሕፍት መደርደር ይቻላል:: አብረሃም ከኢትዮጵያ ወደ ግብጽ የሄደ መሆኑን ሕብራውያን ባይገልጹትም ታሪክ ግን ዘርዝሮት ይገኛል:: ሐሰት ነው እንዳይባል የሰው ልጅ ረጅም እድሜ

ያስቆጠረ አጽም የተገኘው በኢትዮጵያ እንጂ በኢየሩሳሌም አይደለም:: ኢየሩሳሌም ታላቅነቷ የዓለም መዳህኒት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሚወለድባት እንጂ ከኢትዮጵያ ቀዳሚ አይደለችም::

ዲ/ን መንግሥቱ ጎበዜ እና ዲን አሳምነው ካሣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ቁጥር 2 በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 9 "የኢትዮጵያ እምነት ከክርስትና በፊት በሕገ ልቡና እና በሕገ ኦሪት ዘመን በሀገራችን ስለነበረው አጠቃላይ የእምነት ሁኔታ እና ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ታሪካዊ ከሥተቶች የምንምለክትበት ነው:: በሕገ ልቡና ዘመን አምልኮተ እግዚአብሔር በኢትዮጵያ እንዴት እንደ ተጀመረ የብሉይ ኪዳን እምነትና የሕገ ኦሪት ሥርዓት ነው"ሲሉ ጽፈዋል::

የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባሕሎች በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 39" ኅብራውያን ከኢትዮጵያ ተነስተው ወደ ግብፅ ከዚያም የባርነት ቀንበር ቢጠነክርባቸው ጠፍተው ወደ ቀይ ባህር ማዶ ሄዱ"ሲሉ ጽፈዋል:: ኅብራውያን ከኢትዮጵያ ከሄዱ እንዴት እኛ ጥቁር እነሱ ነጭ ሆኑ ትሉ ይሆናል:: ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ መልስ አለው ገጽ 76 "የሰው መልክና ቀለም በየሚኖሩባቸው አካባቢ የአየር ተፅዕኖ ምክንያት የተነሳ ቀስ በቀስ እያለ ከብዙ ዘመኖች በኋላ እየተለወጠ ሊሄድ ችሏል"ሲሉ ጽፈዋል::

ኅብራውያን ከግብጽ ወደ እስራኤል ከሄዱ በኋላ ደግሞ ወንድማቸውን ለባርነት ዮሴፍን ሸጡት:: በዚህ ምክንያት አሁንም ወደ ግብጽ ተመልሰው መጡ:: በዚህ ሰዓት ኅብራውያን የሚያመልኩት ሕገ ልቡና እንጅ ጣኦት አልነበረም:: እነሱን የፈጠረ አምላክ መኖሩን ያውቃሉ:: ሙሴ ተወልዶ ግብጽ ሰው ገድሎ የተሰደደው ወደ ኢትዮጵያ ነው:: ምድያም የምትባለው በዛሬው ጎጃም ክፍለ ሀገር አገው ምድር አውራጃ ናት:: ሙሴም በስደት ሲመጣ ያረፈው ከካህን ቤት ነው:: ኦሪት ዘጸት 2፥15 "ሙሴ ግን ከፈርዖን ፊት ኮብልሎ በምድያምም ምድር ተቀመጠ"ይልና ቁጥር 21 "ሙሴም ከዚያ ሰው ጋር ሊቀመጥ ወደደ፤ ልጁንም ሲፓራን ለሙሴ ሚስት ትሆነው ዘንድ ሰጠው"ይልና 3፥1"ሙሴም የዮቶርን የአማቱን የምድያምን ካህን በጎች ይጠብቅ ነበር"ይልና 18፤ 1"የምድያም ካህን የሙሴ አማት ዮቶር እግዚአብሔር ለሙሴና ለሕዝቡ ለእስራኤል ያደረገውን ሁሉ እግዚአብሔርም እስራኤልን ከግብፅ እንዳወጣ ሰማ በዚያን ግዜ የሙሴ አማት ዮቶር መልሶአት የነበረውን የሙሴን ሚስት ሲፓራን ሁለቱንም ልጆችዋን ወሰደ"ይላል::

ኦሪት ዘጸአት 18፥12 "የሙሴ አማት ዮቶርም የሚቃጠል መሥዋዕትንና ሌላ መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር ወሰደ በእግዚአብሔርም ፊት ከሙሴ አማት ጋር እንጀራ ሊበሉ አሮን የእስራኤልም ሽማግሌዎች ሁሉ መጡ"ይልና ሙሴ የሚያደርገውን የሕግ ሥርዓት ትክክል አለመሆኑን ካህን የቶር ተመልክቶ ዘጸአት 18፥13 "እንዲሁም ሁኖ በነጋው ሙሴ በሕዝቡ ሊፈርድ ተቀመጠ፤ ሕዝቡም በሙሴ ፊት ከጥዋት እስከ ማታ ድረስ ቆመው ነበር:: የሙሴም አማት በሕዝቡ ያደረገውን ሁሉ ባየ ጊዜ ይህ በሕዝቡ የምታደርገው ምንድነው?ሕዝቡ ሁሉ ከጥዋት ጀምሮ እስከማታ ድረስ በዙሪያህ ቆመው ሳሉ አንተ ብቻህን ስለ

ምን ትደክማለህ?አለው:: ሙሴም አማቱን ሕዝቡ እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ወደ እኔ ይመጣሉ፤ነገርም ቢኖራቸው ወደ እኔ ይመጣሉ፤በዚህና በዚያ ሰውም መካከል እፈርዳለሁ፤የእግዚአብሔርንም ሥርዓትና ሕግ አስታውቃቸዋለሁ አለው:: የሙሴም አማት አለው፤አንተ የምታደርገው ይህ ነገር መልካም አይደለም:: ይህ ነገር ይከብድብሃልና አንተ ከአንተም ጋር ያለው ሕዝብ ትደክማላችሁ፤አንተ ብቻህን ልታደርገው አትችልም:: አሁንም እመክርሃለሁና ቃሌን ስማ፤እግዚአብሔርም ከአንተ ጋር ይሆናል፤አንተ በእግዚአብሔር ፊት ለሕዝቡ ሁን ነገራቸውንም ወደ እግዚአብሔር አድርስ ሥርዓቱንም ሕጉንም አስተምራቸው፤ የሚሄዱበትን መንገድ የሚያደርጉትንም ሥራ ሁሉ አሳያቸው አንተም ከሕዝቡ ሁሉ አዋቂዎችን፤እግዚአብሔርን የሚፈሩትን የታመኑ የግፍንም ረብ የሚጠሉትን የመቶ አለቆችን፤የአምሳ አለቆችን፤የአስርም አለቆችን ሹምላቸው፡ በሕዝቡ ላይ ሁልጊዜ ይፍረዱ አውራውን ነገር ሁሉ ወደ አንተ ያምጡት፤ታናሹንም ነገር ሁሉ እነሱ ይፍረዱ፤እነርሱም ከአንተ ጋር ሸክሙን ይሸከማሉ፤ለአንተም ይቀልልልሃል:: ይህንም ብታደርግ እግዚአብሔር እንዲሁ ቢያግዝህ መቆም ይቻልሃል፤ደግሞም ይህ ሕዝብ ሁሉ በሰላም ወደ ስፍራው ይደርሳል:: ሙሴም የአማቱን ቃል ሰማ ያለውንም ሁሉ አደረገ" ይላል::

ካህን የቶር ሙሴ በሕግ ሕዝቡን ማስተዳደርና እግዚአብሔርን እንዲያውቅ የመከረው ሕግንና እግዚአብሔርን የሚያውቅ መሆኑን ያስረዳል:: ይህ ካህን የቶር የሕገ ልቦና ካህን ሲሆን የሕግም ምሁር ነበር:: ይህ አልፎ ሴፓራ የቶር የሙሴ ሚስት በመሆንዋ የሙሴ ወንድምና እህት በማግረምረማቸው እግዚአብሔር የቀጣቸው መሆኑን ዘኁልቁ 12፤1"ሙሴም ኢትዮጵያይቱን አግብቶአልና ባገባት በኢትዮጵያይቱ ምክንያት ማርያምና አሮን በእርሱ ላይ ተናገሩ:: እነርሱም በውኑ እግዚአብሔር በሙሴ ብቻ ተናግሮአልን?በእኛስ ደግሞ የተናገረ አይደለምን? አሉ፤እግዚአብሔርም ሰማ:: ሙሴም በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሑት ሰው ነበረ:: እግዚአብሔርም ወድያው ሙሴንና አሮንን፤ማርያምንም፤ሦስታችሁ ወደ መገናኛው ድንኳን ውጡ፤ብሎ ተናገረ፤ሦስቱም ወጡ:: እግዚአብሔርም በደመና ዓምድ ወረደ፤በድንኳኑም ደጃፍ ቆመ፤አሮንንና ማርያምን ጠራ፤በመካከላችሁ ነቢይ ቢኖር እኔ እግዚአብሔር በራእይ እገለጥለታለሁ፤ወይም በሕልም እናገረዋለሁ:: ባርያዬ ሙሴ ግን እንዲህ አይደለም፤እርሱ በቤቱ ሁሉ የታመነ ነው:: እኔ አፍ ለአፍ በግልጥ እናገረዋለሁ፤በምሳሌ አይደለም፤የእግዚአብሔርንም መልክ ያያል፤ በባሪያዬ በሙሴ ላይ ትናገሩ ዘንድ ስለ ምን አልፈራችሁም አለ:: እግዚአብሔርም ተቆጥቶባቸው ሄደ:: ደመናውም ከድንኳኑ ተነሣ፤እነሆም ማርያም ለምጽም ሆና ነበር"ይላል::

እኛ የሰው ልጆች እግዚአብሔር ተሎ አያደርስልነም ብለን እናስባለን እንጂ ሲፓራ ኢትዮጵያዊቷን የተቃወሙ ማርያምን ለምጻም ያደረገ እግዚአብሔር በአገር ደረጃ ኢትዮጵያን ያደሙ አገሮች ደምተዋል:: በ1985 ዓመተ ዓለም ከሕንድ የመጣው ንጉሥ ራማ ኢትዮጵያን ሊወር ነበር ግን በጀግኖች ተወግቶ ቀርቷል:: ኢትዮጵያ ደክማለች ብለው ለመውረር የመጡት ግብጾች

ኢትዮጵያውያን ገርፈው እነሱን 400 ዓመታት በቅኝ ግዛት ይዘው ነበር:: አሁንም አገሮች ኢትዮጵያን አታድሙ:: ሆዳም የሆናችሁ ወይም ደግሞ ለሥልጣን ብላችሁ ትውልዱን ጠም ለማሳደር የተነሳችሁ አርፋችሁ ቁጭ በሉ፤ትውልዱ ከፈለገው ቦታ ተምሮና ሰርቶ በልቶ ይኑር፤እንደ ደጋ ከብት ከአንድ አካባቢ አትሰብስቡት በቋንቋ በነገድ አጥር አትጠሩት:: ኢትዮጵያ ከዛሬ 3 ሺህ ዓመት በፊት "በሕገ ልቦና ታመልክ ነበር" ተብሎ በብዙ መጻፍት ተጽፎአል:: በ982 ዓመተ ዓለም ቀዳማዊ አጤ ምኒልክ ሕገ ኦሪትን ወደ ኢትዮጵያ ሲያመጡ ቅማንቶች አምነዋል:: ክርስትና ሃይማኖት በ330 ዓም የመንግሥት ሃይማኖት ሁኖ ሲታወጅ ቅማቶች ተጠምቀዋል::

በ610- በ615 ዓም በተለያዩ ዓመታት ወደ ኢትዮጵያ የነቢዩ ሙሐመድ ቤተሰቦችን በእንግድነት መጡ:: ኢትዮጵያም መኖርያ ሰጥታቸው በሰላም ሲኖሩ መካ ሰላም ወርዷል የሚል ዜና በመስማታቸው ተመልሰው ሄዱ:: ግን አልቆዩም ሌሎችን ስደተኞች አስከትለው አሁንም ወደ ኢትዮጵያ መጡ:: ነቢዩ ሙሐመድ ድል አድርገው መካ ከተመለሱ በኋላ ወደ ሳውዲ ተመልሰዋል:: ነቢዩ ሙሐመድም ለንጉሥ አርማህ 3 ደብዳቤ ጽፈዋል:: ንጉሥ አርማህ ማለት የዚያን ግዜ የአጋሜ አውራጃ ንጉሥ እንጂ የመላው ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አልነበሩም::

የታሪክ ሠነድ የሚያትተው ከ595-615 ዓም ንጉሠ ነገሥት አጤ አድርአዝ ሲሆኑ እርሳቸው በትረ ሥልጣኑን የተረከቡት ንጉሠ ነገሥት 1ኛ አጤ አካለ ውደም ከ615-623 ዓም ሲሆኑ ከ623-638 ዓም ድረስ ንጉሠ ነገሥት የነበሩት አጤ ግርማ አስፈሪ ነበሩ:: ስደተኞች ወደ ኢትዮጵያ አክሱም እንደመጡ ንጉሠ ነገሥት አጤ አድርአዝ ለአጋሜው ንጉሥ በጥሩ ሁኔታ እንዲይዟቸው በትዕዛዝ ወደ አጋሜ ላኳቸው:: በዚህ ምክንያት ከስደተኞች ጋር መካ ይኖሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያን አብረው መጥተው ስለነበር አረቦች ቢመለሱም መካ መስጊድ ከመሰራቱ በፊት አጋሜ አውራጃ የመጀመርያ መስጊድ ሰርተዋል:: በነገራችን ላይ ቁጥራቸው ይነስ እንጅ እስልምና ሃይማኖት የተቀበሉ የቅማን ነገድም አሉ::

የኦሪት እምነት በኢትዮጵያ ከሰሜን እስከ ደቡብ፤ከምዕራብ እስከ ምሥራቅ ተስፋፍቶ ቆይቶአል:: ክርስትና ሃይማኖት ሲሰበክ አንጠመቅም ያሉ ቀርተው ነበር:: እነሱም ኦሪት እምነት መነሻ ይሁናቸው እንጂ የሥልጣን ጥማቸውን በ840-880 ዓም ንግሥት ዮዲት ያካሄዱት ጦርነት ማየት ይቻላል:: በዚህ ጦርነት ክርስትና ሃይማኖት የተቀበሉት የቅማንት አባቶቻችን እንደማንኛውም ነገድ አብረው ክርስትና ሃይማኖት እንዳይጠፋ ጥረት አድርገዋል:: ባጠቃላይ ሕገ ልቦና የኢትዮጵያ ቅርስ እንጅ የአንድ ነገድ የግል አይደለም:: አሁንም ሕገ ልቦና እምነት ተከታዮች እንደ በፊቱ በፍላጎታቸው እንጂ ማንኛውም የሃይማኖት ተቋማት አስገድዶ ወደራሱ ሃይማኖት መውሰድ አግባብ አይደለምና ሊያስገድዱ የሚፈልጉ ኃይሎች ካሉ ሊያርፉ ይገባቸዋል::

# ምዕራፍ 5

## ወያኔና አቶ ነጋ ጌጤ 1983 ዓም ግንኙነት

በእደ ማርያም እጅጉ ረታ አጤ ምኒልክና ኢጣሊያኖች በተባለው ረጅም መጣጥፋቸው "የታሪክ ጥናት ለሕሙም አእምሮ ፍቱን መድኃኒት ነው!The Study of history is the best medicine for a Sick mind"ሲሉ ጽፈዋል:: ወያኔ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም አዲስ አበባን እንደያዘ የተለያዩ ነገዶችን ሰብስብ አድርጎ የሽግግር መንግሥት ሊያቋቁም ባቀደበት ሰዓት 3 የቅማት ልጆች መለመለ:: ልጆቹም በቂ የሆነ ድጋፍ ሳያገኙ በመቅረታቸው የስብሰባው ቀን ደርሶ ሳይሳተፉ ይቀራሉ:: እነዚህ የወያኔ ደጋፊ የሆኑ ልጆች ደርጀት ማለት እንዳለባቸው ወያኔ ቅስቀሳውን ቀጥሎ በ1984 ዓም "የቅማት ማህበር" ብለው ሲመሰርቱ የቅማት አባቶችና "በኢትዮጵያ ላይ ያንዣበበውን ቀውስ ትክክል አይደለምና እረፉ፤በንብ ግዜ ዝምብ ይናከሳል እንደሚባለው ስለሆነ አትከፋፍሉን" ይላሉ::

አቶ ነጋ፤ግን ጠንክረው ትግላቸውን ቀጠሉ:: መጽሐፍ ጽፈው ለንባብ አበቁ:: መጽሐፍ አንዱን ነገድ ከአንዱ ነገድ ጋር አንዱ አማኝ ከሌላው አማኝ ጋር የሚያጋጭ ነው:: እኔ ከመጽሐፉ ጠንካራ ጎን በ1996 ዓም ስጽፍ የሕገ ልቦና እምነትን አስመልክቶ ምስል ፎቶ ወስጄ ጽፌ ነበር:: ምክንያቱም ሕገ ልቦና እምነቱን እንጅ ካህናቱ አለባበሳቸውን በፎቶ አስደግፎ ያልተጻፈ በመሆኑ:: ሌላው አቶ ነጋ፤አጤ ቴዎድሮስን አስመልክቶ ከመጽሐፋቸው የጻፉትን የእርሳቸው የፈጠራ ድርሰት በመሆኑ በመረጃ አስደግፌ በ2003 ዓም አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትንአንት ዛሬም ነገም በተባለው መጽሐፌ ተችቼ ጽፌአለሁ::

ደራሲ ነጋ ጌጤ
የመጽሐፉ ርዕስ የቅማንት ሕዝብ ታሪክ
የታተመበት በ1993 ዓም ጎንደር
የገጽ ብዛት 117
የመጽሐፉ ዋጋ አልተጠቀሰም በነጻ የታደለ መሆኑን ሰምቻለሁ
ጥቅስ የተወሰደባቸው መጻሕፍት ብዛት 24
ቃለ መጠየቅ የተደረገላቸው ግለሰቦች 11 ናቸው::

የታሪክ መጽሐፍ አጻጻፍ ፈሊጦች እንደተረዳሁት ሦስት ዓይነት ናቸው:: የእነሱን አጻጻፍ ስልት ላስረዳ:: ጸሐፊዎች የቋንቋ አጠቃቀም ፈሊጣቸው ሊለያይ ይችላል:: ለምሳሌ ይህን የጥቅስ አጠቃቀም ፈሊጥ ተመልከቱ ብዙ ጸሐፊያን ይጠቀሙበታል::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አጭር ታሪክ የተባለ መጽሐፍ ገጽ 4 “ኢትዮጵያ የዓባይ ሸለቆ ተከትሎ በምሥራቅ አፍሪካ ሱዳንን፣ኑቢያንና ደቡብ ዓረቢያን ጭምር የሚቆጣጠር በኢኮኖሚ የዳበረ በፖለቲካም የጠነከረ ታላቅ መንግሥት እንደነበራት ይታወቃል። 9 ስለዚህ ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ የተለያዩ ታሪክ ጸሐፊዎች ተቀራራቢነት ያለው ሐሳብ አስፍረዋል። ኢትዮጵያውያን ጸሐፊት የመንግሥቱ መቀመጫ ከናፓታ ወደ መርዌ እንደተዛወረ ሲተርኩ ግራም ሐንኮክ ትልቁ ከተማ መርዌ የኢትዮጵያ መንግሥት መቀመጫ እንደነበር ጽፈዋል።10 የታላቁ ንጉሥ የአልክሳንደር ታሪክ ጸሐፊ ንግስት ሕንደኬም የመርዌና የአክሱም ንግሥት እንደነበረች ዘግቧል።11 ፕሊኒ የተበላው ፀሐፊ ደግሞ ኢትዮጵያ በዚያ ዘመን 45 ግዛት የነበራት ሲሆን ከእነዚህም ታላቁ መርዌ ነበር ይላል 12” ሲሉ ጽፈዋል። ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የአንደኛው አጻጻፍ ፈሊጥ ከተለያዩ መጽሐፍት ጥቅስ ወስደው ጽፈዋል። የግርጌ ማስታወሺያ መጽሐፉንና ገጻቸው ተገለጾአል። በአንድ አርፍተ ነገር ላይ አራት የታሪክ ማስረጃ ጠቅሰዋል። የዚህ ዓይነት አጻጻፍ ዘዴ በብዛት የተለመደ ነው።

የአጻጻፍ ፈሊጥ የአንድን መጽሐፍ ሀሳብ ይወስድና ከመጽሐፉ መጨረሻ ላይ መጽሐፉን በዋቢነት ይጠቅሳል። ለምሳሌ ከዚህ መጽሐፍ ክፍል ሦስት ምዕራፍ ሁለት ኢትዮጵያን ለመገንባት የተደረገው ጥረት የሚለው ምዕራፍ የጥቅስ ምልክት የለም። እያንዳንዱ ነገሥታት የነገሡበት ቀን ተጠቅሶአል። ሁለተኛው አጻጻፍ ፈሊጥ በዚህ ዓይነት ይጻፋል። ይህ ዓይነቱ የጹሑፍ ፈሊጥ ጥሩ አይመስለኝም። ምክንያቱም ለምርምር የሚጠቅም አይሆንም፡ እኔ የምከተለው ሦስተኛውን አጻጻፍ ፈሊጥ ነው።

ታሪኩ ታመኔታ እንዲኖረው አንድን ጹሑፍ ጥቅስ ለመውሰድ ሲያስብ የጸሐፊውን ስም ይጽፍና በመቀጠል መጽሐፉን ገጹን ጠቅሶ የጥቅስ ምልክት ከፍቶ ከጻፈ በኋላ ሲጨርስ ጥቅሱን ይዘጋል። ለምሳሌ የሐዋርያት ሥራ 20፣28 “በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመበት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ” ይላል። ብሎ ከጻፈ በኋላ ጥቅሱን ዘግቶ የራሱን ትችት ይጠቁማል። ለምሳሌ ጳጳሳቱ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ታዘው ነበር። ነገር ግን የአሁኖቹ ጳጳሳት ገንዘብ ጽድቄ ብለዋልና ለቤተ ክርስቲያን ድህነት ሳይሆኑ ውድቀት አምጥተዋል። አሁን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ድክመት ያመጡብን ምዕመናኑ ሳይሆኑ ጳጳሳቱ ናቸው። ብሎ የራሱን ሊገልጽ ይችላል። ይህን ዓይነት አጻጻፍ ለታሪክ ምርምር ጠቃሚ ነው።

አቶ ነጋ፣ግን ከላይ ከጠቀሱኩት የአጻጻፍ ፈሊጥ አንዱንም አልተጠቀሙም። እርሳቸው ያደረጉት ነገር ምንድነው የፈለጉትን ጽፈው ምንም ዓይነት ጥቅስ ሳይወስዱ ከታሪክ የተገኘ አስመስለው የግርጌ ማስታወሻ ይመዘግባሉ። እርሳቸው ከጠቀሱአቸው መጽሐፍት ውስጥ በእጄ የሌሉት 6 ብቻ ናቸው። እርሳቸው የመሰገቡአቸው መጽሐፍት ያሉትን የሚያንጸባርቁ አይደሉም። እርሳቸው ዓላማቸው የቅማንት ብሔረሰብ በደል ደርሶበታል፣ሃይማኖቱ

ተበድሏል ማንነቱን አጥቷል። ይህ የነገድ ጭቆና ተደርጎበታል የሚለው አባባል አደናጋሪ ሁኖ የኢትዮጵያን ሕዝብ የከፋፈለ በማር የተለወሰ መርዝ ነው። ይህን በጥሞና ለሚያየው ለወደፊቱም የሚያሳድገን አይደለም። ምናልባት እርሳቸው ሆኑ ሌሎች በጥሞና እንዲመለከቱት ለማሳሰብ እወዳለሁ። ምክንያቱም ላም ካልዋለበት ኩበት ለቀማ ነውና።

ዩሱፍ ያሲን አሳሳቢ <u>ማንነት ባንድ ሀገር ልጅነት የኢትዮጵያ</u> እጣ ፋንታ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 62 "ባህላችን ሃይማኖታችን ታሪካችን ሊጠፋ ነው ተብሎ ብሔራዊ ስሜቶችን በማራገብ የሚደረግ ቅስቀሳና ልፍለፋ ይታከልበትና ነገር ዓለሙ ይጦዛል። ተረትና ታሪክ ይድበላለቃል። በዚያን ጊዜ ማንነት ይበልጥኑ የሰው ልጅ ፈጠራ ገፅታው ሲጣመም እንመለከታለን"ሲሉ ጽፈዋል። አሁንም የቅማንትን መብት እናስከብራለን የሚሉ ወንድሞቻችን ከዚህ የተለየ አይደሉም። ታስታውሳላችሁ በነገድ ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲጣላና ሲጋጭ የቆየው ወያኔ ባለመጣው ጦስ ምክንያት ነው። ለመሆኑ የኢትዮጵያን ሕዝብ ማነው የጨቆነው? በእኔ እምነት አንዱ ነገድ አንዱን ነገድ አልጨቆነውም። ሕዝቡን የጨቆነው ሥርዓቱ ነው።

<u>ጥቅምት 23 ቀን 2007 ዓም</u> የወጣው መግለጫ "በቅማንት ብሔረሰብ የማንነትና የራስ አስተዳደር ጥያቄን አስመልክቶ በሰሞኑ የተደረጉ የሕዝብ እንቅስቃሴዎች በአጭሩ የሚከተለውን ይመልከቱ" ይሉና "እስካሁን ባጠቃላይ 80 ት/ቤቶች የተዘጉ ሲሆን 130.000 (መቶ ሰላሳ ሺ)ተማሪ አድማ አድርጓል። በቀጣይ ቀናት ከ100 ያላነሱ ት/ቤቶች የሚዘጉ ሲሆን በአጠቃላይ ከ287.500 የማያንስ ተማሪዎች ያቋርጣሉ ተብሎ ይጠበቃል"ይላል።

አስቡ በአሁኑ ወቅት የሰው ልጅ በአንድ ቋንቋ መግባባት በጀመረበት ሰዓት ልጆችን ከትምህርት ቤት አስቀርቶ ከእውቀት እንዲርቁ ማድረግ በእኔ እምነት የሚገባ አይመስለኝም። የዓለም ሕዝብ አሁን አንድ ሁኖአል። ምክንያቱም የተፈጠረው የዘመናዊ ቴክኖሎጂ መሣርያ አንድ አድርጎታልና ነው። አብሰም ምዕራባውያን ቀደም ሲል በአንደኛውና በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተላልቀው እንደነበር ታርክ ይዘክራል። አሁን ግን የጋራ ሕብረት ፈጥረው አንድ ሁነው ኢሮን አምርተው ባለበት ሰዓት ተምሮ እራሱን እንዳይረዳ ከትምህርት ቤት ማስቀረቱን እንደጀብድ ቆጠሩት ያሳዝናል? ምነው ዛሬ ገለሞና ዓለሜ በጭልጋ ብቅ ባሉ ነበር? ስንቱን ሆዳም ይገርፉት ነበር? እነሱ ሆዳም አይወዱም ነበር! እነሱ በተለወዱበት መንደር ሆዳም በዝቶ ሲያዩት ያን የጫቆ ሽፍታ 30 ቴዎድሮስና ገለሞ፤አለሜና እንግዳ ገርፈው ቀጥተውታል። አሁን እነዚህ 4ቱ ብቅ ቢሉ 30 ብቻ ሳይሆን ሽህ ሽፍታ መግረፍ ይችሉ ነበር። ያለ ግዜው ተወልደዋልና ታዲያ ምን ያደርጋል አሁን እነሱን የሚተካ የሌ?የሚገርፍና ዝም የሚያሰኝ ጀግና???

# ምዕራፍ 6

## የኢትዮጵያ ነገሥታት ጣዖት አላመለኩም

የቅማንት ሕዝብ ታሪክ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 16"በንጉሥ ኢዛና ዘመን የጣዖት አምልኮ ዕድገት ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ እንደነበር የተገለጸው ቃል በቂ ማስረጃ ከመሆኑም በላይ ከአክሱም ከተማ ውስጥ የቆመውና የወደቀው በጣሊያኖች ተነቅሎ የተወሰደው የሦስቱ ሐውልቶች ፈጣሪና ባለቤት ከራሱ ከኢዛና እና ከሱ በፊት የነበሩት ነገሥታት ለመሆናቸው የሚያጠራጥር አይሆንም። ከሁሉም በላይ የእነዚህ ሐውልቶች ሥራና አቀራረፅ በዚያ ዘመን እንዲህ ያሉ የተራቀቁ ከአንድ ወጥ ድንጋይ ሐውልቶችን ቀርፀው ያቆሙት አባቶች አስደናቂው የጥበብ ሥራቸው ነው። በንጉሥ ኢዛና እና ሳይዛና አማካኝነት በዘመነ መንግሥታቸው እጅግ ከፍተኛ ደረጃ አድርሰውት የነበረውን የጣዖት አምልኮ ሥርዓት እንደገና ከውጭ አገር ማለትም በግብጽ በኩል ተስቦ ወደሀገራችን አባ ፍሬምናጦስ ከሳቴ ብርሃን በተባሉ ሰባኪዎች አማካኝነት ለመጣው የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ግምባር ቀደም አማኝ በመሆን ተጠምቀው ኢሳዛ እና ሳይዛና የሚለውን ስማቸውን በአዲስ የኦርቶዶክስ ክርስትና በመለወጥ አብርሃና አፅብሃ ተባሉ" ሲሉ ጽፈዋል።

መልስ እንኳን በ330 ዓም ቀርቶ ከዚያ በፊት የነበሩት ነገሥታት ጣዖት አላመለኩም። ከንግሥት ሳባ ማለትም በ1013 ዓመተ ዓለም በፊት የነበሩት ነገሥታት ከዘውዳቸው ላይ የዘንዶ ምስል ያደርጉ ነበር የሚባለውን አውሮፓውያን ኢትዮጵያውያን በዘንዶ ያመልኩ ነበር ብለው ጽፈውት ይገኛል። በኢትዮጵያ ከነገሡት ነገሥታት መካከል ከዳግማዊ አከናሁስ እስከ አጤ ጴአሪ ማለትም 1985 ዓመተ ዓለም ድረስ የነገሡት 23 ነገሥታት ሀሉም ካማዊ ሲሆኑ ቤተ መንግሥታቸው መርዌ ነበር። የበዓባይ ሸለቆ ስልጣኔ ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ ነበር። በነዚህ ነገሥታት ዘመንም ቢሆን አንዳቸውም በጣዖት አምልከው አያውቁም።

ዶ/ር ኃይሌ ወልደሚካኤል <u>አብሮነት በኢትዮጵያ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 3"የአባይ ሸለቆ የአባይ ወንዝ ውጤት ነው።የአባይ ወንዝ ደግሞ የኢትዮጵያ ስጦታ ነው። የአባይ ሸለቆም የመጀመርያው ጉልህ ማኅበራዊ ሕይወት የተደራጀበት፤የተፈጥሮ ክስተቶች ግንዛቤ ያገኙበትና የሰው ልጅ ጉልህ የኃይማኖት፤የፖለቲካ፤የኢኮኖሚ፤የሥነ ምግባርና የሳይንስ ሥርዓትና ሚስጥር የለየበትና በየፈርጁ ያደራጀበት ነው። መደበኛ ግብርና ማለትም ከብት ማርባት፤አዝርዕት መዝራት፤ የመገልገያና የማምረቻ መሣሪያዎችማምረት አልባሳት መሥራት፤ከብቶችን በወተት፤በሥጋ፥በትራንስፖርትና በእርሻ ምንጭነት መጠቀም፤በመስኖ እርሻ መገልገል፤በውሃ መጓጓዝ፤በአንድ አምላክ ማምለክ፤ የጹሑፍ ባህል፤ማመንጨት፤የሃይማኖት ካህናት ማፍራት፤አስከሬን

ማቆየት፣የጂኦሜትሪን ሳይንስ ማዳበር ወዘተ የመሳሰሉት ሁሉ ብልጭታዎች መጀመሪያ የታዩት በዓባይ ሸለቆ ውስጥ ነው"ሲሉ ጽፈዋል::

ከአባይ ሥልጣኔ ወደ መርዊ ሲዛወሩ ነገሥታቱ አንዴም ጣዖት አምልከው አያውቁም:: ከንግሥት ሳባ በፊት የነገሡት ነገሥታት ከዘውዳቸው ላይ የዘንዶ ምሥል ያደርጉ ነበር:: ያ ማለት እንደዘንዶ ተወርዋሪ ነን ማለት እንጂ ዘንዶውን እናመልከዋለን ማለት አይደለም:: ቀዳማዊ ምኒልክ ከ982 ዓመተ ዓለም "እንደ አባቴ እንጂ እንደናቴ አልነግሥም"ብለው ከዘውዱ ላይ የአምበሳ ምስል እንዲሆን ቀይረውታል:: ያ ማለት አምበሳውን ማምለክ እንዳልሆነ ከ40 ዓመታት በፊት የተወለድን ሁሉ ያጤው ዘውድ አምበሳ መሆኑን ያየን ስንኖር በዚያን ወቅት ያልተወለደ በምስል ድምጽ በቪዲዮን ተቀርጾ ያለውን ማየት ይቻላል:: አቶ ነጋ ከግርጌው የአባ ጋስፓሪኒ መጽሐፍ ገጽ 101 እና 114 ብለው ጽፈዋል:: የአባ ጋስፓሪኒን መጽሐፍ ሌሎች የማናገኘው መስሏቸው ሳይሆን አይቀርም:: አባ ጋስፓሪኒ ግን የጻፉት አቶ ነጋ እንደጠቀሱት ሳይሆን ታሪኩ እንዲህ ነው::

አባ ጋስፓሪኒ <u>የኢትዮጵያ ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 101"ሁሉን በሚችለው በሰማያዊው አምላክ በሰማይና በምድር ባለው ማናቸውንም በሚያሸንፈው በጌታ ስም የእለ ዓሜዳ ልጅ ብእሴ፣ሐሌን፣(የሐሌን ተወላጅ) የአክሱም፣የሕምያር፣የሳባ፣የሳልሒን፣የጽያም፣የቤጋ፣የካሱ፣ንጉሥነገሥት በጠላት ያልተሸነፈው የእለ ዓሚዳ ልጅ:: ለዘላለም የሚነግሠው ጠላት የማያሸፍነው ሰማያዊው አምላክ በሰጠኝ ኃይል ከፊቴ አንድም ጠላት መቆም በስተኋላዬም ሊከተለኝ አይችልም:: የሁሉ ጌታ በሆነው ኃይል የኖባን ሕዝብ ወግቼ ድል አደረግሁት:: እንደዚሁም ያ ደረግሁት የኖባ ሕዝብ በትዕቢት ተነሥቶ ከተከዜ ማዶ ግዛት የለውም ብሎ በጠላትነት በተነሣብኝ ጊዜ ነው:: የኖባ ነገዶች የመንጉርቶን፣የኃሳንና የባርያን ነገዶች ቢያስጨንቋቸው፣ጥቁሮቹን ሰዎች ወጉአቸው:: እንደዚሁም ያደረጉት ሁለት ሦስት ጊዜ መሐላቸውን አፍርሰው ጎረቤቶቻቸውንና እኔ የላኩአቸውን ሁሉ በከንቱ ገድለው ነው:: ይሰሙአቸው እንደሆነ ብዬም መልዕክተኞችን ብልክባቸው እነርሱን በኃይል ይዘው ያላቸውን ገንዘብና መሣርያ ሁሉ ቀሙአቸው:: መልዕክተኞቹን አንሰማም ብለው ሁሉንም በኃይል ካሠሩ በኋላ የግድ ጦርነት አደረጉባቸው::"

"በሰማይና በምድር ጌታ ኃይል ተነሥቼ ብዙዎቹን ከተከዜ አጠገብ ፈጀኋቸው:: ሲሸሹም ተከትዬ 23 ቀን በሚያስኬድ ዘመቻ እነርሱን እየገደልሁ፣እየዘረፍሁና እየማረክሁ መንደራቸውንና ሰፈራቸውን እያቃጠልሁ ፈጀኋቸው:: ከነርሱ ብዙዎቹም በተከዜ ገማ ውስጥ እየገቡ ሲሰጥሙ ጀልባዎቻቸውም እንደነርሱ ወደ ውስጥ እየሰጠሙ ቀርተዋል:: እኔ የጦር ሠራዊቴን ሁሉ እነርሱን እንዲወጉ ልኬ ብዙዎቹን ገድለው የተረፉትን ማርከው አገራቸውን አቃጥለው በደህና ወደቤታቸው ተመልሰው ገብተዋል:: ከዚህ በኋላ ሁለቱ ገሞች ተከዜና ሲዳ ከሚገናኝበት በግንብ ከተሰራው ከተማ ፊት ለፊት አንድ መንበር (ዙፋን) አሠርቼ ከዚያ አኖርሁት:: የሰማይ ጌታ በእጄ የጣላልኝ የጠላት እነሆ የሚከተሉት ነው:: እስረኛ ወንዶች 2014 ሴቶች

4015 የሞቱ ወንዶች 6200 ሴቶች 900 ናቸው:: ከብቶች 10 ሺህ 500 ሰባ:: በግና ፍየል 90 ሺህ ራስ እዚያም መንግሥቴን ለሰጠኝና ለረዳኝ ለሰማያዊው አምላክ መንበር ዙፋን አሠርቼ ከሠርዶ ላይ አቆምሁት:: የሰማይ ጌታ መንግሥቴን ያጽናልኝ:: ዛሬ ጠላቶቼን ለማሸነፍ እንዳበቃኝ ሁሉ እንዲሁም በሄድሁበት ሁሉ በኔ አድሮ በፍትሕና በጽድቅ ያሸነፈልኝ:: ስለምን እኔ የማንንም ሕዝብ በግፍ ማስጨነቅ አልፈልግምና ነው:: ይህነን የሠራሁትንም መንበር ላነገሰኝ ለሰማይና ለምድር ጌታ አደራ አልሁት:: ይህን መንበር የሚያፈርሰው ወይም የሚያበላሸው፤ወይም ደግሞ የሚያፈርሰው ሁሉ እርሱም ዘሩም ከአገሩ ሥሩ ይነቀል:: ይህነን መንበር በሰማያዊው ጌታ ኃይል ያቆምሁት እኔው ራሴ ነኝ"ሲሉ ጽፈዋል:: በአቶ ነጋ አጻጻፍ አንድም ተመሳሳይ ትረካ ሊገኝ አልቻለም::

በመጀመርያ ደረጃ የአክሱም ሐውልት በ4ኛው ክፍለ ዘመን የተሰራ አይደለም፤ ይህ የምዕራባውያን ታሪክ እንጂ የኢትዮጵያውያን ታሪክ አይደለም:: ወያኔ ልክ ነው ብሎ ይቀበላል ወይም ደግሞ አንዳንድ የሠነድ እጥረት ያለባቸው ጸሐፊያን ሊሉ ይችላሉ:: እውነታው ግን የአክሱም ሐውልት ቀደም ብሎ የተሰራ ነው:: የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ የተባለው መጽሐፍ ገጽ 69 " ከ2000 ዓመታት በፊት የአክሱማውያን ሽጣጣ ሐውልት ከትግራይ"ሲሉ ጽፈዋል:: ይህ ከሆነ አውልቱ የተሰራው ከክርስቶስ ልደት በፊት ነው:: ይህ ሐውልት ከልደት በፊት የተሰራ እንጂ ከልደት በኋላ የተሰራ አይደለም::

በላይ ግደይ <u>የኢትዮጵያ ሥልጣኔ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 46 "አብዛኛዎቹ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት የተሠሩ መሆናቸው ነው"ሲሉ ጽፈዋል:: የአክሱም ሐውልት ቀደም ብሎ የተሰራ እንጂ በነአብርሃ አጽብሃ ዘመን የተሰራ አይደለም:: በነገራችን ላይ ኢዛና ሳይዛና የኋላዎቹ አብርሃና አጽብሃ በዘመናቸው ክርስትና ተቀበል አልቀበልም ጦርነት አላደረጉም:: ባሉኝ ሰነድ አንዱም አይጠቅስም:: ገብሩ አንገብርም እንጅ ተጠመቁ አንጠመቅም አልተዋጉም:: ሁለቱ ወንድማማቾች ክርስትናን ለማስፋፋት እስከ መቃድሾ ሕደው እንዲሰበክ አድርገዋል:: አገሪቱን ዙረው አይተው አንዳቸው ሽዋ ላይ አንዱ አክሱም ላይ ተቀምጠው እንዲያስተዳድሩ ተስማሙ:: በዚህ ምክንያት አጤ አብርሃ ሽዋ ኤረር ቤተ መንግሥት ሠሩ:: አጤ አጽብሃ ወደ አክሱም ተመለሱ:: በአጽብሃና አብርሃ ዘመን በሃይማኖት ምክንያት አንድም ጦርነት አልነበረም:: ዜና መዋላቸው ላይ አልተገለጸም::

ስለዚህ የአቶ ነጋ አጻጻፍ ስህተተኛ ነው:: ኢትዮጵያን ሲያስተዳድሩ የነበሩ ነገሥታት እምነት ነበራቸው:: ከ840-880 ዓም የነገሡት ንግሥት ዮዲት አሪትን ያመልካሉ:: ከ1519-1535 ዓም ሥልጣን የያዙት አጤ አህመድ ግራኝ እስልምና ያመልካሉ:: ወደ ቤተ አምልኮ ሳይሄዱ በትረ ሥልጣናቸውን የለቀቁ ርዕሰ ብሔር ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ሲሆኑ ሲሞቱ አስከሬናቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን የሄደው ርዕሰ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ መሆናቸውን ልንመሰክር እንችላለን:: ከእንግዲህ በኋላ ለሚነግሡት ማን ያውቃል?

# ምዕራፍ 7

## ቅማንት ጎንደሬ እንጂ ከትግራይ የመጣ አይደለም

የቅማንት ሕዝብ ታሪክ 17 "ጣዖት አምላኪዎች ደግሞ በአምላካቸው በአስተር በመሕመረምና ምድር ላይ ክፉ የሠራ ሁሉ ዘሩና ልጆቹ ከአገር ተነቅለው ይጥፉ የሚል የከረረ አቋም በነበራሳቸው እምነት ይዘው በመነሳት የሃይማኖት ጦርነት ጀመሩ:: የተጫረው የእሳት ነዲድ የማይበርድ ሲሆንበት ንጉሡ አክሱምንና አካባቢዋን በዚህ የሃይማኖት ብጥብጥ ነፃ ለማድረግ ሲል ጥምቀተ ክርስትናን ያልተቀበለ ሰው ሁሉ አክሱምን ለቆ ከተከዜ ወዲያ ማዶ ሂዶ መኖር ይችላል ሲል ሌላ የትዕዛዝ አዋጅ አስነገረ:: በዚህ አዋጅ መሠረት የኦርቶዶክስ ክርስትናን አንቀበልም ያሉት ቅማንቶች የሕገ ልቦና እና የጣዖት አምልኮ ተከታዮች የሆኑት ሁሉ አክሱምን በኃይል ለቀው እንዲወጡ ተደረገ" ሲሉ ጽፈዋል::

ቅማንት በክርስትና ሃይማኖት ምክንያት በተነሳው ብጥብጥ እምነቴን አልቀይርም ብሎ ከትግራይ ወደ ጎንደር በ330 ዓም የመጣ ነገድ አይደለም:: አቶ ነጋ ወያኔ እንዴት እንደተጫወተባቸው አልገባቸውም:: ወያኔ በግማሽ ወሎንና በግማሽ ጎንደርን ወደ ትግራይ ከልሎ ሊወስድ ስላሰበ በቅማንት ልጅ ከትግራይ የመጣን ነን ብለው እንዲጽፉ አድርጓል:: የእርሳቸው ተከታዮች የወያኔ ጄሌዎች የሆናችሁ ልብ እንድትሉት ያስፈልጋል:: ወያኔ የስነ ልቦና ዘመቻ ማድረግ የጀመረው ቀደም ብሎ ነው:: ወያኔ አቶ ነጋን የመሰለ ማንነት የሚያስደፍር ደራሲ አግኝተዋል:: እኛ የምናውቀው የቅማንት ነገድ ጎንደሬ መሆኑን እንጂ በ330 ዓም ከትግራይ ተከዜን ተሻግሮ የመጣ ነገድ አይደለም:: አቶ ነጋ ከላይ ከትግራይ የመጣ መሆኑን ከገለጹ በኋላ ደግሞ ዝቅ ብለው ጎንደሬ መሆኑን አምነዋል:: ለወያኔ የሚጠቅም ቃል ከሰጡ በኋላ መልሰው ከአምስት ሺህ ዓመት በፊት በጎንደር መኖሩን መስክረዋል:: ሴራ ሁሌም በአንዱ ሲቋጠር በሌላው ሲፈታ ይታያል::

የቅማንት ሕዝብ ታሪክ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 87 "ጎንደርን የሰየሚት ቀደምቶችና ጥንታውያኑ ቅማንቶች ከክርስቶስ ልደት በፊት ከአምስት ሺ ዘመን በፊት እንደሆኑና ጎንደር ማለትም በቅማንት ቋንቋ ትርጉም የጌታ መነሻ ማለት መሆኑን ከላይ የተጠቀሱት አንጋፋዎቹ የቅማንት ህገ-ልቡና ሃይማኖት መሪዎች ይናገራሉ"ሲሉ ከአንድ ቦታ ላይ ገልጸዋል:: እኔም ሆንኩኝ የሌሎች አባባል አዛውንቶች የነገሩዎት ጎንደሬነታቸውን ነው:: ከትግራይ መጣ ያሉት እርስዎ እንጂ አንድም የቅማንት ልጅ አይሉም:: ምናልባት በግማሽ የትግራይ ተወላጅ የሆነ የወያኔ ጄሌ፤ወይም ደግሞ የእርስዎ ዓይነት ካልሆነ በቀር የቅማንት ነገድ ከትግራይ የመጣ አይደለም:: ጎንደር ከተማው የተሰራበት የቅማንት ወረዳ ነበር አዎ! ቀደም ጀምሮ የቅማንት ሕዝብ ይኖርበት ነበር አዎ! ታሪክ የሚዘክረው ሐቅ ይህ ነው::

አለቃ ታየ ወልደማርያም የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 11"የቅማንቶች መኖርያ፤በከርከር፤በጭልጋ፤በጋላ አገር፤በቦባ፤በኮሶጌ፤በጃኒ ፈንቀራ፤በዙሪያቸውም ባሉ አገሮች ነው"ሲሉ ጽፈዋል:: ወያኔ ለራሱ የሚጠቅመውን ያውቃል:: ለዚህም የማሳተሚያውን ገንዘብ አሸጎላቸው አቶ ነጋ የቅማንት ሕዝብ በ330 ዓም ከትግራይ ተሰዶ የመጣ አስመስለው ጽፈዋል:: የሚገርመው ነገር ለጎንደር ሳይሆን ኢትዮጵያን የመምራት አቅም አላቸው የተባሉት ጉዳይ ፈጻሚ አምባሳደር ዘመነ ካሰኝ ዝም ማለታቸው ነው:: መጽሐፉን ረቂቁን ያዩና የተረዱ ናቸው:: እንዴት ሴራው ሳይገባቸው ቀረ? ረቂቁን ተመልከት ሲባል በመጀመርያ አክብሮት ተሰጥቶት ተመርጦ ነው:: ስለዚህ አስቸጋሪ የሆነውን ጉዳይ ዝም አይልም:: ይህ መሆኑን የተከበሩ ጉዳይ ፈጻሚ አምባሳደር ዘመነ ያውቃሉ እንዴት ዝም አሉ? ነውስ እርስዎም ቅማንት ከትግራይ የመጣ ነው ብለው አምነው ነው?

የቅማንት ሕዝብ ታሪክ ምስጋና ላይ "ክቡር አምባሳደር ዘመነ ካሰኝን በየጊዜው በቅርብ ሆነው ለሰጡኝ ጠቃሚና ገንቢ ምክር"ሲሉ ጽፈዋል:: በጉዳይ ፈጻሚው በአምባሳደር ላይ የሚባለው ሁሉ እውነት ነው:: በአጤው ዘመን ሆነ በደርግ ዘመን ብሎም በወያኔ ዘመን ደህንነት ናቸው የሚባለው?ይህ ካልሆነ በቀር እንኳን ይህን ሌላውን የሚያውቁ ምሁር ዝም አይሉም:: ለነገሩ የጎንደርን ማህብር ወደ መቃብር የከተቱት የወያኔ ሰህንነት መሆናቸውን የጎንደር ሕዝብ ሳያውቅ እርሳቸውን አክብሮ ሊቀመንበር ሁኑ ካላቸው በኋላ እርሳቸው ይህን ሴራ በግልጽና በጋራ ሲፈጽሙ ቆይተዋል:: አንድ ሰው የሚከበረው በእድሜው መሆኑን አምናለሁ:: ደግሞም በተግባሩ! ጉዳይ ፈጻሚ አምባሳደር ዘመነ ከላይ ከፍ ብለው የነበሩት ዝቅ ያሉት የቅማንት ማንነት በአቶ ነጋ ጌጤ ተጠግተው ለወያኔ ሸጡ:: ቅማንት ከትግራይ የመጣ ነው የተባለው መጽሐፍ ሲያርሙ እንዴት ዝም ሊሉ ቻሉ?

አንዱ በሳተናው ጋዜጣ "የማያፍሩ ከተስካር ሕደው እንዝፈን አሉ"በሚል ጽፎ ነበር:: ምክንያቱም ለ30 ዓመታት ያክል አማራው ሕዝብ እንዲጠፋ ቅስቀሳ ሲያደርጉ የነበሩ ግለሰብ የግል ጥቅማቸው ሲቀርባቸው የአማራ ወዳጅ ሁነው ሲመጡ ስላየሁ:: ይህን የመሰለውን ግለሰብ ሆነ ድርጅት ፈጽሞ የማልቀበለው ሲሆን እውነቱን ተናግሬ ከመሸበት ባድር እወዳለሁ:: ጉዳይ ፈጻሚ ክቡር አምባሳደር ዘመነም የዚህ ዓይነት ተግባር ሲፈጽሙ በማየቴ ከልብ አዝኛለሁ:: አክብሮቴና ፍቅሬ እንዳለ ሁኖ አሁንም የፈጸሙት ተግባር አሳፋሪ መሆኑን ከመግለጽና ከመጻፍ ፈጽሞ አልመለስም:: የቅማንት ልጆች ሆኑ እኔ ከእርስዎ የምንማረው አንድነታችን እንጅ ልዩነታችን ነው ብዬ አላምንም ነበር:: ለካስ ሰውን ማመን ቀብሮ ነው ያለችው ቀበሮ እውነቷን ነው:: ሌሎች ቢያደርጉት ወይም ዝም ቢሉኮ ማንም አይፈርድም:: ምክንያቱም ሊቀ ጠበብት ፕሮፌሰር ሆነ ሊቅ ዶ/ር ግድም አይሰጠውም አምባሳደርኮ የጎንደር ሕዝብ ታቦት ናቸው? ይህን የቅማንት ሕዝብ ከትግራይ የመጣ ነው የሚለውን አይተው ዝም ካሉ ከእንግዲህ ማነን ልመን?

# ምዕራፍ 8

## የቅማንት ሕዝብ ክርስትናን በግድ አልተጠመቀም

የቅማንት ሕዝብ ታሪክ ገጽ 46 እና ገጽ 47"በ1880 ዓም ገደማ አጤ ዮሐንስ የተባሉ የትግራይ ንጉሥ ከመቀሌ ተነስተው ወደመተማ ከድርቡሾች ጋር ለመዋጋት ሲዘምቱ እግረ መንገዳቸውን በዚህ በጎንደር በኩል ሲያልፉ ሠራዊታቸው በቅማንት አገር ላይ ተመርቶ ወይም በየአንዳንዱ ቅማንት ቤት ተቀምጦ ሀብት ንብረቱን እንዲዘርፍ ከማድረጋቸውም በላይ የቅማንቱን ወጣት ያለፍላጎቱ ወደ መተማ እንዲዘምት ሲያስገድዱ አንዲት እናት ልጄን አትውሰዱብኝ ብላ እየጮኸች ከንጉሡ አጤ ዮሐንስ ፊት ስትቀርብ ንጉሡ የሰጧት መልስ አንቺ ጆሮ ተልታላ ቅማንት ልጅሽ ወደዘመቻው መወሰዱ የግድ ነው አንቺ ግን ግንባርሺን መስቀለኛ ተነቅሰሽ በአንገትሽ የብረት መስቀል አስረሽ ተጠምቀሽ ክርስቲያን ሁነሽ ከመተማ ስመለስ ከአላገኘሁሽ አንገትሽን በሰይፍ ነው የምቆርጠው ብለው ሲዝቱባት"ሲሉ ጽፈዋል::

4ኛው አጤ ዮሐንስ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እንጂ የትግራይ ንጉሥ አልነበሩም:: አጤ ወደ መተማ የዘመቱት በ1882 ዓም ነው:: አጤ ዮሐንስ ከቅማንት ልጆች በግድ ወታደር ሊመለምሉ አልሞከሩም:: ይህ ታሪክ ፈጠራ ነው:: የቅማንት ሕዝብ ታሪክ ገጽ 47 "አጤ ዮሐንስ በጣም አክራሪ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይና አራማጅ ስለነበሩ የቅማንቱን ሕዝብ በአስከተሉት ሠራዊታቸው አስገዳጅነት እንዲጠቃና ክርስቲያን አማራ እንዲሆን ባደረጉት ዘመቻ ተጠመቅ አልጠቀምቅ ትንቅንቅ የብዙ ቅማንቶች ሕይወት አልፏል:: ባጠቃላይ አጤ ዮሐንስ የሕዝቡን ወንድ ልጅ ቀደም ወደ ጦርነት ወታደሮቻቸው ደግሞ የገበሬውን ሚስቶችም ሆነ ሴት ልጆችን አስገድዶ በመድፈር ሀብት ንብረቱን በመዝረፍ ሕዝቡ ሃይማኖቱን እንዲለውጥ በማስገደድ ብሎም የመግደል እርምጃ የወሰዱበት ዘመን በመሆኑ ይህን አስከፊና ተደራራቢ የሰባዊ እርምጃ የወሰዱበት ዘመን በመሆኑ ይህን አስከፊና ተደራራሪ የሰባዊ መብት ገፈፋ ይዝም ግርጋ ይሉታል:: ይዝም ግርጋ ማለት ክፉ ቀን ማለት ነው:: በአጤ ዮሐንስ ሕልፈተ ሕይዎት ምክንያት ሕዝቡ እልል እያለ ከተደበቀበት ዋሻና ጫካ በመውጣት የሠላም ኑሮውን ሲጀምር በኃይል የተቀበለውን የክርስትና ሃይማኖት ወዲያውኑ ትቶ ወደነበረበት የራሱ ሃይማኖት እንደተመለሰ አባቶች የአጤ ዮሐንስን ዘመን በምሬት እያስታወሱ ይናገራሉ"ሲሉ ጽፈዋል::

4ኛው አጤ ዮሐንስ ወደ መተማ ሲዘምቱ ቅማንቱን አስገድደው ክርስትና እንዲቀበል አድርገዋል የሚለው ከውነት የራቀ ነው:: ጣልያን በ1928 ዓም የኢትዮጵያን ዋና ከተማና የክፍለ ሀገር ከተማን ከያዘ በኋላ ጎንደር የነበረው ኮማንዳ ቶሪ ባሊ ፔር የተባለው የቅማንትን አባቶች ሰብስቦ ቅማንት ተገዶ

ክርስትና እንዲቀበል የሆነው ባጤ ዮሐንስ ዘመን ነው ብሎ ለህዝቡ እንዲናገሩ አዘዘ:: ሰሳ እንዳትገደል አዋጅ ያወጡት ባንዳው ፊታውራሪ ዓለማየሁ ቢተዋ ይህን ታሪክ እየዞሩ አወሩ:: በተለይ ባንዶች ደህና ጋዜጣ በመሆን በቅማንት ሕዝብ መካከል ገብተው በስፋት እንዲወራ አድርገዋል:: ከነዚህ መካከል የአቶ ነጋ አባት ፊታውራሪ ጌጤ ለምለም አንዱ ናቸው:: አጤ ዮሐንስ በጎንደር ክፍለ ሀገር ውስጥ ሠራዊታቸው በየቤቱ ተሰርቶ ሕዝቡን አሰቃይቷል ንብረት ዘርፏል÷ሴቶችን አባልጓል፤ሌላም ሌላ በደል ፈጽሟል:: ይህን እኔም ከአቶ ነጋ ጋር የምጋራው ሰነድ ዋቢ በማድረግ ሲሆን በ1881 ዓም የቅማንትን ሕዝብ አስገድደው ክርስትና እንዲነሳ አድርገዋል የሚባለው ውሸት ነው:: አጤ ዮሐንስ ወደ መተማ ሊዘምቱ ሲሄዱ ወንዱን እያስገደዱ አዝምተዋል የቅማንት ልጆች ያሉት አቶ ነጋ ሀሰት ነው::

አጤ ዮሐንስ ወደ መተማ ሲዘምቱ ጎጃምን ከደመሰሱ በኋላ ነው:: ከጎጃም ወደ ጎንደር አልተመለሱም:: በእርግጥ መተማ በጭልጋ አውራጃ ውስጥ ሲሆን በጭልጋ አውራጃ ውስጥ ያለውን የቅማንት ሕዝብ ሳይደርሱበት አልፈው አይሄዱም:: ነገር ግን በድርቡሽ ቀድሞ የተመታው የቅማንት ሕዝብ በመሆኑ ከዚህ ሕዝብ ውስጥ አስገድደው ወታደር ወሰዱ:: አስገድደው ክርስትና እንዲቀበሉ አስደረጉ የሚባለው ሐሰት ነው:: ክርስትና አስተምሮ እንጂ አስገድዶ ማጥመቅ አይፈቀድም:: ይህን በወሎ እስላሞች ላይ የተፈጸመው ሁሌም አጤ ዮሐንስ በታሪክ ይወቀሱበታል::

በነገራችን ላይ አጤ ዮሐንስ በእስላሞች ላይ ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል የነበረውን ካራና ቅባት የሚባለውን ክርስቲያን ግንቦት 1875 ዓም ቦሩ ሜዳ ላይ አከራርከው ነበር:: በዚህ ሰዓት የተረቱትን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ያልሆኑት ምላሳቸውን የተቆረጡ እነ ጉራምቤ እንግዳ ታሪክ አልተፈጸመም ማለት አይደለም:: በቅማንት በኩል አስገድዶ ክርስትና ሃይማኖት እንዲቀበሉ አስደርገዋል የሚለው ትረካ ግን እውነት አይደለም:: ይህን የሰበኩት የፋሽስት አሽከሮች ከላይ የጠቀስኳቸው ፊታውራሪ ጌጤ ለምለም ፊታውራሪ ዓለማየሁ ቢታዋ፤ናቸው:: ከታህሳስ 20 ቀን 2007 ዓም የካቲት 20 ቀን የዱሮ መጻሕፍት ማገላበጥ ጀመርኩኝ:: አንድም ቅማኖታችን በጉልበት አጥምቋል የሚል ሠነድ ማግኘት አልቻልኩም በእርግጥ በ1956-1958 ዓም ለሁለት ዓመታት የመስክ ጥናት ያደረጉ አሜሪካዊ ሊቀጠበብት ከሰዎች የሰሙትን አጤ ዮሐንስ አስመቁ ብለው መዝግበውታል::

የኢትዮጵያ መንግሥት ከአክሱም ወደ ላኮ መልዛ የዛሬው ወሎ ላስታ በ912 ዓም ሲዛወር ቅማንቶችን አስገድዶ ክርስትና አስነስቷል የሚል ሠነድ አላገኘሁም:: የኢትዮጵያ መንግሥት ከላስታ ወደ ሸዋ በ1262 ዓም ሲዞር ከፍተኛ የሆነ ጦርነት ኑሮበታል:: የይፋት ወላስሞች ገብሩ አንገብርም ጦርነት እንጅ የሃይማኖት ጦርነት አልነበረም:: እነ አጤ አምደ ጽዮንና ሌሎች ነገሥታት በባሕር ዳር ማሕለቃቸውን የሚጥሉትን አረቦች ቦታ ማሳጣታቸው ግልጽ ነው:: አባይን ለመገደብ ግብጽን ማስፈራራቱ ሌላውም ብዙ አገራዊ

ክብር ለማስጠበቅ ጥረት ተደርጓል:: በነዚህ ዘመናት ውስጥም ቅማንቶችን አስገድዶ ክርስትና እንዲነሱ አድርገዋል የሚል ተጽፎ አላነበብኩም::

በ1517 ዓም ጀምሮ በተለይ በ1519 ዓም የአጤ ልብነ ድንግልን መንግሥት የነጠቁት አጤ አሕመድ ግራኝ ከሀረር እስከ ባህረ ነጋሽ ሲመጡ አጤ ልብነ ድንግል ከሸምብራ ኮሬ ሽንፈት ወዲህ ከሸዋ፣ጎንደር ሲገቡ 6 ወር የቆዩት ትክል ድንጋይ አካባቢ ሹማራ ማርያም ከምትባል ቤተ ክርስቲያን ላይ ነበር:: በዚህ ምክንያት አጤ አህመድ ግራኝ ተከታትለው ጎንደር ሲመጡባቸው አጤ ልብነ ድንግል ወልቃይት ሄዱ:: አጤ አህመድ ግራኝ አሁንም አርማጭሆ ሄዱ:: ሰሀራ ወጥተው ወደ ደብረ ሲና ማርያም ሳይወርዱ በጦር ታገዱ:: ከአርማጭሆ ሲመለሱ በቅማንት ውስጥ 21 አብያተ ክርስቲያናትን አቃጠሉ:: ሕዝቡንም እንደማንኛውም ክርስቲያን አጠቁ::

ከዚህ በኋላ በኢትዮጵያ ሌላ ጦርነት መጣ:: ያም ከቦረና የተነሱ ኦሮሞዎች በጦር ኃይል የአካባቢውን ስም እያስቀየሩ የአሁኑ ጎንደር ከተማ ካለበት አልፌው ጋላአገር ድረስ መጡ:: በዚህ ሰዓት ቅማንቶች እንደማንኛውም ጎንደሬ ተመተዋል:: ይህ እንዳለፈ ሌላ ጦርነት በኢትዮጵያ መጣ፣ያም ፖርቱጋሎች አጤ ገላውዴዮስን እናግዛለን ብለው መጥተው የነበሩት ኋላ አጤ ስኒዮስ ሲነግሱ በካቶሊክ እምነት አጠመቁአቸው:: አጤ ሰስኒዮስ የካቶሊክ ሃይማኖት የመንግሥት ሃይማኖት ነው ብለው አወጁ:: የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ምዕመናኑ ግን አንቀበልም በማለቱ ምክንያት ከአጤው ጋር ይዋጋ ጀመር:: በዚህ ምክንያት በ1620 ዓም ደንቀዝ ላይ በአንድ ቀን ብዙ ሕዝብ አልቋል:: አንደኛው ሠነድ 24 ሺህ ሲል ሁለተኛው ሠነድ 12 ሺህ፣ሲል ሦስተኛው ሠነድ 8 ሺህ ሰው አልቋል ይላል:: በዚህ ወቅት የቅማንት ልጆች እንደ ሌላው ክርስቲያን አብረው አልቀዋል::

በነዚህ ዓመታት የቅማንት አባቶች እንደማንኛውም ክርስቲያን ምዕመን አብረው መመታታቸውን እንጂ ተለይተው የተወጉበት ጦርነት ተመዝግቦ አላገኘሁም:: በአጤ ሰስኒዮስ ዘመነ ወይዘሮ ፍቅርተ ክርስቶስ የሚባሉ እናት ነበሩ:: እኒህ እናት ብዙ ግፍ ተፈጽሞባቸው ሳይበገሩ ስለቀሩ ቤተ ክርስቲያናችን ቅድስት ብላቸዋለች:: እኒህ እናት ደራ ፎገራ ቢወለዱም እናታቸው ቅማንት ናቸው:: አንዳንድ የታሪክ ጸሐፊያን ሙሉ በሙሉ ሰሜን ጎንደር ብለው መዝግበዋቸዋል:: የኒህ እናት አባት ወንድም አቡነ ሐራ መሆናቸው በታሪክ የተረጋገጠ ነው::

ሊቀ ብርሃናት መርቆሬዎስ አረጋ <u>የቅዱሳን ታሪክ ቁጥር 5ኛ</u> መጽሐፍ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 170 "ቅድስት ወለተ ክርስቶስ የተባለችው ኢትዮጵያዊት እናት ትውልዷ ሰሜን ጎንደር ሲሆን በካቶሊካውያን ጊዜ የነበረች ካቶሊካውያን በጎንደር በመስቀል በመግረፍ ያሰቃዩዋት የቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ዘስጋ ጓደኛ የነበረች:: ትልቅ እናት ነች"ሲሉ ጽፈዋል:: ሌሎች እናቶች የቅማንት ልጆች ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዋጽኦ አበርክተዋል:: ለምሳሌ እማሆይ ወለተ ብርሃን የተባሉት እናት

የቅማንት ተወላጅ ናቸው። እኚህን እናት ክርስቲያናዊ ድርሰት ብዙ የደረሱ ናቸው። ቀደም ሲል የነበሩ ጸሐፊያን መጽሐፍ ከጻፉ በኋላ ስማቸውን ሳይጽፉ ለቤተ ክርስቲያን ይሰጣሉ። ሌሎች በቁም ጽሕፈት እየቀዱ ወደ ሌሎች ቤተ ክርስቲያናትና ገዳማት ያድሉታል። እኚህ እናት የጻፏቸው መጻሕፍት እንዳሉ ሲገለጽ ሌላው በበገና ድርደራ አምላክን ያመሰገኑ ነበር።

መላከ መንክር ቀሲስ ከፍያለው መራሒ ዝክረ ሊቃውንት በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 43 "ልዩ ልዩ ትንቢታዊ ነገር መዝሙረ ሃይማኖት የእመቤታችን ዜና ስደት በበገና መደርደር..ወዘተ የደረሱ ሊቅ ነበሩ። ለምሳሌ ዛሬ በጾመ ፍልሰታ ሴቶች የሚማልሉትን የሱባኤ ምሕላ የደረሱ ወለተ ብርሃን እንደነበሩ መምህራን መስክረውላቸዋል"ሲሉ ጽፈዋል።

"ከሁሉ ሁሉ ጤፍ ታንሳለች
ከጭቃ ወድቃ ትነሳለች
አ!ማርያም ሆይ
ከልጅሽ ጋር ወደኛ ነይ
ጻድቅስ ያለ ተክለ ሃይማኖት
በአንድ እግሩ ቁሞ ሰባት ዓመት
በተአምኖ
ሰባት ባቄላ ምግብ ሁኖ"

የሚለውንና ሌላውን ምህላ ከእነማሆይ ጋር ያደገ ሁሉ ያስታውሳል። አጤ ሰሲኒዮስ ከብዙ እልቂት በኋላ ከማህበረ ሥላሴ ገዳም ለመጡት አበምኔት "ፋሲል ይንገስ ሃይማኖት ይመለስ"የሚል ቃል ተናገሩ። ከዚህ በኋላ ደጃዝማች ፋሲል በኢትዮጵያ ነገሱ። አጤ ፋሲል እንደነገሱ ከእርሳቸው በፊት በጦርነት ኢትዮጵያ ደቃ ስለነበር "ደም በቃ"የሚል አዋጅ አወጁ። እርሳቸው ያ የክርስቲያን ደም ሲፈስበት ከነበረው ደንቀዝ ቤተ መንግሥት ሊኖሩ አልፈለጉምና ወደ አሁኑ ጎንደር መጡ። ቤተ መንግሥቱ ሲሰራ ደም በቃ በተባለ እንጨት ተሠራ። ይህ እንጨት በብዛት የሚገኘው ከቅማንቶቹ መንደር ክርከር ሲሆን በእነሱ ተቆርጠ ግንድ መጠያ አመጡት።

ከግንድ መጠያ ወደ ጎንደር ፈላሾች ወሰዱት። ይህን በመሰለ ትብብር በደም በቃ እንጨት ቤተ መንግሥቱ ተሰራ። ነገር ግን የአጤ ፋሲል ህልም እውን አልሆነም። በኢትዮጵያ ደም መፍሰስ ዛሬ ድረስ አልቆመም። ጎንደር ከተማ ባጤ ፋሲል ከተመሰረተ ወዲህ ብዙ ተግባራት ተፈጽመዋል። የኢትዮጵያ ዳር ደንበር ለማስጠበቅ ጥረት ተደርጓል። በተለይ በሕግ በኩል ከፍተኛ የሆነ ተግባር ተፈጽሟል። ለምሳሌ እስላምና ክርስቲያን ተካሰው ፍርድ ቤት ቢሄዱ ፍርዱን የሚያዩት አጤ ፋሲል ነበሩ። ለጎንደር ከተማ ምስረታ ዋናው ቅማንቱ ቀድሞ ክርስትና ሃይማኖት በመቀበሉ እንጂ በዚያን ወቅት አጤ ፋሲል ክርስትና ሃይማኖት ካልተመሰረተበት ቦታ ገብተው ዛሬ የምናያቸው 44 ቤተ ክርስቲያን አይከፈትበትም ነበር።ጎንደርን ለማሳደግ የቅማንት ሕዝብ አስተዋጽኦ አለበት።

ፕሮፌሰር ሲ ጋምስት እንደጻፈው ቅማንት አረማዊ-አሪታዊ ኢትዮጵያዊ ገበሬ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 188 "ቅማንቶች ነበሩ በሰው ኃይል በእርሻ ውጤቶችና በማገዶ ረገድ የጎንደር ከተማን ቀጥ አድርገው ይዘዋት የነበረው:: በተለይ ማገዶ አቅራቢ በጎንደር ከተማ አካባቢ ባይኖሩ ኖሮ ሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞች እየተመሰረቱ እንደጠፉት ሁሉ የጎንደርም ዕጣ ፈንታ ይኸው ነበር" ሲሉ ጽፈዋል:: የኒህ ሊቀ ጠበብት መጽሐፍ ቅማንት አረማዊ የሚለው ትክክል አይደለም:: ቅማንት አረማዊ ሳይሆን በአንድ አምላክ የሚያምን ነው:: በሕይዎት ካሉ ራሳቸው እንዲያርሙ መንገሩ የኢትዮጵያውያን ድርሻ ይሆናል አረማዊ ባለመሆኑም ሕገ ኦሪት ሲገባ በሰላም ተቀብሎታል:: ሕገ ክርስትና ሲሰበክም እንዲሁ ተቀብሏል:: ሕገ ቁርዓን የተቀበሉም አሉ:: በተለይ ድርቡሽ ከ1878-1881 ዓም ባደረገው ወረራ ምክንያት ተገደው የሰለሙ አሉ::

ብላቴ ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል ዝክረ ነገር በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 819 "ምስክር የሚሆን ታሪክ ብዙ የሚገኝ ሜሮዌ በሚባለው በጥንታዊ ከተማ አሁን ፈራርሶ በመተማ በኩል ባለው ነው"ሲሉ ጽፈዋል:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲወለድ ንጉሠ ነገሥቱ ዋና ከተማ አክሱም ነበር:: ለምሳሌ ንጉሠ ነገሥት አጤ ባዜን ከልደት በፊት 8 ዓመት ከልደት በኋላ 9 ዓመት ሲነግሱ ንጉሠ ነገሥት አጤ ሠርጡ ስመ መንግሥቱ ጽንፌ አሰግድ 21 ዓመት እንዲሁም 2ኛ ንጉሠ ነገሥት አጤ ጽንፌ አርእድ 32 ዓመታት ንጉሠ ነገሥት አጤ ሰጥታህ 8 ዓመት ማለትም 40 ዓም ንጉሠ ነገሥት አጤ ሆርኤምተኩ 2 ዓም ዓመት ሲነግሡ ነገሥተ ነገሥታት ገረሞስ ከ42 ዓም እስከ 50 ዓም ነግሰዋል:: መጽሐፍ ቅዱስ ሐዋርያት ሥራ 8፤ ላይ ተጠቅሶ የሚገኘው ጃንደረባው ከሜሮዌ ከመተማ አካባቢ የሄደ እንጂ ከአክሱም የሄደ አይደለም:: ምክንያቱም ሐዋርያው ፊልጶስ ያጠመቀው በ33 ዓም ነው:: ወደ ኋላ ልመለስና ሙሴም ከአገው ምድር ሜሮይ ገብቶ እንደነበር የታሪክ መጻሕፍት ያስረዳሉ::

ነጋ ኃይለ ሥላሴ ባለታሪክ ኢትዮጵያ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 22 "ሙሴ በሜሮዌ በቆየበት ግዜ" ሲሉ ጽፈዋል:: በእርግጥ አገው ምድርና ቋራ ሜሮይ መተማ እርቀቱ ብዙም አይደለም:: ያም ሆነ ይህ ሜሮዌ ማለት ከ982 ዓመተ ዓለም በፊት የኢትዮጵያ መናገሻ ዋና ከተማ የነበረ ሲሆን ምዕራብ ኢትዮጵያ ከግብጽ ወራሪ ኃይል ሲከላከሉበት ቆይተዋል:: ለምሳሌ የፋርሱ ዳርዮስና የግሪኩ አልክሳንደር፤ሮማውዊ ቄሳር በተለያየ ግዜ ግብጽን አስገብረው ኢትዮጵያን ለማስገበር ሲመጡ የወራሪውን ኃይል ይጋፈጥ የነበረው የሜሮይ ንግሥት ናቸው:: ስትራቦን የሚባለው እንደጻፈው በግብጽ በነበረበረበት ጊዜ የሜርዌን ግዛት ከግብጽ አገናኝቶ ለሮማ ለማስገዛት ሲል ኮርኔሊዎስ ካዩስ የሚባለውን የጦር አለቃውን ላከው:: 7ኛይቱ ሕንደኬ ነበረች የአካባቢው ንግሥት:: ቀደም ብለው ለአውግስጦስ ሐውልትና ምስል እስከ መሥራት ደርሰው ኖሮ ከንግሥት ሕንደኬ የተላከው ወታደሮች ለአውግስጦስ ተሠርቶ የነበረውን ሐውልት አፈረሱት:: የግሪኩ አልክሳንደር ግብጽን ወሮ ከያዘ በኋላ ኢትዮጵያን ሊወር አቀደ:: ሰዎች አትችልም ብለው ቢነግሩት አሻፈረኝ ብሎ ራሱ እንደሰላይ ሁኖ ሜሮይ መጥቶ የተያዘ መሆኑን ግሪኮች የጻፉትን ወደ

አማርኛ ተርጉመው ጳውሎስ ኞኞ የኢትዮጵያና የጣልያን ጦርነት በተባለው መጽሐፍ ገልጸውታል:: እንዲያውም ያለችው ሕንደኬ "እስክንድ ሆይ አለምን አንቀጥቅጠህ የገዛህ ዛሬ እነሆ በሴት እጅ ተያዝክ"ስትለው ደንግጦ እንጋባ ያላት መሆኑን ጽፈዋል:: በዚህ ሰዓት ለቤተ መንግሥቱ ቅርበት ስላላቸው የንግሥት ሕንደኬም ወታደሮች ቅማንቶች ይበዛሉ:: ለክርስትና ሃይማኖት በመጀመርያ በሐዋርያው ጃንደረባ ባኮስ ወንጌል የቀመሱትኮ የሜሮይ ከተማ ሰዎች ናቸው:: ሐዋርያው ማቴዎስ በሜሮይ ወንጌል ሲሰብክ ወንጌልን የቀመሱት ቅማንቶች ናቸው::

መራሪስ አማን በላይ <u>የጥንቷ ኢትዮጵያ ትንሣኤ ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 132 "እቴ ሕንደኬ ዣን ንግሥት በሆነች በአስረኛው ዘመን መንግሥቷ ወንጌላዊው ማቴዎስ ሜሮዬ ከተማ ገብቶ ሲያስተምርና ሲያጠምቅ ሰምታ ወደርስዋ ይዘውት እንዲመጡ ላከች:: ነገር ግን እቴ ሕንደኬ ዣንም እሱ ከመምጣቱ እኔ መሄድ አለብኝ ብላ በብዙ ሺህ ጦር ታጅባ ወረደች" ሲሉ ጽፈዋል:: ይህ ሐቅ ከሆነ እንዴት 4ኛው አጤ ዮሐንስ በግድ አስጠመቁት? የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያን አንድነት ስለምታስጠብቅ ምዕራባውያን አይወዷትም:: ወያኔም እንዲሁ አይወዳትም:: ሌላውን ሁሉ ተውት አቶ ነጋ ለሕገ ልቦና ሃይማኖት መጥፋት ከተቆረቆሩ እርሰወኮ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትተው ጴንጤ ሁነዋል?ለምን ወደ ድግናው አልሄዱም? ለድግናው ለሕገ ልቦናው እምነት የተቆረቆረ ሰው ራሱ ቀድሞ መግባት ነበረበት::

የቅማንት ሕዝብ ታሪክ ገጽ 102 "ሥርዓተ አጤ በ330 ዓም ሲመሰረት በመጀመርያ በህገሬው ላይ የወሰደው እርምጃ ሕዝቡ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖትን በኃይል እንዲቀበል ነበር"ይላል መጽሐፉ:: የክርስትና ሃይማኖት አስተማሪዎች ሙተው እንጂ ገለው ሃይማኖትን አላስፋፉም:: ተርበው እንጂ ጠግበው አላስፋፉም:: ጌታችን ማጥቃት እየቻለ የተጠቃ መግደል እየቻለ የተገደለ፣መስቀል እየቻለ የተሰቀለ፣ለእኛ ትህትና ሊያስተምረን ሲል እየተፉበትና እየዛቱበት፣ያን ሁሉ መከራ እያደረሱበት" አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው"ያለ አምላክ ነው:: እንደዚያ ባሰቃዩት ግዜ የተፈጠረውን ታሪክ እንዲህ ነው::

ሉቃስ 22፣58"ኢየሱስ ግን ይሁዳ ሆይ!በመሳም የሰውን ልጅ አሳልፈህ ትሰጣለህን አለው:: በዙሪያውም የነበሩት የሚሆነውን ባዩ ጊዜ ጌታ ሆይ በሰይፍ እንምታቸው አሉት:: ከእርሱም አንዱ የሊቀ ካህናቱ ባርያ መትቶ ቀኝ ጆሮውን ቆረጠው:: ኢየሱስ ግን መልሶ ይህንስ ፈቃዱ አለ፣ጆሮውንም ዳስሶ ፈወሰው" ይላል:: በዚህ ሰዓት ጆሮው ተበጥሶ የወደቀውን ሰው ሲፈውሰው እያዩ ግደለው ግለደው ያሉት ልበ ደንዳናዎች ነበሩ:: ወንጌል አስተማሪዎችም ተገለው እንጂ ገለው ክርስትና ሃይማኖትን አላስፋፉም:: ሐዋርያው ጴጥሮስ ያስተማራቸው ክርስቲያኖች በሮም አደባባይ ለአንበሳ ሲሰጡአቸው እንደነበር የተጻፈ እያነበብን ነው:: ክርስትና ሃይማኖት በዓለም እየደከመ የመጣው አስገድዶ ቤተ ክርስቲያን አለመውሰዱ ነው:: በተለይ ከ451 ዓም በሥልጣን

ስግብግብነት በሥነ መለኮት ካቶሊክና አርቶዶክስ ሁነው መለየታቸው የጠቀመው አዲስ ለተመሰረተው ለእስልምና ሃይማኖት ነው:: ሁለቱ ክርስቲያኖችን እስላሙ ሲጨፈጭፋቸው ዝምታን የመረጡበት ምክንያት በጦርነት የሰው ልጅ እንዳይሞት በማሰብ ነው:: ውሎ አድሮ በ12ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ ምዕራባውያን ኢየሩሳሌምን ለማስለቀቅ ያደረጉት ጥረት አልተሳካም:: ከዚህ ወዲህ በዓለም ዙሪያ የሃይማኖት ጦርነት ኀልቶ አልታየም:: በእርግጥ ጥቂት እስላሞች እየተገፉ መሆኑ ምልክቶች ይታያሉ:: ጠቅለል ባለ መልኩ የሃይማኖት ጦርነት አይባልም::

ኢትዮጵያ ውስጥ የሃይማኖት ጦርነት ሦስት ናቸው:: 1ኛው በ840 ዓም የተነሱት ንግሥት ዮዲት የክርስትና ሃይማኖትን ካወደሙ በኋላ ረገብ ብለው አገር መምራቱን ጀምረው ነበር:: በ880 ዓም እርሳቸው ሲሞቱ ክርስቲያኖች መልሰው ሥልጣኑን ያዙ:: 2ኛ ከ1517 ዓም ጀምሮ 1535 ዓም ድረስ በኢትዮጵያ የነበረው ጦርነት አጀማመሩ ገብሩ አንገብርም የሚል እንጂ የሃይማኖት ጦርነት አልነበረም:: ኋላ በ1519 ዓም ከየመንና ከቱርክ ከግብጽ የመጡቱ ወታደሮችና የእስልምና ሃይማኖት አስተማሪዎች ወደ ጅሃድነት ለውጠውታል:: በመቀጠል 3ኛው ከ1620 ዓም ላይ አጤ ሰስኒዮስ ካቶሊክ እምነትን ያልተቀበለውን ሕዝብ አጥቅተዋል:: በ14ኛውና በ15ኛው ክፍለ ዘመን የይፋት ወላስሞች ማለትም እስላሞች ጋር ይደረግ የነበረው ጦርነት ገብሩ አንገብርም እንጂ የሃይማኖት ጦርነት አልነበረም:: ሰሜን አውራጃ ይኖሩ የነበሩ ፈላሾች ጋር ይደረግ የነበረ ጦርነት ልክ ነው:: ፈላሾች አንገብርም አሉ:: የዚህን ረጅም ታሪክ በፈላሾች የተጻፈው መጽሐፍ እንዲህ ይገልጸዋል::

ሊቀ ካህናት ባርከው ያለው ከአባት የተገኘ ከጦር የተናኘ በተባለው መጽሐፉ ገጽ 62 "ከተራራው ሁነው ከላይ የጠላትን ጦር በአንድ መንገድ ከቦ እነርሱን ለመውጋት ሲመጣና ወደ ተራራው ጫፍ ለመድረስ ሲቃረብ ተመልክተው ያን የአሰለፉትን የድንጋይ ናዳ በዚያ በመጣው ጦር ላይ አከታትለው ሲሰዱበት ከላይ ከታች የተሰለፈው ጦር ሙሉጭ አድርገው ጨርሰው ይሰዱታል"ሲሉ ጽፈዋል:: ፈላሾች ሰሜን ላይ በር በሩን ይዘው በዚህ ዓይነት ይዋጉ ነበር:: ለመንግሥት አንገብርም ብለው ለብዙ መቶ ዓመታት ቆይተዋል:: በዚህ ምክንያት የትም ይንገሡ የት ገብሩ አንገብርም ተዋግተዋል:: ቅማኖችን በመጀመርያ አንገብርም አላሉም:: በሁለተኛ ክርስትናን ፈቅደው የተቀበሉ በመሆናቸው አንድም የአጤ ጦር ሌሎችን ሕገ ልቡና የሚያመልክቱን ምዕመን ክርስትና ተቀበሉ ብሎ የወጋቸው የለም:: ክርስትና ሃይማኖት በቅማንት ወረዳዎች የተመሠረቱት ቀደም ብሎ ነው:: ለምምሳሌ ከዚህ በታች ከተራ ቁጥር አንድ እስከ ሃያ አንድ ያሉት በሁለቱ አውራጃዎች የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት::

1ኛ ደንጎልቶ መድኃኒዓለም ቤተ ክርስቲያን የተመሰረተው በ1260 ዓም::
2ኛ ደምበሃ ኪዳነምህረት ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተው በ1260 ዓም ነው::
3ኛ ደምባህ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በ1268 ዓም:
4ኛ ማውራ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን የተሰራችው በ1268 ዓም ነው::

5ኛ አርሆና ቅዱስ ግዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የተመሰረተው በ1268 ዓም ነው::
6ኛ ጭልጋ አማኑኤል የተመሠረተው በ1268 ዓም ነው::
7ኛ ደብረ አቡነ ሳሙኤል የተመሠረተው በ1327 ዓም ነው::
8ኛ እማማ ገዳም ማህደረ ሠላም ቅድስት ማርያም በ1327 ዓም ነው::
9ኛ አቦ ገዳም አቦ የተመሰረተው በ1327 ዓም ነው::
10ኛ ወይኖች ቅዱስ ግዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የተመሰረተው በ1335 ዓም
11ኛ ተኩላ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በ1339 ዓም::
12ኛ ጃንካው ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተው በ1355 ዓም
13ኛ ጃንካው ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተው በ1414 ዓም::
14ኛ ድውድው ቅ/ማርያም ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችቅ በ1460 ዓም
15ኛ ከንታው ኪዳነምህረት የተመሠረተችው በ1460 ዓም ነው::
16ኛ አንከር ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን የተመሰረተው በ1460 ዓም ነው::
17ኛ አውደርዳ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተው በ1460 ዓም
18ኛ ሹመራ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የተመሰረተችው በ1460 ዓም ነው::
19ኛ ኢያሆ ቅድስት ማርያም የተመሠረተችው በ1487 ዓም ነው::
20ኛ ምድረአሮን ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የተሰራው በ1500 ዓም ነው::
21ኛ ከረዋ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተው በ1506 ዓም

እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በአጤ አሕመድ ግራኝ በ1531 ዓም ከተቃጠሉት መካከል ናቸው:: ከዚህ በፊት የተመሠረቱ አብያተ ክርስቲያናት በዚህ ጦርነት ሳይቃጠሉ የቀሩ ብዙ እንደነበሩ ሠነዶች ያስረዳሉ:: ይህ ከሆነ ቅማንቶች ተገደው ክርስትና ሃይማኖት በአጤ ዮሐንስ አልተቀበሉም:: ጠቅለል ባለ መልኩ የቅማንት ሕዝብ ክርስትና የተቀበለው ቀደም ብሎ እንጂ አቶ ነጋ እንዳሉት በ1880 ዓም ባጤ ዮሐንስ አይደለም:: የኢትዮጵያ ነገሥታት ጭካኔ ያሳደሩባቸው በሌሎች አማኞች ላይ ሳይሆን ክርስትና ሃይማኖትን ተቀብለው የተሳሳተ ትምህርት ያስተማሩትን ነው:: ልክ ጉራምቤ እንግዳ ሌሎችም በ14ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ ሰባኪያን የኑፋቄ ትምህርት ሲያስተምሩ ተው አንተውም በሚል በክርስቲያኖች ላይ ጭካኔ የተፈጸመ መሆኑን የነገሥታቱ ዜና መዋላቸው ይገልጻል:: በወሎ ክፍለ ሀገር መስጊድና ቤተ ክርስቲያን ማዶ ለማዶ እንደሆነው ሁሉ ቤተ ክርስቲያንና ድግናው ተቀራራቢ ሁነው መኖራቸውን ነው ተጽፎ የሚገኘው ሰነድ ያብራራል:: የቅማንት ልጆች ክርስትና እየተነሱ የድግናው ምዕመን እየቀነሰ መምጣቱ የክርስቲያን ሰባኪያን ስለ ጥምቀት መስበካቸው የድግናው ቁጥር መቀነሱ ልክ ነው:: አሁን በስደቱ ዓለም ካሉት ሰባኪያን መካከል አንዱ የቅማንት ልጅ ናቸው:: ለዚህ መጽሐፍ ዋቢ የጠቀስኳቸው 7 የቅማንት ልጆች የጻፏቸው መጽሐፍት ናቸው:: ከአቶ ነጋ በቀር እነዚህ 7ቱ የቅማንት ልጆች የጻፏቸው መጻሕፍት አንዳቸውም አልጻፉም:: ይህ ቅስቀሳ የወያኔ ወኪል አቶ ነጋ ብቻ ነው::

# ክፍል ሁለት

## ምዕራፍ 1

## ትግራይ የተወለዱ በ1761 ዓም ኢትዮጵያን አፈረሱ

1ኛ አጤ ኢያሱ አድያም ሰገድ ባለቤታቸው የትግራይ ተወላጅ ሲሆኑ ልጃቸው ከእናታቸው ወንድሞች ጋር ተባብረው አባታቸውን በ1698 ዓም ገድለው አጤ ተክለ ሃይማኖት ተብለው በኢትዮጵያ ሲነግሱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን እርጉም ተክለ ሃይማኖት ብሎ ይጠራቸው ነበር:: ይህ የሆነበት ምክንያት አባታቸውን ለስልጣን ሲሉ በመግደላቸው ነው:: በአጤ ኢያሱ አድያም ሰገድ በግፍ መገደል ጎጃሞች ይንገበገቡ ነበርና እርጉም ተክለ ሃይማኖት ለአደን በርሃ ወስደው በጦር ወግተው በ1700 ዓም ገደሉአቸው::

በ2ኛው አጤ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ ዘመን በ1747 ዓም ትግራይን ሲያስተዳድሩ የነበሩት ደጃዝማች ስሑል ሚካኤል ይባሉ ነበር:: እርሳቸው በባሕረ ነጋሽ አርኪኮ ብቅ እያሉ ከሚሄዱ ቱርኮች ጋር ተወዳጅተው የጦር መሣሪያ እያጠራቀሙ ራሳቸውን ማደራጀት ጀመሩ:: ከዚህ በኋላ ሸፈቱ:: አጤ ኢያሱ ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት ብለው ወደ ትግራይ ገሰገሱ:: ከዚያም ቅድሚያ በሰላም ግባ ተብለው ቢጠየቁ አልገባም አሉ:: ምክንያቱም ደጃዝማች ስሁል ዘመናዊ የጦር መሣሪያ የታጠቁ ቢሆንኑም ግን የአጤውን ሠራዊት ሊቋቋሙ አልቻሉም:: ቀድሞ እምቢ ብለው የነበረውን ሰላም በራሳቸው ፍላጎት ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ሽማግሌዎችን ላኩ:: አጤ ኢያሱም ይምጣ ሲሉ ለሽማግሌዎች መልስ ሰጡ:: ደጃዝማች እጃቸውን ሰጥተው ጎንደር በግዞት እንዲቀመጡ ተወሰነ:: ከዚያም ምሕረት ተደርጎላቸው ወይዘሮ አስቴር ኢያሱን እንዲያገቡ ተደርጎ ከደጃዝማችነት ራስ ተብለው ወደ ግዛታቸው ሄዱ::

አጤ ኢያሱ ሙተው ልጃቸው አጤ ኢዮአስ ሲነግሡ ራስ "እንኳን ደስ አልዎ"ለማለት የሚመጡ መስለው 26 ሺህ የጦር መሣሪያ ከቱርክ ተቀብለው ከትግሬ ጎንደር ገቡ:: ከዚያም ግንቦት 8 ቀን 1761 ዓም አጤ ኢዮአስ ኢያሱን በሻሽ አንቀው ገደሉ:: የነገሥታት ዘሮች ከሚታሰሩበት ወኅኒ አምባ አምጥተው ለ70 ዓመቱ አዛውንት እጎታቸውን ድረው እርሳቸው አድራጊ ፈጣሪ ሆኑ: የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባህሎች በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 295 "ራስ ስሑል ሚካኤል የተባለው ሰው ተነሥቶ ነገሥታቱን በየምክንያቱ አንዱን እየገደለ አንዱን እያነገሠ ኢትዮጵያን ለሥርዓት አልበኝነት አመራር ዳረጋት::

ከጥንት ጀምሮ ለኢትዮጵያ አንድነት ምልክት የነበሩት ነገሥታት ከተደፈሩ በኋላ በሌብነት፤በቀማኝነትና በስንፍና ወድቆ የነበረው ሁሉ አሁን በያለበት እኔ ልግዛ እኔ ልግዛ በመባባል ብጥብጥና ጦርነት ያካሂድ ጀመረ:: ትምህርትና ብስለት በሌላቸው ደደብ አለቆች መሪነት የተነሣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሞት

ፍርድ የተፈረደበት ለከፍተኛ የመጨረሻ ውድቀት የተጋለጠ አሳዛኝ ሕዝብ ሆነ:: ዘመነ መሳፍንት በሚባል ዘመን የሌቦች አለቆች ወሮበላ እንዲከተላቸው ዋና መጠቀሚያ ያደርጉት የነበረው መሣሪያ ዘር እየቆጠሩ የጨዋ ልጅ ነኝ በማለት ነበር:: እኔ በጣም የሚገርመኝ ወሮበላዎቹ እርስ በራሳቸው ፊታውራሪ፣ ደጃዝማች፥ ራስ ተባብለው ሕዝቡን እርስ በርስ እያፋጁ ኢትዮጵያን ያጠፉአት መሆናቸው ሲታወቅ መሳፍንትና መኳንንት መባላቸው ነው" ሲሉ ጽፈዋል::

የኢትዮጵያ ሥልጣኔ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 171 "ራስ ስሑል ሚካኤል በ1761 ዓም አጤ ኢዮአስን በሻሽ አሳንቆ አስገደለው:: በንጉሥ ሿሚና ሻሪነቱ የሚታወቀው ኃይሉ ራስ ስሑል ሚካኤል ባለሙሉ ሥልጣን በመሆን ለእርሱ አገዛዝ የሚመቹትን ነገሥታት ብቻ እየመረጠ በየጊዜው አንግሦአቸዋል" ሲሉ ጽፈዋል:: ራስ ስሑል ሚካኤል ኢትዮጵያን በፈላጭ ቆራጭነት በሥልጣን ላይ ሲኖሩ አገሪቱን እንዲያስተዳድሩ የፈቀዱላቸው ከቤተ ክርስቲያኑ እስከ ቤተ መንግሥቱ ለትግራይ ተወላጆች ነበር:: ዛሬ እንዳለው ሥርዓት ማለት ነው::

አንዴ ካንዱ ነገድ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሌላውን ነገድ እያደባደቡ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንዲተላለቅ አደረጉ:: በራስ ስሑል ምክንያት በኢትዮጵያ ውድቀት የታየበት የአንድነት ምልክት የጠፋበት ዘመን ነበር:: እነዚህ ከላይ የጠቀስኳቸው ሁለት የትግራይ ልጆችን ጸሐፊያን ያስቀደምኩት ወድጄ አይደለም:: ምክንያቱም ወቅቱ ክፉ በመሆኑ ነው:: በአሁኑ ሰዓት ታሪክን ገልብጠው የሚያቀርቡ የወያኔ ጸሐፊያን ስለበዙ የሌሎችን ጸሐፊያን የማይቀበሉ በመሆናቸው ነው:: አብሶም አማርኛ ተናጋሪ የጻፏቸው የታሪክ መጻሕፍት ውድቅ ለማድረግ አሁን የወያኔ ጀሌዎች የሥነ ልቦና ዘመቻ ጀምረዋል::

ዶ/ር ላጲሶ ጌ.ድሌቦ <u>የኢትዮጵያ የመከራ ሥርዓትና የኤርትራ ጥያቄ</u> በተባለ መጽሐፋ ገጽ 106 " በ1769 ራስ ሚካኤል ስሑል በጎንደር አጤ ኢዮአስን ጨምሮ የኦሮሞና የአማራ የሥልጣን ባላንጣዎቹን ለመቅጣት 26.000 ወታደሮቹን ይዞ ወደ ጎንደር ከተማ በገባ ጊዜ" ካሉ በኋላ ገጽ 107 "ራስ ሚካኤል ስሑል በአመጽ እርምጃ በጎንደር አጤ ኢዮአስንና ዕጨጌ ሰላማን በማስገደልና ሁለት ሌላ አሻንጉሊት ነገሥታትን ሹም ሽር በማድረግ በአካባቢው ዘመነ መሳፍንት ተብሎ የሚታወቀውንና እስከ ዳ/ዊ ቴዎድሮስ ድረስ የሚቆየውን የጦርነት ዘመንና ሥርዓት ከመሠረተው በኋላ በኦሮሞና በአማራ የጦር አበጋዞች ኅብረት በጦር ሜዳ ተሸንፎ በሰኔ 1772 ወደ ትግሬ ክልሉ በሽንፈት ተመለሰ" ሲሉ ጽፈዋል:: በራስ ስሑል የአገዛዝ ዘመን ኑቢያ የምትባለው የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር ሱዳን እንድትፈጠር ሆኖአል::

ማሞ ውድነህ <u>ዮሐንስ በ</u>ተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 19 "ሚካኤል ሥሑል ንጉሡን ከገደሉ በኋላ ራሳቸው ለመንገሥም አስበው ነበር:: ነገር ግን የአክሱም ካህናት ንጉሥ ገድለሃልና ልትነግሥ አይገባህም ስላሉዋቸው ወኅኒ አምባ ይባል በነበረው የነጋሥያን ዘሮች ማጎሪያ ታስረው ከነበሩት ለእርሳቸው የሚስማሙዋቸውን የሰባ ዓመቱን አዛውንት ዮሐንስን ከእስር ፈትተው አጼ

አሰኝተው አነገሡዋቸውና እርሳቸውም እንደ ተለመደው የእንደራሴነቱን ሥልጣን ያዙ:: ቀጥለውም እኅታቸውን ወ/ሮ ወለተ ሥላሴን ለሽማግሌው ንጉሥ ድረው ከንጉሥ በላቀ ክብርና ሥልጣን ተደላድለው እንደተቀመጡ አሁንም ከንጉሡ ጋር ተጣሉ:: ከአንድ ዓመት ንግሥና በኋላ አጤ ዮሐንስንም በእጅ አዙር አስገድለው የአጼውን ልጅ ተክለ ሃይማኖትን ስመ መንግሥታቸውን ኃያልሰገድ አሰኝተው በ15 ዓመት ዕድሜ አነገሡዋቸው:: እሳቸው በፈላጭ ቆራጭነታቸው ሥልጣን ቀጠሉ" ሲሉ ጽፈዋል::

አጤ ተክለ ሃይማኖት ብቻ በአስር ዓመት ውስጥ አስር ጊዜ ከዙፋን ወርደዋል:: አንዴ ስድስት ወር በሌላ ጊዜ አስር ቀን ብቻ የነገሡበት ጊዜ ነበር:: ራስ ስሑል የገደሉት አጤ ኢዮአስን ብቻ ሳይሆን ራሳቸው ያነገሡአቸውን 2ኛ አጤ ዮሐንስን ገድለዋል:: እኒህ የ70 ዓመት አዛውንት 2ኛው አጤ ዮሐንስ በሚበሉት ምግብ ላይ መርዝ ተጨምሮበት በልተው ሞቱ:: ጎጃም ውስጥ ደጃዝማች ፋሲል ለራስ ስሁል አልገዛም ብለው ሸፈቱ:: ራስ ስሁል ጎጃም ዳሞትና አገው ምድር ለመዝመት ሲያስቡ 2ኛ አጤ ዮሐንስን ይዘው መሄድ ፈለጉ:: አጤው አልዘምትም ሲሉ ራስ ስሁል ያደረጉት ነገር አጤውን ገለው ልጃቸውን የ15 ዓመቱን አነገሱ:: አዲሱን አጤ ይዘው ወደ ጎጃም ዘመቱ:: ልክ ወያኔ እንደሚያደርገው ማለት ነው:: ወያኔ መስራት የፈለገውን ራሱ ከወሰነ በኋላ ሌሎች እንዲፈጽሙለት ያደርጋል:: እንዳይነቃበት የታሰረውን ቤተሰብ ስልጣን ይሰጠዋል:: አቶ ታምራት ላይኔን አባሮ ሌላውን ብአዴን እንደሾመው ሁሉ ማለት ነው::

ወያኔ አንዱን ገድሎ ሌላውን የሚሾመው፤አንዱን አስሮ ሌላውን የሚሾመው ተንኮል የተማረው ከራስ ስሁል ሚካኤል ነው:: ራስ ስሁል በዚህ ምክንያት ዘመነ መሳፍንት በኢትዮጵያ መስርተው የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ እንዳይሆን ያደረጉት ሕዝቡ ሕብረት እንዳይኖረው ለማድረግ ነው:: ወያኔ ከተመሠረተ ጀምሮ ያደረገውን ሴራ ስትመረምሩ የራስን መሰሪ ተግባር በትክክል እየሰራበት ለመሆኑ በዚህ 24 ዓመታት ውስጥ የተፈጸሙትን እኩይ ሴራ መመልከት ይበቃል:: ኢትዮጵያ ከ1761-1845 ዓም የገጠማት ችግር ከባድና አሰቃቂ ነበር:: አሁንም ኢትዮጵያ ከ1983-2007 ዓም የገጠማት ችግር አንድ ነው:: ይህን ዘመነ መሳፍንት እንዳይነሳ ያደረጉት አንድ ለናቱ አጤ ቴዎድሮስ ጀመሩት ሌሎች ነገሥታትና ርዕሰ ብሔሮች አደረሱት::

ማን ያውቃል ከ2007 ዓም በኋላ አንድ ለናቱ ይነሳሳ ይሆን? በ1761 ዓም ነፍጥ አንግበው ከትግራይ ጎንደር የገቡት ቁጥራቸው 3000 መሆናቸው ይነገራል:: ወያኔም ከትግራይ ደደቢት ወደ አዲስ አበባ የገባው እጥፍ ድርብ ነበር:: ራስ ስሁል ከትግራይ ጎንደር ሲገቡ ደረቅ ጦር ይዘው ሲሆን ሌሎችን ወታደሮች የመለመሉ ጎንደር ከገቡ በኋላ ነው:: ወያኔ ደረቅ ጦሩን ይዞ ተከዜን ሲሻገር ሌሎችን ነገዶች እርሱ በፈለገው መንገድ ያደራጀው ጦር ነበረው:: እነዚያ 3000 ሺህ የራስ ስሁል ሠራዊት ብዙ ሆዳም አፍርተው ኢትዮጵያን 84 ዓመታት አመሰቃቀሉ::

# ምዕራፍ 2

## ኢትዮጵያን ለመገንባት የተደረገ ጥረት

ኢትዮጵያ ከ1761-1845 ዓም ደክማ ነበር:: የሚገርመው ነገር በነዚህ ዓመታት ውስጥ በጎንደርና በጎጃም ድንበር ቱርክን ይጋፈጡ የነበሩ መኳንንቶች ብዙ ነበሩ:: በነዚህ ዓመታት ውስጥ ከስናር እያፈገፈጉ ተዋግተዋቸዋል:: በነዚህ 42 ግዜ በሁለቱ ክፍለ ሀገራት የነበሩ መኳንንቶች ቱርክን ወግተዋል:: ከነዚህም መካከል አንዱ ደጃዝማች ክንፉ ኃይሉ የአጤ ቴዎድሮስ ወንድም ናቸው:: የኋላው አጤ ቴዎድሮስ ከትልቅ ወንድማቸው ከደጃዝማች ክንፉ ኃይሉ ጋር ሁነው ገዳሪፍ ላይ ቱርክን ወግተዋል:: ከዚህ ጀምሮ የአገር ፍቅር እሳት ከልባቸው ገብቶ ሊወጣላቸው አልቻለም:: ለዚህ አገር ፍቅር ልባቸው ውስጥ ያስገባው በግብጽና በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩ መነኩሴ ማህበረ ሥላሴ ገዳም ውስጥ ጥሩ አድርገው ስላስተማሩአቸው ነው::

አጤ ቴዎድሮስ ማኅበረ ሥላሴ ገዳም ውስጥ ግዕዝና አረብኛን ያስተማሩአቸው እኚሁ መነኩሴ ሲሆን አጤ ቴዎድሮስም ከገዳማቱ ሁሉ ማህበረ ሥላሴን ይወዱ ነበር:: በ1871 ዓም ልጃቸው ራስ መሸሻ ቴዎድሮስ አጽማቸውን ከመቅደላ ወደ ማኅበረ ሥላሴ የወሰዱበት ምክንያት አንደኛው ገዳሙን ስለሚወዱ ሲሆን ሁለተኛው መሬቱ እንዲጠበቅ ለትውልዱ እንዳይረሳው ለማድረግ ነው:: ይህ አካባቢ ለሱዳን አሁን ሊሰጥ ነው ሲባል ሁሉም ድምጹን አጥፍቷል:: ሆዳምነት አጥቅቶታል:: የታሪክ ተረካቢ መሆኑን ረስቷል::

ኢትዮጵያ አንድነት መሠረቱን የጣሉት ልጅ ካሳ ኃይሉ የኋላው ደጃዝማች ቆይተው አጤ ቴዎድሮስ ሲነሱ ከጋይንት ገብርዬ ከአገው ምድር ጎጃም እንግዳ ከጭልጋ ቅማንት ገለሞ እና አለሜ ሌሎች ተጨምረው ከልጅ ካሳ ጋር ገዳሪፍ ዘምተው ቱርክን ተዋጉ:: ከገዳሪፍ ጦርነት በኋላ ፊታቸውን ወደ ማዕከላዊው ኢትዮጵያ ምስረታ ሲያዞሩ ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው የቅማት ልጆች የኢትዮጵያን አንድነት ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር ሁነው መሰረቱ::

ግንቦት 10 ቀን 1860 ዓም የነገሱት አጤ ተክለጊዮርጊስ የኢትዮጵያ አንድነት ሊያጠናክሩ ሞክረዋል:: ሐምሌ 7 ቀን 1863 ዓም በትረ ሥልጣኑን የተረከቡት 4ኛው አጤ ዮሐንስ አስፋፉት እንጂ አላጠፉትም:: ሚያዝያ 25 ቀን 1881 ዓም "ባለህበት እርጋ ገኸሀ እኔ ነኝ"ያሉት አጤ ምኒልክ አሳደጉት:: ግንቦት 10 ቀን 1901 ዓም በሕዝብ ፊት አልጋ ወራሽ የሆኑት ልጅ ኢያሱ "ቀይ ባህር ፈረሴ ውሃ ሳይጠጣ ዘውድ አልጭንም"ያሉት ጅምሩን ከግቡ ለማድረስ ነበር:: መስከረም 9 ቀን 1909 ዓም በመኳንንቶች ምርጫ ዘውድ የጫኑት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ የኢትዮጵያ ዳር ደንበር ለማስከበር ጥረዋል:: የካቲት 25 ቀን 1922 ዓም በትረ ስልጣኑን ሙሉ በሙሉ አጤ ኃይለ ሥላሴ ሲጨብጡ

ከላይ የተጀመረውን የአገር አንድነት አስፋፍተው ኢትዮጵያ የቀይ ባህር ባለቤት እንድትሆን አደረጉ።

መስከረም 2 ቀን 1967 ዓም በትረ ሥልጣኑ በደርግ የተሰጣቸው ርዕሰ ብሔር ጄኔራል አማን አንዶም ጅምሩን ሊያፈርሱ ጥረዋል። ሕዳር 16 ቀን 1967 ዓም በደርግ በትረ ሥልጣኑ የተሰጣቸው ርዕሰ ብሔር ጄኔራል ተፈሪ ባንቲ ጅምሩን ከፍ ለማድረግ ለፍተዋል። ጥር 29 ቀን 1968 ዓም በትረ ሥልጣኑን በጃቸው ያስገቡት ርዕሰ ብሔር ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ባይሳካለቸውም ጅምሩን ከመግፋት አልተቆጠቡም። ሌላው ቢቀር ጋፋት የጦር መሳርያ ማምረቻ መመስረታቸው አንዱ ምስክር ነው። ግንቦት 13 ቀን 1983 ዓም ለ7 ቀን አገር የመሩት ርዕሰ ብሔር ጄኔራል ተስፋየ ገብረ ኪዳን የአንድነቱ መንፈስ እንደያዙት አብሮአቸው ተቀብሯል።

በነደጃዝማች ገለሞና በነደጃዝማች አለሜ የተጀመረው የኢትዮጵያ አንድነት ማጠናከር ከየካቲት 5 ቀን 1845 ዓም እስከ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም በየወቅቱ በትረ ሥልጣኑን የጨበጡ አጤዎች፤ሆኑ ርዕሰ ብሔሮች የኢትዮጵያን አንድነት ለማስጠበቅ ጥረት አድርገዋል። ዘመነ መሳፍንቱ መስራች ራስ ስሁል ሚካኤል ከትግራይ ጎንደር መጥተው የኢትዮጵያ አንድነት ያፈረሱት ግንቦት 8 ቀን 1761 ዓም ሲሆን ወያኔ ከትግራይ ተነስቶ መላ ኢትዮጵያን ተቆጣጥሮ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም በትረ ሥልጣኑን ሲጨብጥ የኢትዮጵያ አንድነት የፈረሰበት።

ግንቦት 8 ቀን በ1761 ዓም የኢትዮጵያ አንድነት የፈረሰበት
ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም የኢትዮጵያ አንድነት ሁለተኛ የፈረሰበት
ግንቦት 1997 ዓም የኢትዮጵያ ሕዝብ ደም የፈሰሰበት
ግንቦት በ2007 ዓም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ምን ይሆን የምታመጣለት?

ለመሆኑ አሁን ያለው ትውልድ ይህን የአባቶቻችን ተግባር ያውቅ ይሆን? ይህ የእኔው ዓይነት ትውልድ ከላይ ስማቸው የተጠቀሱትን ነገሥታትና ርዕሰ ብሔሮች ከማድነቅ ይልቅ ኢትዮጵያን ያደቀቁትን ርዕሰ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ አስረሱ ተሰማን ነው። ኢትዮጵያን ለመበታተን ልክ ነው ሠርተዋል፤ አንዳንዶችማ የማያፍሩ "ዘላለማዊ ሕይዎት ለጠቅላይ ሚንስትራችን"የሚሉ ካህናት ሳይቀሩ በቅለዋል። ባህር ዳር የተሰራው የሰማዕታት ሐውልት ውስጥ በትልቁ የርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ምስል ፎቶ ገጭ ብሏል። ታዲያ መፈከሩ "ከጠቅላይ ምኒስትር መለስ ዜናዊ ጋር ወደፊት"ይላል። የእኛው ትውልድ አገር አልሚዎችን ወንጅሎ አገር አጥፊዎችን አድንቋል። ለዚህ ተግባር ማህንዲሱ ደግሞ የራስ ስሁልን ዓላማ የተከተለው ሕወሓት ነው። የሕወሓት ዓላማ ኢትዮጵያን መበታተን ነው። ሕወሓት ተሳስቷል ከማለት ሕወሓት ደግ ሰርቷል የሚሉ በየነገዱ ሞልተዋል። ሕወሓት ጥሩ የሰራው ካለ እኔም ማድነቅ እችላለሁ። ግንከ የሰራው ጥሩ ስራ ባለመኖሩ አላደንቀውም።

# ምዕራፍ 3

## ትግራይ የተወለዱ ኢትዮጵያን በ1983 ዓም አፈረሱ!

ራስ ስሁል ሚካኤል ዘመነ መሳፍንቱን እንደመሰረቱ የየጁ አሮሞዎች የቤተ መንግሥቱ ዋናዎች በመሆናቸው ከቋራ አማሮች ጋር አዋጉአቸው:: ምክንያቱም የአጤ ኢዮአስ እናት እቴጌ በርናቤስ አሮሞ ናቸው:: የኢዮአስ አባት አማራ ናቸው በዚህ ምክንያት ሁለቱ ነገዶች አደባደቡ:: ራስ ስሁል ሕግ አዋቂ መሆናቸው ሲነገርላቸው በሰው ልጆች ላይ የፈጸሙት ጭካኔ የሕግ ሰው መሆን ቀርቶ ሕግ መኖሩን የሚያውቁ አይመስሉም:: ከእርሳቸው በፊት ማንም ሰውን ገድሎ ቆዳውን ገፎ ነበር ተብሎ ተጽፎ አላነበብኩም:: ራስ ስሁል ግን በጦርነት የማረኩትን ምርኮኛ ገድለው ቆዳውን ገለባ ሞልተው ማስፈራርያ አደረጉት::

ያሬድ ግርማ ኃይሌ <u>ጎንደር ታሪክ ከኢትዮጵያ ታሪክ አንጻር</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 233 "ራስ ስሁል ሚካኤል የዳሞትን ገዥ ፋሲልን ለመውጋት ንጉሠ ነገሥቱን ይዞ ሄደ:: ፋሲልም የዳሞትና የአገውን ጦር ይዞ ፍጊት በምትባለው ቦታ ሲጠብቅ ጦርነት ተከፍቶ በኃይለኛ ውጊያ ገጥመው ከግራ ቀኙ ቁጥር 10ሺ የሚደርስ ሰው ካለቀ በኋላ ድል የራስ ስሑል ሚካኤል ሲሆን ፋሲል ሸሽቶ አመለጠ:: ምርኮኞቹንም ራስ ስሑል በጭካኔ አስፈጇቸው:: ምሕረቱንም በመሻት የገቡትን የፋሲልን ተከታዮች ሁሉ ወታደሮቹ ኢ-ሰብአዊ በሆነ ጭካኔ እንደከብት ቆዳቸውን ገፈው በውስጡ ገለባ በመሙላት" ማስፈራርያ አደረጉት ሲሉ ጽፈዋል:: ይህን ታሪክ ሌሎችም ብዙ መጻሕፍት ዘግበውታል:: በኢትዮጵያ ታሪክ ብዙ ጨካኞች ኑረዋል:: ብዙ ነፍሰ ገዳዮች ነበሩ ከጭካኔቸው ብዛት የተተነሣ የተማረከን ሰው ገድለው ቆዳውን ገፈው ገለባ ሞልተው ማስፈራሪያ ያደርጉት ግን ራስ ስሁል ብቻ ናቸው::

<u>አሌፍ መጽሔት</u> ቁ 1 ነሐሴ 1984 ዓም ገጽ 17 "የቀድሞ ነገሥታትና ሹማምንት ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረባቸው ናቸው የተባለላቸውን ያህል ኢሰብአዊም ነበሩ:: ሚካኤል ስሁል ጎጃም ውስጥ በተደረገ ጦርነት ከጠላት ወገን የተማረከ ሰው አስገድለው ቆዳውን አስገፍፈው ቆዳውን አሰፍተው ድርቆሽ ከተው ምስል ማስፈራሪያ ማድረጋቸውን ዜና ስንሰማ ወይም እንደ ተረት ሲነገረን የሚያረጋግጠው ኢሰብአዊነታቸውን ነው" ሲል ጽፎአል መጽሔቱ:: ትግራይ የተወለዱ ለስልጣን ሲሉ በኢትዮጵያ ጥፋት ፈጽመዋል:: ምናልባት ይህን ስል አንዳንድ የወያኔ አባላት "ፀረ ትግሬ"እንደሚሉኝ ይገባኛል:: እስኪ ከዚህ ቀጥሎ የምጠቅሰውን በትግራይ ስም የተመሰረቱትን ድርጅቶችና ግለሰቦች ልጥቀሳቸው:: ለምሳሌ ከራስ ስሁል በመቀጠል ለሥልጣን ሲሉ ደጃዝማች ካሳ ምርጫ የኋላው አጤ ዮሐንስ አጤ ቴዎድሮስን ለማስገደልና የኢትዮጵያን ለማፍረስ እንግሊዞችን መርተው አምጥተዋል:: ይህ አልበቃ ብሎ ነሐሴ 5 ቀን 1863 ዓም ዳግማዊ አጤ ተክለ ጊዮርጊስን

የሕታቸውን ባል ገድለው ሥልጣን በጃቸው አስገቡ:: ይህ ከሆነ በኋላ እርሳቸው ኢትዮጵያን ለማሳደግ ጥረት አድርገዋል::
አጤ ዮሐንስ ሚያዝያ 1 ቀን 1881 ዓም ሲቆስሉ ሥልጣኑ ከትግራይ እንዳይወጣ ሲሉ የወንድማቸውን ልጅ ጥሩልኝ ሲሉ መሞቱ ተነገራቸው:: ቀጠል አድርገው አንደኛውን የወንድማቸውን ልጅ ራስ መንገሻን ጥሩልኝ አሉ:: ራስ መንገሻ ሲመጡ "ልጄ ስለሆነ አልጋ ወራሼ ነው"አሉ:: ራስ መንገሻ ጉግሳ ተብለው እንጂ የሚታወቁት ራስ መንገሻ ዮሐንስ ተብለው አልነበረምና አልጋ ወራሽ ነኝ ሲሉ ዳ/ዊ አጤ ምኒልክ ሚያዝያ 25 ቀን 1881 ዓም" ባለሕበት እርጋ ገኘሁ እኔ ነኝ"ብለው በማወጃቸው ሳይነግሡ ቀሩ:: በዚህ ቂም ይዘው ወደጣልያኖች ገብተው ነበር:: ሁኖም በሽምግልናና በእርቅ ተመልሰው ያን ታሪካዊ የአድዋን ድል አብረው ተካፋይ ሆኑ:: ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ሌሎች የአድዋ መኳንንቶች ወደ ጣልያን መግባታቸው አልቀረም::
1ኛ ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ አባ ጋብር ለጣልያን ማደራቸው ሳያንስ የትግራይ ክፍለ ሀገርን ለኤርትራ በወጨፎ መሸጣቸው ነው:: ትግርኛ የሚናገሩት ጥቂት ሰዎች በትግራይ ስም መነገዳቸው አይካድም:: በእውነቱ ከሆነ የአጤ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ለትግራይ ሕዝብ ከሌሎች ክፍለ ሀገራት አብልጦ በድሎም አልነበረም:: የአጤው አማች የነበሩት ደጃዝማች ጉግሣ ኃይለ ሥላሴ ጣልያንን ደግፈው የኢትዮጵያን ሕዝብ አስመትተዋል:: በአንጻሩ ደግሞ ብዙ የትግራይ ልጆች ሸዋ መንዝ ገብተው ጣልያንን የተዋጉ ነበሩ:: ለምሳሌ ደጃዝማች ገብረ መድህን አርአያ እስከ ልጃቸው ከነራስ አበበ አረጋይ ጋር ሁነው ተዋግተዋል::

ራስ ገብረ መድህን አርአያ ማለት የወይዘሮ አልጣሽ ቴዎድሮስ ልጅ ናቸው:: የሞቱት ሸዋ ሲሆን የተቀበሩት ደብረ ሊባኖስ ነው:: ልጃቸው ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ገብረ መድህን ከነራስ አበበ ጋር እንደነበሩ ታሪክ ምስክር ነው:: ይህ ሁኖ አገር ከወራሪ ስትላቀቅ የአጤው መንግሥት ትግራይ ውስጥ ዋጅራት በሚባለው አካባቢ ላይ የተፈጠረ ችግር ነበር:: በዚህ ምክንያት ቀዳማዊ ወያኔ ወይም ደግሞ ዓረና ተመሰረተ:: ከ1934-2000 ዓም ያለውን አንድ ባንድ በትግርኛ ተናጋሪዎች የተመሰረቱትን ድርጅቶች ልመዝግባቸው::

2ኛ የቀዳማዊ ወያኔ እንቅስቃሴ አጀማመር ታሪክ ለሚመረምረው የዋጅራት ሕዝብ በመንግሥት መበደሉ ግልጽ ነው:: ይህን የሕዝብ አመጽ ከፍተኛ እንዲሆን ያስተባበሩት ብላታ ኃይለ ማርያም ረዳ ናቸው:: ታሪኩ እንዲህ ነው፤ ኢትዮጵያ ከወራሪ ነፃ ከወጣች በኋላ ብላታ ሃይለ ማርያም ረዳ ወደ አዲስ አበባ ይሄዳሉ:: አጤው በትውልድ አገራቸው የወረዳ ገዥነት እንዲሰጣቸው ለራስ ስዩም ደብዳቤ ጽፈው ይሰጣቸዋል:: በነገራችን ላይ ብላታ ኀይለ ማርያም አባት ግራዝማች ረዳ ገብሩ የእንደርታና የላስታ ባላባቶች የአገር ተወላጅ ናቸው:: ኃይለ ማርያምን ረዳ ወደ አዲስ አበባ መጥተው አርበኝነታቸውን ተናግረው የወረዳ አስተዳደር እንዲሰጣቸው ደብዳቤ ተጽፎላቸው ወደ ትግራይ መጡ:: በዚህ ሰዓት ለእርሳቸው የተሰጠውን አስተዳደር ሥልጣን ለሌላ ሙሉ በሙሉ የትግራይ ተወላጅ ለሆነ ሰው ሰጡባባቸው:: የብላታ ኃይለ ማርያምን ስልጣን የተሰጠው ወረዳ ገዥው መሬታቸውን አረሰ:: የአካባቢው አዛውንቶች በሽምግልና ሊያዩ ቢሞክሩም ወረዳ ገዥው በንቀት ሸኛቸው:: እርሱና አምርቶ

እህሉን ሊጭን ሲል ብላታ ከአውድማው ሕደው አምስት ራሱን ገለው በርሃ ገቡ:: የእርሳቸው የቀዳማዊ ወያኔ መሪነት ከዚህ ይጀምራል::

አስፋው በላይ ወልድዬ ዝክረ አባ ደብልቅ በላይ ወልድዬ ፊታውራሪ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 155 "የሕዝብን እንቅስቃሴ አስኳል የነበረው የወጀራት ወረዳ ሕዝብ፣በገረብ፣ማለትም በወንዛችን ዳር እንገናኝ ተባብሎ ውስጥ ለውስጥ ተነጋግሮ በደረሰበት በደል ዙሪያ ለመመካከር በጋራ ወንዝ ላይ ተሰባስቦ እንደ ባህሉ መመካከር ጀመረ:: የወጀራት ወረዳ ሕዝብ ሀሳቡን ለመላ የእንድርታ ሕዝብ አሰራጨ:: በደሉ በሁሉም ዘንድ ደርሶ ስለነበር ዓረና ብለው በሃሳቡ ተስማምተው አንድነት ፈጠሩ"ይልና ገጽ 157 "ማን መሪ እናድርግ በሚልም ሽንጎው/ዓረና ተመካክሮ ቀደም ብሎ በደል የደረሰበትና ተበድሎ ጫካ ገብቶ የሸፈተ ብላታ ኃይለ ማርያም ረዳ አለ? እሱ ይምራን በሚል ሽንጎው/ ዓረና ተስማምቶበት ብላታ ኃይለ ማርያምን ጠርቶ የሕዝቡን ወያኔ አንተ እንድትመራው ዓረና ፈቅዶ ወስነዋል ተብሎ ተነገራቸው" ሲሉ ጽፈዋል::

አስፋው በላይ ወልድዬ ዝክረ አባ ደብልቅ በላይ ወልድዬ ፊታውራሪ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 158"1ኛ ዘርንና ሃይማኖትን ሳይለይ ማንኛውም ዓላማውን የሚደግፍ ሁሉ በተፈጥሮው የአፍቅሮ ነዋይ ባሕርይ የሌለበትና በጠቅላላም የሰው ገንዘብ የሚጸየፍ፣ለማስረጃ ያህል ዘርን በተመለከተ ብላታ ገማርያም ረፈሪ (በተለምዶ ገ/ማርያም ቁስጢ የጎጃም ተወላጅ የሽንጎው አባል ነበሩ:: 2ኛ የሥጋ ስግብግብነት የማያሸንፈው የግል ጥቅምን ሳይሆን የብዙሃን የሕዝብ ጥቅምን የሚያስቀድም 3ኛ የመጠጥ ሱስ የሌለበትና በመጠጥ የማይሸነፍ/ የማይሰክር 4ኛ ከሕዝብ ጋር በሆነውና ባልሆነው ጭቅጭቅና ንትርክ የማይወድ /የማይፈጥር 5ኛ በጭምትነቱና በአስተዋይነቱ በሕዝብ የተመሠከለት፣ የተመሰገነና ሕዝብን በሐቅ ለማገልገል ራሱን ያዘጋጀ፣6ኛ የራሱን ቤትና የአካባቢውን በመልካም ሁኔታ ማስተዳደር የሚችል፣7ኛ ከሁሉም በላይ ታማኝነቱን ለፈጣሪና ለሕዝብ የሆነና በሕብረተሰቡ መልካም ዝና ያለው ወዘተ የሚል ያካተተ መስፈርት ነበር" ሲሉ ጽፈዋል:: ይህን ዓላማ ይዞ ነበር ቀዳማዊ ወያኔ ወይም አረና በ1934 ዓም የተመሠረተው::

ይህ ቀዳማዊ ወያኔ ወይም ዓረና በኃይል በመጥፋቱ ምክንያት ትግራይ ውስጥ ታምቆ የቆየ ቂም ነበር:: ከነሐሴ 1953 ዓም ሻዕቢያ ካይሮ ከተመሰረተ ጀምሮ በቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ ዩንቨርስቲ ይማሩ የነበሩ ተማሪዎች መደራጀት ጀምሩ:: ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ጋር በብዛት የተሰለፉ ቢኖሩም ጥቂቶቹ ግን ከሻዕቢያና ከጅብሃ ጋር ሁነው መደራጀት ጀመሩ:: ከወያኔ በፊት የትግራይ ነገድ ድርጅት ተመስርቶ ኤርትራ የገባ ከጅብሃ ጋር ወዳጅነት የመሠረተ ድርጅት ነበር::
3ኛ ከጀብሃ ጋር ተጠግቶ የነበረው የግገሓት ድርጅት በነአቶ ዮሐንስ ተክለ ሃይማኖት እና በሌሎች የሚመራ ድርጅት ነበር:: ይህን ድርጅት ያጠፋው የዛሬው ወያኔ ነው:: ምክንያቱም በኤርትራ ውስጥ የነበሩት ሁለቱ ድርጅቶች ትግራይ ውስጥ ዘበኛ የሚሆናቸው ቡድን ይፈልጉ ነበር:: በዚህ ምክንያት ወያኔን ሻዕቢያ ሲያደራጅ የግሀሓት ድርጅትን ያደራጀ ደግሞ ጀብሃ ነው::

ወያኔ አብረን እንሰራለን ብሎ ለውይይት ጠርቶአቸው ሲወያዩ ውለው ባንድ ሲተኙ የዛሬው ወያኔ ሌሊት ፈጃቸው:: ያመለጡም አሉ:: ግን የዚህ ድርጅት ፍጻሜ የሆነው በወያኔ አምባ ገነንተን ምክንያት ነው:: በትግራይ ውስጥ ሌላም ድርጅት ነበር:: ይህ ድርጅት ጠራናፊት ይባላል::
4ኛ የጠራናፊት ኮሚቴ የተባለው ድርጅት የራሱ መተዳደርያ ደንብ የነበረው ሲሆን ውሎ አድሮ ኢዲዩ ሲመሰረት ከኢዲዩ ጋር ተቀላቅሎ ደርጅቶ ነበር:: የመጀመርያው ጠራናፊት ኋላ ኢዲዩ የሆነው ከትግራይ ጠራርጎ ያስወጣው እንደ ኢሕአፓ ወያኔ ነው:: ይህ ጠራናፊት ዓላማውና መተዳደሪያ ደንቡ ከዚህ ቀጥሎ ይቀርባል::

ግደይ ባህር ሹም <u>አሞራ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 139-140"ዓላማ አንድ ብሔር በህላዌነቱ፤በቋንቋው በባህሉ ወዘተ መበልጸግ አለበት:: ይህም ሲሆን አንድ ብሔር ሌላውን ብሔር በማናቸውም መንገድ ሲጨቁነው ሲረግጠው ግን ከዓለም ሕብረተሰብ ሕግ የወጣ አግባብ (ሥርዓት) ነው:: ከዚህ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው የዓለም ኅብረተሰብ ጉዳና መሠረት፤ይህ ብሔር በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔሮች ጋር በእኩልነትና በአንድነት መኳዝ አለበት:: መሠረተ ዓላማችን እንደሚከተለው ነው:: ዋናው ዓላማችን 1ኛ ለብሔራችን ሕላዌነት 2ኛ ለቋንቋችን፤ለታሪካችንና ባህላችን እድገት 3ኛ ለሕዝባችን የእኩልነት መብት 4ኛ ሕዝባችን ከምጣኔ ሀብት( ኢኮኖሚ) ድንቁርና፤ዝቆና ለማላቀቅና እድሉን በራሱ እንዲወስን ለማድረግ፤5ኛ የእኩልነት መብት ስንልም ሀ.የጹሑፍን ነፃነት ለ.የመሰብሰብ ነፃነት ሐ. ማኅበራት የማቋቋም ነፃነት ወዘተተ ያጠቃልላል 6ኛ የፆታ እኩልነት::"

"7ኛ የሃይማኖት እኩልነት 8ኛ የትግራይ ሕዝብ ከአንድ ሕብረተሰብ ዓለም የመጣ እንደመሆኑ መጠን የዘር ልዕልና ባሕሪይን ለማስወገድም ጭምር ሲሆን ጠራናፊት ኮሚቴ ዓላማው ምንድ ነው? ብሎ ለሚጠይቅ ይህንን ለመረዳት በሁለት ተጨባጭ ሁኔታ እንከፍለዋለለን፤ሀ.መሠረተ ዓላማ ለ.የመደብ ትግል ምንድን ነው? መሠረተ ዓላማው ከፍ ሲል ከአንድ እስከ ስምንት ተራ ቁጥር የተዘረዘሩት ሲሆን ለየትኛው መደብ ይተገላል?ለሚለው ጥያቄ ደግሞ ስለ ጭቁን የተራብ፤የታረዘ፤የትም በየቦታው በስደት ለሚንከራተተው የትግራይ ሕዝብ ለጭቁን ሴቶች ለአፈር ገፊው ገበሬ፤ለተማሪውና ለማንኛውም ሠራተኛው ክፍል ስለ ጠቅላላው ጭቁን የኢትዮጵያ ሕዝብና ጭቁን የዓለም ሕዝብ ይታገላል"ሲሉ አቶ ግደይ ባህር ሹም የትግርኛውን መተዳደርያ ደንብ ወደ አማርኛ ተርጉመው የመጽሐፋቸው አካል አድርገውታል::
5ኛ የአሁኑ ወያኔ የኢትዮጵያን በትረ ሥልጣን የተረከበው ድርጅት የተመሠረተው በየካቲት 11 ቀን 1967 ዓም ነው:: መነሻው ትግራይን ከኢትዮጵያ ገንጥሎ ሪፓብሊክ መንግሥት ለመመስረት እንደነበር የካቲት 1968 ዓም ያወጣው ማኒፌስቶ ዋቢ ነው:: ይህን ድርጅት አመሰራረት እና እነማን እንደመሰረቱት ወዳጄን አቶ ጌታቸው ረዳን መስራቾቹን ምስል ፎቶ ጨምረው ማስታወሺያ ጻፉልኝ ብዬ ጠይቄያቸው ነበር:: እግዚአብሔር ይስጣቸው ወያኔን የመሠረቱትን ግለሰቦች የቀድሞ ፎቶአቸውን ፈልገው ባንድ አድርገው ከማስታወሻ ጋር ልከውልኛል::

ጌታቸው ረዳ <u>የወያኔ መስራቾች ስም ዝርዝር</u> ብለው በጻፉልኝ ማስታወሻ“ የማህበረ ገስገሲት ብሔረ ትግራይ(ማገበት) መስራቾች በኋላ የማህበሩ ስም ወደ (ተሓህት ሓርነት ህዝቢ ትግራይ)ከዚያም (ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ) ብለው የመሠረቱት የድርጅቱ ዋነኛ መስራቾች የሚከለቱት ሰዎች ናቸው:: 1ኛ አረጋዊ በርሔ (በሪሁን) 2ኛ አምሃ ጸሃይ (አባይ) 3ኛ አምባዬ መስፍን( ስዩም) 4ኛ ዘርኡ ገሠሠ (አጋአዚ) 5ኛ ግደይ ዘርአጽዮን (ፈንታሁን)6ኛ ዓለም ሰገድ መንገሻ (ሃይሉ) 7ኛ ገሠሠው አየለ (ስሑል)በቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ ሁለት ግዜ ትግራይን ወክለው ለፓርላማ የተመረጡ 8ኛ ሙሉ ሀጎስ (አስፍሃ) ከላይ የተዘረዘሩት 8 ዋና የማገበት መስራቾች 8ቱ የቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች ናቸው:: እዚህ ላይ ከዋና መስራሮቹ ውስጥ ዓባይ ጸሐይ እና ሃይሉ መንገሻ የትጥቅ ትግል ለመጀመር እነ መለስ ዜናዊ፤ስዕል አብርሃ (ስዬ አብርሃ)ጭምር፤በጥር ወር አጋማሽ 1967 ዓም በቁጥራቸው 10 የሚሆኑ የማገበት አባላት የያዘ ቡድን በቀጥታ ከከተማ መርተው ለሥልጠና ወደ ኤርትራ ሄደው ስለነበር፤መነሺያቸው ሽሬ ያደረጉት ከነአረጋዊ እና ገሠሠው አየለ ጋር ወደ ደደቢት በርሃ አላመሩም:: ከኤርትራ ሥልጠና በኋላ ነው ከደደቢት መሥራቾች ጋር የተቀላቀሉት::”

“እነኚህ ተማሪዎች የበርሃ ልምድ ስላልነበራቸው መንገድ እንዲመሩአቸው እና በርሃውን እና ገጠሩ ለመዳሰስ እንዲረዷቸው የመሳሪያ ትጥቅ ለማካሄድ ትግል ወደ ተመሠረተበት ወደ ደደቢት በርሃ ከሽሬ አውራጃ እንዳስላሴ ከተማ መስራቾቹን መርተው በማታ ጭለማውን ተገን በማድረግ አብረዋቸው ወደ ደደቢት ያቀኑ ሰዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው:: 1ኛ አሰግድ ገብረ ሥላሴ (ትክክለኛ ስሙ ወልዳይ ገብረሥላሴ)በድሮው የቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ የምድር ጦር ሠራዊት አባል የአስር አለቃ ማዕረግ የነበረው እስራኤል አገር ድረስ የኮማንዶ ትምህርት የቀሰመ:: ውትድርናውን ትቶ በወቅቱ ወያኔን ሲቀላቀል በንግድ እና በእርሻ ሥራ ተሰማርቶ ነበር፤የህወሓት የመጀመሪያ ወታደራዊ አሰልጣኝ:: 2ኛካሕሳይ በርሔ (ምስግና) 3ኛ አብተው ታከለ (ሚካኤል ታከለ)ነገደ አማራ፤ የሽሬ ኗሪ ከአቶ ገሠሠው ቤተሰብ ጋር የጋብቻ ዝምድና የነበረው:: 4ኛ መብራሁቱ መላይ (ኮከብ) 5ኛ ብርሃነ አየለ (ፍትዊ) የገሠሠው አየለ ታናሽ ወንድም 6ኛ ንጉሠ ታዬ (ቀለበት) 7ኛ አረፋይነ ካሕሳይ (ፀሓይ) እዚህ ላይ ለማስገንዘብ አንዳንዱ ለምሳሌ አሰግድ ገብረ ሥላሴ ከተጠቀሱት ውስጥ 4 ብቻ ነን ከተመዘገቡት 6 የማገበት መሥራቾቹ ጋር ተቀላቅለን ወደ ደደቢት የሄድን ሲልሌሎች ደግሞ 5 እስከ 6 ያደርሷቸዋል፤ምክንያቱም አንዳንዶቹ ግማሽ መንገድ ሲቀላቀሏቸው ስለነበር ይመስላል:: እነኚህ ነጋዴዎች/ገበሬዎች እና ተማሪዎች የነበሩ ናቸው”ሲሉ የድርጅቱን ሕገ ደንብ ጽፈውልኛል::

6ኛ የካቲት 19 ቀን 1993 ዓም ሲሆን በኢሳት ቴቬዥን ሳምንታዊ ዜናና ቅስቀሳ ያደርጋል:: የቴሌቭዥኑ መርሃ ግብር የየካቲት ውለታ ይላል:: ድምህት በጦር መሣሪያ ወያኔን እፋለማለሁ ብሎ ኤርትራ ያለ ድርጅት ነው:: ይህ ድርጅት ዘመናዊ የጦር መሳሪያ የታጠቀ ቢሆንም ከ1993-2007 ዓም አንድ ቀበሌ አልያዘም:: ወያኔ በ14 ዓመቱ ከግማሽ በላይ ትግራይ ክፍለ ሀገርን ይዞ ነበር:: ውስጥ ለውስጥ ወሎና ጎንደር ገብቶም ነበር:: ታዲያ ድምህት

ሻዕቢያን እንዲጠብቅ ወያኔ የላካቸው ይሆን እንዴ? ያ ካልሆነ እንዴት በ14 ዓመታት ውስጥ አንድ ወረዳ ቀርቶ አንድ ቀበሌ ያልያዙ ናቸው::
7ኛ ዓረና መሠረታቸው የትግራይ ሕዝብ ነው:: ሌላም ጋሻ ለኢትዮያ የሚባል ድርጅትም ሲኖር የነሊቅ ዶ/ር አረጋዊ በርሄ የሚመሩት ተአንድ የሚባለው ድርጅት አለ:: 73 ዓመታት ያክል ትግራይ የተወለዱ ጥቂት ግለሰቦች የሚያነሱት ትግል አካባቢያዊ እንጂ አገር አቀፋዊ አይደለም:: በነገራችን ላይ ትግራይ የተወለዱ ከአገር አቀፍ ድርጅት አባል ሁነው የሞቱትንና የቆሰሉትን መካዴም አይደለም:: በአንጻሩ ከፍ ብዬ የጠቀስኩት ድርጅቶች ለሥልጣን ካልሆነ በቀር ሌላ ምን ሊባል ነው? በዚህ ዓይነት እያንዳንዱ ትግርኛ ተናጋሪ ሥልጣን ካልተሰጠው ለኢትዮጵያ ሰላም አይሰጥም የሚሉት አንዳንዶች ትክክል ነው ብሎ ለመቀበል የሚዳዳቸው አይጠፉም:: ትግርኛ ተናጋሪው ወሳኝ ከሆነ ወዲህም የተመሰረቱ ድርጅቶች አሉ:: ያም ሆነ ይህ ወያኔ ከትግራይ ወጥቶ እርሱ የሚያዘው ግንባር በራሱ አምሳል መሠረተ::

ከኢሕአፓ ተከፍሎ ትግራይ የገባ ቡድን ነበር:: ይህን ቡድን አሰልጥኖ ኢሕዴን የተባለ ድርጅት እንዲመሰረት አደረጉ:: ይህ ድርጅት ሕብረ ብሔር ድርጅት ነበር:: ኋላ ድርጅት ሌሎችንም ጨምረው ኢሕአዴግ የሚል ቅብ ቀብቶ መላ ኢትዮጵያን ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም ያዘ:: ከዚህ ወዲህ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን ነገዶች ብሔር የሚል ካባ አልብሶ ኢትዮጵያን በ9 ሲከልል በግማሽ ጎሳዎች ማንነታቸውን አጡ:: ለምሳሌ ደቡብ ክልል 45 ጎሳዎች ባንድ እንዲከለሉ ሲደረግ በምን ቋንቋ እንደሚግባቡ አልተወሰነም ነበር ቆይቶ ውጋጉዳ የሚባል ቋንቋ ይሁናችሁ ሲል ሕዝቡ አንቀበልም በማለቱ የፈሰሰው ደም ብዙ ነው:: ወያኔ ከማንኛውም ይልቅ ለአንቀጽ 39 ክብር ይሰጣል::

<u>የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ረቂቅ</u> ሚያዝያ 25 ቀን 1986 ዓም አንቀጽ 39“ 1. ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፤ብሔረሰብ፤ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከመገንጠል ያለው መብት በማናቸውም መልኩ ያለ ገደብ የተጠበቀ ነው:: 2.ማንኛው የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰብ ሕዝብ በቋንቋው የመማር፤የመጻፍ ቋንቋውን የማሳደግ እና ባህሉን የመግለጽ፤የማዳበርና የማስፋፋት እንዲሁም ታሪኩን የመንከባከብ መብት አለው:: 3.ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰብ፤ሕዝብ ራሱን የማስተዳደር ሙሉ መብት አለው ይህ መብት ብሔሩ፤ብሔረሰብ፤ሕዝቡ በሰፈረበት መልክዓ ምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋም እንዲሁም በክልልና በፌዴራል አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብትን ያጠቃልላል”ይላል::
አንቀጽ 39 ለኢትዮጵያ ሕዝብ አይጠቅምም::
አንቀጽ 39 የኢትዮጵያያ ብሔራዊ ማንነት ያስደፈረ ነው::
አንቀጽ 39 ኢትዮጵያ የባህር በር አልባ ያስቀረ ነው::
አንቀጽ 39 የኢትዮጵያን ትውልድ የከፋፈለ ነው::
አንቀጽ 39 የኢትዮጵያን ዳር ደንበር ያስደፈረ ነው::
አንቀጽ 39 አንዱ ነገድ ሌላውን ነገድ እንዲያጠቃው ያደረገ ነው::
አንቀጽ 39 ኢትዮጵያውያን ተዘዋውረው እንዳይኖሩ ያደረገ ነው::

አንቀጽ 39 በንግድ ስም መሬቷን ለውጭ ድርጅቶች ያሰጠ ነው::
አንቀጽ 39 የኢትዮጵያን ዜጎች ከመሬታቸው ያፈናቀለ ነው::
አንቀጽ 39 ፀረ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ነው::
አንቀጽ 39 ለሆዳሞች፤ለጥቅም ፈላጊዮች ካልሆነ በቀር ለማንም አይጠቅምም::

ሌላም የኢትዮጵያን ዳር ደንበር የሚያስደፍር አንቀጽ 2 "የኢትዮጵያ የግዛት ወሰን የፌዴራሉን ወሰን የሚያጠቃልል ሆኖ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት የተወሰነ ነው"ይላል:: ይህ አንቀጽ የኢትዮጵያን ወሰን እንዳይከበር የሚያደርግ አንቀጽ ነው:: አንድ ሕገ መንግሥት ደንበራችን ከዚህ እስከዚህ እያለ መገለጽ ነበረበት:: ወያኔ የኢትዮጵያን ዳር ደንበር እንዲከበር አይፈልግም:: ምክንያቱም ትግራይ ጠቅላይ ግዛት ያሉትን ወረዳዎች ለኤርትራ ሊሰጥ ያዘጋጀው አንቀጽ ነው:: ማስረጃ በባድሜና በሌሎች የትግራይ ክፍለ ሀገር ወረዳዎች ላይ ከሻዕቢያ ጋር በተደረገው ጦርነት ከ70-100 ሺህ ሕዝብ አልቆበት ያ ሁሉ የምጣኔ ሀብት ወድሞበት ርዕሰ ብሔር አቶ መለስ አልጀርስ የፈረሙት ኢትዮጵያን መሬት ለሻዕቢያ የሚያሰጥ ውል ነው::

ታጋይ ገሠሠ እንግዳ ታሪክ አጉዳፊው የአልባንያ ደብተራ የተባለው መጽሐፍ ገጽ 202 "ሻዕቢያ የኢትዮጵያ መሬትና ሉዓላዊነት በተለይም የትግራይን ሕዝብ ክብርና ማንነት እንዲደፈር ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ራሳቸው የሕወሓት መሪዎች መሆናቸው የተረጋገጠ ነው:: ይሁን እንጂ የትግራይ ሕዝብ ወልዶ ያሳደጋቸውና በደሙ ሥልጣን ላይ ያስቀመጣቸው መሪዎቹ ሲክዱት በአንጻሩ ቀፎው እንደተመታበት ንብ በቁጣ ከጫፍ እስከ ጫፍ ተነስቶ በጋራ ጠላት በሻዕቢያ ላይ በመዝመት በቀውጢ ቀን በመድረስ ከሞትና ከጥፋት ያዳነው ክብርና ምስጋና ይድረሰው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው:: የትግራይ ሕዝብ ደግሞ ከመበታተንና ከጥፋት ያዳኑት የሕወሓት መሪዎች ሳይሆኑ በአንጻሩ በየጊዜው ጠላትህ ነው እያሉ ሲያስተምሩት የነበሩትን ሰፊው የአማራ፤የኦሮሞ፤ጋምቤላ፤ደቡብ ሕዝብ፤አፋር፤አደሬ፤ጉራጌ የኢትዮጵያ ሱማሌና ሌሎች ብርቅዬ የቀውጢ ቀን የኢትዮጵያ ልጆች ናቸው"ሲሉ የወያኔው ታጋር ምስክርነታቸውንና ለትግራይም ሕዝብ ምክር ሰጥተዋል:: ወያኔ ሲነሳ ጀምሮ ትግራይን መንግሥት ለማድረግ አቅዶ እንደነበር ግልጽ ነው:: ለዚህም በትረ ሥልጣኑን እንደያዘ ኢትዮጵያን ልክ እንደራስ ስሁል ከፋፍሎ ማስተዳደር ጀመረ:: ይህ አስተዳደር ትክክል እንዳልሆነ እኛ የወያኔን አቋም የማንደግፈው ብቻ ሳንሆን የወያኔው መሥራች አቶ አሰግድ ገብረ ሥላሴ ወልደ ሚካኤል የወያኔ አስተዳደር ጥሩ እንዳልሆነ ጽፈዋል::
አሰግድ ገብረ ሥላሴ ወልደ ሚካኤል ገሐዲ2 በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 188 "መለስ ቋንቋ መሰረት ያደረገ ፌደራሊዝም ማዋቀሩ የሀገራችን ሕዝቦች በንጉሡና መንግሥቱ ስርዓቶች እንኳ ማንም ኢትዮጵያዊ በማንኛውም ክፍለ ሀገር ወረዳ ዞን ወዘተ..ሂዶ እንደትውልድ ቦታው ቆጥሮ ሙሉ መብት አግኝቶ ይሰራና ይኖር ነበር:: የመለስ ፌደራሊዝም የፈጠረው ችግር ግን ትግራይ አማራ፤ኦሮሞ ሂዶ አማራ ኦሮሞ ወይም ሱማሌ ኦሮሞ ደቡብ ጋንቤላ ሂዶ፤ዜጋ ነኝ ሀገሬ ነው ብሎ የማይሰራበትና የማይኖርበት ሁኔታ የፈጠረው ሌላው ቀርቶ ኩታ ገጠም በቅርብ የሚገናኙና በጋብቻ ይተሳሰሩ የነበሩ ሁሉ አሁን

ሁሉም የአስተዳደር ክልል ቋንቋ ስለተከለለ ጋብቻቸውና የገብያ ግንኙነታቸውን ሳይቀር እንዲለያዩ አድርጓቸዋል"ሲሉ ጽፈዋል። ይህ የወያኔ የከፋፍለህ ግዛው ዓላማ አርቆ አሳቢ ኢትዮጵያውያን ሁሌም ከመቃወም አልተቆጠቡም። ታዲያ ወያኔ መሰንበት የሚችለው በዚህ ዓይነት መሆኑን ከላይ ከራስ ስሁል የተማረውን በዶ/ር ዘውዴ ገብረ ሥላሴ ጥናት ተቀብሎ እየሰራበት ይገኛል። ወያኔ የሚሰራበትን ተግባር አጥንተው የሰጡት አንቱ የባሉት ዶ/ር ዘውዴ ናቸው።

አብነት ዘገየ፤ብሔርን መሠረት ያደረገው የሕወሓት/ኢሕአዴግ ፌዴራሊዝም ለኢትዮጵያ ይበጃል?በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 24 "አንድ አገር ሕዝቦችን በዘር እንዲከፋፍሉ (እርስ በርስ እንዳይስማሙ) አድርጎ መግዛት ከዚህ ሸፊትም እንደ ጣሊያንና እንግሊዝ ያሉ የአውሮፓ ቅኝ ገዥዎች የተጠቀሙበት ዘዴ መሆኑ በታሪክ በሰፊው ተዘግቧል። የከፋፍሎ መግዛት ዋና ዓላማ ቅኝ ገዥዎቹ ሕዝቦች በጋራ አምጸው ድል እንዳያደርጉ መከላከል ነው። አባምገነኑ ሕወሓት/ኢሕአዴግ ለመከላከል የሚሞክረውም የዚህ ዓይነት የጋራ አመጽ መጥቶበት ከሥልጣኑ እንዳይለይ ነው። ሟቹ አቶ መለስ ዜናዊ የአገሪቱን አንድነት ለመጠበቅ የሚቻለው ይህን (የብሔር ብሔረሰብና ሕዝብ የመገንጠልን መብት የሚደነግግ)ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም በመከተል ብቻ መሆኑን በወቅቱ መናገራቸው ይታወሳል። ሆኖም ይህን ምክንያት የሰጡት በይፋ በሚነገሩ ምክንያቶች ላይ ከፋፍሎ መግዛት የሕወሓት ዓላማ መሆኑ በይፋ ስለማይነገር (ማለትም ይህ ድብቅ ዓላማው መደበቅ ስላለበት)እንጂ ብቸኛው አማራጭ በመሆኑ አልነበረም"ሲሉ ጽፈዋል።

አሎ አይዳሂስ መሐመድ የአፋር ሕዝብ ትግል እና የፖለቲካ አቅጣጫ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 208 "በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የተሳሳተ አመለካከት የነበራቸው ሟቹ የሕወሀት መሪ መለስ ዜናው በዚህ እምነታቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሰማኒያ በላይ የተለያዩ ቋንቋዎች ያሏቸው የተለያዩ ብሔረሰቦች ስብስብ በመሆናቸው የሚያስተሳስሯቸው ምንም ነገር የላቸውም፤ስለዚህ ይህን የተለያየ ቋንቋ ያላቸውን ሕዝቦች ይበልጥ እንዲራራቁ በማድረግ ብሔረሰቦች መብት ስም ለረጅም ጊዜ ከፋፍሎ መግዛት ይቻላል በማለት ለዚሁ ስልጣናቸው ሲሉ በሕዝቡ መካከል ጥላቻን በመዝራት ባለፉት ሃያ ሁለት ዓመታት ከፍተኛ ማሕበራዊ ቀውስ እንደፈጠሩ ይታወቃል"ሲሉ ጽፈዋል። ወያኔዎች ለወደፊቱ ኢትዮጵያ የምትባል አገር እንድትኖር አይፈልጉም። ምናልባት ወያኔን የምትደግፉ የጥቅም ተጋሪ የሆናችሁ ልትስቁ ትችሉ ይሆናል አልፈርድባችሁም። በዚህ በ24 ዓመታት ውስጥ የተፈጠረውን ችግር አጥኑ። ዛሬ ያለችው የኢትዮጵያ ገጸምድር ካርታ ከዛሬ 20 ዓመት በኋላ ላትኖር ትችላለች። በትግራይ ለሻዕቢያ እንደሚሰጡት፤በጎንደር ለሱዳን እንደሰጡት በጋንቤላ ለደቡብ ሱዳን መስጠታቸው አይቀርም። እንዲሁም ለኬንያና ለሁለቱ ሱማሎች ሆነ ለጁቡቴ አከፋፍለው ኢትዮጵያን ከማጥፋታቸው በፊት ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል ሁሉ ወደ ጸሎት ቤት እንደሚጓዘው ምዕመን በአንድነት ወጥቶ ወያኔ አደብ እንዲገዙ ካላደረገ በቀር ኢትዮጵያ የምትባል አገር ነበረች መባሏ አይቀርም።

# ምዕራፍ 4

## ወያኔ እንደራስ ስሁል ቤተ ክርስቲያንን አደማ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዘመነ መሳፍንቱ ከፍተኛ የሆነ ውድቀት ደረሰባት፡፡ የቤተ ክርስቲያን ታሪክን ለሚመረምረው ከንግሥት ዮዲትና ከአጤ ግራኝ አህመድ፤ በአጤ ሱስንዮስ ከደረሰባት ውድቀት ይልቅ የዘመነ መሳፍንቱ የከፋ ነበር፡፡ ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግል ካህን በመጥፋቱ በተለይ በደቡብ ኢትዮጵያ በክርስቲያንነት ጸንተው የኖሩ ሁሉ በዘመነ መሳፍንቱ ወቅት አስተማሪ በማጣት ክርስቲያን እምነታቸውን ትተው እስልምና ሃይማኖት እንዲቀበሉ ሁነዋል፡፡

አባ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሊቀ ጳጳስ <u>የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 73 "ኢትዮጵያ በመሳፍንት በተከፋፈለች ጊዜ ግን የደቡብና የምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ብዙው ወደ እስልምና ወደ አረማዊነት ተለወጠ፡፡ በክርስትናቸው የጹኑትም እስከ አራት ትውልድ ድረስ ካህን አይተው አያውቁም ነበር፡፡ ሃይማኖታቸውንም የሚያውቁት ካባቶቻቸው ባገኙት ልማድ ብቻ ነበር፡፡ ለምሳሌ በሊሙ (እናርያ) አጠገብ ኖኖ በሚባለው አገርና ባካባቢውም ጥንት ሳይለወጥ የመጣውና የአባቶቻቸውን የክርስትና ሃይማኖት ጠብቀው የኖሩ ክርስቲያኖች ነበሩ፡፡ አጽዋማት በዓላትን ሳይቀር ባሕረ ሐሳብ ሳይኖራቸው ራሳቸው በልማድ ያወጧቸው ነበር፡፡ በአካባቢዋ ላሉት የክርስቲያን አውራጃዎችና መንደሮች መሪ ብርሃን የነበረችው ኖኖ ለመቶ ዓመታት ያህል ካህን አይታ አታውቅም ነበር፡፡ በቄስ ማጣት ምክንያት ብዙዎቹ ክርስቲያኖች እምነት እንጂ ጥምቀት አልነበራቸውም፡፡"

"ከኖኖ ቀጥሎ ብዙ ሕዝበ ክርስቲያን የሚኖርበት አገር ሞቻ የተባለው ነው፡፡ በሞቻ ግራኝ እንኳ ያላፈረሳቸው ብዙ አብያተ ክርስቲያንት ነበሩ፡፡ የዚህ አገር ክርስቲያኖች በየሳምንቱ እሑድ ወደ ቤተ ክርስቲያን በሚሰበሰቡበት ጊዜ ቀድሶ የሚያቆርብ ቄስ ስላልነበራቸው ልጆቻቸውን አዝለው ቤተ ክርስቲያኑን እየዞሩ ÷ንስእለኪ ማርያም ÷እያሉ ልመናቸውንና ጸሎታቸውን ለእግዚአብሔር አሰምተው ይመለሱ ነበር፡፡ ይህ ዓይነቱ የክርስቲያኖች ችግር በጣም እየባሰበት ሔደ፡፡ የዚህ ክፍል ባላባቶችና ታላላቅ ሰዎችም ከሱዳንና ከዓረብ አገሮች የሚመጡ ሽቱና ልዩ ልዩ የጌጥ ዕቃዎችን ለማግኘት ሲሉ ከዓረብ ነጋዴዎች ጋር ወዳጅነት አበጁ በዚህ ሳቢያ ዓረቦች ሃይማኖታቸውንም ቀስ በቀስ አስጠኗቸው÷የእስልምናን ሃይማኖት ያለምንም ችግር ተቀበሉ" ሲሉ ጽፈዋል፡፡በኢትዮጵያ ዳር በዳር ያሉ ክፍለ ሀገራት በዓረብ ነጋዴዎች እስልምና ሃይማኖትን ከፍተኛ እድገት አሳይቷል፡፡ ቀደም ሲል ጸረ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ናቸው ከተባሉት 3 ጦርነቶች ይልቅ ክርስቲያኑ ሕዝብ የባለገበት ጊዜ ነበር፡፡ "አንድ ወንድ ላንድ ሴት" ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው ትምህርት የተናቀበት ጊዜ ነበር፡፡ በተለይም በዚያን ወቅት ቄሶች

ሆዳቸው ከሞላ "በጎቼን ጠብቅ÷ጠቦቶቼን ግልገሎቼን አሰማራ "ተብሎ ለጴጥሮስ የተሰጠውን ትእዛዝ የነሱ አልመሰላቸውም ነበር::

ገብረ ዮሐንስ ገብረ ማርያም ክርስትና በኢትዮጵያ ክፍል 2 በተባለው መጽሐፋ ገጽ 59 "ያለምንም ቁጥጥር በየብስና በባሕር ንግድን እያመካኙ ወደገር የሚገቡ ዓረቦች የኢትዮጵያ የተቀደሰ ክርስቲያናዊ ጋብቻ እንዲበላሽ አድርገዋል:: በጋብቻ ላይ ጋብቻ መፈጸም ከዚያ በፊት እንኳን ድርጊቱ ጨርሶ አይታሰብም ነበር:: ዓረቦች የኢትዮጵያን ሕዝብ የጎዱት በጋብቻ ሥርዓት ማበላሸት ብቻ አይደለም:: ፉቅራ÷ቃልቻ÷እየተባሉ በየሰፈሩ በመስገድ በጥንቆላና በመተተኝነት እና እንዲመካ አድርገውታል:: ብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን ሥራዬ ብለው በዚሁ የአታላይነት ተግባር እንዲሰማሩ አድረገዋል:: ጠንቋዮች ክርስቲያኑን የኢትዮጵያን ሕዝብ እርስ በርሱ እንዳይተማመን በወንድሙ ላይ በጥላቻ እንዲነሣ እንዲገዳደል ሲያደርጉ ኑረዋል" ሲሉ ጽፈዋል::

የዘመነ መሳፍንቱ ድክመት ከአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በኢየሩሳሌም የነበረን ርስት ከ1010 ዓመተ ዓለም ጀምሮ የኢትዮጵያ የነበረውን ዴር ሱልጣን ገዳምን ግብጾች ኢትዮጵያውያን መነኮሳትን ገድለው ቁልፉን በእጃቸው ያስገቡበት ወቅት ነበር:: ዘመነ መሳፍንቱ እንኳን ኢየሩሳሌም ላሉት የገዳም ጠባቂዎች ቀለብ ሊልክ ቀርቶ መኖራቸውንም ረስቶአቸው ስለነበር ግብጾች በዚያን ወቅት የወሰዱት ቁልፍ ዛሬ የዓረብና የእስራኤል የሥነ መንግሥት ፖለቲካ መደራደሪያ ሁኖአል:: ይህን ገዳም የተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች፤ብቻ ሳይሆን የእስላሞችና የኦሪታውያን ርስት መሆኑ ታውቆ ለወደፊቱ ያላሠለሰ ጥረት የሚያስፈልገው ነው:: በእስራኤል የሚኖሩ የኦሪት አማኝ ኢትዮጵያውያን ዴር ሱልጣን ገዳም በሚፈጠረው ችግር ግንባር ቀደም ታሪክ ተረካቢዎች እንደምትሆኑ አልጠራጠርም:: ከኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር ልዩነታችን ጌታችን መወለዱን በመቀበልና ባለመቀበል እንጂ ልዩነት ስለሌለን የታሪክ ቅርሳችን የሁላችን ነው::

ዛሬም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ልክ በዘመነ መሳፍንቱ ወቅት እንደደረሰባት ዓይነት ችግር ገጥሟታል:: አሁን በቤተ ክርስቲያን ላይ የደረሰው ችግር ልክ በዘመነ መሳፍንቱ ወቅት እንደነበረው ነው:: በዘመነ መሳፍንት አገዛዝ የነበረው ቅባትና ካራ የፈጠረው ጭቅጭቅና ንትርክ ለቤተ ክርስቲያን ውድቀትን አስከትሎ ነበር:: ዛሬም ይህ የሃይማኖት ልዩነት እንዲበራከት ያደረጉ ናቸው:: በወያኔ ዘመን ቤተ ክርስቲያን እሳት የበላው ምዕመኑ በአንገታቸው የታረዱበት ገዳማቱ የፈረሱት ቅርሳቸው የተዘረፉት አንዱ ለምን ሲል ሌላው ዝም ሲል የተጎዳችው ቤተ ክርስቲያን ናት:: ለምሳሌ በጅማ ሆነ በሌላው ቦታ ቤተ ክርስቲያን ተደፈረ ማለት ጠብ ጫሪነት ነው ተብሎ ተወስዷል::

በጅማና በኢሉባቡር ክርስቲያኖች ሰማዕትነት ተቀበሉ ጥቅምት 2 ቀን 1999 ዓም ዳጎስ ያለ መጣጥፍ በሰፊው ዘግቦ ለአንባቢያን አቅርቧል:: 6 ምስል ፎቶ ጨምሮበታል:: ከሞት የተረፉትን ክርስቲያኖች ጥያቄና መልስ አድርጎ አቅርቦታል፤ በዚህ ዘገባ መሠረት ካህናቱ ታርደዋል:: ቤተ ክርስቲያናት

ተቃጥለዋል:: በግድ እንዲሰልሙ ሁነዋል:: ቤት ንብረት ወድሟል:: በገጽ 4"ከ620 ምዕመናን መካከል አምስት ሰዎች ብቻ አምልጠው ወደ አጋሮ ሲገቡ ሌሎች ሙሉ በሙሉ ተገደው እንዲሰልሙ ሁነዋል"ይልና ገጽ 7 "የኢሉባቦርና ጋምቤላ አህጉረ ሥራ አስኪያጅ እንደገለጹት በዴዴሳ ወረዳ የቤተ ክርስቲያን አካላት የሚናገሩት 800 የክርስቲያን ቤቶች ናቸው የተቃጠሉት ይላሉ:: የመንግሥት አካላት ደግሞ ከ450 በላይ የግለሰቦች ቤት መቃጠሉን ስድስት ክርስቲያኖች በአሰቃቂ ሁኔታ መገደላቸውን 987 ምዕመናን ከቤት ንብረታቸው በደንቢ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት ተጠልለው እንደሚገኙ ገልጿል"ሲል ጽፏል:: ከዚህ በኋላም የፕሮቴስታን ቤተ ክርስቲያን ከ59 በላይ ተቃጥለዋል:: የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን በወያኔ ዘመን ተበድለዋል::

ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል <u>በኢትዮጵያ የሃይማኖት መቻቻል</u> አለን? ከተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 25 "የሙስሊሞች እድር ከክርስቲያኖች እንዲለዩ እየተደረገ ነው:: ሠርጋችሁ ላይ ክርስቲያኖቹን አትጥሩ የተባለውን ትምህርት አንዳንዶች በመተግበር ላይ ናቸው" በማለት ጽፈዋል:: እኔ ሳውቃቸው እስላም ኢትዮጵያውያን ከክርስቲያኖች ጋር አብረው መኖራቸው ሲሆን በደስታና በመከራ አብረን ተባብረን መኖራችን ታሪካችን ነው:: ይህ አኩሪ ባህላችን አሁን የለም:: ከስደቱ አብረውኝ የነበሩ ኢትዮጵያውያን እስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ባልንጀሮቼ መካከል ትቶኝ ያልሄደው አንድ ለእናቱ አቶ ሞረች ብቻ ነው:: በዘመነ መሳፍንቱ ዘመን ክርስትና ሃይማኖት ብቻ ሳይሆን ስርዓቱ የተበላሸው በእስልምና ሃይማኖትም ጭምር ነው:: ለምሳሌ ከ1761 ዓም በፊት ፋቅራና ቃልቻ የሚባል አይታወቅም ነበር:: በዚህ በዘመነ መሳፍንቱ ዘመን ወቅት ግን በከፍተኛ ደረጃ ተስፋፍቶ ነበር ነበር::

ራስ ስሁል ለመንገስ አስበው በ1743 ዓም በቱርኮች አማካኝነት ጳጳስ ከአንጾኪያ አስመጥተው ነበር:: ወያኔም ለእስልምና ሃይማኖት አሰልጣኝ ከሶርያ አስመጥቷል:: ይህ አንሶት መሪያችሁን የምንመርጥላችሁ እኛ ነን ሲል አንተ ልትመርጥልን አትችልም ያሉትን አሸባሪ ብሎ ማሰሩ ግልጽ ነው:: በራስ ዘመን እስልምና ሃይማኖት ተስፋፍቷል ብልግናና አምልኮ ፋቅራና ቃልቻ በዝቶ ነበር:: በወያኔ ዘመን ደግሞ ተመልምለው የተሰለፉ በክርስቲያን ወንድሞቻቸው ላይ መሆኑ ነው:: በነገራችን ላይ ብዙኃኑ እስልምና ሃይማኖት ሳይሆን ጥላቻ የሚያካሂዱት አናሳዎች የወያኔ ጀሌዎች ናቸው::
በኢትዮጵያውያን እስልምና ሃይማኖት ውስጥ ገብቶ ሰላም ነሳው ወያኔ ሲሆን ርዕሰ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ በምክር በት ስብሰባ አዲሱን አልህበሽ የሚባለው እምነት ጥሩ መሆኑን መስክረዋል:: ቀጥሎም መሪዎቻቸው ራሳቸው መምረጥ አይችሉም መባሉ አግባብ አይደለም:: በነገራችን ላይ ከውስጥ እስከ ውጭ የወያኔን አቋም የሚደግፉ አሉ!ከዚህ ላይ ልንገነዘበው የሚገባን ነገር አለ:: ያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን የቤተ ክርስቲያንን መሪ ወያኔ ሲመርጥ አንቀበልም ያሉት በጣት የሚቆጠሩ ናቸው:: በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ግን እኛ ካልመረጥን አንተ አትመርጥልንም ያሉት ብዙኃኑ ናቸው::

# ምዕራፍ 5

## ትግራይ የተወለዱ ለሥልጣን ሲሉ አገር ሸጡ

በማንኛውም መንገድ በታሪክና በሕግ አሰብ የኢትዮጵያ አካል ናት። ይህ የእኔ አቋም ሳይሆን የ90 ሚልዮን ኢትዮጵያዊ አቋም ነው። እንኳን እኔና ብዙ ሚሊዮን ኢትዮጵያዊ ቀርቶ በወቅቱ በስልጣን ላይ የነበሩ ወያኔዎች ዛሬ የአሰብ ጉዳይ የእግር እሳት ሁኖባቸዋል። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አሰብን አትርሳ ከኢትዮጵያ ገጸምድር ካርታ አትለያት። ወያኔና የጥቅም ተጋሪዎቹ የሚሉትን አትስማ አሰብን አትርሳ።

ኤርትራ ሰላም የምታገኘው ትውልዱ በጉርብትና አብሮ የሚኖረው አሰብ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ ብቻ ነው። ይህን ከዚህ በፊት አሰብ የኢትዮጵያ አካል ናት ብዬ በጻፍኩት መጽሐፍ ገልጨዋለሁ አሁንም ይህን አቋሜን ከመግለጽ አልቆጠብም። አሰብ በዓለም አቀፍ ሕግ በፓሪስ ሆነ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኢትዮጵያ መሆኑን ነው። አፋሮች ረጅምና ትልቅ መጽሐፍ ጽፈዋል። ይህ ረጅምና ትልቅ መጽሐፍ 946 ገጽ ያለው ሲሆን እጅግ በጣም ትልቅ መጽሐፍ ነው። ይህ መጽሐፍ የታተመው“ 2000 ዓም 2007”ይላል። ይህ መጽሐፍ ቀይ ባህር የአፋር ግዛት መሆኑን ይገልጻል።

ሸህ ጀሉዲን ኢብራሂም ኸለል አ-ሻሚ <u>የአፋር/ደናኪል/ታሪክና መረጃ</u> አርኪ ምንጭ/አልመንሀል በተባለው መጽሐፍ ገጽ 29 “የሰሜን ሸለቆ ቀይ ባሕርን ይዞ ባሪ፤አራእታ፤ጋሊማሕ፤መብራ፤ ዓዶ ባዶ ጊኒበድ ራሓይታን አጠቃሎ ከራሓይታ እስከ ሐዮን እስከ ጅቡቴ ድረስ ይዘረጋል”ሲል ጽፈዋል። ከዚህ ከፍ ተብሎ ከተጠቀሰው መጽሐፍ የአፋር ገጸምድር ካርታ ነው። በ1983 ዓም ኢትዮጵያውያን ንብረታቸውን አሰብ ወደብ ላይ በሻዕቢያ ተዘርፈዋል። ይህ ዝርፊያ የተደረገው ወያኔ ተባባሪ በመሆኑ ነው። ሌላው ቀርቶ ትግርኛ ተናጋሪዎች ሻዕቢያ “አጋሜ”እያለ ንብረታቸውን ብቻ ሳይሆን በሕክምና ጥርሳቸው ውስጥ የገባላቸውን ወርቅ ሳይቀር ተወልቆ ተወስዷል። በዚህ ሰዓት መሬት ይክበዳቸውና ርዕሰ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ “የደርግ ሰዎች ናቸው” ብለው ተናግረዋል። ኢትዮጵያውያን በመላ ኤርትራ የተወረሰው ንብረት ብዛቱ አምላክ ይወቀው። በ1983 ዓም አሰብ በኩል የቀረውን ንብረት።

ዘውገ ገድሉ <u>ሪፖርተር ጋዜጣ ሰኞ ሰኔ</u> 8 ቀን 1990 ዓም ገጽ 5“ግንቦት 16 ቀን 1983 ዓም ሻዕቢያ ከመግባቱ በፊት አሰብ ወደብ ላይ ወደ 378 ሺህ ቶን የዕርዳታ ጭነት ከ5000 እስከ 7000 የሚደርሱ አውቶሞቢሎች ነው ጥለን የወጣነው። ከዚህ ውስጥ 178ሺህ ቶን የሚሆነው አጠቃላይ ጭነት ሲሆን 200 ሺህ ቶን የሚሆን ጭነት ነበር። ከአውቶምብሎቹ ጥቂቶቹን የተወሰኑ ነዋሪዎች ለሽሽት ይዘዋቸው ወደጅቡቴ ሄደዋል ተብሏል። በኋላም በጅቡቲ መንግሥት በተደረገ ትብብር ግለሰቦች እንኳን የደበቁት ሳይቀር ተመልሶ የጅቡቲ

መንግሥት ለኢትዮጵያ መንግሥት አስረክቧል"ሲሉ ጽፈዋል ይህን ያህል ንብረት የኢትዮጵያ ሕዝብ በአሰብ ወደብ አጥቷል። አቶ ዘውገ በአሁኑ ሰዓት አሜሪካ ስለሚኖሩ በ1990 ዓም የቀረ ንብረት እንዳለ ብዬ ጠይቄያቸው ነበር።

አቶ ዘውገ ገድሉ "ምን ይህ ብቻ በ1990 ዓም ብዙ ንብረት በአሰብ ወደብ ኢትዮጵያውያን ተነጥቀዋል። የማስታውሰው በመጠኑ ይህ ጀኔራል ካርጎ በአጠቃላይ የንግድ እቃ 145 ሺህ ቶን የእርዳታ እቃ 74 ሺህ ቶን ነዳጅና ቅባት 49 ሺህ ቶን ንጅ ወይም ካርታሜ 39 ሺህ ቶን 340 የጭነት መኪና 2000 ሺህ አውቶ ሞቢል 200 ማሽኖች ቀርተዋል"ሲሉ ነግረውኛል። ከላይ እርሳቸው በሪፖርት ጋዜጣ የጻፉት በ1983 ዓም የወጣው ትክክል መሆኑን አስረድተውኛል። ስለዚህ ኢትዮጵያውያን ብዙ ንብረት በአሰብ ወደብ አጥተዋል። ስለዚህ አሰብን በሕግ ማምጣት ይቻላል። በዚህ ወቅት ርዕሰ ብሔር አቶ መለስ አሰብን እንደማይጠይቁ ለኢትዮጵያውያን ሳይሆን ለምዕራባውያን ጋዜጠኞች ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵ ጋዜጣ መስከረም 24 ቀን 1993 ዓም ገጽ 7"በብሔራዊ ፕሬስ ክለብ ዋሽንግተን የአሰብን ወደብ የመጠቀም ጉዳይ በሰላም ድርድሩ ውስጥ የተካተተ ጉዳይ አይደለም። እኛም ልናደርገው አንፈልግም። ወደብ አልባ አገር መሆናችን እውነት ነው። በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት የወደብ መጠቀም መብት ያለን መሆኑም እውነት ነው። ይህን ጉዳይ በሰላም ድርድሩ ይዘት ውስጥ ያላካተትንባቸው የተወሰኑ ምክንያቶች አሉ" ሲሉ ተናግረው ነበር። በኢትዮጵያ ታሪክ መሬት የሸጡ ትግራይ የተወለዱ ግለሰቦች ናቸው። ቀደም ተከተሉን ስዘረዝር ለፈረንሳይ መንግሥት የባህር በር ለመሸጥ የተስማሙ ደጃዝማች ንጉሤ ወልደ ሚካኤል ቀዳሚ ናቸው። ለምሳሌ ደብዳቤያቸው እንዲህ ይላል።

ሰኔ 2 ቀን 1848 ዓም አባቴ ይሁኑ እኔም ልጅዎ እሆናለሁ። አሁን አንድ ንጉሥ ተነስቶ እኔን በማጥፋት ላይ ነው። ክርስቲያኖችንም እያ ጠፋ ነው። እንደ እውቀትዎ ይርዱኝ፤ ቢቻል በነሀሴ ባይቻልም በመስከረም እስከዚያም እቆያለሁ ከወዲያ ወዲህ እያልኩ። አቡን ያዕቆብን አባቴ አድርጌአለሁ። የእርስዎንም ትእዛዝ የማልጥስ ነኝ"ሲሉ ጻፉ። አጤ ቴዎድሮስ የካቶሊክን ካህናት ከኢትዮጵያ አባረዋቸው ስለነበር ነው "ክርስቲያኖችንም እያጠፋ ነው" የሚል ደብዳቤ ለፈረንሳይ መንግሥት ደጃዝማች ንጉሴ ወልደ ሚካኤል ሰኔ 1848 ዓም ደብዳቤ የጻፉት። ደጃዝማች በዚህ አላቆሙም ሌላም የእርዱኝ ደብዳቤ ጨመሩ እንጂ?

ጥቅምት 22 ቀን 1851 ዓም የአገሬን ነጻነት እንዲጠብቁልኝ እለምናለሁ፤ ከዘራፊውና ከአመጸኛው ከቴዎድሮስ እጅ ይጠብቁኝ። ይህንንም ለማድረግ ሁለት ነገሮች ያስፈልጉኛል፤መጀመርያ ከእናንተ ተወካይ ቢላክ ከዚህ በፊት እንደጠየክሁት ይህ በሀገሬ ውስጥ ያለውን ነገር ሁሉ እንዲመለከት እርሱም በአገሬ እንደራሴ አድርጌ እጠብቀዋለሁ። የፈረንሳይን ባንዴራ እተክላለሁ፤ ሁለተኛ የምፈልገው ሁለት መድፎች ከተኳሾቻቸው ጋር ነው። ለአደረጉልኝና

ለአገሬም ለሚያደርጉት እርዳታ ከባህር ዳር ዳርቻ ራስ ዱሚራ የሚባል ዙላን እሰጥዎታለሁ”የሚል ደብዳቤ ነበር።

በዚህ ምክንያት ፈረንሳይ ተወካዮች ወደ ትግራይ ገብተው ውሉን ሳይፈርሙ አጤ ቴዎድሮስ ገስግሰው ደርሰው ደጃዝማች ንጉሴ ወልደ ሚካኤልን ድል በማድረጋቸው የባህር በር መስጠቱ ተቋረጠ። ከደጃዝማች ንጉሴ ወልደ ሚካኤል በመቀጠል የኢትዮጵያ መሬት የሸጡ ሱልጣን ኢብራሂም ናቸው። እርሳቸው አሰብ ላይ ለከሰል መጋዘን የሚሆን 12 ጋሻ መሬት ለካቶሊክ መነኮሳት የሸጡ። በዚህ መሬት ተሳቦ ጣልያን ወደ ኢትዮጵያ መግባት ለአድዋ ጦርነት መንስኤ ሆነ። ለወደፊቱም የአሰብ ጉዳይ የማይጠፋ የተዳፈነ የእሳት ረመጥ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ አሰብን ካላስመለሰ ሰላም እንደማይኖረው ግልጽ ነው። በነገራችን ላይ ሱልጣን ኢብራሂም አፋር እንጂ ትግራይ አይደሉም። ሦስተኛው መሬት ለሥልጣን ሲሉ የሸጡ ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ አባጋብር የደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴ አባት ናቸው።

ግደይ ባህር ሹም <u>አሞራ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 276-277
“እኔን ይብላኝልኝ ኢትዮጵያ ውዲቱ
የመሀል አገሩስ ምናለ ወጣቱ
ምነው አይናገር የሸዋ ወጣት
ኦሮሞና ትግሬ ሲቀራመቱት
ጎጃምና ጎንደር፤ከማን ጋር ነህ አሉህ
ከግራና ከቀኝ ሲከፋፍሉህ
ኦሮሞ ነህ ብለው ተገንጠል ሲሉት
ምን አለ ጎጃሜ፤ ሲቀራመቱት።”

“መተማና ወልቃይት ለትግራይ ነው ሲባል
በአገር መቆራረስ ጎንደር ምን ያድባል
ጠቅልለው ሲያርቁት አሰብን ከወሎ
አፋር ምን ያስባል?ጉድ አሰማኝ ብሎ
ትግራይ ምን ያስባል ምስጢር ያላወቀ
በሰሜን በደቡብ የተጠረቀቀ
በእውነት የተሸጠ ማስመለስ ከቻሉ
ምነው ታድያ አውጋሮን ትግራይ ነው አላሉ?”

“ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ለሸጡት ምድር
በምዕራብ ትግራይ የከሰላ ምድር
የትግራይ ባላባት ያስቆጣው ነበር
በወጨፎ ብረት ተሸጦ ምድር
ትግራይ ተቆርሳለች በሰቲት ድንበር
አውጋሮና ጎልጅ ኡምሀጅር ተሰነይ ደንበር
መቶ ዓመት በአልሞላ የትግራይ ነበር
የአድዋ ባላባት ደጃዝማች ገረሥላሴ

ሸጡት በወጨፎ ሕዝብ እየወቀሰ
ካለነሱ በቀር የለም ሌላ ባንዳ
ለትግራይ መቆረስ ዓድዋ ነው ባለዕዳ"ሲሉ ጽፈዋል::

አራተኛው ወያኔ ኢትዮጵያ የባህር በር እንዳይኖራት አደርጓል:: ይህ አልበቃ ብሎ ልክ እንደ ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ የትግራይን መሬት ለሻዕቢያ ሊሰጥ ነው:: አምስተኛ የኢትዮጵያ አርሶአደሮች መሬታቸውን እየነጠቀ ለውጭ ድርጅቶች የሸጠ ወያኔ ነው:: ዓለም አቀፍ ተቋማት እየጮሁ፤የኢትዮጵያ መሬት በንግድ ኢንቨስትመት ስም እየሸጠ ነው:: መሬት መስጠቱን አስመልክቶ ገብሩ አስራት ገጽ 488 "በአሁኑ ጊዜ ከመሬት መፈናቀል የኢትዮጵያን አርሶና አርብቶ አደሮችን ሥጋት ላይ ጥሏል:: የኢሕአዴግ መንግሥት እድገት ለማስመዝገብ ከነደፋቸው ዕቅዶች አንዱ ሰፊ መሬት ለውጭ በተወሰነ ደረጃም ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ሰጥቶ ዘመናዊ አርሻዎችን ማቋቋምን ነው:: በዕቅዱ መሠረት 5 ሚልዮን ሂክታር መሬት ለአልሚዎች ከመርሻል እንቨስተር ይሰጣል ተብሏል:: ይህ የመሬት ስፋት ከምዕራብ አውሮፓዋ ከታላቋ ብሪታንያጋ ይመጣጠናል:: ይህ ለልማት ይውላል የተባለው መሬት በአብዛኛው በጋንቤላና በቤኒሻንጉል የሚገኝ ቢሆንም በኦሮሚያ፤በአማራ፤በደቡብ፤በአፋርና በሌሎች ክልሎችም ለልማቱ የሚውል መሬት ተቀይሷል"ሲሉ ጽፈዋል::

ስድስተኛው ከሁመራ እስከ ጋንቤላ 1600 ኪሎ ሜትር ለሱዳን ሊሰጥ ነው:: ታላቁ ማህበረ ሥላሴ ገዳም አብሮ ለሱዳን ይሰጣል:: የአጤ ቴዎድሮስ አጽም ያረፈበት ገዳም ለሱዳን ሊሰጥ ነው:: የአጤ ቴዎድሮስ አጽም ከማህበረ ሥላሴ ገዳም ይውጣና ወደ መቅደላ ይወሰድ:: ወያኔ እንኳን የአማራውን ክፍለ ሀገር ሊያስጠብቅ ቀርቶ የትግራይን መሬት ለሻዕቢያ አሳልፎ የሰጠ ድርጅት በመሆኑ ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክህንና አገርህን መጠበቅ የምትችለው በራስህ መሆኑን ተረዳ:: ወያኔ ነገ ሌላም አገር ይሸጣል በዚህ አያቆምም:: የአባይ ጉዳይም እንዲሁ በውዝፍ ላይ ነው:: ከቅድመ ዓለም እስከ አሁን ድረስ የኢትዮጵያ ነገሥታትና ርዕሰ ብሔር አባይን አስመልክቶ የተኙበት ወቅት ፈጽሞ የለም:: የደርጉ መንግሥት ጠቅላይ ምኒስትር ሻምበል ፍቅረ ሥላሴ ወግደረስ ጹሑፍ ዋቢ ነው:: ይህን የአባይ ጉዳይ የወያኔም መንግሥት ሊፈርም ተቃርቧል ተብሎ እየተናፈሰ ነው:: ጥቅሙ ለኢትዮጵያ ይሁን ለግብጽ ግልጽ የሆነ ነገር ባለመኖሩ አስተያየት ባልሰጥ ይሻላል::

ይህን መሬት የሚሸጥ መንግሥት ደጋፊው መሬት ቅርምቱን ስደተኛው ሕዝብም ከግማሽ በላይ ማለት ይቻላል የወያኔ ካዝና አሚይ ሁኖአል:: ውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና በየክልል ከተማው "የዲያስፓራ"ዴስክ የሚባል ቅርንጫፍ ተቋቁሞአል:: ይህ በወያኔ ቋንቋ ዲያስፓራ የሚባለውን ሆዳም ቡድን አስመልክቶ አንዱ ወዳጄ መጽሐፍ እየጻፈ እንደሆነ ነግሮኛል:: ይህ መጽሐፍ ወጥቶ አይቸው ደስ ባለኝ:: በ9ኙ ክልል "የዲያስፓራ ዴስክ"ከሚባለው የስም ዝርዝ ያገኜ መሆኑን ነግሮኛል::

# ምዕራፍ 6

## ወያኔ ሆዳም ስደተኛውን በጥቅም ያዘው

ትንቢተ ኢሳይያስ 5፤20"ክፉውን መልካም፤መልካሙን ክፉ፤ለሚሉ፤ጨለማውን ብርሃን፤ብርሃኑንም ጨለማ ለሚያደርጉ፤ጣፋጩን መራራ፤መራራውንም ጣፋጭ ለሚያደርጉ ወዮላቸው"ይላል ቅዱስ መጸሐፍ:: አሁን ከወያኔ በላይ ወያኔ የሆኑ ሆዳም ስደተኞች ናቸው:: ወያኔ ስደተኛውን ሕዝብ በጥቅም መሳሪያ አድርጎታል:: በግልና በጋራ መሬት ነጠቃውን ተያያዘው ከወያኔ ጋር እየተነጋገረ ወደ ሀገር ቤት ይገባ ጀመር:: እርሱ ውጭ ያጠራቀመውን ዶላር ይዞ አገር ቤት ሲገባ ነዋሪው ሕዝብ ከገብያ አስወጣ::

የንግዱን ዓለም ውጭ የሄደው ሲቀላቀል ነዋሪው ነጋዴ የያዘውን ትንሽ ቤት በልማት በእንቨስትመት ስም እንዲለቅ ተደረገ:: ይህ ነዋሪው ነጋዴ ተገዶ ሲለቅ የገባበት ስደተኛው ነው:: ፍርድ ቤት ሕደው አቤት ሲሉ ቅሬታ አስወጋጅ ሕግ አውጥተው ሰሚ እንዲያጣ ተደርገዋል:: ለነዚህ ወገኖቻችን ወያኔ ብቻ ሳይሆን ስደተኛው ሕዝብም ተባባሪ ነው:: አንዲት እህት ቤታቸው ተወስዶባቸው አቤት ብለው ሰሚ መጣታቸውን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ገልጸዋል::

እታገኝ መኮነን ካሣ <u>ነገረ ኢትዮጵያ ጋዜጣ</u> ግንቦት 15 ቀን 2006 ዓም ገጽ 4" መጋቢት 24 ቀን 2006 ዓም በፖሊስና በመሣርያ ኃይል ከግቢ አውጥተውኝ ስምንት ቤተሰቤን ይዤ ንብረቴን ውጭ ተጥሎ ለዝናብና ለፀሐይ እንዲጋለጥ በማድረግ ከፍተኛ ውድመት እንዲደርስብኝ አድርገዋል:: በየደረጃው ላሉት የመንግሥት አካላት በተደጋጋሚ አቤት ብልም ቤቱን ለፈለጉት ሰው ለመስጠት ሲሉ ያላደረኩትን አድራጎት እያቀረቡ ጥፋተኛ ነሽ በማለት ለረዥም ወራት እያንከራተቱኝ መሂጃው ጠፍቶብኝ እገኛለሁ:: ሁከት ስለፈጠሩብኝ ይወገድልኝ ጥያቄ ለፍርድ ቤት ባቀርብም የወረዳ 09 ቤቶች ልማት ጽሕፈት ቤት የሀሰት ማስረጃ እያቀረቡ ሁከት አልፈጠርነም በማለት ውሳኔ ተሰጠብኝ"ሲሉ ተናግረዋል:: ይህን የሚያደርግ መንግሥት ነው ሆዳቸው አምላካቸው ክብራቸው ነውራቸው የሆኑ ስደተኞች የሚደግፉት?

<u>ዘራፍ</u> የተባለው ተውኔት ከልብ ለተመለከተ ትምህርት ይሰጣል:: በአሁኑ ሰዓት ቻይና ሰራሽ እቃ የኢትዮጵያን ሕዝብ እያሰቃየ እንደሆነ የሚገልጽ ነው:: ታዲያ ይህን የመሰለ ሕዝቡን የሚጠቅም መልዕክት ተውኔት ወጭውን ካልሸፈነ ባለሞያዎች ሁለተኛ አይሰሩም:: ባለሞያዎች ካልሰሩ ሕብረተሰቡ መበደሉን ሊያውቅ አይችልም:: ዘራፍ የተባለውን ተውኔት ስደተኞች ባለሱቆች ቸብችበውታል:: ሌሎችንም የተውኔን ውጤቶች ሆኑ ዘፈኖች ያለ ባለቤቱ ፈቃድ የሸጡባቸው መሆናቸውን ባለሞያዎች እያለቀሱ ይገኛሉ:: ማቴ 21፤13 "ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ ተጽፎአል፤እናንተ ግን የወንበዶች ዋሻ አደረጋችኋት አላቸው "ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስተምሮ ነበር::

ከዚህ ላይ ላስገነዝበው የምፈልገው ነገር ቢኖር ስደተኛው የወያኔ ዋሻ መሆኑ ነው። ርዕሰ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ መሬት ይክበዳቸውና ሲሞቱ አዲስ አበባ ያሉት ብቻ ሳይሆኑ "አልሞቱም" ብለው ሲከራከሩ የነበሩ ሆዳሞች ስደተኞች ናቸው። ልብ በሉ የሞቱትን ሰው አልሞቱም ያሉ ግለሰቦች እንዴት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም ሊቆሙ ይችላሉ?

ቀደም ሲል የልደት በዓል ወደ ኢትዮጵያ የሚሄዱ ስደተኞችን ወያኔ እራት ይጋብዝ ነበር። ከዚያም መሬት ይሰጣቸዋል። አንዳንዶቹ እየመጡ ስላፈነገጡ መላ ፈለገ። ያም ቤት የገዛውን ሁሉ የእጣት አሻራ አዲስ አበባ ሕዶ እንዲሰጥ ማስታወቂያ ለጠፈ። ስደተኛው አንዳንዱ ወደ አዲስ አበባ አለመሄዱን ሲያውቅ ካናዳ እቶኋ ዋሽንግተን ዲሲና ሎስ አንጀለስ የጣት አሻራ እንዲሰጥ አደረገ። በዚህ ምክንያት የእስታር ባክስ አርበኛ ሎስ አንጀለስ ያለው ዋሽንግነት ሕዶ የጣት አሻራ ሲሰጥ ዋሽንግተኑ ካናዳ እቶኋ ሕዶ እንዲሰጥ። ካናዳ ያለው ዋሽንግተን ሕዶ የጣት አሻራ ሰጥቷል። ስንቱ ጳጳሳትና መነኩሳት የጣት አሻራ ሰጥተዋል። ከዚያ በኋላ ወያኔ ጠንከር ያለ ንግግር እንዳያደርጉ በገንዛ ገንዘባቸው መያዣ አደረጋቸው።

አንድ የጎንደር ሰው መጽሐፍ ጽፈው ለማሳተም ወሰኑ። በኋላ ግን ተውት። እኔም አንዴ በአካል አግኝቻቸው መጽሐፉ ታተመ እንዴ ስላቸው መልሳቸው "ንብረት ስላለኝና ቤተሰቦቼም በስልጣን ላይ ስላሉ ላሳትመው አልቻልኩም" ብለውኛል። ተመልከቱ ሌሎች ሕይዎታቸውን ይሰጣሉ እኒህ ሆዳም ግን ይህን አሉ። አንድ አዛውንት የሕይወት ታሪካቸውን ዳሰስ ያለ መጽሐፍ ጽፈዋል። ሊታተም ሲል ልጆች እንዳይታተም አደረጉ። አባት ለምን ሲሉ የተሰጣቸው መልስ" ኢሕአዴግን ወቅሰሃል። ይህ መጽሐፍ ከታተመ የእኛ ንብረት ይወረሳል አሉአቸው። አንድ ቀን የባልንጀራቸው ልጅ "ስልክ ይደውላሉ። እኒህ አባት የተሰማቸውን ለባልንጀራቸው ልጅ ተናገሩ። እኒያ ወይዘሮ ሞረሽም ወደኔ ስልክ ደውለው የሆነውን ሁሉ አስረዱኝ። እኔ የተጻፈው መገኘት የሚችል ከሆን ማተሚያ ለማግኘት ይቻላል አልኳቸው። እኒያ ወይዘሮ ሞረሽ አዛውንቱን ሲጠይቁ ሲዲውን ላኩላቸው። ሲዲውን ወይዘሮ ሞረሽ ሰጥተውኝ ልከፍት ብል ሙሉ በሙሉ ሳይሆን ከአንድ ገጽ ላይ ግማሽ ትቶ ግማሹን ይነበባል። ሙሉ በሙሉ ባለመከፈቱ ምክንያት እኔም መለስኩላቸው። እነዚህ የአባታቸውን ታሪክ እንዳይወጣ ያደረጉ የአዛውንቱ ልጆች ኢትዮጵያውያን አይሆኑም።

ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከእግዚአብሔር፤ከአላህ ጋር እንዲለዩ አድርጓል። ቃሉ" ሰላም ነው፤አማን ነው"የተሻሻሉት ደግሞ "ፒስ ነው" ይላሉ። ቀደም ወያኔ በርሃ ሳለ ጠባቂዎች በር ሲጠብቁ የሚያድሩት ጥዋት "ሰላም ነው"የሚል ዘገባ ያቀርቡ ነበር። ይህ ቃል በ1984 ዓም መጀመሪያ "ሰላምና መረጋጋት" ብለው ሕዝቡን አወናብደውበታል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአይሁድ ካህናት ከተገደለ በኋላ ተከታዮቹ ፈርተው ቤት ዘግተው ቁጭ ብለው እየተጨነቁ ባለበት ሰዓት ክብር ይግባውና የተዘጋው ቤት ሳይከፈት ከመሀላቸው ቁሞ" ሰላም ለናንተ ይሁን" አላቸው። ከዚያም አጽናኝ መንፈስ

ቅዱስ ላከላቸው:: ከዚህ በኋላ ሞት ሳይፈሩ ወንጌልን ሰበኩ:: ወያኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደተጨነቅ አውቋል:: መፍትሄ ሳይሰጥ ሰላም ሳይኖር ሰላም ያለ አስመስሎ "ሰላም ነው፤አማን ነው"የሚል ፈሊጥ አምጥቶ ከኢትዮጵያ አልፎ ስደተኛው" እንደምን አደርክ፤ሽ" ስትሉ የምታገኙት መልስ እግዚአብሔር ይመስገን ሳይሆን"ሰላም ነው"ወይም "አማን ነው" ይላል:: ይህ ወያኔ የፈበረከውን ነው:: ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ እግዚአብሔር ይመስገን እንዳይል እያደረገው ነው::

አይ ስደተኛ!ስደተኛ
ሆነ ወያኔን ከዶላር ላይ የሚያስተኛ
ኢትዮጵያውያንን የሚስለቅስ ዘመነኛ!

ትናንሽ በነጻ የሚታተሙ ጋዜጦች በየከተማው ተስፋፍተዋል:: ድጄ ዘፈን የሚያከራዩ ወጣቶች ተሰግስገዋል:: ትግርኛ ቋንቋው ለማያውቅ የትግርኛ የባህል ዘፈን አስመስለው የወያኔን ቅስቀሳ የፖለቲካ ዘፈን ያዘፍናሉ:: ለምሳሌ ከጎንደርና ከወሎ ተከፍለው ወደ ትግራይ የገቡትን ወረዳዎች ከትግራይ ወረዳዎች ጋር አስገብተው የዘፈኑትን ዘፈን የትግርኛ የሰርግ ዘፈን ነው ብለው በሌሎች ኢትዮጵያውያን ሰርግና ቀለበት ድግስ የነገድ ዘፈን ሲዘፈን ይህ ዘፈን ቀዳሚ ሁኖ እንዲለመድ እየተደረገ ነው:: ይህን የሚያደርጉት ሆነ ብለው በወያኔ ተመልምለው በየከተማው የተሰለፉ ጄሌዎች ናቸው::

ትንቢተ ኢሳይያስ 57፤11"መብል ወዳጆች ከቶ የማይጠግቡ ውሾች ናቸው፤ እነርሱም ያስተውሉ ዘንድ የማይችሉ እረኞች ናቸው፡ ሁሉ ወደ መንገዳቸው ከፍተኛው እስከኋለኛው ድረስ ሁሉ እያንዳንዳቸው ወደ ጥቅማቸው ዘወር ብለዋል"ይላል:: አዎ ልክ ነው ሆዳቸው አምላካቸው የወያኔ ተባባሪ ሁነዋል:: ልክ ነው ቻይና ሰራሽ መንገዶች ተሰርተዋል:: በግለሰቦች ጥረት በተለያዩ ከተማዎች ትላልቅ ሕንጻ ተገንብተዋል:: ይህን ማንም አይክድም:: ግንኮ ስንቶች አርሶ አደሮች መሬታቸውን አጥተዋል:: የጋምቤላ ሕዝብ አርሶአደሮች የደረሰባቸው ችግር ይታያችሁ ይሆን? በሌሎችም ክልሎች የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም አርሶ አደሮች እየተሰቃዩ ናቸው::

በአዲስ አበባ ዙርያ ያሉ የኦሮሞ አርሶ አደሮች የገጠማቸውን ችግር ትመለከቱት ይሆን? አያት እሪል እስቴት የሚገነባቸው ከማን መሬት ላይ ነው ?እነዚህ አርሶአደሮች መብት ይከበር በማለታቸው የኦሮሞ ተማሪዎች የደረሰባቸው ኢሰብአዊ ድርጊት ለእናንተ አይታያችሁም? በሌሎች ክልሎች መሬታቸውን ተነጥቀባቸው ጎጂቻቸው ፈርሶባቸው ቀን ጸሐይ ማታ ብርድ የሚፈራርቅባቸው ወገኖቻችን ጉዳት ልትመለከቱ አልቻላችሁም:: ምክንያቱም በጥቅም ተይዛችኋልና:: ወያኔ በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም የተለገሰለት ገንዘብ ምን ተሰራበት?ከውጭ ባገኘው ገንዘብ የሰራው ቀደም የተሰሩ ጎዳናዎችን እስፓልት አልብሷል:: የተገኘው ገንዘብና የተሰራው ሲወዳደር ሰማይና መሬት ነው:: ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ታዛቢዎች የሚሉት የተሰራው መንገድ ለወያኔ የንግድ መኪኖች መጓጓዣ እንዲሆን ተብሎ እንጂ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ታስቦ አይደለም ይላሉ::

አንዳርጌ መስፍን በሙት መንፈስ አገር ሲታመስ የተባለው መጽሐፍ 227 "ለመሆኑ መንገዶቹን ድልድዮቹንና ግድቦቹ የነማን ኩባንያዎች ናቸው የሚሰሩአቸው? ይህንን አጥብቃችሁ ጠይቁ!በከተማም ሆነ በገጠር የሚገነቡትን ግንባታዎች የሚሠሩት ሰባ ከመቶውን የኢሕአዴግ ኩባንያዎች መሆናቸው ያደባባይ ምስጢር ነው" ይሉና ገጽ 228 "ኢሕአዴግ 21 ዓመታት ተጉዞ አንዳንድ ያረጁ መንገዶችን መጠገኑና አዳዲስ መሥመሮችን መዘርጋቱ እንዲሁም ባዲስ አበባና በክልል ዋና ዋና ከተሞች ፎቆችን ማቆሙን እንደ ትልቅ ነገር በመቁጠር በፕሮፖጋንዳ ትልቅ መንግሥት ለመባል ይውተረተራል፡፡ በ1983 ዓም መቶ ኪሎ ጤፍ ከ40-50 ብር ይሸጥ የነበረው ዛሬ ከ1300-1800 ብር ደርሷል፡፡ ኪሎ ሥጋ በ1983 ዓም ከ3-5 ብር ይሸጥ የነበረው ዛሬ ከ140-160 ብር ደርሷል፡፡"

"የዚህ ምስጢርም ጅዳ፤ሮም፤ለንደን፤ቶሮንቶ፤ዋሽንግተን ዲሲና ኒዮርክ የተከፈቱት ግዙፍ ግዙፍ ሬስቶራንቶች የነማን እንደሆኑ ጠይቁ ሀቁን ማወቅ ይቻላል" ይሉና ገጽ 225 "ቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ በ43 ዓመታት የግዛት ዘመናቸው ከውጭ ብድርና ርዳታ ያገኙት የገንዘብ መጠን 250 ሚሊዮን ያሜሪካ ዶላር ሲሆን ባመት 625 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር ብቻ ነበር፡፡ የደርግ መንግሥት በበኩሉ በ17 ዓመታት የግዛት ዘመኑ ከውጭ ያገኘው የብድርና የርዳታ መጠን 4 ቢሊዮን ዶላር ወይንም 8.2 ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር ነበር፡፡ ይህ በመሆኑም በንጉሡ ነገሥቱም ሆነ በደርግ ጊዜ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ የመሠረተ ልማት አውታሮች ተዘርግተዋል፤ይህንን ሀቅ ግን ኢሕአዴግ አይቀበልም፡፡ ባንጻሩ የኢሕአዴግ መንግሥት በነዚህ 21 ዓመታት ውስጥ ከውጭ ብድርና ርዳታ ያገኘው የገንዘብ መጠን 50 ቢሊዮን ዶላር ይሆናል፡፡ የዓመት ፈሰሱ 162 ቢሊዮን 500 ሚሊዮን ብር ነው"ሲሉ ጽፈዋል፡፡

ትንቢተ ሕዝቅኤል 13፤10"ሰላም ሳይኖር ሰላም እያሉ ሕዝቤን አታልለዋልና አንዱም ሰው ቅጥር ሲሠራ እነሆ ገለባ በሌለበት ጭቃ ይመርጉታልና"ይላል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም አጥቶ ከወያኔ ብሳችሁ ሰላም ወርዷል ብላችሁ የምታላዝኑ እናንተ የወያኔ ደጋፊዎች ናችሁ፡፡ ከነገረ ቀደም የወያኔ መጠቀሚያ መሆናቸው ምስክሩ በስደተኛው ሲኖዶስ ቤተ ክርስቲያን ብቅ አይሉም፡፡ ምክንያቱም ወያኔ ይቆጣቸዋል፡፡

በነገራችን ላይ ከስደተኛው ቤተ ክርስቲያን ሕዱ ተብለው የተመደቡ ቦርድና ሌላም ሌላ ተግባር ይዘው የሚያመሳቅሉ የሉም ማለት አይደለም አሉ፡፡ ከአዲስ አበባው ሲኖዶስ ቤተ ክርስቲያን አንድም የኢትዮጵያ ችግር አይገባም፡፡ ገዳም ፈረሰ ቤተ ክርስቲያን ታረሰ፤ምዕመኑ ክብሩ ተገረሰሰ ብሎ ማውራት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም "ሰላም ነው!አማን ነው"የቄሱም ስብከት እንዲሁ ነው በኢትዮጵያ ታይቶ የማይታወቅ ዲሞክራሲ ይንበሸበሻል ብለው ይሰብካሉ፡፡

# ምዕራፍ 7

## ወያኔ ስደተኛውን ቤተ ክርስቲያን ሊያፈርስ ነው

ወያኔ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም በትረ ሥልጣኑን ከያዘ በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ላይ ዘመቻው ቀጠለ:: በአዲስ አበባ ሰላማዊ ሰልፍ የወጡት የወያኔ የውስጥ አርበኞች እነ መምህር ሀብተ ማርያም ተድላ ሲሆኑ አማሮች አላጨበጨቡም አይባልም:: ጳጳሳቱ ሳይቀሩ ወያኔ በሉ ያላቸውን አሉ:: ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሱን "አሞኛል ብለው ሥልጣን ይልቀቁ"ሲሉ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሱ "ሳያመኝ አመመኝ አልልም" ሲሉ ጳጳሳቱ ሁሉ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ከወያኔ ጋር ሁነው አፈረሱ:: "አንድ ፓትርያርክ በሕይዎት እያለ ሌላ አይሾምም" የሚለውን ሕግ አብረው ጣሱ::

ይህን አረንጋዴ መብራት ከጳጳሳቱ ወያኔ ካገኘ በኋላ ለመከፋፈል እንዲያመቸው ዘመቻው በጎንደር ተወላጆች ላይ አጠነከረ:: የሚገርመው ነገር በሊቀ ጳጳስነት ማዕረግ የተሾሙት ሳይቀሩ" የጎንደርን ምንጭ ማድረቅ የምንችለው አሁን ነው"በማለት ተናገሩ:: ብፁዕ አቡነ ገብርኤል እና ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ተጠቃሽ ናቸው:: አቅም አጥሯቸው እንጂ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱላቸው ቤተ ክርስቲያን እንዳይመሰርቱ የአሜሪካን አምባሳደር ብፁዕ ወጣያት አቡነ ጳውሎስ መጠየቃቸው አልቀረም::

<u>ውክሊክ ፋይል ይፋ</u> ያደረገውን ሰነድ አቢይ አፍወርቅ ትርጉም "የአዲስ አበባዋ ቤተ ክርስቲያን በኤምባሲያችን በኩል የአሜሪካ መንግሥትን ርዳታ ለመጠየቅ ማሰቧን ተረድተናል:: የሚለው የኤምባሲው መልዕክት:: በአሜሪካ ያለው ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚለውን ስም መጠቀም እንዳይችል እንድናግድላቸውና ዋና ዋናዎቹን የቤተ ክርስቲያናን ሀላፊዎችም ወደ ኢትዮጵያ አስገድደን እንድንመልስላቸው ይፈልጋሉ" የሚለውን ልመና የለመኑት ብፁዕ ወጣያት አቡነ ጳውሎስ ናቸው:: በሕይወታቸው እያሉ ምስላቸውን ጣያት ስላቆሙ ብፁዕ ወጣያት እላቸዋለሁ:: ልብ በሉ ወያኔና የአዲስ አበባ ሲኖዶስ አንድ ሁነው በስደት አገር ያለው ኢትዮጵያዊ በግድ የአዲስ አበባው ሲኖዶስ ስር ለማስገባት ያሰቡት ዛሬ ሳይሆን ቀደም ብሎ ነው:: ለዚህም ነው አሁን በገለልተኛነት የቆዩትን አብያተ ክርስቲያናት ተራ በተራ ወደ አዲስ አበባው ሲኖዶስ እንዲገባ እያደረጉ ያሉት::

ይህን እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ መጠን ባጀት ተመድቦለት እየሰሩ ናቸው:: በተለይ እንዲጠናከር የተወሰነው ግንቦት 2002 ዓም ምርጫ አቸነፍን ካሉ በኋላ በሰኔ 2002 ዓም መቀሌ ዝግ ስብሰባ አድርገው"ከአገር ውስጥ ያለውን ስልጣን የፈለገውን ስልጣን ሰጥተን፤ገንዘብ የፈለገውን ገንዘብ ሰጥተን በቁጥጥራችን ስር አድርገነዋል:: የቀረን አሁን ዲያስፓራው ነው:: እርሱንም የ2007 ዓም ምርጫ

ከመድረሱ በፊት ከቻልን ተቆጣጥረን ካልቻልን ሰላም መንሳት አለበን" ሲሉ ወሰኑ:: ይህን ተግባር ለመፈጸም 40 ሚሊዮን ዶላር ተመድቧል:: በዚህ ምክንያት መጀመርያ ተጠቂ የሆነው የሰሜን አሜሪካ እስፖርት ፌዴሬሽን ነው:: አሁን በማንኛውም ቦታ ወያኔ ከቁብ ጀምሮ እየተቆጣጠረ ነው:: በዚህ ምክንያት በስደተኛው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መልምለው ባስገቧቸው ወዶገባዎች ሰላም እንዲጠፋ እያደረጉ ይገኛሉ::

የወያኔ ወዶገባዎች ስደተኛው ሲኖዶስ ጥንካሬ እንዳይኖረው ለማድረግ ከሚጠቀሙበት ዘዴያቸው አንዱ አሉባልታ ነው:: አሉባልታው ሰባኪያንን" ተህድሶ ናቸው" ብለው ያስወራሉ:: ባጠቃላይ የስደተኛውን ቤተ ክርስቲያን ሁሉ "ተህድሶ " ነው ይላሉ:: ወያኔ የተጠቀመባቸው ማህበረ ቅዱሳንን ነው:: ማህበረ ቅዱሳን ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዋጽኦ ማድረጉን አምናለሁ:: ድክመቱ ደግሞ ለማህበረ ቅዱሳን አባል አልሆንም ያለውን ሁሉ ማሳደዱ ሲሆን ሌላው ስደተኛው ሲኖዶስን ማጥላላት ማዳከም ነው:: የጅ አይቀርምና አሁን እነሱንም ወያኔ ማሳደድ ጀምሯል:: ብፁዕ አቡነ ማትያስ አፍቅሮተ ሴት ዘሕወሓት "ቅኝ ገዥ"ብለዋቸዋል:: ማኅበረ ቅዱሳን በስደተኛው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ሰባኪያን አሳደው ነበር:: አሁን ደግሞ እነሱ እየተሳደዱ ናቸው:: በነገራችን ላይ ማህበረ ቅዱሳንን መሳደዳቸውን በፍጹም አልደግፍም:: ምክንያቱም ከስተታቸው እንዲማሩ እንጂ እንዲሳደዱ ፍላጎቴ አይደለም:: ሌላው ቢቀር ገዳማቱን መርዳታቸውና ቀደም ሲል በግዕዝ ቋንቋ ተጽፈው የነበሩ መጻሕፍት መታተማቸው ታላቅ ተግባር ነው ብዬ አምናለሁ::

አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ ስምዐ ተዋሕዶ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 35" ለቤተ ክርስቲያናችን እድገት እና ለምዕመናን ክርስቲያናዊ ሕይወት መታነጽ እንቅፋት የሆነው አሉባልታና ውዥንብር መንዛት"ሲሉ ጽፈዋል:: ስደተኛውን ቤተ ክርስቲያን በማጥላላት ምዕመኑ ወደ ስደተኛው ቤተ ክርስቲያን እንዳይሄድ የሚያደርጉት ጥረት እንደቀጠለ ነው:: አሁንማ ይባስ ብለው በስደተኛው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ አባ ሽልቅቅ የወያኔን ከበሮ እየመቱ ናቸው:: ታዛቢዎች እንደሚሉት አባ ሽልቅቅ በአዲስ አበባ ያላቸው ቤት ወያኔ እንዳይቀማቸው ብለው ነው የሚሉ አሉ:: ባልተጠበቀ ሁኔታ ቤተ ክርስቲያኑን ወደ ውድቀት እየጣሉ ናቸው:: ገንዘብ እንጂ የክርስትና ምግባር የጎደላቸው እነ መላከ ጽልመት ስደተኛው ቤተ ክርስቲያን እንዲሽመደመድ እያደረጉ ይገኛሉ:: ሴሰኛው አባ ፍቅር ሆኑ የሰይጣን ቁራጩ መነኩሴ የኢትዮጵያን አንድነት ያፈረሰው ወያኔ የጠነሰሰው ሴራ በጃዙር እየፈጸሙ ይገኛሉ:: በመካከል ገብተው የሚያምሱት ከሊቆች እስከ ጳጳሳት የጥቅም ሰዎች ናቸው:: አሁን በቅርቡ የምናነበው ታሪክ ግልጽና ትክክለኛው ስደተኛውን ቤተ ክርስቲያን ለማፍረስ የተነሳው ቡድን ተልከው የመጡ ቤትና መሬት አዲስ አበባ ያላቸው ከሊቅ ዶ/ር እስከ መነኮሳት ብዙ ናቸው::

በእርግጥ ቁጥራቸው ይነስ እንጂ ለስደተኛው ሲኖዶስ እድገት የሚጥሩ አባቶች የሉም ማለት አይደለም አሉ:: ነገር ግን መቅደሱን የሚያረክሱ ካህናት በዙና

ሊያሰሩአቸው አልቻሉም። ትንቢተ ሶፎንያስ 3፤4"ካህናቶችዋም መቅደሱን አርክሰዋል፤በሕግም ላይ ግፍ ሠርተዋል"ይላል ቅዱስ መጽሐፍ። ልክ ነው፤ ካህናቱ መቅደሱን አርክሰዋል። አንዳንዱማ የሚናገረውን አያውቅም። ከአንደበቱ የሚወጣው ቃል ያስደነግጣል።

ለዚህ ይሆን እንዴ?ትንቢተ ሚልክያስ 2፤7 "ካህኑ የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር መልዕክተኛ ነውና፤ከንፈሮቹ እውቀትን ይጠብቁ ዘንድ ይገባቸዋል፤ሰዎችም ሕግን ከአፉ ይፈልጉ ዘንድ ይገባቸዋል" ይላል። ካህኑ እንኳን የእግዚአብሔር መልክተኛ ሊሆን ቀርቶ አሁንማ የአፍራሽ መልዕክተኛ ሁኖአል። ምዕመናኑም ከካህኑ አፍ መልካም ነገር መስማት ቀርቷል። ከካህኑ አንደበት የሚፈልቀው አፍራሽ ሁኖአል። ወደው አይደለም አጤ ቴዎድሮስ" እንዳይርቅህ መንፈስ ቅዱስ ብዙ ግዜ አትቅረብ ወደቄስ"ያሉት። አሁን ከሆነ የተረዳሁት ነገር ቢኖር የቆብ ቅዳቸው አንድ መሆኑን ነው።

ማቴዎስ 12፤እርስ በርሱ የሚለያይ ከተማም ሁሉ ወይም ቤት አይቆምም። ሰይጣንም ሳይጣንን የሚያወጣ ከሆነ እርስ በርሱ ተለያየ"። የሚለውን ጥቅስ ካህናቱ እያነበቡ ሲደርሱበት ሳይጨርሱት ይዘሉታል። ማርቆስ 6፤9" በእግራችሁ ጫማ አድርጉ፤እንጂ ሁለት እጀጠባብ አትልበሱ"ተብለው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ተነግሯቸው ነበር። ዛሬ ግን መነኮሳቱ ለእግራቸው ጫማ ሳይሆን ባንካቸው በገንዘብ እንዲሞላ ቤተሰቦቻቸው በሃብት እንዲንደላቀቁ እያደረጉ ናቸው። የዚህ ዓይነት ካህናት ጳጳሳት በመሾማቸው ቤተ ክርስቲያንን ሊያጠፏት ነው። የሐዋርያት ሥራ 20፤28"በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ" የሚለውን አሁን "መንጋውን ማሳደዱ ያድናችሏል"የሚል ትርጉም ሰጥተውታል።

ስደተኛው ሕዝብ በስደተኛው ሲኖዶስ ተስፋ እንዲቆርጥ ያደረጉት በወያኔ ተልዕኮ ያላቸው ናቸው። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ከነሐሴ 28 ቀን 1983 ዓም "አሞኛል ብለው ሥልጣኑን ልቀቁ"የተባሉት በጳጳሳቱ ነው። በዚህ ሰዓት እኚህ አባት አልታመሙም እነሆ 24 ዓመት ሊሆናቸው የቀረው ጥቂት ወራት ነው። ወያኔ ጳጳሳቱን አሳምኖ ከሰልጣን ካወረዳቸው በኋላ መልሶ ከአገር እንዲለቁ አስገደዳቸው። ከሚኖሩበት ቤት ሕደው "ከአገር ይውጡ፤እኛ እርስዎን መግደል አቅቶን አይደለም ችግሩ በእርስዎ ምክንያት የጎንደርንና የትግራይን ሕዝብ ማጋጨት አንፈልግም" ያሉት አቶ ክንፈ ገብረ መድህንና አቶ አባይ ጸሐይ ናቸው። በዚህ ምክንያት መኪናቸው ነዳጅ ተሞልቶ በግድ ከአገር አስወጡአቸው። አንድ የቤተ ክህነት አርማ ያለው መኪና በሞያሌ ኬላ እንዴት አልፎ ኬንያ ሊገባ ቻለ?

ተስፋዬ ገብርዓብ <u>የጋዜጠኛው ማስታወሻ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 225 "አቡነ መርቆሬዎስ በኬንያ በኩል ሲሸሹ ክንፈ ገብረመድህን ያውቅ!የነበረ

ሲሆን ችግር እንዳይገጥማቸው ጥበቃም ያደረግላቸው ነበር"ብሎ ጽፏል። ይህን ካደረጉ በኋላ "ሕዝባቸውን ትተው ኮበለሉ"ተብሎ ከበሮ መደለቅ ተጀመረ። ከዚያም ከኬንያ ወዴ ሌላው አገር እንዳይሄዱ ወያኔ በኢምባሲው በኩል ያተከላከሉ። ወደ አዲስ አበባ አፍኖ ሊወስድ እየተዘጋጀ ባለበት ሰዓት ወደ አሜሪካ መምጣታቸው ወያኔን ሰላም ነሳው። ውክሊክ ፋይል ይፋያደረገውን ሰነድ"ዋናዎቹን የቤተ ክርስቲያኗን ሀላፊዎችም ወደ ኢትዮጵያ አስገድደን እንድንመልስላቸው ይፈልጋሉ" የሚለውን ልመና እኚህን አባት ለመያዝና ወስዶ ለማሰር ነበር ዓላማቸው።

ሲኖዶስ መቋቋም ነበረበት አልነበረበትም!ለሚለው ጉንጭ አልፋ ክርክር ለአሁኑ ልለፈው። ይህ ስደተኛ ሲኖዶስ ግን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሃይማኖትና ነገድ ሳይለይ በሚደርስበት በደል እሪ ከማለት አላቆመም። በየስድስት ወሩ ሲሰበሰብ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን መጎዳት ሆነ ሕዝብ የደረሰበትን በደል አቤት ይላል። ከሁለቱ ሲኖዶስ አንገባም ብለው ገለልተኞች ቤተ ክርስቲያንን አሁን ወያኔ ጠቅልሎ ወደ አዲስ አበባው አስገብቷቸዋል። ሦስት ከመሆን ሁለት መሆኑ መልካም ነው። ምክንያቱም ሕዝቡን ከሚከፋፍሉ ወደ ወያኔ መግባታቸው ይሻላል። ቤትና ንብረት ያላቸው የወያኔ የውስጥ አርበኞች ስለነበሩ መጠቅለላቸውን ወድጄዋለሁ። ዱሮም የኢትዮጵያን ሕዝብ መበደል እያወቁ እንዳላወቁ የሆኑ ነበሩ። በነገራችን ላይ የለንደን ጵዮን ማርያም የሕዝብና የቤተ ክርስቲያን ችግርን አስመልክታ መግለጫ ትሰጥ ነበር።

ሌላው ቀርቶ የቅዱስነታቸው በዓለ ሲመት ለማክበር ተብሎ ተደጋግሞ መግለጫ መውጣቱ ይታወሳል። መልሰው ይሰርዙታል፤ ይህ የተደረገው ስደተኛውን ምዕመን ተስፋ ለማስቆረጥ በረቀቀ መንገድ እየሰሩ ነው። አንዱን አባት ከፍ አድርጎ አንዱን ዝቅ ማድረግ ሆነ ተብሎ የተፈጸመ ደባ ነው። የራሻ ቤተ ክርስቲያን ከ78 ዓመታት በኋላ አንድ የሆነችው ስደተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ጠንክራ መዋቅር ስለነበራት ነው። እኛም ስደተኞች ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለቤተ ክርስቲያን ጩኸት ማሰማት የምንችለው ጠንካራ አመራር ሲኖር ነው።

ለምሳሌ የአዲስ አበባው ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያን ይዞታ ማለትም የመስቀል በዓል ማክበሪያ ሆነ የጥምቀት በዓል ማክበሪያ ቦታ ሲወሰድ ድምጹን አያሰማም። በአዲስ አበባ የጥምቀት ማደርያው መስጊድ የተሰራበት መሆኑን ቤተ ክርስቲያን ፈርሶ ታቦታቱ በፖሊስ መኪና ተጭኖ ሲወሰዱ ቤተ ክርስቲያን ምን ያህል ውርደት እየመጣባት እንደሆነ አልተረዱትም። ይህን አስመልክቶ የአቶ ኤርመያስን መጽሐፍ ማንበብ ይጠቅማል። የአዲስ አበባው ሲኖዶስ ቤተ ክርስቲያን ስትደፈር ዝም ስለሚል ስደተኛው ሲኖዶስ ሌላ ባይሰራም በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚደርሰውን ችግር ከመግለጽ እስካሁን ድረስ አልተገታችም። ለወደፊቱ ግን ሊገቷት የተቃረቡ መስለውኛል። ሌላው ቀርቶ የዋልድባ ገዳም አልተደፈረም ብለው የሚናገሩ ሆዳም መነኮሳት ባሉበት ቤተ ክርስቲያን እንዴት ነው እውነት ይነገርበታል የምንለው?ኅበዝ ልብ በሉ? ያን የምስል ድምጽ ቪዲዮን በይቱብ ለቀውታል እነዚህ ምስክሮች ካድሬዎች ወይስ መነኮሳት?ፍርዱን ለታሪክና ለተመልካች እተወዋለሁ።

# ምዕራፍ 8

## ኢሳ 12፤11 "የትዕቢተኞችንም ኩራት እሽራለሁ"

ትንቢተ ኢሳይያስ 12፤11"የትዕቢተኞችንም ኩራት እሽራለሁ፤የጨካኞቹንም ኩራት አዋርዳለሁ"ይላል ቅዱስ መጽሐፍ። በአሁኑ ሰዓት እንደ ወያኔ የኮራና የተንጠራዘዘ ድርጅት የለም። ግንኮ አንድ ቀን ጎማው መተንፈሱ አይቀርም። የእኔ ምክር ከመውደቁ በፊት እንዲያስብበት ነው። ታሪክ መስታይት ነው ይላሉ አበው። ኢትዮጵያን ለመገንባትና የአድዋን ጦርነት ድል ታሪክ ለሚመለከት ከአጤ ምኒልክ በመቀጠል እቴጌ ጣይቱ ብጡል አንዷ ናቸው። አጤ ምኒልክ ካረፉ ከቤተ መንግሥት እንዲለቁ በግዞት ወደ እንጦጦ እንዲሄዱ ከተደረገ በኋላ እንዲህ ማለታቸው በታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል።

አምባሳደር መንግሥቴ ደስታ <u>ግርማዊት እቴጌ ጣይቱ ብጡል</u> ብርሃነ ዘኢትዮጵያ 1832-1910 በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 152
"ነጋሪት ማስመታት ነበረ ሥራችን
እምቢልታ ማስነፋት ነበረ ሥራችን
መለከት ማስነፋት ነበረ ሥራችን
ሰው መሆን አይቀርም ደረሰ ቀናችን" ብለዋል።

ኃያላን የምንላቸው አገሮች በአሁኑ ሰዓት የሉም። በዓለም ኃያላን የነበሩት የቀድሞ አገሮች በቅኝ ግዛት ተይዘው ተከፋፍለው ሰላም ማጣታቸውን ነው። ለምሳሌ ከክርስቶስ ልደት በፊት በዓለም ኃያላን ከነበሩት አገሮች መካከል ሕንድ ግንባር ቀደም ነበረች። ንጉሥ ራማ የሚባለው በ1985 ዓመተ ዓለም ኢትዮጵያን ሊወር መጥቶ ከዚሁ ሙቶ ቀርቷል። የሞተበት ቦታ ዛሬ ድረስ ራማ ተብሎ ይጠራል ትግራይ ውስጥ ነው። በመቀጠል ግብጽ ኢትዮጵያን ልትወር መጥታ በመመታቷ ምክንያት ኢትዮጵያውያን በመሄድ ግብጽን ለ400 ዓመታት ገዝተዋል። የኢትዮጵያውያንን ኃይል ከግብጽ ያባረረው የግሪኩ አሌክሳንደር ሲሆን እርሱን ደግሞ ከግብጽ ያስወጣው የፋርሱ ሥርዎ መንግሥት ነው፤የፋርስን ሥርዎ መንግሥትን ከግብጽ ያባረረው ሮማውያኑ ሲሆኑ ሁሉም ኢትዮጵያን ለመውረር ሞክረው ሳይሳካላቸው ቀርቷል። እንዲሁም ሮማውያንን ከግብጽ ጠራርጎ ያስወጣው ማህመዳውያን በ7ኛ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ሲሆን የነሱን ኃይል ያደከመው የቱርክ ኦቶማን ነበር።

የትናንቱ የአውሮፓው ኃያላን መካከል በእንግሊዝ ግዛት ጸሐይ አትገባም የምትባለው አገር ዛሬ ደክማለች። የደርግን መንግሥት ለመጣል ስንቶች የዓረብ ሀገራት ተባባሪ ነበሩ። የይራኩ ሳዳም፤የግብጹ ሙባረክና የየመኑ፤ የሶርያውና የሊብያ፤ሌሎችም እንደ አበባ ታይተው ማታ የሞቱ ናቸው። ይህ ነው ታሪክ የሚያስተምረን። በኢትዮጵያ የአጤ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ይወድቃል የሚል ማንም አልነበረም። በአፍሪካ ወታደራዊ ኃይል አጠንክሮ

የነበረው የደርግ መንግሥት ወድቋል፡፡ ያውም ሕብረ ብሔር የነበረው? ታዲያ ወያኔ ምን ይማራል? የወያኔ አቋም አጥፍቶ መጥፋት ነው፡፡ ያ ከመሆኑ በፊት መሪዎችንና ደጋፊዎቻቸውን ታሪክ እንዲያነቡ እጋብዛለሁ፡፡

ከኢትዮጵያ መሪዎች መካከል የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያንቋሽሹ ርዕሰ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ ነበሩ፡፡ እንደ አገር መሪ አስከሬናቸው ተከፍቶ አልታየም፡፡ ምክንያቱም ብጥስጥሳቸው ወጥቷል የሚሉ አሉ፡፡ አንዳንዶች አስከሬናቸው ተከፍቶ ያልታየው ወደ አገር አልገባም አለበለዚያም በድብቅ አድዋ ሊቀብሯቸው ነው ይላሉ፡፡ ማን ያውቃል መላ ምቱ ሆነም አልሆነ ያ ትቢት የለም፡፡ ለዚህም ነው "የትቢተኞችን ኩራት እሽራለሁ፤የጨካኞችን ኩራት አዋርዳለሁ"የሚለው ቅዱስ መጽሐፍ ስለዚህ ወያኔዎች አደብ ግዙ፤ስለ ኢትዮጵያ አርቃችሁ አስቡ፡፡

የትግራይ ሕዝብንና ወያኔን ለይተን ማየት አለብን፡፡ በእርግጥ ማህል አገር ነዋሪ የሆኑ ትግርኛ ተናጋሪ እና ትግራይ ክፍለ ሀገር የሚኖሩትን ለይተን ማየት አለብን፡፡ በማህል አገር የሚኖረው ትግርኛ ተናጋሪ የወያኔ ትርፍራፊ ቀማሽ ነው፡፡ በነገራችን ላይ ማህል አገር ከሚኖሩት መካከልም ሐቀኛ የትግራይ ልጆች የሉም ማየት አይቻልም አሉ፡፡ ለማንኛውም የትግራይን ሕዝብና ወያኔን አንድ አድርገው የሚሰብኩት የወያኔ ጸሐፊዎች ናቸው፡፡ ከመሠረቱ ጀምሮ የትግራይን ሕዝብ አማራው ሕዝብ የበደለው አስመስለው ሰብከውታል፡፡ የትግራይ ሕዝብ ኢትዮጵያን የባህር በር አልባ አደረጋችሁ እንዳይላቸው አሰብን የሸጡት አጤ ምኒልክ ናቸው ብለው ማስተማር ጀምረዋል፡፡ ይህን ሰምቶ ያደገ የትግራይ ወጣት እውነት ይመስለዋል፡፡ በእርግጥ ሌሎች የትግራይ ልጆች ኢትዮጵያውያን በወያኔ የተሰጠውን የተዛባ ትምህርት እያስተካከሉ ናቸው፡፡

ጌታቸው ረዳ <u>ይድረስ ለጎጠኛው መምህር</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 58" መምህር ገብረ ኪዳን ደስታ ምኒልክ ኤርትራን ከኢትዮጵያ፤ትግራይ ነጥሎ ለጣልያን ሰጠ፤ እያለ በክህደት ክስ ሲወነጅላቸው ወደቦቻችንን እንዳንጠቀምባቸው የማድረጉ ወያኔ ትግራይን ክህደት ግን የለረባ ዓይነ ደረቅ ደብቆታል፡፡ ይህ ቡድን መንግሥት ነኝ ብሎ ወደ ሥልጣን ከመምጣቱ በፊት ቀደም ብሎም ቢሆን የጠላቶች ወኪል በመሆን አባቶቻችን የባሕር ወደባችን እንዳይነጠቅ በተዋጉባቸው የጦር ሜዳዎች ሁሉ ከጠላቶች ከሻዕቢያ ከተባለው የዓረቦች ተቀጣሪ ጋር ወግኖ በማሰለፍ የራሱን 60.000 (ስድሳ ሺህ)የትግራይ ነፃ አውጪ የሽምቅ ተዋጊ ጦር ወደ አልጌና እና ምፅዋ ወደብ ልኮ ሻዕቢያን ከኃያሉ የኢትዮጵያ የደርግ ጦር መንጋጋ ለማስጣል" ሲሉ ጽፈዋል፡፡ አቶ ጌታቸው ረዳ ከላይ የተጠቀሰውን የመምህር ገብረ ኪዳን ደስታ አባባል ትክክል አለመሆኑን ገልጸው የወያኔን ተንኮል እንደሆነ እወቁ!ከሌላው ኢትዮጵያውያን ጋር ቅራኔ አትፍጠሩ ብለዋል፡፡ ለዚህም ነው የትግራይን ሕዝብና ወያኔን ለይቶ ማየት የሚገባው፡፡ አቶ ጌታቸው ረዳ የትግራይ ክፍለ ሀገር የአክሱም አውራጃ ተወላጅ ኢትዮጵያዊ ናቸው፡፡

ይኩኖ መስፍን የትግራይ ሕዝብ የአርባ ዓመት ሰቆቃ በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 2 "ሕወሓት የትግራይ ሕዝብ ባለውለታ መስሎ ይቅረብ እንጂ የሕዝቡን ነፃነት መሬት ሉዓላዊነትና ክብር ለባዕዳን ያስደፈረ፤ለወራሪ አሳልፎ የሰጠ ድርጅት መሆኑ የትናትንት ትዝታ ነው:: ታዲያ የትግራይ ሕዝብ የሕወሓት 40ኛ የልደት በዓልን ሲያከብር ምን እያስታወሰ ነው ሰልፍ የሚወጣ? እውነት የባሕር በሯን የተዘጋ ሽባ ሀገር ይዞ በመቅረቱ? ያ ሁሉ ወጣት የወደመበትን ባድሜን ለሻዕቢያ መሸለሙ!የኢትዮጵያ አንጡራ ሀብትና ብሔራዊ ጥቅም ለባዕዳን መሸጡ፤ባጠቃላይ በሻዕቢያ ተደፍሮ የዓይደር እልቂትንና አሁንም ቢሆን በየቀኑ በታጣቂ ኃይል እየታፈኑ ወደ ኤርትራ የሚሻገሩትን ልጆቹ ሞት አሜን ብሎ በመቀበልና በመደሰት ይሆን? መልሱን የጥቃቱን ሰለባ ለሆነው የትግራይ ሕዝብ እተወዋለሁ"ሲሉ ጽፈዋል:: በነገራችን ላይ ወያኔ ትግራይ ውስጥ ትላልቅ ተቋማት::ትላልቅ ኩባንያዎች ተክሏል:: ትላልቅ ሕንጻዎች ገንብቷል:: ያ ማለት የትግራይ ሕዝብ ይጠቀምበታል ማለት አይደለም:: ይህን ለይተን እንድናይ ያስፈልጋል::

ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ አድምጡ፤የሕዝቡን አንድነትና ፍላጎት ብታከብሩ ሰውን ሳይሆን እግዚአብሔርን ታስደስቱት ነበር:: ትንቢተ ኢሳይያስ 48፤18" ትእዛዜን ብትሰማ ኖሮ ሰላምህ እንደ ወንዝ ጽድቅህም እንደ ባሕር ሞገድ በሆነ ነበር፤ዘርህም እንደ አሸዋ የሆድህም ትውልድ እንደ ምድር ትቢያ በሆነ ነበር፤ ስሙም ከፊቴ ባልጠፋና ባልፈረሰ ነበር"ይላል ቅዱስ መጽሐፍ:: ስለዚህ የያዛችሁት ግትር ዓላማ ለእናንተም ሆነ ለኢትዮጵያ አይበጅም:: መደረግ ያለበት ብሔራዊ እርቅ ነው:: ከ1983-2007 ዓም አንዱን ነገድ ከአንዱ ነገድ፤ አንዱን ሃይማኖት ከአንዱ ሃይማኖት ጋር አጋጭታችሁታል:: በሞቴ እስኪ ተመልከቱ ሕገ መንግሥት የሚሽረው ራሱ አይደለም እንዴ?

ከአንቀጽ 1እስከ አንቀጽ 106 ድረስ ካሉት አንቀጾች መካከል እንዲከበር የምትፈልጉት አንቀጽ 39 ብቻ ነው:: ለምሳሌ አንቀጽ 18/1"ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት ኢሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው"ይላል:: ይህ ከሆነ እንዴት ነው በሸዋ ውስጥ የአንድ አማራ ባለቤት ከሕዝብ ፊት የባሏን ኀፍረተ ሥጋ እየተመታች እንድትስም ተደረገ? ስንቱን እስረኞች ናቸው ሴቶች በጡታቸው ላይ ጉዳት የደረሰባቸው፤ወንዶች በጠርሙስ ውኃ ሞልቶ በብልታቸው የሚንጠለጠለው? ስንቱ ኢትዮጵያዊ ነው ሰባዊ ክብሩ የተነካው?ሌላው ቀርቶ ራሳቸው የጻፉትን ሕግ ልትፈጽሙ ቀርቶ መጻፉን እንኳ የምታውቁ አይመስላችሁም::

አንቀጽ 20/1"የተከሰሱ ሰዎች ክስ ከቀረበባቸው በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት አላቸው:: ሆኖም የተከራካሪዎቹን የግል ሕይወት፤የሕዝብን የሞራል ሁኔታና የሀገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክሩ በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል" ይላል:: ይህ አሁን እየተፈጸመ ነው? ስንቶች ታስረው ሁለትና ሦስት ዓመት በላይ የተከሰሱበትን የማያውቁ ዜጎች ቁጥር እናቱ ትቁጠረው፤ የሀገር ደህንነት የሚያሰጉ ቢሆንም እንኳን ወደ ፍርድ ቤት መቅረብ ነበረባቸው:: ለምሳሌ

በኬንያና በሱዳን እንዲሁም በየመን ታፍነው ወደ አዲስ አበባ የተወሰዱት ፍርድ ቤት አልቀረቡም። በሱዳን ታፍነው የተወሰዱት ሻለቃ አጣናው ዋሴ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ እንደታሰሩ ሙተዋል። ሌሎችም እንዲሁ ፍርድ ቤት አልቀረቡም።

አንቀጽ 25/1 "ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው፤በመካከላቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል። በዚህ ረገድ በዘር፤በብሔር ብሔረሰብ፤በቀለም፤በጾታ፤በቋንቋ፤በሃይማኖት፤በፖለቲካ፤በማኅበራዊ አመጣጥ፤በሀብት፤በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው"ይላል። ይህ አንቀጽ በጣም ሽጋ ነበር?ግን ይፈጸማል፤እንኳን ሊፈጸም በሕግ አንቀጽ የተጠቀሰ አይመስላቸውም። ያ ከሆነ ታዲያ ምነው የአማራ ነገድ ሦስት ሚልዮን ቁጥሩ ቀነሰ? ያ ከሆነ ታዲያ እንዴት ነው ሁሌም ነፍጠኛ ተብሎ የሚሰደበው? ጋላ አትበሉ ኦሮሞ በሉ ተብሎ የተደነገገው በ1966 ዓም ነው። አሁን በዘመነ ወያኔ ደግሞ ጋላ ያለ ይቀጣል የሚል ሕግ ወጥቷል። አማራው እኮ እየተዋረደ ነው። ሕጉ ባልፈጸመው አንዴ ነፍጠኛ በሌላ ግዜ ትምክህተኛ ሌላም ሌላ ተብሎ እየተዋረደ ነው። ሰዎች በሕግ እኩል ከሆኑ ከርዕሰ ብሔር አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ጀምሮ አማራውን መሳደቡና ማዋረዱ ይተው።

አንቀጽ 27/2"ማንኛውንም ሰው የሚፈልገውን እምነት ለመያዝ ነፃነት በኃይል ወይም በሌላ ሁኔታ በማስገደድ መገደብ መከልከል አይቻልም"ይላል። ይህ ከሆነ እንዴት ነው በጅማና በሌሎች ቦታዎች ላይ ክርስቲያኖች እንዳያመልኩ በአንገታቸው ሳይሆን በጋንጃቸው ታርደዋል!ያ ከሆነ አዲስ አበባ ውስጥ እንዴት ቤተ ክርስቲያን ሊፈርስና ለንግድ ቤት ሊሰጥ ቻለ? ያ ከሆነ እንዴት 59 የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን በኦሮምያ ክልል እሳት ሊበላው ቻለ? ያ ከሆነ በባህር ዳር የክርስቲያን ማምለኪያ ቦታ እንዴት ለልማት ተብሎ ሲታቀድ የእምነት ቦታችን ይከበር ስላሉ ክርስቲያኖች ሊገደሉ ቻሉ? እኒያ እማሆይ መመታት ነበረባቸው አሁንስ በዝቋላ ገዳም ሊደርስ የታሰበው ችግርስ? ዋልድባ ገዳም መታረስና ሌሎች ቤተ ክርስቲያናት መፍረሳቸውን ከላይ የተጠቀሰው ሕገ መንግሥቱን የጣሰው ማነው?

አባ ሳሙኤል በኢትዮጵያ የሃይማኖት መቻቻል አለን?በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 39 "ወሎ ከሚሴ ውስጥ አሁንም ቤተ ክርስቲያን ማቃጠል ክርስቲያኖችን መተናኮል የጥምቀትና የደመራ በዓላትን ማወክ አልቀረም ነበር። ለምሳሌ በ1998 ዓም የጥምቀት በዓል ጊዜ በከሚሴና ባቲ ክርስቲያኖች ተደብድበዋል፤ በታቦታት ላይ ድንጋይ ተወርውሯል። በ2000 ዓም የግሸን ማርያም በዓል ለማክበር የተጓዙ ምዕመናን በድንጋይ ተደብድበዋል፤ንብረት ወድሟል የሰው ሕይወት አልፎአል። ባሌ ውስጥ በ1998 ዓም በአንድ ቀን ብቻ 18 የክርስቲያን ገበሬዎች የዕህል ክምሮች ተቃጥለዋል። ከገጠሩ ክፍል ክርስቲያኖች ይፈናቀላሉ፤አብያተ ክርስቲያኖችም ይቃጠላሉ። ወለጋ ውስጥ በ1998 ዓም

ቶንጎ በምትባል ቦታ ቢያንስ ሁለት የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለዋል:: ክርስቲያኖችም በመሰደድ ላይ ናቸው::"

"በአርሲ ሀገረ ስብከትም ወለጋ ጠረፍ ላይ እንዲሁ አንድ ቤተ ክርስቲያን ተቃጥሏል:: ለእነርሱም የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዲበራላቸው የዚህ ዓለም አምላክ ለማያምኑትን የልባቸውን አሳብ አሳወረ:: 2ኛ ቆሮ፤4/4 ወሕቢያ ሌላው ተግባሩ ከሳኡዲ በሚመነጭ ገንዘብ መስጊዶችን ማስፋፋት ነው:: በጠቅላላ የተሰሩትን መስጊዶች ብዛት በአዲስ አበባ ብቻ 180 መስጊዶች ይገኛሉ:: ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ግን 130 ብቻ ናቸው:: የሙስሊሙንና ክርስቲያኑን ቁጥር በአዲስ አበባ ከመስጊዱና ቤተ ክርስቲያኑ ቁጥር ጋር ስናነጻጽረው የሚከተለው ይሰጠናል:: ሃይማኖት መቶኛ የቤተ ክርስቲያንና የመስጊድ ቁጥር ኦርዶቶድስ 86.70 ቤተ ክርስቲያን 130 እስልምና 12.70 መስጊድ 180 ከላይ ከጠቀስኩት 180 መስጊዶች መካከል ከ130 በላይ የሚሆኑት ባለፉት 14 ዓመታት የተሰሩ ናቸው"ብለው የመስጊዶችን ስም የተሰሩበትን ዓመት ዘርዝረው ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል የጻፉት መጽሐፍ በ2000 ዓም ላይ ነው:: በአሁኑ ሰዓት 184 መስጊዶች በአዲስ አበባ አሉ:: ከ130 ቤተ ክርስቲያን ከመጨመር ይልቅ ቀንሷል 127 ደርሰዋል::

ከዚህ በኋላ ደግሞ መሪያችሁን የምመርጥላችሁ እኔ ነኝማለቱና አልሀበሽ የተባለውን እምነት አስገብቶ አሁን በእስልምና ወንድሞቻችን ላይ የሚደርሰውን በደል ፈጽሞ አልደግፍም:: ከዚህ ላይ ሳልጠቅሰው ማለፍ የሌለብኝ ጉዳይ አለ:: የክርስቲያኖች ማምለኪያ ቦታዎች ሲደፈሩና ቤተ ክርስቲያኖች ሲቃጠሉ አንዳቸውም የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ትክክል አይደለም ብለው አልጠየቁም:: ከአገር ውስጥ ያሉት ይፍሩ ውጭ አገር ያሉት ዝምታን መርጠው ነበር:: እንዲያውም በያመቱ እየተሰበሰቡ የኢትዮጵያ እስላሞች በክርስቲያኖች መበደላቸውን ይናገሩ ነበር:: አሁን ወያኔ በእስላሞች ላይ ሲነሳ አንዳንዶች ክርስቲያኖች ዝም አሉን ይላሉ:: ክርስቲያኑማ ሕዝብ አብሯችሁ ቁሞአል:: ትክክል አለመደረጉን ወያኔን ጠንክሮ አውግዟል:: ለወደፊቱም ትክክል ያልሆነውን ከመግለጽ አይቆጠብም:: እናንተም ብትሆኑ ባልንጀሮቻችሁን ሳይቀር ትታችሁ የሄዳችሁ መሆኑን መዘንጋት የለባችሁም:: በነገራችን ላይ ክርስቲያን ይቅር ባይ ነው:: ቂምና በቀል እንድንፈጽም አምላካችን አይፈቅድም::

አንቀጽ 29/2"ማንኛውም ሰው ያለምንም ጣልቃ ገብነት ሀሳቡን የመግለጽ ነፃነት አለው:: ይህ ነፃነት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጹሑፍ ወይም በሕትመት፤በሥነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ፤ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሀሳብ የመሰብሰብ የመቀበልና የማሰራጨት ነፃነቶችን ያካትታል"ይላል:: ለመሆኑ ይህ ሕግ እየተሰራበት ነው? እንኳን ከሀገር ውስጥ ይቅርና ከሀገር ውጭ የሰውን ሀሳብ የመግለጽ ነጻነት የገፈፈው ወያኔ አይደለም እንዴ? ዋሽንግተን ዲሲ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ ኢምባሲ ቅጥር ግቢ ላይ ሰላማዊ ሰልፍ ሲያደርጉ

የኢምባሲው ሰራተኛ በሰልፈኞች ላይ ሽጉጥ ሲተኩሱ ታይተዋል። በዚህ ምክንያት ከአሜሪካ እንዲባረሩ ሁነዋል።

ወያኔ በውጭ ኢትዮጵያውያን ላይ ስለላ ያካሂዳል። ከአውሮፓ ሆላንድ ሲሰልል የተገኘ ሰላይ ተከሶና ተፈርዶበት ከአገር እንዲባረር ተደርጓል። ብዙ ሰላዮች አሁንም በተለያዩ ከተማዎች የተሰማሩ አሉ። ወያኔ እንኳን ኢትዮጵያ ውስጥ ቀርቶ በውጭ አገር ያለውን ሕዝብ የከፋፈለና የመናገር ሰላም የነሳ ነው። ይህ ባይሆንማ የሕዝብ ይግባኝ ሰሚ የሆኑ የግል ጋዜጦችና መጽሔቶች አይዘጉም ነበር። የወያኔ ባሰልስጣናት ወደ አውሮፓና አሜሪካ ብቅ ሲሉ ሰላማዊ ሰልፍ ሲደረግባቸውና በመዝናኛና በገብያ ሲያገኙአቸው ሲወቅሷቸው ተወቀስን ብለው ሲከሱና ሲረቱ ተመልክተናል። የሚገርመው ነገር ደግሞ አንዱ የወያኔ የሱማሌ ክልል ርዕሰ ብሔር መጠጥ ቤት ላይ በመገኘቱ ሲወቅሱት የተሳደበው ስድብ ይሰቀጥጣል። የአንድ ክልል መሪ ይህን ቃል ያውም በእንግሊዘኛ ቋንቋ ሲጠቀመው እጅግ ያሳፍራል። ወያኔዎች ጋጥወጥነታቸውን ቁልጭ አድርጎ ያሳየ ነበር።

አንቀጽ 31/1"ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማኅበር የመደራጀት መብት አለው። አግባብ ያለውን ሕግ በመጣስ ወይም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓትን በሕገ ወጥ መንገድ ለማፍረስ የተመሰረተ ወይም የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያራምዱ ድርጅቶች የተከለከለ ይሆናል"ይላል። ለመሆኑ ይህ ሕግ በኢትዮጵያ ይሰራል? ይሕ ሕግ የሚሰራ ቢሆንማ ኑሮ ድርጅቶች እንዲቀጭጩ አይደረግም ነበር። ታዲያ አንድነት ድርጅት ሆነ መኢአድ ለምን ሊዘጉ ቻሉ? የሚገርመው ደግሞ ሌላውን ሕዝብ እህል ከአፈር ለይቶ የማያውቅ አስመስለው የሚያዩ ድርጅቶች የተዘጉበትን ምክንያት ሊደረድሩ ይዳዳቸዋል!አይ አለማፈር?

አንቀጽ 32/1"ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም በሕጋዊ መንገድ ሀገር ውስጥ የሚገኝ ሰው በመረጠው የሀገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት፤እንዲሁም በፈለገው ጊዜ ከሀገር የመውጣት ነፃነት አለው"ይላል። ይህ መብዕት የተሰጠው ትግርኛ ቋንቋ ለሚናገረው ለወያኔ ቡድን እንጂ ለመላ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይደለም።

ብርሃኑ ደሴ ጣሰው <u>የፍቅር መቅረዝ</u> በተባለው መጽሐፋቸው
ገጽ 198 "የወላድ መካን ነሽ እረኛ የለሽ
ተወግተሽ ተወግተሽ በልጅሽ
መንጋሽ ተበትኖ የትም ጠፋለሽ"ሲሉ ጽፈዋል።

ወያኔ ኢትዮጵያን የወላድ መካን አደረጋት። እርሱ የሚፈልገው የኢትዮጵያን ልጆች በአንድነት ሁነው እንዳይቆሙ ለማድረግ ሲል አስቀድሞ ልዩ ቁጥር ታርጋ ለጠፈባቸው። ወያኔ እጅግ የሚጠላው አገር አቀፍ ድርጅትን ነው። በዚህ ምክንያት በመነጠር እየተፈለጉ አገር አቀፍ ድርጅቶች እንዲከስሙ እየተደረገ ነው። በአንጻሩ የአካባቢያዊና ነገዳዊ እንቅስቃሴ ለኢትዮጵያ

ይበጃል ተብሎአል፡፡ ወደኋላ መለስ ልበልና በ1965/2000 ዓም ብዙ የነገድ ድርጅቶች ተመስርተዋል፡፡ ለምሳሌ አዲስ አበባ የምርጫ ቦርድ የተመዘገበው የነገድ ድርጅት ቁጥሩ 80 ይሆናል፡፡

በሙት መንፈስ አገር ሲታመስ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 208 "የፓሪቲዎች ቁጥር አዲስ የተቋቋሙትን ሳይጨመሩ የክልልና አገር አቀፎች ጨምሮ 80 ገደማ ይሆናሉ፡፡ አዲስ የተቋቋሙትና እውቅና ያላገኙት ሲጨምሩ ቁጥራቸው ወደ 98 እንደሚደርሱ ይታመናል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔር ቁጥር 85 በላይ ናቸው፡፡ የፓርቲዎች ብዛት ግን ከብሔረሰቡ ብዛት በላይ ናቸው"ሲሉ ጽፈዋል፡፡ በኢትዮጵያ የአማራ ነገድ እስከ 1984 ዓም አልተደራጀም፡፡ ወያኔ ኢሕአዴግና ኦነግ ተባብረው በበደኖና በአርሲ በአርባ ጉጉና በሌሎችም ቦታዎች አማራውን ሲጨርሱት "ሕዝቡ አለቀ "ሲባሉ ወያኔዎች" ተደራጅታችሁ ጠይቁ"ሲባሉ ሳይወዱ በግድ መአሕድ ሲመሰረት ስሙ ካልሆነ በቀር አገር አቀፍ ድርጅት ነበር፡፡ አማራው ግድያው ቀለል ሲልለት መኢሕአድ ሁኖአል፡፡ ሌሎች ነገዶች በነገድ ስም ተደራጅተው ትውልዱ ትልቋ ኢትዮጵያን እንዲያይ አያደርጉም፡፡ አማራው በአማራ ስም መደራጀት የማይፈልገውና የነገድ ድርጅቶች የማይደግፋቸው ለትልቋ ኢትዮጵያ ስለሚያስብ ነው፡፡ ቁጥራቸው ይነስ እንጂ ከሌሎች ነገዶች የተወለዱ ለትልቋ ኢትዮጵያ አያስቡም ማለቴ አይደለም የሚያስቡ አሉ፡፡ ግን አማራው አሁንም በየእሰር ቤቱ የገባው እርሱ ነው፡፡ ምክንያቱም ለትልቂቱ ኢትዮጵያ ስለሚያስብ፡፡

ዳግማዊ ቴዎድሮስ <u>ሕወሓት በብአዴን ጉዳይ አስፈጻሚነት</u> ጥቃቱን በአማራ ሕዝብ ላይ አጠናክሮ ቀጥሏል በተባለው መጣጥፍ ገጽ 15 "ህወሓት ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያካሄደው አሰቃቂና ዘግናኝ በሆነ ሁኔታ በዜጎች ላይ የሚፈጽመው የአፈናና የእስር ዘመቻ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ሄዷል፡፡ የሕሓትን የእስር ቤት ሁኔታ ለማጣራት ባካሄድነው ጥረት በአገሪቱ ውስጥ ከ1350000 በላይ እሰረኞች አሉ፡፡ ይህ በየቀበሌው በየወረዳው ፖሊስ ጣቢያዎች በየጦር ካምፖችና በደህንነት የማሰቃያ እስር ቤቶች ያሉትን ዜጎች ሳይጨምር የተገኘ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ 545.000 በአማራ ክልልና በአዲስ አበባ የታሰረ አማርኛ ተናጋሪ ነው፡፡ ከነዚህ ውስጥ በፖለቲካ ጥላቻ ምክንያት የታሰሩና የተሰቃዩ ብዙ የእስር ዓመታት የተፈረደባቸው ምሁራኖች፤የጦር መኮነኖች፤ጋዜጠኞች፤አርሶ አደሮችና ነጋዴዎች በጣም ብዙ ናቸው"ሲሉ ጽፈዋል፡፡ ከዚህ በላይ በተጻፈው ስንገረም አሁን በቅርቡ ደግሞ የእስር ቤቶችን ብዛት የሚያብራራ ጹሑፍ ወጥቷል፡፡

<u>ኢትዮጵያን ርቪው</u> ድረገጽ የካቲት 19 ቀን 2007 ዓም "በአማራ ክልል 31 እስር ቤቶች አደገኛ እስር ቤቶች ተባሉ፡፡ የካቲት 19 ቀን 2007 ዓም ኢሳት ዜና በጃፓን መንግሥት የሚደገፈው የግልግል ዳኝነት ይፋ ባደረገው ጹሑፍ በአማራ ክልል የማረሚያ ቤቶች በሕግ ታራሚዎች አያያዝ እና አስተዳደር ከፍተኛ ችግሮች አሉባቸው ብሎአል፡፡ 31 እስር ቤቶች በእስረኞች ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንደሚደርስባቸው ተገልጿል"ይላል፡፡ የኢሳት ዜና አክሎ

እንደገለጸው እስር ቤቶች ያሉበትን ዘርዝሮ ዘግቧል፡፡ ይህን ያደረገው የወያኔው ልጅ ብአዴን ነው፡፡ ብአዴን አንዱና ዋናው ለአማራው ሕዝብ ውድቀት በወያኔ የሚታዘዘውን የሚፈጽም ድርጅት ነው፡፡ የሚገርመው ነገር አንዱ ጀግና ይመስል ወንድሙን ገሎ ሐውልት የሚሰራ የእንግዲ ልጅ ነው፡፡

ለአንድ አገር አኩሪ ተግባር የፈጸሙ ጀግኖች ሐውልት ይሰራላቸዋል፡፡ ለምሳሌ በኢትዮጵያ ውስጥ ለአጤ ቴዎድሮስ የሚሰራላቸው ከመጀመርያ ጀምሮ ከውጭ ተስፋፊዎች ጋር የተዋጉ በመሆናቸው ነው፡፡ ለ4ኛው አጤ ዮሐንስ ሐውልት የሚሰራላቸው ግብጽን ገርፈው የሰደዱ በመሆናቸው ሲሆን በ1882 ዓም ድርቡሽን አይቀጡ ቅጣት ቀጥተውታል፡፡ ድርቡሽ ድል አላደረጋቸውም፡፡ የተገደሉት ምርኮ እየተቀበሉ ባለበት ወቅት በተባራሪ ጥይት ነው፡፡ ድርቡሽን ስለተዋጉና ግብጽን ስለወጉ ሐውሕት ሊሰራላቸው ይገባል፡፡ አጤ ምኒልክ አውሕት የሚሰራላቸው የአድዋን ድል ባለቤት በመሆናቸው ነው፡፡ እውነቱን እንነጋገር ከተባለ ለአጤ ኃይለ ሥላሴ ሐውልት ሊሰራላቸው አይገባም፡፡ የደርግ መንግሥት ከሱማሌ ወራሪ ኃይል ጋር በመዋጋቱ ለኢትዮጵያ ሠራዊት ሐውልት ሊሰራለት ይገባል፡፡

አሁን ወያኔ የሰራው ሐውልት ግን ትክክለኛ ነው ብዬ አላምንም፡፡ ወያኔ ብቻ ሳይሆን ብአዴንም ሐውልት ሰርቷል፡፡ በኦሮሚያ እንዲሁ ሐውልት ተሰርቷል፡፡ ደርግ ኢትዮጵያዊ እንጂ ወራሪ የውጭ ኃይል አይደለም፡፡ ሐውልት መሠራት ካለበት ሻዕቢያ የፈጃቸው የአይድር ተማሪዎችን ደም ለመበቀል ከወራሪው ሻዕቢያ ጋር ሲዋጉ ለተዋደቁት ከ70-100 ሺህ የኢትዮጵያ ልጆች እንዴት አትሰሩም ነበር? አሁን 40 ዓመታቸው ሲያከብሩ ኢትዮጵያውያንን የሚያቀራርብ ሳይሆን ኢትዮጵያውያንን የሚያቃርን በዓል ነበር፡፡ ልዩነት ምን ያህል መቀርሳ እንደሆነ የተረዱት አልመሰለኝም፡፡

<u>ገናናው</u> ጋዜጣ የካቲት 3 ቀን 1992 ዓም ገጽ 6"ከ40 ሚሊዮን ብር በላይ ወጭ የተደረገበትና ከመሬት 51 ሜትር ከፍታ ላይ ያለው የመቀሌ የሰማዕታት ሐውልት"ሲል ጽፏል፡፡ ለመሆኑ በዜትኛው የዓለም ታሪክ ነው ወንድመን ገድሎ ሐውልት የሰራው? የወያኔ ሰዎች የገደሉአቸው ወገኖቻቸውን እንጂ ማነን ነው? ደርግ እኮ ኢትዮጵያዊ ነው? ኢትዮጵያውያንን ገድሎ ሐውልት የሰራ ወያኔ ብቻ ነው፡፡ ወያኔ ልትማሩ ይገባችኋል! ትቢትና ኩራቱ አይጠቅም በዚህ አሁን በያዛችሁት የጥፋት ጎዳና አጥፍቶ መጥፋት እንዳይሆን ማሰቡና ብሔራዊ እርቅ መፍጠሩ እጅግ ይጠቅማል፡፡ አሁን ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያስፈልገው ወንድሙን ገሎ ሐውልት መስራት ሳይሆን ብሔራዊ እርቅ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ለሁሉም መድህን ይሆናልና አስቡበት!!!፡፡

ጀግና ይመስል ወንድሙን ገሎ የሚፈክር
አትከተሉት ተውት ይቅር
አይጠቅምም ለኢትዮጵያ ክብር
ነውና ወንድሙን ገሎ የሚፈክር
አገር አጥፊ የትውልድ ፀር

# ክፍል ሦስት

## ምዕራፍ 1

## አቶ ነጋ ጌጤ የወያኔ መጠቀሚያ ሁነዋል

ምሳሌ 22፤1"መልካም ስም ከብዙ ባለጠግነት ይሻላል" ባለው መሠረት ገንዘብ አግኝቶ ክፉ ስም ከማግኘት እውነትን ይዞ መጠላትና ውሎ አድሮ ሁኔታው ሲጣራ ጥሩ ስም ማግኘት ይበልጣል:: ለዚህም ነው "ስም ከመቃብር በላይ" የሚባለው መልካም ስም ከብዙ ሐብት ይበልጣል:: አበው "ተፈርቶ ከመከበር ተንቆ መወደድ ይበልጣል"የሚሉት አባባል ትክክል ነው:: አቶ ነጋም ገልዜያዊ ጥቅም ሲሉ የማይጠፋ መጥፎ ስም ጥለዋል::

የቅማንት ሕዝብ ታሪክ ገጽ 114 "በተለይም በሐገራችን ውስጥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሁሉም ብሔረሰቦችና አናሳ ሕዝቦች ሙሉ ተሳፍቶ የፀደቀው ሕገ-መንግሥታችን የሁሉን ሕዝቦች መሠረታዊ ጥያቄ አሟልቶ መልስ የሰጠ ሆኖ ሳለ ይህንም ዕድል ሌሎች ሕዝቦች በልጆቻቸው ግንባር ቀደምትነት ተጋድሎ የሕገ መንግሥቱ በረከት ተቋዳሽ እየሆኑ ባሉበት በአሁኑ ወቅት እኛ የቅማንት ልጆች የሆን ምሁራን ተዋቂ ግለሰቦች የብሔረሰቡ የአካባቢ ተጠሪዎችና የሃይማኖት መሪዎች ሁሉ በዚህ በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ ተጠቅመን አባቶቻችን ታግለው ሳይሳካላቸው የቀረውን የብሔረሰባችን ሕልውና ማረጋገጥ የሚለውን ዋነኛ ጥያቄ ምላሽ አሳክቶ ከግብ ለማድረስ የማንነሳበት ምክንያቱ ምንድነው?"ሲሉ ጽፈዋል:: ከዚህ በላይ ወያኔነት ሌላ ማስረጃ ሊኖር አይችልም:: የወያኔው ሕገ መንግሥቱአንቀጽ 39 የኢትዮጵያን ሕዝብ የከፋፈለ ሕግ የደገፈ በምንም ይሁን በምን ወያኔ ነው:: ሕገ መንግሥት እንዲጸድቅ ሲለፉ ከነበሩት መካከል አንዱ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ነበሩ:: እርሳቸው ውለው አድረው ነገሮችን ሲመረምሩ የፈጸሙት ስህተት ሰላም ስለነሳቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ ጠይቀዋል::

ዳንኤል ተፈራ ጂ. <u>ዳንዲ የነጋሶ መንገድ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 295 "በሕገ-መንግሥቱ ላይ ሕዝቡ ተወያይቶበታል ማለቴ ስህተት ስለሆነ የኢትዮጵያን ሕዝብ ታላቅ ይቅርታ እጠይቃለሁ"ሲሉ ጽፈዋል:: ሕገ መንግሥቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንደማይጠቅም ብዙዎች እየተናገሩ ናቸው:: አቶ ነጋ ግን ቅማንቶች ይህን መብት መቀበል እንዳለባቸው ደግፈው ቀስቅሰዋል:: ይህ አንቀጽ 39 ማለፍ ተደስተው ከጉባኤው ማህል ሁለት ሰዎች ሲጨፍሩ በወቅቱ ታይተዋል:: አንዷ ከጎንደር የሄዱ ሲሆን ሁለተኛው ከባሌ የሄዱ ናቸው:: የባሌው ቤታቸው ሲደርሱ ባልታወቀ ሰው ተገድለዋል:: እኒያ ከጎንደር የሄዱ ሲጨፍሩ የታዩት እመቤት የት ቦታ እንደሄዱና አላወኩም ገና:: ያም ሆነ ይህ ለሕዝብ ማሰብ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ሊቅ ዶ/ር ነጋሲ ከፍ ተብሎ ከተጠቀሰው መጽሐፋቸው ገጽ 309 "ለሕዝቡ የምናስብ ከሆነ ሕዝቡ

ተከባብሮና ተቻችሎ እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል"ሲሉ ጽፈዋል:: ሌሎች የነገድ ድርጅቶች ሕዝቡ ራሱ ያውቃል ማንም ጎስጓሽ አያስፈልገውም::

አቶ ነጋ ወያኔ አልተጫወተባቸውም ማለት አይቻልም:: ለምሳሌ በጥር 2007 ዓም የወያኔ ምልሻ ዳንሻን ተሻግረው ነዋሪውን ማጥቃት ጀመሩ:: በዚህ ሰዓት ሕዝቡ ይነሳል:: ከመንግሥት የተውጣጡት ባለሥልጣናት ውይይት ሲያደርጉ ወያኔዎች ያቀረቡት ሀሳብ "የምንነጋገረው ከእናንተ ጋር ሳይሆን ከቅማንት ሕዝብ ጋር ነው"በማለት ተናግረዋል:: ይህን አስመልክቶ የጎንደር ክፍለ ሀገር ተወላጆች በኢሳት የጎንደር ሕብረት አባላት መካከል በደረሳቸው መረጃ መሠረት በአየር ላይ እንዲውል አድርገዋል::

አቶ በየነ አስማረ ኢሳት ቴሌቭዥን "የምንነጋገረው ከእናንተ ጋር ሳይሆን ከቅማንት ሕዝብ ጋር ነው አሉአቸው"ሲሉ ተናግረዋል:: አቶ በየነ እንዳሉት ወያኔ ሌሎችን አማራዎች በመሬት ይገባኛል ምክንያት ለውይትት ከናንተ ጋር አንወያይም ያሉት እውነት ነው:: ለዚህም የአቶ ነጋ መጽሐፍ ቅስቀሳ ለወያኔ ጥሩ በትር ሁኖአል:: ጥቅምት 23 ቀን 2007 ዓም የወጣው መግለጫ የቅማንትሕዝብ ይኖርበታል ያሉት አንጻ ጠገዴና አዳርቃይ በየዳና ደባርቅ የአማራ ነገድ የሚኖርበትን የቅማንት አስተዳደር ይመስረት ባዮች አልገባቸው ብሎ እንጂ ለወያኔ መጠቀሚያ ነው:: ለዚህም የአቶ ነጋ መጽሐፍ ዋና በር ከፋች ነው:: ምክንያቱም የወያኔዎች እቅድ በግማሽ ጎንደርን ወደ ትግራይ ለመከለል ዓላማቸው ነውና::

አቶ ነጋ የወያኔዎች ዓላማ አልገባዎትም:: ወያኔዎች ዓላማቸው ሕዳሴው ግድብ ካለበት ለመድረስ ነው:: ከዚያ ለመድረስ ደግሞ ወልቃይትን እንዳጠፉት ሁሉ አርማጭሆን ጫቆንና ቋራን እያጠፉ ከሕዳሴው ለመድረስ ያመቻቸው ዘንድ እርስዎንና እርስዎን የመሰሉ አግኝተዋል:: ዓላማቸው ግልጽ የሆነ ቀደም ብሎ ነው:: ለዚህም በጎንደር ክፍለ ሀገር ውስጥ የወረዳ ማህበር እንዲመሠረት ጥረት ሲያደርጉ የወረዳው ማህበር ምስረታ አገር ለማጥፋት የሚያግዝ እንጂ ልማት እንደማይለማ ይህን ዓላማ የሚያራምዱትን ሁሉ እንዲረዱት ለማድረግ ባለችኝ አቅሜ እንዲተው መምከር የጀመርኩት በ2001 ዓም ጀምሮ ነው:: እንዲያውም "የወረዳ ማህበር ቫይረስ ነው"የሚል ቃል ከመጽሐፌ በማስገባቴ ብዙዎች አኩርፈውኝ ነበር:: ከ6 ዓመታት በኋላ የወያኔ አቋም ግልጽ የሆነላቸው ስልክ እየመቱ "ይቅርታ"ያሉኝ አሉ:: በግሌ ቢጠሉኝና ቢያስጠሉኝ ግዴ የለኝም:: የምጠላው የወያኔ መጠቀሚያ ሁኖ በታሪክ መወቀስን ነው::

አቶ ነጋም የወያኔን ማኒፌስቶ ወደ ሕገ መንግሥት ተቀይሮ አንቀጽ ተሰጥቶት የሕግ አካል ሁኖ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚከፋፍል 39ኝ ሲያደንቁ ከዚህ በላይ ምን ማስረጃ ይኖራል?በምንም ይሁን በምን አንቀጽ 39 የኢትዮጵያ አንድነት አያስከብርም፤ይህን አንቀጽ 39ኝን የደገፈ ሁሉም በፀረ ሕዝብነትና በፀረ ኢትዮጵያዊነት የሚፈረጅ ነው:: የግል መብትዎን መንካቴ ሳይሆን አንቀጹ በማር የተጠቀለለ መርዝ በመሆኑ ነው::

# ምዕራፍ 2

## ወያኔ በጎንደር ላይ የፈጸመው አረመኔነት

ራስ ስሁል ሚካኤል ከትግራይ ጎንደር መጥተው አጤ ኢዮአስን እንደገደሉ ሁሉ ደጃዝማች ካሳ የኋላው አጤ ዮሐንስ እንግሊዞች አጤ ቴዎድሮስን ሊያጠቁ ሲመጡ መርተው አምጥተው አስገደሉ:: ነገር ግን 4ኛው አጤ ዮሐንስ ሥልጣኑ በጃቸው ካስገቡ በኋላ አጤ ቴዎድሮስ ያቀዱትን ኢትዮጵያን የማስፋፋት ዓላማ ቀጥለውበታል:: ወያኔ የአጤ ዮሐንስን ዓላማ ሳይሆን የያዘው የራስ ስሁልን ዓላማ በመሆኑ ኢትዮጵያውያኑ ሁሉ ስለ ትልቋ ኢትዮጵያ እንዳያስብ አደረገ:: ወያኔ ሀ.ብሎ ትግል ሲጀምር ከጎንደር ክፍለ ሀገር ሰፊ የእርሻ መሬት ወደ ትግራይ ከልሎ ተነሳ::

<u>የካቲት 1968 ዓም የሕወሓት ማኒፌስቶ</u> "ይህ መጽሔት የትግራይ ሕዝብ ሀቀኛ ልጅ የሆነው የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭ ድርጅት (ተ.ኃ.ነ.ት)መግለጫና የትግል መመርርያ ነው በተባለው መጽሔት "የትግራይ መሬት በደቡብ አለውኃ በመለስ መረብ ሲያካልሉት በምዕራብ በኩል ደግሞ ወልቃይትንና ጠገዴን ያጠቃልላል" ይላል:: ይህን የተሳሳተ ተግባር ብዙኃኑ የትግራይ ሕዝብ አልተቀበለውም:: ለናሙና ልጥቀስ::

1ኛ ራስ መንገሻ ስዩም በዶቼቬላ ሬዲዮን ቃለ ምልስ፤

2ኛ አቶ ግደይ ባህር ሹም አሞራ በተባለው መጽሐፋቸው

3ኛ አቶ ጌታቸው ረዳ በተለያዩ መጽሐፍቶቻቸው

4ኛ ሊቅ ዶ/ር አረጋዊ በርሄ

5ኛ ታጋይ ገሠሠ እንግዳ

6ኛ አቶ ገብረ መድኅን አርአያ በተለያዩ መጣጥፎቻቸውና ንግግሮቻቸው ሌሎችም የትግራይ ልጆች ያረጋገጡት ሐቅ ነው:: የወልቃይት ጠገዴንና የስሜን አውራጃ ተወላጆች ቁጥር ለመቀነስ ታስቦ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ይገደሉ ጀመር:: እንኳን ወያኔ ከተቆጣጠረው መሬት ቀርቶ ወያኔ ደርግ ውስጥ ባስገቧቸው ደጋፊዎቹ አዛውንቱን ኢዲዩ፤ወጣቱን ኢሕአፓ በሚል የጠለምትን አማሮች በ10 አለቃ ገብረ ሕይወት ገብረ እግዚአብሔር የስሜን አውራጃ አስተዳዳሪ የተፈጁት ቁጥራቸው አይታወቅም::

የጎንደር ክፍለ ሀገር አስተዳዳሪ ሻለቃ መላኩ ተፈራ በአብዮተኝነት ሌላውን ጎንደሬ ሲጨርሱ የአስር አለቃ ገብረ ሕይዎት በመሰሪነት ከደርግ ጽፈት ቤት ልዩ ፈቃድ አስወጥተው የሰሜን አውራጃ ተወላጆች በሊማሊሞ ገደል ወረወሩ:: ሰሜነኞችን ብቻ ሳይሆን ወሎየዎች ምህረት ሲገቡ በሊማሊሞ ገደል ተወረወሩ:: ደጃዝማች ጉግሣ አምባው ተጠቃሽ ናቸው:: ይህ ሴራ የታወቀው የአስር አለቃ ገብረሕይወት ከሞቱ ወዲህ ከቤታቸው ሰነዱ በመገኘቱ ነው:: ወያኔ ከ1973 ዓም ጀምሮ ወልቃይት ገብቶ ቀስ በቀስ አድማሱን እያስፋ ሌሎችን ወረዳዎች ለመያዝ ቻለ:: ከዚያም ወልቃይት "ትግሬ ነው"በሉ ሲባሉ የወገራ አውራጃ ተወላጆች አማሮች "አንልም" ያሉት ተገደሉ:: ከሞት

የተረፉት ተሰደዱ፤ንብረታቸውን ተቀሙ:: ይህን ሁሉ ችግር በወልቃይትና ጠገዴ ጠለምት ተወላጆች ጎንደሬዎች ላይ ግፍ መከራ ተፈጽሟል አሁንም እየተፈፀመ ነው:: በተለይም በወያኔው እስር ቤት አማራው ሕዝብና ወልቃይቴዎች ማለቃቸውን አስመልክቶ የወያኔው ታጋይ እንዲህ ሲሉ መስክረዋል::

ታጋይ ገሠሠ እንግዳ <u>ታሪክ አጉዳፊው የአልባንያ ደብተራ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 71 "የሕወሓት መሪዎች የትግራይን ሕዝብ ድጋፍ ለማግኘት ለጋ ወጣቱ ወደ ትግሉ ሜዳ ለማሰለፍ ይጠቀሙበት ከነበሩት ሌሎች የቅስቀሳ ዘዴዎች አንዱ በጥላቻ ላይ የተመሠረተ ፕሮፓጋንዳ ማካሄድ ነበር:: የአማራ ገዥ መደቦች የትግራይ ሕዝብ ታሪካዊ ጠላቶች ናቸው:: ታሪካችንና ቅርሶቻችንን ያጠፉት አማራዎች ናቸው:: ለድህነትና ለስደት የዳረጉን አማራዎች ናቸው:: በአማራ የተወሰዱት እንደ ወልቃይት ጠገዴ፤ሁመራ፤አልውሃና ሌሎች የትግራይ መሬቶች እናስመልሳለን ወዘተ እያሉ ነጋ ጠባ በመቀስቀስ ሕዝቡ በሌላው ወገኑ ላይ የከረረ ጥላቻ እንዲኖረው ለማድረግ ይሞክሩ ነበር"ይሉና ገጽ 229 "ገሀነም ተብሎ የሚጠራው የስቃይ ቤት የተሰራው በምዕራባዊ ትግራይ በተከዜ በርሃ የነበረው እስር ቤት ነው:: በዚሁ እስር ቤት አብዛኞቹ ያለቁት ለወያኔ አንገዛም ብለው ያመፁ የወልቃይትና የጠገዴ ሕዝቦች፤ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች አባላት ከደርግ የተማረኩ መኮንኖችና ሰላዮች ፀረ ወያኔ ተብለው የሚጠረጠሩ ንፁሃን ዜጎች ናቸው:: የዚሁ ዓይነት ተመሳሳይ የእልቂት እስር ቤቶችም በወልቃይት፤በዔኢ በወርዔ፤በፆሮናና እንዲሁም በሌሎች አካባቢዎችም ነበሩ:: ዛሬ በነዚህ እስር ቤቶች አካባቢ ያለው መሬት ቢቆፈር ምናልባም በአዲስ አበባ ዙሪያ በቡልዶዞር ተቆፍሮ ከወጣው የቀይ ሽብር ሰለባ የሆኑትን የንፁሃን ዜጎች አጥንት የሚበልጥ እንጂ አያንስም"ሲሉ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል::

የወልቃይትና የጠገዴ፤የጠለምት አርሶአደሮች ችግሩ ሲብስባቸው ከፋኝ ብለው ተነሱ:: የአርሶአደሮች ስብስብ ጥንካሬው ከፍ እንዳይል ሊደግፏቸው ይችላሉ ያሉአቸውን ሁሉ ወያኔ ባገኘው አጋጣሚ ይፈጃቸው ጀመር:: ሌላው ቀርቶ ሱዳን የሚኖሩትን በርካታ የወልቃይ ጠገዴና የአርማጭሆ ተወላጆች ታፍነው ተወስደው ተገደሉ:: ወያኔ የኢትዮጵያን በትረ ሥልጣን እንደያዘ ከፋኝ ከነበረው ይበልጥ ጠንከር ብሎ ድርጅታዊ መዋርቅ መያዝ ጀመረ:: በዚህ ሰዓት ከውጭ አገር ደጋፊ አግኝቶ ሲንቀሳቀስ በወቅቱ አቶ ገብሩ አስራት የትግራይ ክፍለ ሀገር አስተዳዳሪ አባቶችን ለሽምግልና ወደ በርሃ ላኩአቸው::

ሻማግሌዎች በአባት አደሩ ሽምግለው በግማሽ እጃቸውን እንዲሰጡ ሲያደርጉ ወያኔ መቀሌ ወስዶ ከ1000 በላይ አሰራቸው:: ሽምግለው ያስገቧቸው አባቶች አቶ ገብሩን "ሽምግለን ያስገባናቸውን ፍታልን" ሲሉአቸው የተመለሰላቸው መልስ "ለባርኖሶች ግዜ የለኝም"ብለው ነበር:: ባርኖስ ማለት በትግርኛ ቋንቋ ትል ወይም ተባይ እህል የሚበላ ማለት ነው:: ሻዕቢያ ግልጽ ወረራ ካደረገ ወዲህ በውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን ከወያኔ ጋር አብረው ቁመው ነበር:: ወደ አገር ቤት ባልሄድም እኔም ደጋፊ ነበርኩኝ:: ከዳላስ የሄደው አንዱ የጎንደር

ክፍለ ሀገር የወገራ አውራጃ የወልቃይት ተወላጅ አቶ ገብሩን መቀሌ ሕደው "በሽምግልና የገቡትን ፍታልን ብለው" ሲጠይቁ በአቶ ገብሩ የተሰጣቸው መልስ "በባርኖስ አትምጣብኝ" የሚል ነበር:: ይህን በሚመከት አቶ ገብሩ ሚያዝያ 2 ቀን 2002 ዓም ሲያትል መድረክን ወክለው መጥተው ስብሰባ ላይ ይህ ጸሐፊ ጠይቆ እንዲህ ሲሉ መለሱ::

አቶ ገብሩ አስራት "ባርኖስ ለተባለው ጉዳይ በወቅቱ እኔ አስተዳዳሪ ነበርኩኝ:: በዚያን ሰዓት ጦርነት ነበር:: ዛሬም ጦርነት አለ፤ጸጥታውን አስጠብቄአለሁ" ብለዋል:: በምህረት ከገቡት መካከል ሊይዟቸው ሲል እጄን አልሰጥም ብለው ተታኩሰው የሞቱትን የአቶ ኪዳመናርያምን ፎቶና የአንድ እስረኛ ፎቶ ያስታውሱ እንደሆን ስሰጣቸው ተሰብሳቢው እያያቸው ሁሉንም ምስል ፎቶዎች ከቦርሳቸው ከተው ወስደዋል:: ወያኔ፤ጎንደሬዎችን ጥላቻ የድርጅቱ ዓላማ ነው:: ለምሳሌ ዋልድባ ገዳም መፍረስ አስመልክቶ ቬ.ኦ.ኤ ለአቶ ሲሳይ መረሳ፤ ጥያቄ አቅርቦ ነበር:: ሲመልሱ "የሚፈርሱት ቤተ ክርስቲያን 18 ሳይሆኑ 4 ናቸው::የሚፈልሰው አጽም የቅዱሳን አጽም ሳይሆኑ የወልቃይቴዎች አጽም ነው"ሲሉ መልሰው ነበር:: በፓል ቶክ አንድ ወያኔ" እነዚህ ጎንደሬዎች አኒማል ናቸው"ብሎ ሲያንቋሽሽ ተሰምቷል:: ይህ መከረኛ ፓል ቶክ ላይ አማራውን አንዱን ደፋር ሌላውን ፈሪ አድርጎ ለማሳየት በረቀቀ ሴራቸው እንዲህ ሲል ተናገረ "እኛ ጎንደርን በመከራ ወሎን በጦንቻ፤ጎጃምን በፍጥጫ፤ ሸዋን በከዘራ የያዝነው ስልጣን አንለቅም" ሲል ተናግሮ ነበር:: ታሪክ እንደሚመሰክረው ወያኔ ሸዋን በከዘራ ሳይሆን በመከራ ነው ያለፈው፤ሌላውን ቢክዱ የአምቦ ጦርነት ሊክዱ አይችሉም:: ጎጃምን በፍጥጫ እንዳላለፉ ራሳቸው ያውቁታል:: ታሪክም ይዘክረዋል፤

ገብሩ አስራት ገጽ 215" ኃምሳ አራት ሺህ ያህል ሰው እንደተሰዋ ተረጋግጧል::ይህ አኃዝ ሕይወታቸውን ያጡትን ብቻ የሚመለከት ሲሆን ቁጥራቸው በውል ያልታወቁ የአካል ጉዳተኞችና የደረሱበት የማይታወቅና የጠፉም አሉ"ሲሉ ገልጸውታል:: ወያኔዎች ይህን ያህል ሰው አልቆብናል፤ የሚሉት እነሱ ጠበንጃ ያነሱት ለሥልጣን እንጂ ለዲሞክራሲ አልነበረም:: ለዚህም ትክክል አይደላችሁም ያላቸውን ሁሉ "አሸባሪ ነው፤ሕገ መንግሥቱን ሊንድ ነው፤ጸረ ልማት ነው"የሚሉት ጉንጭ አልፋ ልፍለፋ አብዝተዋል:: አንዴ ይህው ፓል ቶክ ላይ "ከሁሉ ይልቅ ጸረ ሰላም የሆኑ ጎንደሬዎች ናቸው:: በአሸባሪነይ ከታሰሩት 23 መካከል 11 ጎንደሬዎች ናቸው:: እኛኮ ከሸዋ አማራ ነጻ አውጥተናቸዋል" ሲል ተናገረ:: ለመሆኑ አጤ ኃይለ ሥላሴ ሆኑ ደርግ ማነው የሸዋ አማራ ያደረጋቸው? ይህ ሁሉ ሀሰት ነው::

የየካቲት ውለታ ፕሮግራም ቴሌቭዥን 65 ሺህ ሠራዊት ሲያስጨርስ ከመቶ ሺህ በላይ ቁስለኞች አሉ" ይላል:: የወያኔ ሰራዊት ቀይ ኮከብ ዘመቻ ሻዕቢያን ከናቅፋ ለማዳን ሕዶ ከሞቱት ባሻገር ሽሬ አልቆበታል:: ከዚያ ቀጥሎ ደብረታቦር ላይ አልቆበታል:: ወዲ ቀሺ የተባለውን ፊልም ማየት ይቻላል:: የዛሬውን አያድርገውና የጴንጤ ቄስ ከመሆናቸው በፊት አቶ ታምራት ላይኔ ደብረታቦር ሕደው "የአማራውን አከርካሪት የሰበርንበት" ሲሉ ተናግረው

ነበር፡፡ ወያኔ ከደብረታቦር ቀጥሎ የመጨረሻ የተመታው ሸዋ አምቦ ነው፡፡ አጋጣሚ ጥር 1988 ዓም ከአዲስ አበባ ወደ ጎንደር ስሄድ አቶ ስዬ አብርሃ ጋር ነበርን፡፡ እኔ ስዬ መሆናቸውን አላውቅም ነበር፡፡ አውሮፕላኑ ከቦሌ ተነስቶ ወደ ላሊበላ ስንሄድ ልጇ አባይነሽ "ይህ አካባቢ ማን ይባባል"ብላ ስትጠይቀኝ የማላውቀው መሆኔን ስነግራት ሰሙ፡፡

አቶ አብርሃ "ይህ አካባቢ ሰሜን ሸዋ ይባላል"አሉና በእንግሊዘኛ መለሱላት፡፡ እኔ ጋርም ጨዋታ ጀመርን ከዚያም ከአሜሪካ የሄድን መሆናችን አወቁና ዲል ያለ ጨዋታ በተለይ በኢትዮጵያ ታሪክ ዙርያ ብዙ ብዙ አውርተናል፡፡ ላሊበላ መድረሳችንና እርሳቸው መውረዳቸው አቋረጠን፡፡ እርሳቸው ከዚህ አካባቢ ደርግና ኢሕአዴግ ከፍተኛ የሆነ ጦርነት ገጥመው ነበር፤የደርግ ወታደር ብቻ ሳይሆን ሕዝቡ ጭምር ተዋግቷል አሉኝ፡፡ እኔ እርሳቸው ይሆናሉ ብዬ አልጠረጠርኩም፡፡አለባበሳቸው አይመስሉም፡፡ ላሊበላ ሲወርዱ መልካም ጉብኝት ብለውኝ ወረዱ፡፡ የአውሮፕላኑ አስተናጋጅ ሽማግሌ ወደኔ መጡና ከማን ጋር ስትጫወት እንደነበር ታውቅ ነበር አሉኝ እኔም እንደማላውቅ ነገርኳቸው፡፡ ከሲያትል የሄደ አቶ አስማማው ወዳጄ እንዲሁ መጥቶ "ስለ ፖለቲካ አንስታችሁ ነበር"አለኝ እኔም አላነሳነም፡፡ ስለ ታሪክ ነው የተጨዋወትነው አልኩና አቶ ስዬ አብርሃ መሆኑን ባውቅ ኑሮ ፎቶ እንነሳ እላቸው ነበር አልኳቸው፡፡ ይህን ገጠመኝ ያነሳሁት ወያኔ ሸዋ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ጦርነት ገጥሞት እንደነበር ለመግለጽ ፈልጌ ነው፡፡

የአዲስ አበባው ቴሌቭዥን የካቲት 11 ቀን 2007 ዓም "ከ60 ሺህ በላይ ሞቱ ከመቶ ሺህ በላይ አካለ ስንኩላን ሁነዋል"ሲል ዘግቦአል፡፡ ያውም ሰፊው የትግራይ ሕዝብ በ1976 ዓም በእርሀቡ ያስጨረሱትን ሳይጠቅሱ ነው፡፡ ወድከውሊና ፋአ፤በስደተኝነት መጥቶ የሞተው ሕዝብ አልተቆጠረም፡፡ ይህ ጸሐፊ ራሱ ገዳሪፍ የገባውን ስደተኛ እንጉርጂ እንድንቀብር በሱዳን ኤድ ዋና አላፊ አቶ ገብረወልድ ለአንድ ሳምንት የሱዳን ኤድን ሰራተኞች ከስራ አቁመው እነዚህን ስደተኞች እንዲቀብሩ መመርያ ሰጡ፡፡ እንጉርጃ ገብቶ የሚሞተውን ወገኖቻችን ስንቀብር ሰንብተናል፡፡ አምራኩባ የገባውን ስደተኛ መላከ ሰላም ሲሰይ አየለ ኮሎምቦስ አጓዮ መጥተው የሞቱት አባት ሕዝቡ ወጥቶ እንዲቀብር አድርገዋል፡፡ ወድከውሊ የነበረው ሕዝብ ብዛት ስንት እንደሆነ አይታወቅም፡፡ ባጠቃላይ የትግራይ ሕዝብ በጦርነት ከሞተው ይልቅ ምግብ እንሰጥሃለን ብለው አሰድደው ያስፈጁት ይበልጣል፡፡ ምክንያቱም በ1977 ዓም ድርቅ ገብቶ ስለነበር ወደ ሱዳን ወስደው ገድለውታል፡፡ የዓለም ሕዝብ የሰጣቸውን ርዳታ ለማሌሊት ፓርቲ ድግስ ደገሱበት፡፡

አረጋዊ በርሄ ጀኔራል ፃድቃንና ጤዛዋ ማሌሊት በ40ኛው በተባለው መጣጥፋቸው ኢትዮ ሚዲያ ድረገጽ ገጽ 2-3"ማሌሊት ተመስርቶ ወርዒ የህወሓት/ማሌሊት ማዕከላዊ ኮሚቴ እቅድ ለማውጣትና ባጀት ለመመደብ ተሰበሰበ፡፡ በእቅዱ መሠረት ባጀቱ ለመመደብ የቀረበው ጥሬ ገንዘብ 100 (አንድ መቶ)ሚልዮን ብር ነበረ፡፡ ይህ ገንዘብ ፃድቃን እንደሚተርከው ከደርግ የተነጠቀ አልነበረም፡፡ ወይም ደግሞ ከሕዝቡ የተዋጣ አልነበረም፤በድርቅ

የሚቆላው ሕዝብ ስም ከውጭ ረዳቶች የተሰበሰበ ነበር። ይህ ገንዘብ በድርቁ ምክንያት ከግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ከተሰበሰበው ከፊሉ ሆኖ የያኔ የማህበረ-ኢኮኖሚ ሃላፊ አውዓሎም ወልዱና የውጭ ጉዳይ ሃላፊ ስዩም መስፍን ለማሌሊት ምስረታ ከሱዳን ሲመጡ እግረመንገዳቸውን በጆንያ ጭነው ያመጡት እንደነበረ እናውቃለን። በባጀት ምደባው መለስ ዜናዊ የውሳኔ ሀሳብ ሲያጸድቅ 50/ለማሌሊት ማጠናከርያ 45/ለሕወሓት ስራ ማስኬጃ 5/ ለድርቅ ጉዳተኞች ብሎ አረፈው። ለድርቅ ጉዳተኞች 5/ ብቻ መመደብ በቂ አይደለም ከፍ ማለት አለበት የሚል አንድ ድምጽ ተሰማ፤ይሁን እንጂ በማሌሊት ምስረታ የተሳከረው ማ/ኮ ተማፅኖውን ከጉዳይ አልቆጠረውም"ሲሉ ሊቅ ዶ/ር አረጋዊ ጽፈዋል። ለዚህም ነው ወያኔ አይታመንም የትግራይን ሕዝብ አስጨርሷል ለሌሎችም አይሆንም የምንለው።

ወያኔ ይህን ሁሉ አልፎ መላ ኢትዮጵያን ሲይዙ ቅድሚያ ጎንደሬው አማሮች ሆኑ ሌሎች ነገዶች እንዲጠሉት አድርገዋል። የአማራውን ቁጥር ሊቀንስ ሲል መርፌ አስቀድሞ የወጋቸው የጎንደር እናቶችን ነው። አሁን የአማራ እናቶችን የማምከኛ መርፌ ተወግተዋል። ወያኔ "ትግራይ ውስጥ በአንድ ቀን 300 ህጻናት ተወልደው አደሩ ስማቸው ሀያሎም ተባሉ" ብለው ጽፈዋል። ከወያኔው ምክር ቤት ስብሰባ ወ/ሮ ሶፊያ "2.5 ሚልዮን አማራው ቁጥሩ ቀንሷል" ብለው ሲናገሩ ከአማራ ክልል ተወክለናል ያሉት የምክር ቤት አባላት ለምን ብለው ሳይጠይቁ ቀሩ። ሌላው ቀርቶ ትንታጉ አቶ ልደቱ አያሌው እየተቁለጨለጨ ዝም አሉ። ሊቅ ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ "እንዴት ሊሆን ቻለ"ብለው ጠየቁ። አሁን ደግሞ በቅርቡ ወ/ሮ ሶፊያ "3 ሚልዮን አማራ ቁጥሩ ቀነሰ"ሲሉ በይቱብ ተናግረዋል። ያ ማለት ጎንደርን ይጨምራል።

ወያኔ ጎንደር እንደገባ መጀመሪያ ቅርስ ማጥፋት ጀመረ። ቤተ መንግሥቱ የነበረው አንበሳ ምግብ አጥቶ ሞተ። ሳያወጡት በመቅረታቸው ሽታው ከተማውን አበላሽቶት ነበር። ይህ የሆነው የጎንደር ሕዝብ አንበሳውን የኢትዮጵያ ቅርስ አድርጎ ስለሚያየው ያነን አመለካከት ከጭንቅላቱ ለመፋቅ ሲሉ የፈጸሙት ሴራ ነበር። በመቀጠል ሌሎች በቤተ መንግሥቱ ይኖሩ የነበሩ ቅርሳቅርሶች እየተዘረፉ ወደ ትግራይ ተወስደዋል። ጣልያን ጎንደር በነበረ ሰዓት ለከተማው መገልገያ ጄኔሬተር ተክሎ ነበር። ወያኔ ከወሰዳቸው ቅርሳቅርስ አንዱ ይህ ጄኔሬት ነው።

ጣልያን የተከለው የኮረንቲው ሞተር
አገልጋይ የነበረው የመብራቱ የኮረኒተው ሞተር
ጀግና በማጣቱ ተነቅለ ጎንደር
ትግራይ ላይ ተከሉት ከሚለማው መንደር
ብሷል አዛውንቱ አባዬ ሲናገር
ይህን ሁሉ እያየ ዝም አለ እንዴ ጎንደር?

ቋግሜ 1985 ዓም አደባባይ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በጸሎት ላይ ያሉትን ገደለ። አዛውንቶችን አሰረ። ከከተማ እስከ ገጠር ይቃወማሉ የተባሉትን ሁሉ ተራ በተራ ይገድሉአቸው ጀመር። አርሶአደሩን መሳሪያን አስወረዱት።

ቅማንቶችን ለማደራጀት ሲሞከር የቅማንት አባቶች ሁኔታውን ሰምተው እንደማይቀበሉት አስጠነቀቁ። ወያኔ አንዱን አውራጃ ካንዱ አውራጃ ጋር ለማጋጨት ጥረት አደርጓል። በጎንደሬው በኩል ፍንጭ ሊያገኝ አልቻለም። በዚህ ምክንያት ወያኔ ይበልጥ ተበሳጨ፤ከዚህ በኋላ ሻለቃ መላኩ ተፈራን ከጅቡቲ ጠልፎ ጎንደር ወስዶ "ልጆቻችሁን የፈጀው መላኩን ፍረዱበት"ሲል የጎንደር ሕዝብ "ሻለቃ መላኩን ሕግ ይፋረደው"ብሎ መለሰለት። ጎንደሬው ይህን በማለቱ ለወያኔ የራስ ምታት ሆነው። ከዚህ በመቀጠል ወያኔ መሬት ሲያከፋፍል የአንዱን መሬት ለአንዱ በወረዳና በአውራጃ ልዩነት ሊፈጥሩ ጥረት አድርጓል።

የአማራውን ለቅማንቱ የቅማንቱን ለአማራው በመስጠት ያደረገው ጥረት ሁለቱ ነገዶች ሳይጋጩ በመቅረታቸው ወያኔ አሁንም ተበሳጨ። እስኪ ከልብ አስቡ፤ሰውን በሰውነቱ የምታዩ ሁሉ ወያኔ በጎንደር ሕዝብ ላይ የፈጸመውን ክፉ ተግባር። ከጢስ አባ መብራት ጠልፎ በደብረ ታቦር አውራጃ እና በጋይንት አውራጃ አድርጎ ትግራይ አስገባ። ታዲያ መብራቱ አልፎ በሚሄድበት አካባቢ አገልግሎት እንዲሰጥ አልተደረገም። አንዳንድ አርሶአደሮች አልፎ የሚሄደውን መብራት ሊያበላሹ መሞከራቸው አልቀረም። ወያኔ በወኪሉ በአማራው ክልል ባለስልጣናት አማካኝነት እያንዳንዱ አርሶአደር መብራቱ አልፎ በሚሄድበት አካባቢ መጠበቅ አለበት ተብሎ እንዲታዘዝ ይደረጋል። በዚህ ሰዓት የሁለቱ አውራጃ ተወላጆች ሙሉ ሌሊት ሲጠብቁ ያድራሉ። አንዱ አዋጁን ያልሰማ አርሶ አደር አልፎ ሲሄድ ሌላው አርሶአደር በመሬቱ ላይ አልፎ የሚሄደው መብራት ከተተከለበት ላይ ቁሞ ያየዋል።

አያ እንዴት ዋልክ ሲመሽ ምንታደርጋለህ ሲለው የትግራይን ልጆች እራት ሲበሉ ቁሜ እያበላሁ ነው ብሎ መልሶለታል። ይህን ተግባር ማሰብ ለሚችል ሰው ሊያፍርበት እንጂ ሊኮራበት አይገባም። የቅማንት እናቶች ማምከኛ መርፌ ተወግተዋል፤የቅማንት ሕዝብ እንደሌሎች ነገዶች ሁሉ በወያኔ ተደብድበዋል፤የቅማንት ወጣቶች እንደሌሎች ወጣቶች ሰላም አጥተዋል። በቋግሜ 1985 ዓም አደባባይ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ከተገደሉት መካከል ሦስቱ የቅማንት ልጆች ናቸው።

አቶ ነጋ የአማራን ሕዝብ "ዘራጢ"እያሉ ከማዋረድ ይልቅ ወያኔ በቅማንት ወገኖቻችን ላይ ያደረሰውን ጥፋት አንዱን ሳይጠቅሱ ቀርተዋል። የቅማንት ልጆች በቅንጅት የታሰሩና ጭልጋ ውስጥ የተገደሉ ነበሩ። ምንም እንኳን መጽሐፉ የተጻፈው በ1993 ዓም ቢሆንም በቅንጅት የተጎዱት የቅማንት ልጆች ጎንደሮች በ1997/1998 ዓም ላይ ነው። ሌሎች አሁን ወያኔን የምትደግፉ እንዴት ሳይታያችሁ ቀረ? መተማ ወያኔ ሲወስደው የጭልጋ አርሶአደር ከብቶች የት ሊውሉ ነው? የአባቶቻችሁ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ሥላሴ ገዳም ለሱዳን ሊሰጥ ነው እየተባለ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ በሚጨነቅበት ሰዓት ዝምታው ምንድነው?

# ምዕራፍ 3

## ቅማንትና አማራን ለመለያየት የተደረገው ጥረት

የቅማንት ሕዝብ ታሪክ ገጽ 68 "የቅማንት ሕዝብ የልማትና ተራድኦ ማህበር የሚል የልማት ድርጅት ተቋቁሞ"ሲሉ ጽፈዋል። ይህ ማህበር የተቋቋመው በ1984 ዓም ሲሆን ወያኔ ሆን ብሎ ያዘጋጀው ማህበር ነው። ምክንያቱም በነሐሴ 1983 ዓም በግልጽ በሽግግሩ መንግሥት ወቅት ከጎንደር ወደ ትግራይ መሬት መወሰዱን አወጀ። በጭልጋ አውራጃ አንድ ወረዳ ወደ ቤኒሻንጉል መሰጠቱ የጎንደር ተወላጆችን አበሳጨ። በዚህ ምክንያት የክፍለ ሀገሩን ገጸምድር ስፋት ለማስታወቅ ይረዳ ዘንድ የጎንደር ማህበር በአባቶች ተመሰረተ። መሬቱ በግልጽ ወደ ትግራይ መወሰዱን ሕዝቡ እያወቀ መምጣት ጀመረ። የቅማንት ማህበር ለብቻ እንዲመሰረት የተደረገው ጎንደሬው አንድ እንዳይሆን ስለተፈለገ ብቻ ነው።

ወያኔ የጎንደርን ማህበር ለማዳከም ጥረት አደረገ። ማህበሩ ሲመሰረት ጀምሮ የክፍለ ሀገሩን ስፋት ለመግለጽ አስቦ እንጂ በወያኔ አገዛዝ ዘመን ልማት እንደማይለማ አሳምሮ ያውቀዋል። በዚህ ምክንያት አሜሪካ ያለውን ማህበር ለማድከም ሲል ወያኔ አቶ ክንፈ ገብረ መድህንን ወደ አሜሪካ ላከ። አቶ ክንፈ ገብረ መድህን የተወለዱት ጎንደር ክፍለ ሀገር ወገራ ሲሆን ያደጉት ዳባት ነው። አሜሪካ መጥተው ባልንጀሮቻቸውን ሌላ የልማት ማህበር መመስረት እንዳለባቸው መከሩ። ምክሩን የተቀበሉ ራስ አገዝ ጎንደር ብለው መሰረቱ። ዓመት ጠብቀው የጥምቀት በየወረዳው የተሰባሰቡ ልጆችን በእስፖርት እንዲገናኙ ማድረግ ጀመሩ። በዚህ ሰዓት ወደ ትግራይ የተከለሉ ሆኑ በጭልጋ አውራጃ ወደ ቤኒሻንጉል የተከለለው ወረዳ ልጆች ወደ ጎንደር ሳይመጡ ቀሩ። ወያኔ የፈለገው ይህ ነበርና የተወሰኑ ዓመታት በዚህ ቀጠሉ። እነዚህ ወገኖች ውለው አድረው ራስ አገዝ ጎንደር የወልቃይትን ጉዳይ ሲያነሱ እነሱም ከወያኔ ጋር ተለያዩ። ከዚህ በኋላ ወያኔ በውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ በየመጣበት አካባቢ የልማት ማህበርና ሌላም ሌላ እንዲሰሩ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መስርያ ቤት መመርያ ሰጠ።

<u>ውጭ አገሮች በሚገኙ ሚሲዮኖቻችን የኮንስቲትወሲ ግንባታ</u> የሚመራበት ማንዋል የተባለው መጣጥፍ ገጽ 8"ተወልዶ ያደገበት መንደሩን፣ክልሉን አገሩን በሚመለከት ሥራዎች በገንዘብም ሆነ በሙያው እንዲያግዝ ማበረታታት" ይላል። ይህ ከሆነ በኋላማ እያንዳንዱ በየትውልድ መንደሩ ትንሽ ነገር ለመስራት መሰባሰብ ሲጀምር ሰምቶት የማያውቀውን በደል ይነገራቸው ጀመር። የበደሉ ብዛትና የችግሩ ብዛት አናሳ ነገዶችን የአካባቢ ልማት እንዲመሰርቱ ገፋፋቸው። ከዚህ በመቀጠል ወያኔ የጎንደር ክፍለ ሀገር ተወላጆችን አንድ ሁነው እንዳይመጡ ለማድረግ ጥረት ያደርግ ጀመር።

አንደኛው ጎንደር አንዱን ጎንደር የበደለ አስመስሎ ቅስቀሳ ማድረጉን ሴት ተቀን ተያያዘው።

እከክን ስናከው የተወን ይመስለናል። ቆይቶ ሲደማ ቁስሉ ሰላም አይሰጥም በጎንደር ክፍለ ሀገር ከነሐሴ 1967-983 ዓም ጦርነት ኑሮበታል። ጦርነት ድርጅታዊ ሥርዓተ መዋቅር የሌለው በመሆኑ እንጅ አሁንም አለ። ኢሕአፓ፤ ሆነ ኢዲሁ፤ኋላም የቀድሞው ኢዴህን የአሁኑ ብአዴን ወያኔ ተጨምሮ በተለያዩ አውራጃዎች ጦርነት በጎንደር ክፍለ ሀገር ነበር፤ደርግ ትምህርት ቤት ሲሰራ ከላይ የተጠቀሱት ድርጅቶች ሲያፈርሱ መህይምነት በጎንደር ላይ ነግሶ ቆይቷል። በዚህ ምክንያት ትምህርት ቤት እንስራ የሚለው ቅስቀሳ ገፍቶ መጣ። ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ በነገድ ከከፋፈለ በኋላ በውጭ አገር ያሉት ኢትዮጵያውያን በያካባቢያቸው የልማት አውታር እንዲዘረጉ ከፍተኛ የሆነ ዘመቻ አካሂዷል። የተወሰኑ የጎንደደር ልጆች በተለያዩ ቦታዎች ትምህርት ቤት፤ለመስራት ጥረት ተደርጓል። ይህ በዚህ እንዳለ ወያኔ መሬት ለሱዳን ሊሰጥ ነው እንነሳ ሲባል ከወያኔ በልጠው የተነሱ እነዚህ የወረዳ ማህበር መሪዎች ሆኑ። የጎንደር መሬት ለሱዳን መሰጠቱን የተረዱት የተወሰኑ የሌላ የወረዳ ማህበር አባላት ትክክል አይደለም ብለው ተዋቸው። ወያኔ ያደራጃቸው የተወሰኑ የቅማንት ማህበር አባላት ጎንደሬው አንድ እንዳይሆን ለፍተዋል። አልገባቸው ብሎ አርቀው ማሰብ ያቃታቸው በመሆናቸው እንጂ መሬቱ የነሱም ነበር።

የአርማጭሆ ልጆች መሬት ሲያጡ፤የቅማት ልጆች ይቸገራሉ። እኔ እንደማውቀው የቅማንት ልጆች አርማጭሆ ዋልያ ማርያም ሮብ ገበያ ሕደው የነሱን ሽጠው የፈለጉትን ሸምተው ሲሄዱ አይቻለሁ። ስለዚህ አርማጭሆ መሬት ካጣ እኮ ያ በገበያ ላይ የፈለጉትን መግዛት አይኖርም። ምክንያቱም ገበሬው መሬቱን ካጣ ካላረሰ የቅማንት ልጆች ያላቸውን ሸጠው የሌላቸውን መግዛት አይችሉም። ወያኔ በ1968 ዓም ይፋ ባደረገው ማኒፌስቶው ደንበሩ ወገራ አውራጃ መሆኑ ካርታው ምስክር ነው። በ1983 ዓም ነሐሴ ላይ በሽግግር መንግሥቱ ስም ይፋ ያደረገው ካርታ የክልል አንድ ደንበር መተማ ነው። ከዛሬ 8 ዓመት በፊት ወያኔ አብደራፊ ጡረታ የወጡትን ወታደሮቹን አስፍሮ ቆይቷል። ውለው አድረው ክልል አንድ እንጨመር ብለው ሰላማዊ ሰልፍ ወጥተው ጥያቄ ያቀረቡት እነሱ የወያኔ ታጋዮች የነበሩ ናቸው።

<u>ዋይታ ቅጽ</u> 2 ቁጥር 1 ታህሳስ 29 ቀን 2004 ዓም "ትግራይ ተብላ ለምትጠራ አገር ዋናው ቅድመ ዝግጅት የምዕራብ ጎንደርን ሕዝብ (የጠለምት፤ የወልቃይትጠገዴና አርማጭሆ ቋራ፤ማፈናቀልና የትግራይን ሕዝብ በሰፊው ማስፈር መሆኑን"የሚገልጽ መጣጥፉ ጽፈው ነበር። ልክ ነው የወያኔ ዓላማ ይህ ነው። ዋልድባን እንታደግ ወይም ደግሞ (ሴቭ ዋልድባ)የሚለው ብሎግ መስከረም 2007 ዓም ጹሑፍ አውጥቷል።

<u>Save Waldebba</u> ብሎግ "ከዚህም በተጨማሪ ከዓመት በፊት በልማት ሰበብ በርካታ ነዋሪዎች ቀያቸውን ለቀው በምትኩ ሌላ ቦታ ይሰጣችኋል በማለት

የትም ሚዲያ ተበትነው እንደሚገኙ ከስፍራው የደረሰን መረጃ ያመለክታል። አሁንም መንግሥት በሚቀጥሉት ወራት ውስጥ 3900 አባወራዎችን ሊያናሳ እና ቦታቸውን ሊወስድ እንደሆነ በሰፊው እየተነገረ ይገኛል። ነዋሪዎችም ከዚህ በፊት ተነስተው የት እንደደረሱ ያልታወቁት በርካታ ነዋሪዎችን እጣ ፈንታ በእነሱም ላይ ሊደርስ እንደሚችል በመገመት በርካቶች በከባድ ስጋት ላይ እንደሚገኙ ለመረዳት ችለናል"ሲል ብሎጉ ጽፏል። ዋይታ የዛሬ 3 ዓመት የጻፈው አሁን እየተፈጸመ መሆኑን ተግባሩ እያረጋገጠ ይገኛል።

ነጋ አንዳርጌ ሪበል ጎንደር በሚለው ጹሁፉቸው "ወያኔ በጎንደር ላይ ያለው ስትራቴጂ ግልጽ ነው። ሰሜን ጎንደርን ወደ ትግራይ ለማጠቃለልና ለመውሰድ ነው"ሲሉ ጽፈው ነበር። እኔ ደም አይፍሰስ በቃ የሕወሓት ማኒፌስቶ ያብቃ ብዬ መጽሐፍ ስጽፍ የወሎ ልጆችን ጠይቄ ነበር። ከነዚህ መካከል አቶ ዮሐንስ ተስፋዬ "ሰሜን ወሎን ወያኔ ለወደፊቱ ጠቅልሎ ሊወስድ እቅድ አለው" ብለውኛል። ወያኔ ጎንደሬ እርስ በርሱ መጋጨት ስላለበት ብቻ ሳይሆን መሬት ከዚህ በፊት ሲነጥቅ ሕዝቡ ሆነ ብሎ ስላልተነሳ አሁንም ደግሞ ተጨማሪ መሬት ለመውሰድ በማሰቡ ነው።


ሊቀ እጅጉና አዳነ አጣናው የወያኔን የእብሪት እስከ መቼ እንሸከማለን በተባለ በድረገጽ በወጣ በራሪ ገጽ 2 "ወያኔዎች በነደፉት ትግራይን የማስፋፋት አዲስ እና ቀጣይ ዓላማ ካሁን ቀደም በኃይል ይዘው የትግራይ ክልል ነው ብለው ከወረሩት ዳንሻ ከተማ ወደ ደቡብ ምዕራብ 103 ኪሎ ሜትር በርሃውን አቋርጦ ከአብደራፊ ጋር ለማገናኘት ብሎም ሰፋፊ የእርሻና የትግራይ ሠፋሪ ለማካሄድ ታስቦ ሱር በተባለው የወያኔ የመንገድ ሥራ ድርጅት ጠረጋ ተጀምሯል። ለዚህ መንገድ ሥራ የሚወጣውን 300 ሚሊዮን ብር ወጭ የኢትዮጵያ መንግሥት መድቧል።"

"በዚህ ሳያቆም ከሰሜን ወደ ደቡብ የሱዳንን ጠረፍ እያዋሰነ ማለትም ከሁመራ ጫፍ ከልጉዲ ተነስቶ ወደ አብደራፊ የሚያገናኘው መንገድ በአስፋልት እየተሠራ ነው። የዚህ ወረራ ማዕዘን ትርያንግል ቅርጽ የያዘ ሲሆን በዚህ አካሄድ የትግራይ ምድራዊ አቀማመጥ ተቀይሮ በእስራኤልና አረቦች ያለው ካርታ ዓይነት እየሆነ መጥቷል። ይህም ብቻ ሳይሆን መተማን አልፎ እስከ አባይ ግድብ ድረስ እንሄዳለን የሚል ህልም አላቸው"ሲሉ ጽፈዋል። ልክ ነው ሰው አያምንም እንጂ የሚሰማ ከሆነ ቤኔሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከጎንደርና ከጎጃም የሰጡአቸውን ወያኔዎች እንደሚያስቡ ምላሴ በጨርቅ። ወያኔ አንዴ ደግሞ ጎንደር ልጆቻችሁ ትግርኛ ቋንቋ እንዲማሩ ማለቱ ታውቋል።

በላይ እንዳለ ዓሥራት ጋዜጣ መጋቢት 23 ቀን 1992 ዓም ገጽ 8 "የጎንደር ተማሪዎች በትግርኛ እንዲማሩ በሚል ያስተላለፈው ውሳኔ ዓላማው በውል ስለአልታወቀ ሁኔታውን በጥርጣሬ መመልከቱ ተገቢ ይመስለኛል"ሲሉ ጽፈው ነበር። ይህ ጹሑፍ የወጣው የዛሬ 15 ዓመት ነው። ጎበዝ ምኝና ተንቀናልና በጉልበት ልጆቻችን ተገደው ትግርኛ ቋንቋ መማር አለባቸው? አይመስለኝም!

ምክንያቱም ትግርኛ ቋንቋ መናቄ ወይም ማቃለሌ ሲይሆን ወቅቱ ዓለም ዓቀፋዊ እንጅ ክፍለ ሀገራዊ ቋንቋ ለእድገት ብቁ ይሆናል ብዬም አላምንም።


ገገጸምድር ካርታ፣




ሕወሓት ሲመሰረት ከማኒፌስቶው የጻፈው ታሪክ ይህ ገጸምድር ካርታ ሲሆን ስሎ ያወጣው ታላቅ ሤራ ከተባለው መጽሐፍ ነው። ከዚህ ገጸምድር ካርታ ተቀንሶ የቀረው አሰብ ሲሆን ከወሎና ከጎንደር የተጠቀሱት ዛሬም ወደ ትግራይ ገብተዋል።

የካቲት 1968 ዓም የወጣው ካርታ፣

በ1968 ዓም ከወጣው ካርታ ላይ ተቀንሶ የቀረው አሰብ ነው። ወያኔ አሰብ አስተዳደር የትግራይ ነው ብሎ ከካርታው ላይ ከሳለው በኋላ ሻዕቢያ እንዳያኮርፍበት ትቶታል። ይህ ገጸምድር ካርታ የተገኘው እነአቶ ገብረ መድኅን አርአያ በ1982 ዓም አዲስ አበባ ገብተው በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን የሰጡት መግለጫ መጽሐፍ ሁኖ ታትሟል። ታላቅ ሤራ በቀድሞው አባላቱ ሲጋለጥ ከተባለው መጽሐፍ ገጽ 34 የተወሰደ።




ይህ ገጸምድር ካርታ የወጣው በሽግግር መንግሥቱ ወቅት ሲሆን
የተጻፈው ራሱ ዋቢ ነው::

ነሐሴ 1983 ዓም የሽግግር መንግሥቱ ካርታ፤

ይህ ካርታ በነሐሴ 1983 ዓም የተለቀቀው ሲሆን ከጎንደር ዙርያ አውራጃ እና ከጭልጋ አውራጃ መተማ ድረስ መምጣቱን ገጸምድር ካርታው ሳያል:: በ1878 ዓም ድርቡሽ ጎንደርን ሲወር ደራሽ በማጣቱ የጎንደር ሕዝብ እጅግ አዝኖ ነበር:: በዚህ ወቅት የጭልጋ ቅማንት እንዲህ ሲሉ ገጥመው ነበር:: ይህ ግጥም በጎንደር አሁን የወል ግጥም ነው::

ወገራ አሳሳፊ ደንቢያ እንጀራ ጣይ
ተበላህ ጎንደሬ አትነሳም ወይ

ብለው ነበር:: ይህን ገጸምድር ካርታ ያየህ የጎንደር ትውልድ ወደውጭ እንዳትገናኝ የተዘጋህ መሆኑን እወቅ:: ምን የጎንደር ትውልድ ብቻ አማራው ጭምር እንጂ?

ጎንደሬ ተበዳይ ተገዳይ
ወሎዬ ተበዳይ ተገዳይ
ሸዌ ተበዳይ ተገዳይ
ጎጃሜ ተበዳይ ተገዳይ
በሩ ተዘጋብህ እንደአለላ ሙዳይ
ምን ነካህ ወገኔ አትነሳም ወይ
መሬትክን ሲቀሙህ ዝም ትላለህ ወይ?
አያስብ አይሰማው አይቆጨው
የአባቶቹን መሬት ሰጠው በጥረጨው
ለሆዱ የኖረው የታሪክ አተላው
ብአዴን የሚሉት የሕዝብ ጠላት ነው?

# ምዕራፍ 4

## ጎንደሬው የመጣውን ሁሉ በጋራ አሳልፎታል

በጎንደር ክፍለ ሀገር ነዋሪ የሆኑ አማሮች ቅማንቶችን በድለዋል የሚለው ለክፍለ ሀገሩ ሰላም የሚያመጣ አይሆንም:: መናናቅ በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ አለ፤ይኖራል:: ቆለኛው ደገኛውን ደገኛው ቆለኛውን መናቁ ይህ በማንኛውም ማህበረሰብ ያለ ለወደፊቱም የሚኖር ነው:: አሜሪካን ያቀኗት እንግሊዞች መሆናቸውን ይታወቃል:: እንግሊዞች አሁን አሜሪካኖችን ይቀልዱባቸዋል::ያም "እንግሊዘኛ ቋንቋ እንግሊዝ አገር ተወለደ፤አሜሪካ ታመመ፤ሕንድ አገር ሞተ"ይላሉ:: በሌላውም አገር የሳውዲ አረብያ አረብኛ ተናጋሪ የግብጹ እንዲሁ፤ሲሆን የመኖች ከሌሎች የተሻሉ መስለው ይታያሉ:: በጎንደር ውስጥ አንዱን ወረዳ፤አንዱ ምን እንደሚለው እናውቃለን:: ይህ በቀልድ መልክ የሚነገረው ራሱ በአማራው እንጂ በቅማንቱ ብቻ አይደለም::

ጣልያን የኢትዮጵያን ሕዝብ ክርስቲያኑን ከእስላሙ እስላሙን ከክርስቲያኑ፤ ትግሬውን ከአማራው፤አማራውን ከኦሮሞው ጋር ለያይቶታል:: ወደ አማራው ሲመጣ ደግሞ ጎንደሬውን ከጎጃሜው ጋር ወሎየውን ከጎንደሬው ጋር፤ሁሉም አማራዎች የሸዋን አማራ እንዲጠሉ ምክር ለግሶአል:: በአሁኑ የኦሮሞ ክፍለ ሀገራት የአንድ አማራ እራስ በ30 ብር ይሸጥ ነበር:: ይህን አይነት ከፋፍለህ ግዛው የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያፋጅ መሆኑን የተረዱ አባ ዶዮ የተባሉ ኦሮሞ አዛውንት አማራውን አድኖ ለመግደል ከእርሳቸው ሊመረቁ የሄዱትን ቅድሚያ ሰርገኛ ጤፍ አምጡልኝ አሉ:: ከዚያም ሰርገኛውን ጤፍ ሲያመጡላቸው በሉ ቀዩንና ነጩን ምረጡልኝ ሲሉ ማን ይምረጠው መልሳቸው አማራና ኦሮሞን ለመለየት እንደዚህ አስቸጋሪ ነው አሉአቸው::

ጣልያን በኛው በጎንደር እንዲሁ እስላም ከክርስቲያን ቆላና ደጋ፤ካህንና አርሶአደር ሲለያይ ከቆየ በኋላ ወደ ቅማንት ነገድ ገባ:: በዚህ ሰዓት የሰላ ቆዳን እንዲያመልኩ፤ሰሳም እንዳትገደል ሲያዝ ተግባራዊ ያደረጉት የጭልጋው ቅማንት ባላባት የደጃዝማች ቢተዋ ልጅ ፊታውራሪ ዓለማየሁ ቢተዋ ናቸው:: ደጃዝማች ቢተዋ ማለት የጭልጋ አውራጃን ወጣቶች አስከትተው ከአጤ ዮሐንስ ጋር ዘምተው ግብጽን የተዋጉ ሲሆን ድርቡሽ በ1878 ዓም ጀምሮ ወደ ጎንደር ሲመጣ ሲደበድቡት የነበሩ ጀግና፤በ1881 ዓም መተማ ዘምተው በድርቡሽ ላይ ጎመጫቸውን የተወጡ ታላቅ አርበኛ በ1888 ዓም አድዋ ዘማች የታወቁ ታዲያ ምን ያደርጋል የሳት ልጅ አመድ እንዲሉ ልጃቸው ፊታውራሪ ዓለማየሁ ቢተዋ ጣልያን ሰሳን እንዲያመልኩ ሲሰጣቸው ጭልጋ ወስደው ከትልቅ እንጨት ላይ ሰቅለው ሕዝቡን ጠርተው ሲጨፍሩ ከርመዋል::

ከኦሮሞ ባላባቶች አባ ጂቤር ለአንድ አማራ እራስ 30 ብር ሲከፍሉ አባ ዶዮ ሰርገኛውን ጤፍ ቀዩንና ነጩን ለዩልኝ እንዳሉ ሁሉ የቅማንት ባላባት

የአድዋው አርበኛ የወቅቱ ቀኛዝማች የኋላው ደጃዝማች ጣሹ እንግዳ ጣልያን የሰጣቸውን ሰሳ ወደ ቤታቸው ሊወስዱ አልፈለጉም:: "ቅድሚያ ሕዝቡን ላማክር"ብለው ሄዱ:: በሳምንቱ "ሕዝቡ አልፈለገም"ብለው መለሱለት:: ወያኔ ኢትዮጵያን ለማፍረስ ትምህርት የወሰደው ከጣልያን በመሆኑ አቶ ነጋ አማራው እንደበደላቸው ለወደፊቱ አብሮ መኖር እንደማይጠቅማቸው መክረዋል:: የጎንደር ተወላጆች የሚያምኑት ግን አንድነታቸውን ነው::

<u>አቶ ሞረሽ የተላቪቡ</u> እስራኤል ነዋሪ በስልክ እንደነገረኝ "እኛ አይከል ከተማ ስንኖር ክርስትና የተቀበለው ቤተ ክርስቲያን ይሄዳል:: ክርስትና ያልተቀበለው ቅማንት ወደ ድግና ይሄዳል:: እኛም ይሁዶች እንዲሁ ስንሆን የአይከል ልጆች ሁላችን በአንድነት ኑረናል" ሲሉ ነግረውኛል::

እኔ እንደሚገባኝ ቅማንትና አማራ ሌላውም ነገድ ስማችን እንኳ አንድ ነው:: እንኳን ከቅማንት አካባቢ ካሉት ወረዳዎች ይቅርና ለእኔ ከደብደረ ታቦር ለመጣሁት ጎንደሬ ከቅማንት ልጆች ጋር ተዛምደናል:: ሱዳን በስደቱ አብረን ከአንድ ቤት ኑረናል:: ሌሎችም እንዲሁ ነበሩ:: ይህን የምለው ጹሁፌን ለማሳመር አይደለም:: ለዚህም ነው ጠቃሚ ሰነድ ከቅማንት ባልንጀሮቼ የማገኘው:: አሁንም አበልጆቼ በኮለምበስና በመኒሶታ አሉ:: ባልንጀሮቼ በዋሽንግተን ዲሲና በአትላንታ፤በሎስ አንጀለስና በሲያትል በሌሎች ከተማዎች አውስትራልያ አሉ:: ከፋኝ ኢትዮጵያ የጀግኖች ግንባር ድርጅት አባላት በብዛት የቅማንት ልጆች ነበሩ:: የሌሎችን ትቼ ከኔ ጋር የግል ግንኙነት ከሚያደርጉት መካከል አቶ ደሴ ታደሰን ልጥቀስ:: ከእርሱ ጋር አብረን ብዙ ደክመናል:: በኋላ በስነ ጹሁፍ መሳተፍ እንዳለብን ወሰንን:: አቶ ደሴ በተለያዩ መጽሔቶች ጠቃሚ ጹሁፎችን ይጽፉ ነበር:: ኋላም እኔ ጉግሣ መጽሔት ማዘጋጀት ስጀምር አንዱ አምደኛ አቶ ደሴ ነበር:: ኢትዮጵያን በሚመለከት ሲዲ አቅርቦአል:: መጽሐፍም ጽፎ አሳትሟል::

ደሴ ታደሰ <u>የእናት ውለታዋ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 125
"ሹልክልክ እያለ ሲያወናብድ ያዝኩት
ተው አይሆንም ብዬ ወደኔ መለስኩት" ሲሉ ጽፈዋል::

ከዛሬ 12 ዓመት በፊት የምኖረው ሎስ አንጀለስ ነበር:: ጥምቀት በዓል በድግንል ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በ1990 ዓም ሲጀመር ከዚያው ስለነበርኩኝ ደስ ይለኛል:: ሲያትል ከመጣሁ ወዲህ ጥምቀት ሎስ አንጀለስ እሄዳለሁ:: በ2005 ዓም ሕጄ ሳለ አንድ የቅማንት ልጅ ወንድሜ ጋር አብረን አመሸንና ማታ ሆቴል ሲያደርሰኝ ትልቅ ጥቅል ሰጠኝ:: ምንድነው ስለው" አደራ!እኔ ይህን መጽሐፍ ሳላሳትመው ብሞት እንድታሳትመው" ብሎ ሰጠኝ:: ከዚህ መጽሐፍ አለፍ አለፍ እያልኩኝ ጥቅስ ልውሰድ::

<u>ደመ ነፍስ ትውልድ እና የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍጻሜ ዋዜማ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 103 "ጎረቤቶቼ እነማን ነበሩ?

በሰላም የኖሩ ባንድ እየጋገሩ
የኔታ ማን ነበሩ?
የሰፈሩን ሕፃን ፊደል ያስቆጠሩ
በደህናው ቀን ባንድነት የኖሩ
ሲወለድ እልል ያሉ
ሲሞት ያለቀሱ
ከሰርጉ ከክርስትናው አብረው የተደሰቱ
አብረው ያዘኑ ከተስካሩ ከፍታቱ
በዚያ በደህናው ቀን ጎሳ ያልቆጠሩ
አሉ ወይ እስካሁን ባንድ እየጋገሩ?

ገጽ 289 የወንድሙን ሥጋ ዘልዝሎ እየበላ
አገሩን የሸጠ የጠላት ደላላ
እናቱን ደፍሮ ማሕፀኗን ያደማ
አእምሮ የለውም ቢነግሩት አይሰማ
የብረት አተላ ነው ቢገድሉት አይደማ
እንዳትታለሉ ይሞታል ብላችሁ
ቀደም ነው የሞተ ምንም ቢገድላችሁ
ምንም ባትቆሙ አፈር ባታላለብሱ
ትልም ባይበላችሁ ባትበሰብሱ
እናንተም ሙት ናችሁ አትሻሉም ከእርሱ
የብረት አተላ ከእራስ ላይ ወጥቶ
ሁሉን በላው በቋንቋ በጎሳ በልቶ በልቶ"::

በገጽ 374 አገርን በማፍረስ ጡንቻችን ዳብሮ
አእምሮአችን በደም ሰክሮ
ማይረዳ ሆነ ጥፋታችን አንብቦ መርምሮ
ባለበት ይረግጣል በደም ተለውሶ
መንፈሳችን ሞቶ ውስጣችን በስብሶ
ማንረዳ ሆንን የአገርን መሞት
የሰቆቃን ዘመን የሕዝብን ዕልቂት"
በገጽ 438 በአፍሪካ መሬት ሕይወት ረከሰ
ደሙ ተንጣለለ እንደ ውኃ ፈሰሰ
ምሁር የተባለ ሕዝብ እየነከሰ
ሬሳው ይታያል በደም ተዘፍቆ
የትም ተዝረክርኮ እንደ ግንድ ወድቆ::

በገጽ 561"አይ እናት ሀገሬ ስንቱ አረረ ነደደ
ስንቱ ለሕይወትሽ እንደ ማውዳ ተማገደ
ስንቱስ ዕጣ ነፍሱን ተሰደደ
እግዚአብሔር የባረከው አንችን የሚወርስ
አርሶ የሚበላ በወንዞችሽ ተፋሰስ

ልብ ይስጠው የተራቆተውን ምድርሽን በደን እንዲያለብስ
በደሙ የማያጥብሽ፤የማያቆሽሽ
እግዚአብሔር አምላክ ደግ ሕዝብ ይስጥሽ"::

በገጽ 648 ከምድረ ገጽ ፍቀው ሊያጠፉን
ምለው ተገዝተው ለተነሱብን
ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምረው ለሚወጉን
በመርዝ ለሚያፍኑን፤ለነፍስ ገዳዮቻችን
ለሕይወታችን አድራጊ ፈጣሪ አደረግናቸው
በሕይወታችን ላይ ፈላጭ ቆራጭ
አዛዥ ናዛዥ፤ገዳይ ገናዥ አደረግናቸው
በድፊት እንደተያዘች ጠጣ
የዓይን ርጎራጌ የምትለምን ልትወጣ
ነፍሳችን በመዳፋቸው ውስጥ ናት
እጃቸው ከእልቅታችን ላይ ናት"::

በገጽ 703 "በሕሌና ጉዞ ወደ ኋላ ቃትቱ
ኢትዮጵያን ዙርያ ተመልከቱ
በገጽ 706 የወደቀችውን እናታችሁን አንሱ
የክልሉን ግንብ ባንድነት ንዳችሁ አፍርሱ
አምጡልኝ ክራሬን የኔዋን ጓደኛ
እያንጎራጎርኩኝ አብሬው ልተኛ
ከመቅደላ ሁኜ ደወሉን ልደውል
ጎበዝም ይነሣ ጠበንጃ ይወልውል
ኢትዮጵያ እንዳትጠፋ ቀኑም እንዳይጨልም"::

በገጽ 753 የደም ዕንባ እያለቀሱ ምርኮኞች እንደ በግ ተነዱ
ከገቢያ ሊሸጡ ወደ ሱዳን ምድር ወረዱ
ሰለሙ በሰይፍ እየተገደዱ
በሰልፍ ቁመው በየተራ እንደበግ ታረዱ
ከተሞች መንደሮች አብያተ ክርስቲያናት እንደ ደመራ በእሳት ነደዱ
በገጽ 762 ካሣ ሲወድቅ ኢትዮጵያ ሰማች
እሪ ብላ አልቅሳ ልጆችን ወለደች
በካሣ ደም አጥባ ወልዳ እያሳደገች
ጠላት እያጠቃች እስከዛሬ ቆየች
በክብር በጸጋ እኛን አሳደገች
በገጽ 763 "የኢትዮጵያ ድምጽ ይጣራል
ከመቃብር አውጡኝ ይላል
ልብሳችን በኢትዮጵያ ደም ቀልሟል
ምግባችንም በደሟ ተለውሷል
ደም በውኃ ታጥቦ አይጠራም
ወደድነም ጠላነም የኢትዮጵያ ደም ነን

በደም በአጥንታችን ኢትዮጵያዊ ነን"ሲሉ ጽፈዋል።

በጎንደር ላይ ችግር ሲመጣ ቅማንቱ ከሌላው ነገድ ጋር አብሮ ተደብድቧል። ለምሳሌ የንግሥት ዩዲትና የአጤ አህመድ ግራኝ፤የኦሮሞ ጦርነትና ዘመነ መሳፍንቱ እንዲሁም ድርቡሽ በ1878-1880 ዓም በተለያየ ግዜ ጎንደር ሲወር ተደብድቧል። በ1888 ዓም አድዋ ሲዘመት የቅማንት አባቶቻችን ዘምተዋል። ከላይ የተጠቀሱት ሁለት አባቶች ለናሙና ነው። ደጃዝማች ጣሹ የአድዋ አርበኛ ከአጤ ምኒልክ የተሸለሙ ታዋቂ ኢትዮጵያዊ ቅማንት ጎንደሬ ናቸው። ራስ ጉግሳ ወሌ "የጎንደርን ጥቅም ለተፈሪ አልሰጥም"ብለው በ1922 ዓም አንችም ሲዘምቱ ደጃዝማች ጣሹ የቅማንት ልጆችን አስከትለው አንችም የዘመቱ ናቸው። ደጃዝማች አያሌው ብሩ ለሥልጣን ብለው ለንጉሥ ተፈሪ አሽከር ሲሆኑ ደጃዝማች ጣሹ አንችም ዘመቱ። ኋላም በ1928 ዓም ጣልያንም ኢትዮጵያ ሲገባ የቅማን አባቶቻችን እንደማንኛውም ጎንደሬ ዱር ገብተው ጠላትን ወግተዋል። ጣልያን የሰጣቸውን መደለያ የተቀበሉትን ባንዶች ወግተዋል።።

ቅሜ ጨጎጎቱ፤ጨጎጎቱ
ዝቅ ሲል ከጉልበቱ ከፍ ሲል ከአንገቱ
መልሶ ሰደደው ወደመጣበቱ
በማለት ይሸልሉ ነበር። ይህን ሽለላቸውን አቶ ነጋ ቀይረው አማራውና ቅማንቱ ተጣልተው ቅማንት አጥቅቶ አማራዎች ዘራጢዎች ተጠቅተው ሲመለሱ የተገጠመ ግጥም ነው ብለው በገጽ 113 ጽፈውታል። ከእውነት የራቀ ነው።

የቅማንት ልጆች ጣልያን ከኢትዮጵያ ከተባረረ ወዲህ እንደማንኛውም ጎንደሬ ሁሉ አገር ለማቅናት ደፋ ቀና ያሉ ናቸው። ሊቆች/ዶክተሮች በጎንደር የሕክምና ትምህርት ቤት ኢትዮጵያውያንን ያስተማሩ ምሁራን ብዙ ናቸው። የአጤ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ለመጣል በተደረገው ትግል የቅማንት ልጆች ተማሪው በተማሪነቱ ወታደሩ በወታደርነቱ ተሳትፈዋል። ደርግ 108 አባላት ነበሩት። ከነዚህም መካከል የመቶ ዓለቃ ተስፋዬ ተክሌ ቅማንት ናቸው። ሱማሌ ኢትዮጵያን ስትወር እንደማንኛውም ጎንደሬ የቅማንት ልጆች ደማቸው አጋዴ ፈሷል። የተማሩት ለማስተማር ገጠር ለገጠር ተንከራተዋል። በኢሕአፓ ድርጅት አሁን ድረስ በብዛት አሉ።

አንዱን ጠቅሶ አንዷን መተው እንዳይሆን። ባይሆን አሜሪካን መጥተው ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት አርቆ አሳቢው አቶ ደረጀ ብርሌን፤ብቻ ጠቅሸ ልለፍ። ሌላው ደርግ አገር ለማሳደግ ጥረት በሚያደርግበት ወቅት የቅማንት ልጆች በካድሬነት አገር ለአገር የተንከራተቱ ብዙ ናቸው። ይህን ያደረጉት ለመላ ኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ብለው እንጅ እንደዛሬዎቹ ጥቂት ግለሰቦች ለቅማንት ብቻ ብለው አልታገሉም።

ኢ.ዲ.ዩ. የተባለው ድርጅት በጎንደር ሲንቀሳቀስ የቅማንት ልጆች ብዛታቸውን ዘርዝሬ አልጨርሰውም:: በሻለቃ አጣናው ዋሴ ሠራዊት ውስጥ በብዛት ነበሩ:: የጭልጋ አርበኛ ከነበሩት መካከል ፊታውራሪ አየለ አባጓዴና ሌሎችን መጥቀስ ይቻላል:: ወያኔ ያስፈሩኛል የሚላቸውን ከኢትዮጵያ አልፎ ሱዳን ገብቶ አፍኖ ሲወስድ ብዙ የቅማንት ልጆች ተወስደው ተገለዋል:: የ80 ዓመቱ አዛውንት ሻለቃ አጣነው ዋሴ ታፍነው ሲገደሉ ከነዚህ መካከል የቅማንት ልጆችም ነበሩ:: ከላይ የጠቀስኩት ከፋኝ በወልቃይትና በአርማጭሆ ልጆች ይመስረት እንጂ የቅማንት ልጆች ተሳትፎ ነበረበት:: ወያኔ በምህረት እንዲገቡ ሲያደርግ በግማሽ ሲገባ ያልገባው አርበኞች ግንባር ተብሎ ትግሉን መሠረተ:: እነሆ አሁን የግንቦት ሰባት አስኳል የሆነው ይህ የጎንደር ሕዝብ ሲሆን የቅማንት በብዛት አሉበት::

ቅንጅት በጎንደር እንዲመረጥ ጥረት ሲያደርጉ የነበሩት ሠላማዊ ታጋዮች የጎንደር ልጆች መካከል የቅማንት ልጆች በብዛት ነበሩ:: በጎንደር ላይ የመጣውን ችግር ቅማንቶቹ እንደ ጎንደሬው አብረው ተወጥተውታል:: አንዱ አንዲቱን አግብቷዋል:: አንዲቱ አንዱን አግብታለች:: እንኳን ሰዎች ከብቶቻቸው አብረው ይውላሉ:: ገበያና ማንኛውንም ማህበራዊ ጉዳዮች አብረው ፈጽመዋል ይህ አኩሪ ታሪካችን ነው:: ይህን አንድነታችን ወያኔ ሊለያየን ሲሞክር አንዳንዶች ሲከተሉት ትክክል አይደለም ብሎ መነሳት አግባብ ነው:: ለምሳሌ እኔ ደጋ ልወለድ እንጂ ያደኩት በቅማንትና በአማራው ደንበር አርማጭሆ ነው:: ከ1966-1973 ዓም ነበርኩ:: አስታውሳለሁ ሦስት ሰዎች እግራቸውን ያጠብኳቸው ከዚህ አሜሪካን አሉ::

በገንበራ በኩል እዳይት ማጠቤያ ውባ አሞኝ ብዙ ሳምንታት ተቀምጫለሁ:: ይህ አካባቢ ሙሉ በሙሉ የቅማንት ነገድ ሲሆን አንድም ሰው አማራ ነህ ብሎ ያስቀየመኝ አልነበረም:: በ1969 ዓም ትክል ድንጋይ ከኢዲዩ ጋር ከከተማው ገብቼ ነበር:: ያየሁት አንድም ነገር የለም::

አይቆረጠምም ደረቁ ባቄላ
ጎንደር አበቄለሽ ፋርጣ የኔ ገላ

ብለው የሚያዜሙት የቅማንት ሕዝብ እንኳን ከአካባቢው ጋር ቀርቶ ከደብረታቦሬዎች ጋር ሕብረት እንደነበራቸው ነው:: አሁንም አላቸው:: ይህን ችግር አለ ብሎ ያመጣው ወያኔ እንጂ የቅማንት ልጆች አይደሉም:: ወያኔ ለራሱ ሊጠቀም ፈልጎ የፈጸመው ተግባር ነው:: ሽልታው ለወያኔና ለአንዳንድ ልጆች እንጂ የቅማንት ልጆች ግን ወያኔን አሁን በሠሮቂ ላይ ወግተዋል:: መጀመርያ የወያኔን ምንሻ ገርፈዋል:: በመቀጠልም ብሔራዊ ሠራዊቱ ታጥቆ ሲመጣባቸው ተዋግተዋል:: ታንክ ማረኩ፤ ግን “በጄት ከማጥፋታችን በፊት ታንኩን መልሱ”ተብለው በሽምግልና መለሱ ይህ የሆነው አማራ ቅማንት ሳይሉ ደንበራችን ተከዜ ነው:: ወያኔ መሬታችን ሊወስድብን አይገባም ብለው በሕብረት በመነሳት ነው::

# ምዕራፍ 5

## ወያኔ ቅማንት የለም ብሎ ካደ?

ወያኔ በ1983 ዓም የቅማንት ድርጅት እንዲመሰረት ለፍቶ አልተሳካለትም:: ነገር ግን 1984 ዓም በማህበር ስም እንዲደራጁ ተሞክሮ አልተሳካም:: ይህ የሆነው ደግሞ የቅማንት ታላላቅ አዛውንቶች የወያኔን ሀሳብ ቀድመው ስለተረዱ ነው:: ወያኔ ጎንደር ውስጥ በቅማንት ሕዝብ ላይ ብቻ ሳይሆን ሌሎችን ነገዶች እንዲሁ ሊቀሰቅስ ሞክሮ ነበር:: ለምሳሌ አሞራ ገደል ላይ አውራምባ የሚባል ተራራ አለ:: ከዚያ አካባቢ የሚኖሩ ወንዱ ወጥ ይሰራል፤ ሴቷ በሬ ጠምዳ ታርሳለች:: እነሱን ነገድ ሁኑ ብሎ ቅስቀሳ አድርጎ ነበር:: በዚህ በተራራው ስም አውራባ የሚባል ጋዜጣ መውጣት ጀምሮ ነበር:: የዚህ ጋዜጣ ባለቤት ዋዲት ከበደ የትግራይ ልጅ ነበር:: ዋዲት ከበደ ፊያሜታ ሳይሆን ዳዊት ከበደ አውራምባ:: እርሱም በዚህ ጋዜጣ ስም ታሰርኩ ብሎ ተሸልሞአል:: ስደተኛ ነኝ ብሎም ከወጣ በኋላ ተመልሶ ከአድዋው ቡድን ገብቷል::
ወያኔ የአውራምባ አካባቢ ነዋሪዎች ብሔረሰብ ናችሁ ቢባሉ የቀድሞው አባ ዙንባ የአሁኑ ዶ/ር ዙምባ አልተቀበሉም አሉ:: ጭቅጨቃው ሲበዛባቸው ቤጨንቃቸው "አውራምባ ጎንደር"ብለው ዘፈኑ:: እነዚህን ከወሎ መጥተው የሰፈሩትን ሰዎች ነገድ ለማስመሰል ለፍቶ አልተሳካለትም:: ባለፈው በነሀሴ 2006 ዓም አዲስ አበባ አምጥተው "የአውራምባ ማህበረሰብ 42ኛ የምስረታ በአሉን አከበረ" ተብሎ ዳንኪራ ሲመታ ሰንብቷል:: ወይጦጭንም ለማደራጀት ተሞክሮ አልተሳካም:: አገዎችንም እንዲሁ ተጥሮ ከሽፏል:: የሚገርመው ጭሀራ ሕደው ከያንያን አዝማሪዎችን በነገድ ለማደራጀት ሞክረው ነበር:: ጋፋት ከጠፋ ከርሟል:: የጋፋትን ነገድ ፈልጎ ለማግኘት የተደረገው ሙከራ አልተሳካም:: ጋፋት ቋንቋው የጠፋፋው ቀደም ብሎ ሲሆን የመጨረሻዎቹ ቋንቋውን ይናገሩበት ከነበረው ቦታ ላይ አጤ ቴዎድሮስ አፈሩን አስቀልጠው መድፍ የሰሩበት ቦታ ነው:: ጋፋቶቹ ያለ ምንም ተጽእኖ ቋንቋቸው ጠፍቶ አማርኛ ተናጋሪ ሁነዋል:: ወያኔ ጎንደር ውስጥ ያለውን ሕዝብ ለማበጣበጥ ጥሮአል::

ኮሎኔል አስናቀ እንግዳ ሸክም የማይከብደው ሕዝብ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 271 "ወያኔ ባሻው መንገድ እየተጓዘ የጎንደርን ሕዝብ በስልታዊ ዘዴ ዘር ከማጥፋት ባልተለየ ሁኔታ እያጠፋው ነው"ሲሉ ጽፈዋል:: ይህን አድርጎ ያልረካ በመሆኑ አሁንም መልሶ ቅማንትን ከሌላው የጎንደር ክፍለ ሀገር ነገድ ጋር ለማጋጨት አሰበ:: ታሪኩ እንዲህ ነው!ቀደም ብሎ የመለመላቸው የማያዋጡት ሲሆን አዲስ ፈሊጥ ፈብርኮ አገኘ:: ያም ከፌዴሬሽን ምክር ቤት የቅማንትን ነገድ የለም ብሎ መዘረዝ ሆነ:: ይህ ተግባር እንኳን ቅማንቱን ሌላውን ጎንደሬም አስቆጥቷል:: ምክንያቱም ቅማንት ነገድ መሆኑን ሁሉም ጎንደሬ ያውቃል! ይህ የተደገረው ሆን ተብሎ ነው::

ሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 61 "የፌዴሬሽን ምክር ቤት በፌደራሉ መንግሥት አባል ክልሎች የሚገኙት ብሔሮች ብሔረሰቦች፤ሕዝቦች የሚልኩዋቸው አባላት የሚወክሉትን ምክር ቤት ነው:: እያንዳንዱ ብሔር፤ብሔረሰብ፤ሕዝብ ቢያንስ አንድ ተወካይ ይኖረዋል፤በተጨማሪም የብሔር ወይም ብሔረሰቡ አንድ ሚሊዮን ሕዝብ አንድ ተጨማሪ ወኪል ይኖረዋል:: የፌደሬረሽን ምክር ቤት አባላት በክልል ምክር ቤቶች ይመረጣሉ፤የክልል ምክር ቤቶች በራሳቸው ወይም በቀጥታ በሕዝብ እንዲመረጡ በማድረግ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባል እንዲወከል ያደርጋል"ይላል:: ከዚህ በታች የሚነበበው ጎንደር የሚኖሩ ባልንጀሮቼ የላኩልኝ ማስታወሻ ይሆናል::

በቅማንት ብሔረሰብ ስም ከማህበር ወደ አስተዳደር የተለወጠበት ምክንያት?

4/20/2007 ዓም

ወያኔ መላ ጎንደርን ከተቆጣጠረ ጀምሮ የቅማንትን ብሔረሰብ እንዲደራጅ ጥረቱ ቀጠለ:: ቀደም ሲል የመለመለው በአባቱ ትግራይ እናቱ ቅማንት የሆነ ጎንደር ያደገ፤ሁመራ አስተማሪ እያለ ወያኔ የያዘው ግለሰብ ሁለት ሌሎች ቅማንቶችን ሰኔ 1983 ዓም መለመለ:: በ1983 ዓም የቅማንት ድርጅት እንዲመሰርቱ ጥረት ሲደረግ አባቶች በመስማታቸው ሦስቱን ግለሰቦች በግል "በንብ ግዜ ዝንብ ይናከሳል፤አሁን የኢትዮጵያ ሁኔታ አስቸጋሪ በሆነበት ዘመን እኛ በቅማንት ስም መደራጀት አስፈላጊ ነው ብለን አናምንምና እርፋችሁ ተቀመጡ ከወገኖቻችን ጋር አትለያዩን" ብለው በ1984 ዓም ተጀምሮ የነበረው የቅማንት ልማት ማህበርም አስቆሙ:: በዚህ ምክንያት 1ኛው ግለሰብ ወደ ውጭ አገር በኢምባሲ ውስጥ እንዲሰራ ተደረገ::2ኛው ግለሰብ ወያኔ ገንዘብ መድቦለት መጽሐፍ ጽፎአል:: አንዱም ችግር ፈጣሪው ይህ መጽሐፍ ነው:: 3ኛው ግለሰብ የአባቶችን ምክር ሰምቶ ጠብ እርግፍ አድርጎ ትቶት ሳለ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል:: ይህ በመሆኑ የቅማንት ድርጅት ባለመመስረቱ ወያኔ ከልቡ አዝኗል::"

"ወያኔ የጎንደር ሕዝብ ሰላም አይፈልግምና ከደርግ ግዜ ጀምሮ ቅማንት በብሔር ተመዝግቦ የታወቀ መሆኑ ተረስቶ ወያኔ የቅማንት ብሔረሰብ የለም በማለቱ ምክንያት ቅማንት አለ እንጂ ለምን የለም በሚለው የመብት ጥያቄ ሁኖ በብዙዎች ተነስቷል:: እኛ እንደተረዳነው የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን ሊሰጥ በማሰቡ አንዱን ብሔረሰብ ካንዱ ብሔረሰብ ጋር ለማጋጨት ያሰበበት ምክንያት ብቻ ሳይሆን ቆላውን በርሃ ለራሱ ሊጠቀም በመፈለጉ ነው:: ይህን እቅድ የተነደፈው በአቶ ጌታቸው አሰፋ፤ ጽፈት ቤት የደህንነት አላፊው መሆኑን ደርሰንበታል:: ምክንያቱም ቅማንት የለም ሲባል ሕዝቡ ይነሳል ተብሎ ተጠንቶ የተፈጸመ መሆኑን ከውስጥ አወቅ መረጃ ሰምተናል:: ሌላው የሚያስፈራው አሁን ጎንደር ከተማ ብቻ ሳይሆን በየዞኑ የትግራይ ነዋሪው ምሳ ለምሳ ሁኗል:: ይህን በሕዝብ ላይ የተጋረጠውን ችግር ለኢትዮጵያውያን እንድታደርሳት አደራ ጥለንብሃል!ከሚመጣው ፈተና አምላክ ጎንደርን ያድነን" ባልንጀሮችህ ነን ጎንደር"የሚል ደብዳቤ ጻፉልኝ::

ከላይ እንዳልኩት የፌዴሬሽን ምክር ቤት የነገዶች ስም ዝርዝር የተሰጠው ሲሆን አቶ ካሳ ተክለ ማርያም ቅማንት የለም አሉ:: እርሳቸው የራያ ተወላጅ

ሲሆኑ ማንነታቸውን ያጡ ወገኖቻቸውን በወያኔ እንዲጨፈጨፉ ያደረጉ ለቅማንት ነገድ ሊሆኑ አይችሉም:: ምክንያቱም ራያ ከወሎ ከተከፈለው ወረዳ ወደ ትግራይ የተከለሉ ናቸው:: የወሎ ራያ በወያኔ ሲያልቅ ዝምታን የመረጡ መሆናቸውን ማንም ያውቀዋል:: ራሳቸውን ትግራይ ያደረጉ ናቸው:: "አንቀጽ 39ኝ ተቀብላችሁ የብሔር ውክልና ልታገኙ ትችላላችሁ ይህን ካላደረጋችሁ ቅማንት አለ ብለን አንቀበልም"ተብለዋል:: ይህን የሰሙት ናቸው አንዳንዶች ለሥልጣን ጓጉተው የቅማንት አስተዳደር እንዲመሰረት ጥረት ማድረግ የጀመሩት:: ያም ሆነ ይህ በእኔ እምነት ቅማንት ነገድ አለ::

አማረ አፈለ ብሻው <u>ደም አይፍሰስ በቃ የሕወሓት ማነፌስቶ ያብቃ</u> ባልኩት መጽሐፍ ገጽ 60 "የቅማንት ቋንቋ ለማስፋፋት ብሎ መንቀሳሰቅ ተጀምሯል:: የቅማንት ቋንቋ ለልጆቻቸው ማስተማሩን አልጠላም፤ግን ዛሬ የቅማንት ዞን ተፈቅዶለት አስተዳደሩ ራሱን ይቻል የሚል መግለጫ ወጥቶ ነበር"ስል ገልጬ ነበር:: ችግሩ ያለው የመሬት ክለላ ሲመጣ ነው:: አርቃችሁ አስቡ:: የቅማንት ዞን የሚለው የራስ አስተዳደር ሲመሰረት የቅማንት ልጆች በሌላው ክፍለ ሀገር ገብተው የመስራት ችግር ሊገጥማቸው ይችላል:: ምክንያቱም ከላይ እንዳልኩት ከጎንደር የመጣው ደብዳቤም እንዳተተው የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን ሊሰጥ ሲያስብ ቅማንት ከሌላው ነገድ ጋር አንድ ሁነው እንዳይነሱ በመፈለጉ ነው::

በቅማንት <u>ብሔረሰብ የማንነትና የራስ አስተዳደር ጥያቄን</u> አስመልክቶ በሰሞኑ የተደረጉ የሕዝብ እንቅስቃሴዎች ከተባለው መጣጥፍ ገጽ 5 "በአጠቃላይ ከ287.500 የሚያንስ ተማሪዎች ያቋርጣሉ ተብሎ ይጠበቃል"ይላል:: ይህ የተጠቀሰው ተማሪ እነሱ በጠቀሱት በ8 ወረዳዎች ሰርተው ነው የሚበሉት? ይህን ነው ማሰብ ያለባቸው:: ሌላው ከዚህ መጣጥፍ ገጽ 6 የወጣው ገጸምድር ካርታ ሲከለል የሚመጣው ችግር ማን እንደሚወጣው አምላክ ይወቀው:: ምክንያቱም የቅማንት ሕዝብ የሚኖርበት አካባቢ የሚለው አስፈሪ ነው:: ይህ እንደሚመጣ ፈርቼ የካቲት 2005 ዓም ባሳተምኩት መጽሐፍ እንዲህ ብዬ ነበር:: ደም አይፍሰስ በቃ የሕወሓት ማነፌስቶ ያብቃ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 60 "የቅማንት ዞን ይከለል ሲባል ብዙ ችግር የሚፈጥር ይመስለኛል:: ምክንያቱም ከዚህ በፊት በጎጃምና በሸዋ በወሎ ዞን ለመከፋል ሲሉ በይገባኛል ጭቅጭቅ ብዙ ሕዝብ አልቋል:: ይህ ችግር በጎንደር ላይ እንዲነሳ ጥረት እየተደረገ ነው:: መስከረምና ጥቅምት 2005 ዓም ላይ ከጎንደር ወደ አሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ መጥተው ይህን ጥያቄ የቅማንት ሕዝብ ማስተጋባት እንዳለበት ቅስቀሳ ሲያደርጉ ሰንብተው ሕደዋል:: ከዚያ በፊት በኢምባሲው ውስጥ የነበሩት ግለሰብ የቤት ሥራ ሰርተዋል:: ይህ ለወደፊቱ የጎንደርን ሕዝብ ግጭት የሚያስነሳ የወያኔ ሲራ ከማር ውስጥ የተጠቀለለ መርዝ መሆኑን ሁሉም እንዲያውቀው እፈልጋለሁ"ስል ጽፌ ነበር:: የፈሩት ይደርሳል እንዲሉ ችግሩ አይኑን አፍጥጦ ጥርሱን አግጥጦ መጥቷል:: ወያኔ የጎንደርን መሬት ለሱዳን ሰጥቷል:: ቆለኛው ሕዝብ ለምን ሲል በጀርባ የነሱ የሆኑትን የቅማንት ልጆች ለማሰለፍ ነው ዓላማቸው::

# ምዕራፍ 6


## የቅማንት ዞን ሲከለል የሚፈጠረው ችግር

ሉቃስ 8፤21"ጻድቃን መስለው በቃሉ የሚያጠምዱትን ሽማቂዎች ሰደዱበት" እንዳለው ቅዱስ መጽሐፍ:: ጎንደር ክፍለ ሀገር የተወለዳችሁና የገጸምድር የጅግራፊ ተማሪ የሆናችሁ አስቡት:: ይህን በቅማንት ሕዝብ ስም የወጣው ካርታ ሕዝብን የሚያፋጅ ነው:: ለዚህም በቅማንት ብሔረሰብ የማንነትና የራስ አስተዳደር ጥያቄን አስመልክቶ በሰሞኑ የተደረጉ የሕዝብ እንቅስቃሴዎች በአጭሩ የሚከተለውን ይመልከቱ የተባለው መጣጥፍ በገጽ 6 ያሰፈረው ገጸምድር ካርታ ይህ ከዚህ በታች የሚታየው ነው:: ይህ ገጸምድር ካርታ ጠገዴን፤አዳርቃይን፤በየዳን፤ሳንጃን፤ደንቢያን፤መተማን ያጠቃልላል:: ከአቶ ነጋ ጌጤ መጽሐፍ ገጽ 106 ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው:: በጥቅምት 32 ቀን 2007 ዓም ከወጣው ብዙም ልዩነት የለውም:: ለዚህም ነው የቅማንት ዞን ሲከለል ችግር ይፈጠራል የምለው::

## The Qimant Land: Qimant Populated Woredas




**Tth Qimant Land Qimant Populated Woredas**




/// በአሁኑ ወቅት
የቅማንት ሕዝብ
አሰፋፈር

106

ከአቶ ነጋ መጽሐፍ ገጽ የተወሰደ፤

አንድ የዓይከል ከተማ የቅማት ልጅ ንግድ ያለው የአማራዎች እየተመረጠ ጉዳት ሲደርስበት በማየታቸው ሲከላከሉ ታይተዋል። ወያኔ ያሰለፋቸው ሰልፈኞች የእርሳቸውን ንግድ እንደ አማራዎች አጠቁ። ባሳለፍለው በወያኔ ታሪክ ሰላማዊ ሰልፍ ወጥቶ ሳይታሰር፤ሳይደበደብ፤ሳይገደል በሰላም ቤቱ የገባ የለም። አይከል ከተማ ሆነ ጎንደረ ከተማ ላይ ይህ ሲፈጸም ያልታየው ሰላማዊ

ሰልፈኞችን ያደራጃቸው ወያኔ በመሆኑ ነው። በእርግጥ በሰልፉ አቋሙን የነቀፉትን ማሰሩ ግልጽ ነው።

ትንቢተ ኤርመያስ 49፤24"ደማስቆ ደከመች፤ትሸሽም ዘንድ ዘወር አለች፤ እንቅጥቅጥም ያዛት፤እንደ ወላድም ሴት ጣርና ምጥ ያዛት"ይላል። በዚህ አያያዝ ከሆነ ጎንደር ላይ የሚነሳው ችግር በቀላሉ የሚፈታ አይሆንም። የሚገርመው በውጭ አገር ያሉ የተማሩ ቀደም ሲል በተማሪው ማህበር እና ኋላም ኢሕአፓ ሁነው ባልንጀሮቻቸውን በአሲንባና በበለሳ በሌላውም ቦታ ከደርግ ጋር በተደረገ ጦርነት ቀብረው የተሰደዱ የዚህ ቡድን አቀንቃኝ መሆናቸው ነው። ወያኔ በ1993 ዓም በክፍፍሉ ምክንያት በውጭ የሚኖሩ የትግራይ ልጆች የርዕሰ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ አቋም አልደገፍ ብለው ነበር። በዚህ ምክንያት በጥቅም ሊይዝ ያደረገውን ጥረት አቶ ገብሩ፤እንዲህ ሲሉ ይገልጹታል።

ገብሩ አስራት ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 404 "ሕወሓት በአገር ውስጥ እንዳደረገው ሁሉ በውጭ የሚኖሩትን የትግራይ ተወላጆች በጥቅም እየደለለና እያስፈራራ ሊቆጣጠራቸው ሞክሯል። በአንድ በኩል በውጭ የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆችን ድጋፍ ለማሰባሰብ ሰፊ የመሬት ዕደላ አካሂዶ እንዲያውም መጀመሪያ ላይ መሬት በነጻ ይሰጣቸው ነበር። ብዙዎቹም ያገኙትን መሬት በከፍተኛ ዋጋ ቸብችበውታል። ይህ አላዋጣ ሲለው ደግሞ ሕወሓት በዝቅተኛ የሊዝ ዋጋ መሬት እንዲሰጣቸው ቃል እየገባላቸው ዛሬም የፖለቲካ ድጋፋቸውን ለመግዛት እየሞከረ ይገኛል።"

"በመሬትና በሌላ ጥቅማ ጥቅም ሊደለሉ ያልቻሉትን ደግሞ እያስፈራራ እያንዳንዶቹን አገር ቤት ያሉትን ቤተሰቦቻቸውን እንደሚያጠቋቸው ዝተውባቸዋል። በተጨባጭም ቤተሰቦቻቸውን እያገኙ ልጃችሁ አደብ ይግዛ ብለው ያስፈራሯቸው አሉ። ከዚህ ሌላ የሻዕቢያ ያህል ባይሆንም እያንዳንዱ በውጭ የሚኖር ኢትዮጵያዊ አምስት መቶ ዶላር እየከፈለ ብጫ መታወቂያ እንዲያወጣ መመሪያ አውጥተዋል። መታወቂያው ባይከፋም ይህን መታወቂያ ያልያዘ በውጭ አገር የሚኖር ኢትዮጵያዊ በጥርጣሬ እንደሚታይና ጥቅማ ጥቅሞችን እንደማያገኝ ታውጇል"ሲሉ ጽፈዋል።

እናንተም ወያኔ በዚህ አጥምዷችሁ ይሆን? ማን ያውቃል ወያኔኮ እጁ ረጅም ነው። ወያኔ ብዙ ኢትዮጵያውያንን አታሎ ከአገር ቤት አስገብቶ መሬት እንዲያገኙና ቤት እንዲገዙ አድርጓል። ሰይጣን ሔዋንን እንዳሳሳተ ሁሉ ወያኔ እናንተንም አሳስቶ ይሆናል። ለዚህም ነው ስማቸውን ለአሁኑ ባልጠቅሰውም እነ አቶ ሞረሽ "አማሮች ከጎንደር ከተማ ይውጡ"እያሉ የሚያላዝኑት። አንዳንድ ኦነጎች "ነፍጠኞች ከፍንፍኔ ይውጡ"እንደሚሉት አማሮች ከጎንደር ከተማ መውጣት አለባቸው ሲሉ እንዴት ወያኔዎችን ይውጡ ሳይሉ ቀሩ? ይህ ነው በቅማንት ነገድ ስም እንቅስቃሴ የጀመሩት ቡድኖች የወያኔ መጠቀሚያ ሁነዋል የምለው። ለመሆኑ የጎንደር ከተማ የማን ነው? የኢትዮጵያውያን ዋና ከተማ የነበረ አሁንም የኢትዮጵያውያን ከተማ መሆኑን ልትረዱ ይገባል።

# ምዕራፍ 7

## ምሳ 26፤22 የጆሮ ጠቢ ቃል እንደ ጣፋጭ መብል ነው

ምሳሌ 26፤22"የጆሮ ጠቢ ቃል እንደ ጣፋጭ መብል ነው፤እርሱም እስከ ሆድ ጉርጆች ድረስ ይወርዳል:: ክፋት በልቡ ሳለ ፍቅርን የሚናገር ከንፈር በብር ዝገት እንደ ተለወጠ የሸክላ ዕቃ ነው"ይላል ቅዱስ መጽሐፍ:: በነገራችን ላይ ጆሮ ጠቢ ማለት ሰላይ ማለት ነው:: ሌላም ስም አለው!ነጭ ለባሽ ይባላል:: ደህንነት፤ጸጥታም ይባላል:: ጆሮ ጠቢ ማለት ወዳጅና ዘመድ የለውም:: ከሰው ቤት ገብቶ ያየውን ሁሉ ተመልክቶ ለላከው አካል የሚያደርስ ነው:: ጉዳይ ፈጻሚ አምባሳደር ዘመነ ካሰኝ በጎንደር ሕዝብ የተከበሩ ሲሆን ከጎንደር አልፈው በኢትዮጵያ የተከበሩ በመሆናቸው ኢትዮጵያን ወክለው የግብጽ አምባሳደር ሁነዋል:: በዚህ ተግባር ላይ ተሰማርቶ የነበረ ሰው ዝቅ ሲል ያስደነግጣል፡እርሳቸውን የጎንደር ሕዝብ ከመውደዱ የተነሳ የክፍለ ሀገሩን ሕዝብ በአንድ ዓይን ያያልሉና የጎንደር ማህበር ሊቀመንበር ይሁኑ ብሎ መርጧቸው ነበር:: ምን ያደርጋል የማህበሩን አቋም አወቁት:: እንዲያንስራራ አደረጉት ለካስ ጆሮ ጠቢ ስለነበሩ ነው:: የጎንደርን ማህበር የመሰረቱ አባቶች በወያኔ ዘመን ልማት ይለማል የሚል አቋም አልነበራቸውም::

ዓላማቸው የጎንደርን ክፍለ ሀገር ስፋት ትውልዱ እንዲያውቅ ይሆናል የሚል ነበር:: አሁን በቅርቡ የተረዳሁት ነገር ቢኖር ለጎንደር ማህበር መጥፋት ተጠያቂው ጉዳይ ፈጻሚ አምባሳደር ናቸው:: ምክንያቱም የሚያውቁትን ለወያኔ አስረድተዋል:: ጥቅምት 2006 ዓም ከአንድ የቅማንት ተወላጅ ወዳጄ ጋር በስልክ ስለ ጎንደር አንስተን ጨዋታ ጀመርን:: ታዲያ በመስከረም ከጎንደር ዋሽንግተን ዲሲ መጥቶ ቅማኖቶችን ሲቀሰቅሱ የሰነበቱ ሰዎችን እንደነበሩ ነገሩኝ:: እኔም ለዚህ ሁሉ ችግር አቶ ነጋ ጌጤ የጻፉት መጽሐፍ እንደ ወያኔ ማኒፌስቶ ነው አልኳቸው::

አቶ ሞረሽ <u>"ነጋ ቀድሞ በአደባባይ ስለወጣ</u> እንጂ ሌሎች ብዙ ብዙ አሉ ይህን ጉዳይ የሚያንቀሳቅሱ"አሉኝ:: በወቅቱ እኔ የወሰድኩት ወያኔዎችን ይሆናል ብዬ እንጅ ሌሎች የቅማንት ምሁራኖች አብሰም የተከበሩ ጉዳይ ፈጻሚ አምባሳደር ዘመነ ይጨመሩበታል የሚል ጥርጣሬ ፈጽሞ አልነበረኝም:: የተከበሩ ጉዳይ ፈጻሚ አምባሳደር በ80 ዓመታቸው ተገለጸ ተግባራቸው:: በዚህ ዓመት አይኑን አፍጥጦ ጥርሱን አግጦ ችግሩ ሲመጣ የጎንደር ሕብረት ሲመሠረት በተደጋጋሚ መግለጫ አውጥቷል:: አንዱ በመግለጫው ላይ የተከበሩ ጉዳይ ፈጻሚ አምባሳደር ዘመነን ስም ተመዝግቦ ሳየው ጥቅምት 2006 ዓም" ነጋ ቀደም በአደባባይ ስለወጣ እንጂ ሌሎች ብዙ ብዙ አሉ ይህን ጉዳይ የሚያንቀሳቅሱ" ብለው ወዳጄ የነገሩኝ የሚያውቁት ነገር ስላለ ነው አልኩኝ::ብዙም ሳይቆይ ራሳቸው በኢሳት ሬዴዮን "አማካሪ ነኝ"ብለው መጡ::

እኔም ሆንኩኝ ሌሎች የምናውቀው ቅማንትና አማራ ሌላውም ነገድ የተጋቡና የተዋለዱ መሆናቸውን ምስክሮች ነን:: ልዩነት አለ ብሎ የሚያምን አቶ ነጋ ጌጤና ወያኔ የመለመላቸው ካድሬዎች ካልሆኑ በቀር ሌላ አለ ብዬ አላምንም:: አሁን ግን ይህ ቅዱስ ጋብቻ ልዩነት መፍጠሩን ተጽፎ እያነበብን ነው:: ሙሉቀን ተስፋው የተባሉ ከጎንደር በድረ ገጽ አንዲት ገጽ ተኩል ለቀዋል:: ጹሁፉ የተለቀቀው ጥር 26 ቀን 2015 በጎርጎርዮስ ቀመር መሆኑን ያመለክታል:: ሙሉውን ጹሁፍ ከዚህ ቀጥሎ ገልብጨዋለሁ::

ሙሉቀን ተስፋው <u>የአማራና ቅማንት ጉዳይ በድረገጽ</u> "ይህን ጉዳይ ስሸሸው የቆየሁት ነገር ነው:: እርግጥ አንድ ግዜ ፋክት መጽሔት ላይ ነካክቸው ነበር (ያኔ ኢዲት ሲደረግ የኔን ሀሳብ ሙሉ በሙሉ ይዞ ባይወጣም) ግን እስከ መቼ እየሸሸሁት እቆያለሁ? የማያስኬድ ነገር ሲሆንብኝ ይሆን ሀሳብ ለመሞነጫጨር ተገደድኩ  ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በዚህ መልክ ማስቀመጡ ጠቀሜታውም ጉዳትም ይኖረዋል:: ጉዳቱ አንዳንድ የአስተሳሰብ ስንኩላን ከእሳቱ ላይ ቤንዚን ሊጨምሩ ይችላሉ:: በሌላ መልኩ ጠቀሜታው ደግሞ የህብረተሰቡን ንቃተ ህሊና በመጨመር እየተፈጠረ ላለው ሁናቴ መፍትሄ ሊያፈላልጉ የሚችሉ ግለሰቦችና ምሁራን አይጠፉም:: ጥቅሙንም በመመዘን ለአንባቢያን ማሳወቁ ይጠቅማል ብዬ ስላሰብኩ በሚከተለው መልኩ አስቀምጨዋለሁ::"

"የዛሬ ወር አካባቢ መሆኑ ነው:: ከአዘዞ አጤ ቴዎድሮስ አውሮፕላን ማረፊያ ወደ ፒያሳ አንዲት ቢጫ ታክሲ ኮንትራት ይዣለሁ:: የታክሲው አሽከርካሪ ደስተኛ አለመሆኑ ፊቱ ቢመሰክርም ምን እንደሆነ መጠየቅ አልፈለኩም:: ግን በራሱ ጊዜ የሆነውን ነገረኝ:: እድሜው በአርባዎቹ መካከል የሚገኘው የታክሲ አሽከርካሪ ያስከፋው ነገር ሚስቱንና የልጆቹን እናት ያጣበት ምክንያት ነው:: አስራ (17)ዓመታት ከሚስቴ ጋር አብረን ስንኖር ስለ እርሷ ብሔር የማውቀው ነገር አልነበረም:: ሰውነቷ ብቻ በቂዬ ነበር:: እውነቴን ነው የምልህ የጎንደር ልጅ ከመሆኗ ውጭ የማውቀው አልነበረኝም:: በጋብቻችን ለአቻዎቻችን አርአያ የምንሆን ነበርን:: በትዳራችን 3 ልጆችን አፍርተናል:: የመጀመሪያዋ 16 አመቷ ነው:: ባለፈው የጥቅምት መድኃኒዓለም እናቷ ይደውሉልኝና ለመድኃኒዓለም ዝክር ዝግጅት ታግዘኝ ላካት አለችኝ:: እኔም እናቷን እንድታግዝ መሄዷን በደስታ ተቀበልኩት::"

"የጥቅምት መድኃኒዓለም አልፎ ግን ከነገ ዛሬ ትመጣለች እያልኩ ከልጆቹ ጋር ብያት የውሃ ሽታ ሆነች:: ስልክ ስንደውል ስልኳን ዘግታለች:: መጨረሻ ቤተሰቦቿ ካሉበት ቦታ ትክል ድንጋይ ሰው ተላከ:: ልጃችን አማራ አግብታ አትኖርም!የሚል መልስ ከእናቷ ሰሙ የተላኩት ሰዎች:: ሦስት ዓመት ያልሞላውን ህጻን ልጅ እና ሌሎቹንም ልጆቿን ትታ ለመቅረት እንደወሰነች ሰማሁ:: በቁስ በሽማግሌ አስቀጠየኳት:: ወይ ፍንክች የአባ ቢለዋ ልጅ፤ልጆቹ ሲያድጉ ሰራተኛ አላሳየናቸውም:: ሙሉ በሙሉ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እርሷ እና እኔ ነን የምናሟላላቸው:: ሠራተኛ አሁን አስገብቼ ለትምህርት ቤት ምሳ እንድትቋጥር ሳደርግ ልጆቹ ሳይበሉት እየተመለሱ እርሃብ ሊገድላቸው

ሆነ፡፡ አሁን የቤቱንም የውጭውንም ሥራ ብቻዬን ይዤዋለሁ በማለት ልብን የሚሰብረውን ግለ ታሪክ አጫወተኝ፡፡ ሌላው አጋጣሚ ደግሞ እንዲህ ነው፡፡”

“በህዝብ ትራንስፖርት ወገራ አውራጃ ውስጥ ኮሶዬ ከሚባል ቦታ ደርሼ ለመምጣት ተሳፈርኩኝ፡፡ መኪና ውስጥ ከፖለቲካ ውጭ የሚወራ ወሬ መጥፋቱን አስተዋልኩ፡፡ በቃ ግማሹ መንግሥትን ተቃውሞ ከፊሉ ደግሞ መነታረክ ነው፡፡ ስሄድ ምንም ሳልናገር ደረስኩኝ፡፡ ስመለስም ሌላ የፖለቲካ ንትርክ ካለበት ሚኒባስ ውስጥ ገባሁ፡፡ እርግጠኛ ነኝ የፓርላማ ሰዎች ያን ያክል ውይይት አያደርጉም፡፡ ወደ ጎንደር ከተማ ስንቃረብ ግን ፖለቲካው ቅማንትና አማራ ሆነ፡፡ አንድ መሀል ሰፋሪ ወጣት ነገሩን አቀጣጠለው፡፡ ከአምባ ግዮርጊስ የተሳፈረ ግለሰብ ሽምበቂት ከምትባል አንስተኛ መንደር ሲወርድ አቀጣጣዩን ልጅ ቅማንት ስለሆንክ እወድሃለሁ ብሎት ወረደ፡፡ ከደቂቃዎች በኋላ ከጀርባዬ ካለው ወንበር የተቀመጡት ሁለት ሰዎች ሊደባደቡ ሲታገሉ ዞርኩ፡፡ መኪናው ቆሞ ሰዎቹን መገላገል ያዝን፡፡ ከአፍታ በፊት በወዳጅነት ሲያወሩ የነበሩት ግለሰቦች ለምን እንደተጣሉ አጣራንና የበለጠ አዘንን፡፡ ሊደባደቡ የሚገለገለው ሰውዬ እኔ በአባቴ ቅማንት ነኝ እርሱም ቅማንት ነው፡፡ የሚኖረው ጎንደር ዙርያ ሆኖ ሳለ እባክህ በእናንተ አካባቢ ኮሶዬ ሚስት ፈልግልኝ አለኝ፡፡ ጎንደር ዙርያ ጠፍቶ ነው ኮሶዬ ድረስ ሚስት ፍለጋ የምትመጣው?ስለው ከዚያማ ሁሉም አማራ ሆኑብኝ፡፡ ቅማንት ከእናንተ አካባቢ ብዙ አለ ብዬ እኮ ነው ይለኛል፡፡ አማራ ቢሆን ምን ችግር አለው?ብዬ ስመልስለት ደሞ ከነዚህ እንቶቶች ጋር ነው የምጋባው?ሲለኝ ስሜቴን መቆጣጠር አቃተኝ በማለት ሲያብራራ እኔ የምናገረው ስላልነበረኝ ዝም አልኩ፡፡”

“አብረው የነበሩ ሊደባደቡ የከጀሉት የተጨቃጨቁም ብዙ ያወሩም አሉ፡፡ የተሳደበው ግለሰብ ዝምታን መርጧል፡፡ ጥፋተኛነቱን ያመነ ይመስላል፡፡ ግን ከዚህ ሁሉ ምን እንመለከታለን ዘረኝነት ጎጠኝነት ገጠር ካልተማረው ማህበረሰብ ድረስ ገብቷል፡፡ በአርማጭሆ፣ወገራና መተማ በዚህ ዓመት ብቻ ጥንዶች ትዳራቸውን አፍርሰዋል፡፡ ልጆቻቸውን በትነዋል፡፡ በሰሜን ጎንደር ዞን ያሉ ፍርድ ቤቶች በዚህ ዓመት ያስተናገዱት የፍች ጥያቄ ከዚህ በፊት ካለው ዘመን የሚነጻጸር አይደለም፡፡ ለእኔ እስከሚገባኝ ቅማንትና አማራ መካከል ምንም ልዩነት አላየሁም፡፡ የሚኖሩበት ቦታ የሚናገሩት ቋንቋ የሚያመልኩት ሃይማኖት የሚመገቡት ሁሉ ተመሳሳይ ሳለ ለምን ግን መለያየት አስፈለገ? የቅማንት ብሔረሰብ አለባቸው በተባሉ ቦታዎች ሁሉ ዞሬ ለመታዘብ እንደቻልኩት ከአማራው የተለየ ቋንቋና ባህል አልገጠመኝም፡፡ ይህ መሬት ላይ ያለ እውነታ ነው፡፡ ቅማንት የሚባል ቋንቋ ነበር፡፡ አሁንም በእድሜ ገፋ ያሉ ሰዎች ያሉ አሉ፡፡ አባ ወንበሩ መርሻ (የቅማንት መሪ) ከመሞታቸው በፊት ይህን ጉዳይ አረጋግጠዋል፡፡ በእኔ እምነት ይህ ቋንቋ ፈጽሞ ከመጥፋቱ በፊት ዩንቨርስቲዎቻችን (በተለይም የጎንደር ዩንቨርስቲ)መዝገበ ቃላትና ሰዋሰውን ማስቀረት አለባቸው፡፡ ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎችም ሊማሩበት ይችላሉ፡፡ ነገር ግን መሰረታዊ እውነታ መሬት ላይ ባለው መልኩ እርስ በርስ ቅራኔ ውስጥ መግባቱ እጅግ ኋላ ቀር አስተሳሰብ ነው”ሲሉ ጽፈዋል፡፡

የጉዳይ ፈጻሚ አምባሳደር ዘመነ የዘሩት ዘር በቅሎአል:: ትዳር ፈርሷል ለአገርና ለሕዝብ መከታ ሊሆኑ የሚችሉ ሕፃናት ተለያይተዋል:: በአማራና በቅማንት ነገድ መካከል ጋብቻ እንዲቃረን ሁኖአል፤ሕዝቡ እንዳይተማመን ሁኗል:: ይህ እየተደረገ መሆኑን ጉዳይ ፈጻሚ አምባሳደር ዘመነ ሊቆጫቸው ይገባል:: የወረዳ ማህበር መመስረት ከተጀመረ ጀምሮ ጎንደር ውስጥ የሚሰማው ልዩነትን አለ:: ይህን የሰሙ እነ አቶ ሞረሽ ከአሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ ሲሄዱ እግር መንገዳቸውን ጉዳይ ፈጻሚ አምባሳደርን ሊያነጋግሩ ቀጠሮ ይዘው ከሆቴላቸው ሕደው ነበር:: ጉዳይ ፈጻሚ አምባሳደር በጎንደር ሕዝብ ዘንድ ይከበራሉና:: ተገናኝተው የተባባሉትን አቶ ሞረሽ መጋቢት 5 ቀን 2007 ዓም ስልክ ደውለው የተባባሉትን ነግረውኛል:: እንደ ወረደ አስቀምጠዋለሁ::

<u>አቶ ሞረሽ</u> "ቀኑ መስከረም 27/2004 ዓም ይመስለኛል:: ክቡር አምባሳደር ዘመነ ካሰኘን ከሆቴላቸው ሕደን ልናገኛቸው እንደምንፈልግ ቀነ ቀጠሮ እንዲሰጡን ጠየቅን:: በተባለው ቀን እግዚአብሔር ይስጣቸው ጠበቁን:: እኛም በክፍለ ሀገሩ አንዳንድ ልዩነት የተጀመረ መሆኑን አነሳንና እርስዎ እያሉ እንዴት ይህ ይሆናል አልናቸው:: መልሳቸው "ልዩነት አለ የምትሉ እናንተ ናችሁ!በእኛ በኩል ልዩነት ወይም ግጭት የለብነም"ብለው ውይይቱን ዘጉብን:: አሁን ደግሞ እንዲህ ብለው መጡ"ሲሉ ነግረውኛል:: ጉዳይ ፈጻሚ አምባሳደር አሁን በመጋቢት 2007 ዓም "ቋንችን ሊጠፉ ነው"አሉ:: የቅማንትን ቋንቋ መጥፋት ዛሬ ነው እንዴ ያወቁት? ለቅማንት ቋንቋ እንዳይጠፋ ካሰቡ ታዲያ ለምን በ1968 ዓም የሌሎች ነገድ ምሁራን የመማርያ መጽሐፍ በየቋንቋቸው አዘጋጅተው መሠረተ ትምህርት ልጆቻቸው እንዲማሩ አድርገዋል:: በዚህ ሰዓት እርስዎ የት ነበሩ? አሁን አንቀጽ 39ኝን መከታ ከማድረግ ይልቅ ሕብረ ብሔር በነበረው በደርግ ዘመን መፈጸም አይቻልም ነበር?

ወያኔ የርሱ የሆኑትን የተወሰኑ የቅማት ልጆች ከያዘ በኋላ በፀረ አማራ ቅስቀሳ አድርጎ እንዲቃረኑ ሁኖአል:: መልሶ ደግሞ ወደ አማራው ነገድ ገብቶ "ልጆቻችሁ በቅማንት አስተማሪ መማር የለባቸውም"ብሎ ተናገረ:: በዚህ ምክንያት ከማስተማር ገበታቸው ተባረው አይከል ከተማና ትክል ድንጋይ መሰብሰባቸውን አስመልክቶ የተከበሩ አምባሳደር ዘመነና አቶ በየነ አስማረ በኢሳት ሬዴዮን ስትከራከሩ የጠየቁዎትን አልመለሱም:: እነዚህ አስተማሪዎች ያ ለምንም ሥራ ተቀምጠዋል:: በእርግጥ ደሞዛቸውን ሊከፈሉ ይችላሉ:: ግን በነዚህ ወንድሞቻችን ላይ የሞራል ችግር ሊገጥማቸው ይችላል:: ለነዚህ ሁሉ ችግሮች ተጠያቂ የተከበሩ አምባሳደር መሆናቸው መዘንጋት የለበትም:: ሁሌም ሰላይ ለትውልድና ለህዝብ የሚቆም አይሆንም:: ከመጣው መንግሥት ጋር አብሮ መንጎድ ተግባሩ ነው:: የሰላይ ተግባር ሽሚዝ መቀየር ነው:: የተከበሩ አምባሳደርም ከአጤው ዘመን እስከ ደርግ አልፎም በወያኔ ዘመን ከመሰለል አልተቆቋቡም::

የተከበሩ ጉዳይ ፈጻሚ አምባሳደር ዘመነ እንደ ደጃዝማች ቢተዋና ደጃችማች ጣሹ እንግዳ፤እንደ ፊታውራሪ አየሌ አባ ጓዴና እንደ ፊታውራሪ ረዳ፤ሌሎች ስመጥር የቅማንት ልጆች ጀግኖች ሸረገና ይሆናሉ ስንል ባልተጠበቀ መንገድ እንደ አቶ ነጋ ጌጤ ፈሸከና ሆኑ!ያሳዝናል::

# ምዕራፍ 8

## ጎንደሬ አትበገር ለወያኔ!

ወያኔ በርሃ ሲገባ አቶ ገሰሰው አየለን "ስሁል"ብሎ ስም ሰጣቸው። በራስ ስሁል ምክንያት ዘመነ መሳፍንቱ በኢትዮጵያ ተመስርቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደም ፈሷል። ዘመነ መሳፍንት ከግንቦት 1761 ዓም እስከ የካቲት 1845 ዓም የኢትዮጵያን ሕዝብ ደም አፍሷል። ዘመነ መሳፍነቱ የኢትዮጵያን አንድነት አስደፈሯል። ይህን ደም አፍሳሽ ዘመነ መሳፍንት ከጎንደር የተነሱት የኢትዮጵያን አንድነት መሰረቱ። ሌሎች ነገሥታትና ርዕሰ ብሔሮች እጅግ ከፍ ከፍ አደረጓት። የአጤ ቴዎድሮስን ታሪክ ስታነቡ ሁሌም የደጃዝማች ገለሞና የደጃዝማች ዓለሜ ታሪክ ይነሳል። በተለይ ደጃዝማች ገለሞ የጥይት ድምጽ እስኪሰሙ ድረስ የሚተኩሱ አይመስሉም ነበር ይባላል። የጥይት ድምጽ ከሰሙ በኋላ ግን የተዋጣላቸው ተዋጊ ለመሆናቸው በጉራምባው ጦርነት ደጃዝማች ካሳና ደጃዝማች ጎሹ በተዋጉበት ቀን ጦር በጉንጫቸው ይገባል።

በዚህ ሰዓት ከበቅሎ ላይ እንዳሉ ተሰውረው ሲመለሱ የጎጃም አቀንቃኝ እንዲህ ትላለች።
አይሸሽም ያልከው ገለሞ እንኳን ሸሸ
የደንቢያን ሜዳ እያበላሸ
ብላ ስትቀኝ ደጃዝማች ካሳ የኋላው አጤ ቴዎድሮስ እንዲህ ሲሉ መለሱላት።
አብለሽ ነው እንጂ አልተናገርሽም
በዙበት እንጂ ገለሞ አይሸሽም
ሲሉአት ደጃዝማች ገለሞም ከጉንጫቸው የገባውን ጦር መዘው ጥለው እንዲህ ሲሉ መለሱላት።
ተይኝ አንቺ ሴት ደም አስክሮኛል
የታጠቅ አሽከር ድሉ ጠምቶኛል
ያነን ያጨደው ማን ይመስልሻል
ወጊ እንደጌታው እንደ አባ ታጠቅ
ሕግ አስከባሪ ደርሶ እንደመብረቅ ሲሉ መለሱላት። ጎንደሬው በወያኔ የምትጠላው አገር ለመገንባት ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኖችህ ጋር ሁነህ እንዳትነሳ ስለተፈለገ ነው።
ጎንደሬ ወያኔ ያለ ይበል ሆዳም ለሆዱ ይደር
አንተ ግን ለወያኔ አትበገር
ከካህን እስከዲያቆን ሲያሰድድህ
መሬት ለሱዳን አሳልፎ ሲሰጥብህ
ከሌላው ሕዝብ ጋር አንድ እንዳትሆን ሲዶለትብህ
የቴዎድሮስ ልጅ ነህና ለኢትዮጵያ አንድነት ኑር በእምነትህ።

ወያኔዎች በአሽባሪነት የከሰሱት አቶ አንዱዓለም አራጌ ሆነ አቶ ናትናኤል መኮነን፤ሌሎች የጀመሩትን ትግል አጧጡፈህ ኢትዮጵያን አድን። አባቶችህ ያስተማሩህን የአገር ግንባታ ታሪክ ኢትዮጵያን አስከብር ብለው ነው። ጎንደሬ አባቶችህ ያስተማሩህ አንድነት እንጂ ለልት አይደለም። በመካከልህ ያሉትን ሰፈርተኞችንና ሆዳሞችን አጋልጠህ ለአንድነት ተሰለፍ።

የጎንደር ትውልድ ልብ በል ለሆድህ አትደር
የአባቶችህን ታሪክ አስከብር
ለልጆችህም እውነቱን ተናገር
የነዓለሜን የነገለሞን መንደር
አንድ ሁነህ ጠንክርና አጠንክር።

ፍሊፕ ማድሰን ትርጉም መኮንን ተክለየስ <u>አጤ ቴዎድሮስ የትንሣኤው</u> ሰማዕት በተባለው መጽሐፍ “እንደ ቴዎድሮስ በድህነት እየኖረ ለሀገሩ እድገትና ብልጽግና ለሚያምጡ ተገቢውን ዋጋ የሚከፍል መሪ? የትኛውስ ንጉሥ ነው በእግዚአብሔር ብቻ ተማምኖ ይህንን ያልተረጋጋ በእርስ በርስ ሽኩቻና የወደመ ወደኋላ የቀረን ሀገር ታሪክ እቀይራለሁ ብሎ የሚሰራ ማንም የለም” ሲሉ ጽፈዋል። አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ አንድነት መሠረት ሲጥሉ ተመችቷቸው ሳይሆን ተንገላተው ነው። ለዚህ ለኢትዮጵያ አንድነት መሠረት መጣል የቅማንት ልጆች ቀዳሚ ተዋናይ ነበሩ!አሁንስ?የቅማንት አባቶቻችን ለአንድነት እንጂ መቼ ለሰፈር ተዋግተዋል? ይህን ታሪክ እንዴት ልንዘነጋው ቻልን? አሁንም አልመሸም!የሌሎችን አላውቅም በእኔ እምነት ሰፈርተኝነት ቁምጥና ነው። ለአንድነት መታገል ጀግንነት ነው።

ጎንደሮች አሁን መሰባሰብ የጀመሩት በወያኔ መሬታቸው ቀደም ለትግራይ አሁን ለሱዳን ሊሰጥ በመቃረቡ የወልቃይት ሕዝብ የዘር ማጥፋት ዘመቻ መደረጉ አንሶ የክፍለ ሀገሩን ነገዶች አንድነታቸውን ለማሳጣት በመጣሩ ነው። ከተጠቀመባቸው በኋላ ይጥላቸዋል። አንድ ታሪክ ልጥቀስላችሁ ብፁዕ አቡነ አረጋዊ ሲሞቱ ቀብራቸው ታይቶ በማይታወቅ ሥርዓት ተፈጸመ። ብፁዕ አቡነ አረጋዊ በጎንደር ክፍለ ሀገር በሰሜን አውራጃ ጠለምት የተወለዱ ሲሆን ወያኔ ሲጠቀምባቸው ቆይቶ ሲሞቱ ቀብራቸው እንኳን ለአንድ ሊቀጳጳስ ይቅርና ለአንድ ምዕመን ሊደረግ የሚገባውን ክብር ነፈጉአቸዋል። ይህ ማለት ወያኔ ከተጠቀመ በኋላ ሲጥል እንዲህ ያደርጋል። የቀብሩን ሥርዓት አስመልክቶ ሀራ ተዋሕዶ ብሎግ በፎቶ አስደግፎ አውጥቶታል።

<u>ሐራ ዘተዋሕዶ</u> ብሎግ ጥር 1 ቀን 2007 ዓም የ106 ዓመት አረጋዊ የብፁዕ አቡነ አረጋዊ ሥርዓተ ቀብር ባረፉበት ዕለት ተፈጸመ፤ የሥርዓተ ቀብሩ መጣደፍ ሽኚው ሸኚ ሲያጣ! እስኪያሰኝ ድረስ አባቶቻችንና ምዕመናንን አሳዝኗል። የሥርዓተ ቀብሩ አፈጻጸም ይቅርና ለአረጋዊ ሊቀ ጳጳስ ለአንድ ደግ ምዕመን እንኳ የሚገባ እንዳልኾነ ከሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንና ከአበው ትውፊት አንጻር የሚመዝኑ አባቶችና ምዕመናን በወቅቱ ፓትርያርክ ዘመን የቤተ ክርስቲያናችን ክብርና ሞገስ እየተፈተነ ለሚገኝበት አስከፊ ሁኔታ

አመልካች አድርገውታል"ሲል ብሎጉ ትዝብቱን ጽፏል:: በቤተ ክርስቲያን ትውፊት መሠረት አንድ ሊቀ ጳጳስ ሲሞት አስከሬኑን የሚከቡት ጳጳሳት ነበር በብፁዕ አቡነ አረጋዊ ግን ይህ አልተደረገም:: ስለዚህ ወያኔን የምታገለግሉ ሁሉ በዚህ ዓይነት የምትዋረዱ መሆናችሁ ተረዱ:: የጎንደርን ተወላጆች ወገኖቼን የምለው ነገር ቢኖር መቻቻል እንዲያሳዩ ነው::

የቅማንት አስተዳደር መፈቀዱ ያስደነግጣችሁ፤ሆናችሁ የተደሰታችሁ አርቃችሁ እንድታስቡ እለምናለሁ:: ረጋ ብሎ የሚወርድ ኮለል ያለ ውኃ ዝናብ ዘንቦ ጎርፍ ሲጨመርበት የውሓይ መልክ ሲቀየር ከጎርፉ መብዛት ምክንያት እንጨቱን ሆነ እሳሩን ጠራርጎ ይወስደዋል:: የጎርፉ ውኃ ካለፈ በኋላ ቀሪው እንደነበረው ኮለል ብሎ ሁሉም ሰላማዊ ሁኖ መሄድ ይጀምራል:: በጎንደር ሕዝብ ላይ የደረሰው የዚህ ዓይነት በመሆኑ ወያኔ ዝናብ ሲሆን እርሱም ያልፋል:: ከዚህ በፊት በጣልያን ግዜ የነበረው ዓይነት ነው:: አሁንም በግራ ቀኙ ያጎንደሬዎች ረጋ ትሉ ዘንድ አሳስባለሁ:: በሰሜን አሜሪካ የተጀመረው አይነት አንድነት ፍቅር በጎንደርም ሊጀመር ይገባል::

ሰሜን አሜሪካ የተመሠረተው የጎንደር ሕብረት "የጎንደር ሕዝብ ተጠሪ" መባል ይኖርበታል:: ተጠሪ የሚለው ቃል ነገድ ሃይማኖትን አይጠቅስም:: ሁሉን አንድ አድርጎ ለመያዝ ያመች ዘንድ "የጎንደር ሕዝብ ተጠሪ" ቢባል ለአንድነታችን የሚያጠነክር ሲሆን ከፋፋያችን ወያኔንም ሊያሳፍር ይችላል:: ጎንደሬው ቴዎድሮስና ገለሞ ከቋራ ተነስተው 84 ዓመታት ኢትዮጵያን የከፋፈለን ዘመነ መሳፍንት ያፈረሱት ጠንክረው በመታገላቸው ነው::

ሌሎች ክፍለ ሀገራት አብሶም አማራው አብሮት ከኖረው ከህዳጣን ነገዶች ጋር ሊያዋሕደው የሚችለው "የመሀል ኢትዮጵያ ሕዝብ ተጠሪ" ብሎ ሲደራጅ ነው:: የሸዋና የወሎ፤የጎጃምና የጎንደር ሕዝብ በዚህ መልክ አንድ ከሆነ ከጥፋት ሊድን ይችላል:: ምክንያቱም በነገድ ስም እንዲደራጁ ወያኔና ሆዳሞች ቅስቀሳ ሊመክን ይችላል:: ለምሳሌ ደቡብ ኢትዮጵያ 45 ነገዶች አንድ ክልል ሁነው ተደራጅተዋል:: በዚህ መልክ ከተደራጀሕ በአራቱ ክፍለ ሀገራት ያለው ሕዝብ አንድነቱ ይጠበቃል:: ምሁራን አስቡበት:: ከዚህ በመቀጠል ሁሉንም አንድ የሚያደርግ "ጠቅላላ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት" ብሎ ሌሎችን ክልሎች አስተባብሮ መታገል ይቻላል:: በዚህ መልክ ከተደራጀን ኢትዮጵያን ማትረፍ ይቻላል::

አቢይ አበ <u>አውቀን እንታረም</u> በተባለው መጽሐፋቸው "መሥራት አስቸጋሪ ነው! ማፍረስ ግን በጣም ቀላል ነው:: የፈረሰን ደግሞ መልሶ መሥራት ከሁሉ የበጠለ አስቸጋሪ ነው!ያንን የተከፋፈለ አሳብ ያንን የተወሳሰበ መጥፎ ልማድ" ማስወገድ ከባድ መሆኑን ጽፈዋል:: የዚህ ዓይነት ዓላማ ይዞ ለሚነሳ ሰው ከባድ መሆኑ ይገባኛል:: መፍትሂው ግን ይህ ይመስለኛል:: ምክንያቱም በያንዳንዱ ክፍለ ሀገር የተለያዩ ነገዶች ሰላሉ ልላሉ ብቻ ሳይሆን በዚህ በ24 ዓመታት ውስጥ ብዙዎቹ መጥፎ ልማድ ወያኔ አስተምሯቸዋል:: አጤ ቴዎድሮስ ሲነሱ የገጠማቸው ይህን የልዩነት ቀንበር ከሕዝቡ ማላቀቅ ነበር:: ከብዙ ትግል በኋላ

ከባዱን ቀንበር ከሕዝቡ እንዲላቀቅ አድርገውታል:: ከታሰበበት ሊደረግ ይችላል:: ችግሩ በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ ሕዝብ የተማረ ይግደለኝ ብሏልና ምሁራኖች ካደረጉት ይደረጋል::

መስፍን ወልደ ማርያም ኢትዮጵያ ከየት ወዴት በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 34 "የእግዚአብሔርንና የኢትዮጵያውያንን ግንኙነት የሚያመለክት አንድ ነገር አለ:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ለክፉም ሆነ ለደጉ ለሐዘኑም ሆነ ለደስታው ኃላፊነቱ በሙሉ የእግዜአብረው ነው እንጂ የራሱ እንዳልሆነ አድርጎ የሚመለከተው ይመስላል"ሲሉ ጽፈዋል:: ያሰብነውን ዓላማ እግዚአብሔርና አላህ እንዲረዱን በየእምነታችንን እንጸልይ:: በዘመናዊው አባባል "አንድነት ኃይል ነው፤ድር ቢያብር አንበሳ ያስር"የሚለውን መጽሐፍ ቅዱስም "ሁለትም ሦስትም ሁናችሁ በስሜ ብትሰበሰቡ ከመካከላችሁ እገኛለሁ"ባለው መሰረት የቤተ መቅደሱ ካህን ሆነ የድግናው ወንበር፤የቤተ ክርስቲያኑ ቄስ ወይም የቤተ መስግዲ ህጅ ሌላው ምዕመን ኢትዮጵያን ከፈተና እንዲያድንለት በጸሎት አምላካችን እንለምነው:: ሰይጣን አንድነት እንደማይወድ ሁሉ ወያኔ አንድነትን ይጠላል:: ሕዝቡ አብሮ በመነሳቱ የዛሬዋን ኢትዮጵያን አስረክበዋል:: ሴረኛው ወያኔ አገርህን አንድ ሁነህ እንዳታስከብር እያደረገ መሆኑን ተረዳ:: ወያኔ ሞራህል ሊመታ ሲፈልግ አባቶች የፈጸሙትን ተጋድሎ ዋጋ አሳጥቶታል::

አንዳርጌ መስፍን ቅሌት በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 148 "አባቶቻችን በባዶ እግራቸው ላይ ወጥተው ታች ወርደው ያህያ ሽንት እየጠጡ ከቅኝ ገዥዎች ጋር ተናንቀው ዛሬ የምንመካባትን አገር ቢያቆዩን የስድብ ናዳ ይወርድባቸዋል ይባስ ተብሎ መሬት ፍለጋ ነው የሄዱት ተባለልህ? እውነት አጋዴን ወርደው ከኢጣሊያን ጋር የተናነቁት የነዳጅ መሬት ፍለጋ ነበር? አደዋ ድረስ ዘልቀው የፋለሙትን የከበረ ድንጋይ ፍለጋ ነው? እሩቅ ምን አስኬደን፤ትናንት 1969 ዓም ከሶማሌ ጋር በተካሄደው ጦርነት ከጎንደር፤ ከጎጃም፤ከወሎ፤ ከሸዋ ሞፈር ቀንበሩን ሰቅሎ የዘመተው ሚሊሽያ ሠራዊት መሬት ፍለጋ ይሆን?ይኽ ሠራዊትም ነፍጠኛ ይሆን እንዴ? የዛሬው ሠራዊትስ ሠራዊትስ ከትግራይ ተነቅንቆ የመጣው የመሀል ኢትዮጵያንና የደቡብ ኢትዮጵያን ሕዝብ ካማራ ቅኝ ተገዥነት ነፃ ለማውጣት ይሆን? ሁሉንም ታሪክ ይፍረደው"ሲሉ ጽፈዋል::

ታሪክ ይታመማል እንጅ አይሞትም:: ስለዚህ ለታሪክህና ለአንድነትህ መነሳት ያለብህ ወቅቱ አሁን ነው:: ወያኔ አንድነትህን ፈጽሞ አይፈልገውም አንተ ግን ልታሳየው ይገባል:: ጎንደሬው ኢትዮጵያዊው የቴዎድሮስ ልጅ፤አንድነትህን አጠንክረህ ለትልቋ ኢትዮጵያ ትነሳ ዘንድ የቴዎድሮስ አጽም ከመተማ አካባቢ ካለው ከማህበረ ሥላሴ ገዳም ሁኖ አድኑኝ ወደ ሱዳን ሊከልሉኝ ነው ብሎ ጥሪ አቅርቧልና ጥሪውን ተቀብለህ የጎንደር ሕዝብ ከከፋፋይ አድን::
ሆዳም ለሆዱ ይደር ጎንደሬ ለወያኔ አትበገር
የኢትዮጵያን አንድነት ከሌሎች ጋር ሁነህ አስከብር
በተመሳሳይ መጣጥፍ እስክንገናኝ ድረስ በቸር ይግጠመን::

# ጠቅላላ ዋቢ ሠነድ

1 መጽሐፍ ቅዱስ 1980 ዓም እትም
2 ወይዘሮ ሰናይት ኃይሌ ጀግንነት ቢወረስ
3 ዶ/ር ሀብተማርያም አሰፋ የኢትዮጵያ ታሪክ ጥናቂዎችና ባሕሎች
4 ዶር ላጵሲ ጌ ድሌቦ የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ
5 ዶር ላጵሶ ጌ ድሌቦ የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መሣርያዎች
6 አለቃ አያሌው ታምሩ ኢትዮጵያ በሦስቱ ሕግጋት
7 ቀሲስ ዘመነ አቡሃይ ደስታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አጭር ታሪክ
8 ቀሲስ ከፍያለው መራሒ የቤተ ክርስቲያን አስተዋጽኦ
9 ዘመድኩን በቀለ ቅዱሳን መካናት በኢትዮጵያ
10 ነጋ ጌጤ የቅማንት ሕዝብ ታሪክ
11 ዲ/ን መንግሥቱ ጎበዜና ዲን አሳምነው ካሣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ቁጥር 2
12 የሱፍ ያሲን አሳሳቢነት ባንድ ሀገር ልጅነት የኢትዮጵያ እጣ ፈንታ
13 ዶ/ር ኃይሌ ወልደሚካኤል ሮብሮነት በኢትዮጵያ
14 አባ ጋስፓሪኒ የኢትዮጵያ ታሪክ
15 በላይ ግደይ የኢትዮጵያ ሥልጣኔ
16 አለቃ ታዬ ወልደማርያም የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ
17 ሊቀ ብርሃናት አረጋ የቅዱሳን ታሪክ ቁጥር 5
18 ፕሮፌሰር ሲጋምስት እንደጻፈው ቅማንት አረማዊ-ኦሪታዊ ኢትዮጵያዊ ገበሬ
19 ብላቴ ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል ዝክረ ነገር
20 ነጋ ኃይለ ሥላሴ ባለታሪክ ኢትዮጵያ
21 መሪራስ አማን በላይ የጥንቷ ኢትዮጵያ ትንሣኤ ታሪክ
22 ሊቀ ካህናት ባርከው ያለው ከአባት የተገኘ ከጦር የተናኘ
23 ዶ/ር ላጵሶ ጌ ድሌቦ የኢትዮጵያ የመከራ ሥርዓትና የኤርትራ ጥያቄ
24 ማሞ ውድነህ ዮሐንስ
25 ያሬድ ግርማ ኃይሌ የጎንደር ታሪክ ከኢትዮጵያ ታሪክ አንጻር
26 አስፋው ወልድዬ ዝክረ አባ ደብልቅ በላይ ወልድዬ ፊታውራሪ
27 ግደይ ባሕር ሹም አሞራ
28 የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት 1986 ዓም
29 ታጋይ ገሠሠ እንግዳ ታሪክ አጉዳፊው የአልባንያ ደብተራ
30 አሰግድ ገብረ ሥላሴ ወልደ ሚካኤል ገሐዲ 2
31 አሎ አይዳሂስ መሐመድ የአፋር ሕዝብ ትግል እና የፖለቲካ አቅጣጫ
32 አባ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሊቀ ጳጳስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ
33 ገብረ ዮሐንስ ገብረ ማርያም ክርስትና በኢትዮጵያ
34 ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል በኢትዮጵያ የሃይማኖት መቻቻል አለን?
35 ሸህ ጀሉዲን ኢብራሂም መለል አ-ሻሚ አፋር/ደናኪል/ታሪክና መረጃ አርኪ ምንጭ/አልመንህል
36 አንዳርጌ መስፍን በሙት መንፈስ አገር ሲታመስ
37 አባ ወልደትንሣኤ አያልነህ ስምዐ ተዋሕዶ
38 ተስፋዬ ገብርዓብ የጋዜጠኛው ማስታወሻ
39 አምባሳደር መንግሥቴ ደስታ ግርማዊት እቴጌ ጣይቱ ብጡል ብርሃነ ዘኢትዮጵያ 1832-1910
40 ጌታቸው ረዳ ይድረስ ለጎጠኛው መምህር
41 ብርሃኑ ደሴ ጣሰው የፍቅር መቅረዝ
42 ዳንኤል ተፈራ ጀ.ዳንዴ የነጋሶ መንገድ
43 ገብሩ አስራት ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ
44 ደሴ ታደሰ የእናት ውለተዋ

45 ደመነፍስ ትውልድ እና የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍጻሜ ዋዜማ
46 ኮሎኔል አስናቀ እንግዳ ሸክም የማይከብደው ሕዝብ
47 አማረ አፈለ ብሻው ደም አይፍሰስ በቃ የሕወሓት ማኒፌስቶ ያብቃ?
48 ፍሊፕ ማድሰን ትርጉም መኮንን ተክለየሱስ አጤ ቴዎድሮስ የትንሣኤው ሰማዕት
49 አቢይ አበበ አውቀን እንታረም
50 መስፍን ወልደ ማርያም ኢትዮጵያ ከዜት-ወዴት?
51 አንዳርጌ መስፍን ቅሌት

## መጣጥፍ

52 የሕሐሃት ማኒፌስቶ የካቲት 1968 ዓም
53 በእደ ማርያም እጅጉ ረታ አጤ ምኒልክና ኢጣልያኖች
54 አብነት ዘገየ ብሔርን መሠረት ያደረገው የሕወሓት/ኢሕአዴግ ፌዴራሊዝም በኢትዮጵያ ይበጃል?
55 በጅማና በኢሊባቡር ክርስቲያኖች ሰማዕትነትን ተቀበሉ ጥቅምት 2 ቀን 1999 ዓም
56 ይኩኖ መስፍን የትግራይ ሕዝብ የ40 ዓመታት ሰቆቃ
57 ዳግማዊ ቴዎድሮስ ሕወሓት በብአዴን ጉዳይ አስፈጻሚነት ቁጥቋጡን በአማራ ሕዝብ ላይ አጠናክሮ ቀጥሏል።
58 በውጭ አገሮች በሚገኙ ሚሚዮኖቻችን የኮንስቲትወሲ ግንባታ
59 ዋይታ ቅጽ 2 ቁጥርት 1 ታህሳስ 29 ቀን 2004 ዓም

## መጽሔት

60 መጽሔት የካቲት 2004 ዓም ገጽ 13
61 ሐሌፍ መጽሔት ቁ.1 ነሐሴ 1984 ዓም ገጽ 17

## ጋዜጦች

62 አቶ ዘውገ ገድሉ ሪፖርተር ጋዜጣ ሰኞ ሰኔ 8 ቀን 1990 ዓም ገጽ 16
63 ጠ.ሚ አቶ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵ ጋዜጣ መስከረም 24 ቀን 1993 ዓም ገጽ 17
64 በላይ እንዳለ ዓሥራት ጋዜጣ መጋቢት 23 ቀን 1992 ዓም ገጽ 8
65 እታገኝ መኮንን ካሣ ነገረ ኢትዮጵያ ጋዜጣ ግንቦት 15 ቀን 2006 ዓም ገጽ 4
66 ገናናው ጋዜጣ የካቲት 3 ቀን 1992 ዓም ገጽ 6

## መግለጫዎች

67 ጥቅምት 2/23/ 2007 ዓም በቅማንት ብሔረሰብ የማንነትና የራስ አስተዳደር ጥያቄን አስመልክቶ

## ደብዳቤዎች

68 ደጃዝማች ንጉሴ ወልደ ሚካኤል ሰኔ 2 ቀን 1848 ዓም ለፈረንሳይ
69 ደጃዝማች ንጉሴ ወልደ ሚካኤል ጥቅምት 22 ቀን 1851 ዓም ለፈረንሳይ
70 ጎንደር የሚኖሩ የቅማንት ተወላጆች ደብዳቤ ለእኔ የተላከ።
71 ጌታቸው ረዳ የወያኔ መስራቾች ስም ዝርዝር

## በድረ ገጽ

72 አቢይ አፈወርቅ ትርጉም ውክሊክ

73 ኢትዮጵያ ርፊው ድረገጽ
74 አረጋዊ በርሄ ጄኔራል ፃድቃን ጤዛዋ ማሌሊት
75 ሴቭ ዋልድባ ብሎግ ነጋ አንዳርጌ ሪበል ጎንደር
76 ሊቁ እጅጉና አዳነ አጣናው የወያኔን እብሪት እስከ መቼ እንሸከማለን?
77 ሙሉቀን ተስፋው የአማራና ቅማንት ጉዳይ
78 ሐራ ተዋሕዶ ጥር 1 ቀን 2007 ዓም

## በቴሌቭዥን

79 አቶ በየነ አስማረ ኢሳት ቴሌቭዥን
80 የየካቲት ውለታ ምድህት
81 የአዲስ አበባው ቴሌቭዥን የካቲት 11 ቀን 2007 ዓም
82 ዘራፍ የተባለ ተውኔት

## በሬዲዮን

83 አምባሳደር ዘመነ ካሴና አቶ በየነ አስማረ ኢሳት ሬዲዮን

## በስብሰባ የተነገረ

84 አቶ ገብሩ አስራት

## ከነሞረሾች ጋር ያደረኩት ውይይት

85 አቶ ሞረሽ የቅማንት ተወላጅ
86 አቶ ዘውገ ገድሉ ምን ይህ ብቻ በ1990 ዓም ብዙ ንብረት በአሰብ ወደብ
87 አቶ ስዩ አብርሃ ጥር 1988 ዓም
88 አቶ ሞረሽ የተሳቢው እስራኤል ነዋሪ
89 አቶ ሞረሽ "ነጋ ቀድሞ በአደባባይ ስለወጣ እንጅ ሌሎች ብዙ ብዙ አሉ"
90 አቶ ሞረሽ "ቀኑ መስከር 27/2004 ዓም ይመስለኛል"

**ከዚህ በታች ያለች ግጥም የአያናዝጊ ጹሁፈ. ናት:: አያናዝጊ ተዋናይ ታማኝ በየነን ይወዳሉ:: ስለ እርሳቸውና ስለ ሌሎች የሞያ ባልንጀሮቻቸው አድንቀው የገጠሟት ናት::**

# ታማኝ ልጅ ወለደ!

**እልል እልል ታማኝ ልጅ ወለዴ እሰይ የምስራች**
**ሁለት ሴት ልጆች**
**ልክ እንዳባታቸው እውነቱን ተናግረው ከመሸ አዳሪዎች**
**አባታቸው ዛብጥያ የማይፈራ**
**ነዋይ ያላጠቃው ለማተቡ ኩሩ**
**ልጆቹም እንደዝያው ገና ከጅምሩ**
**ጥሩውን፤በጥሩ፤ብሶቱን ጥፋቱን ግፍና በደሉን ሁሉን ተናገሩ**
**አልፈሩ አላፈሩ**
**ክፉ ነገሩ ግን ቁናው ስለሞላ እጅግ አመረሩ**
**በንግግር ማህል ሲቃ እየያዛቸው እንባ እየቋጠሩ::**

አንዷ የብሶቷን የሕዝቧን መበደል የሕዝቧን መከፋት
በአፈሯ ለውሳ አፈር ጭቃ አቡክታ
እንደፈጣሪዋ እስትንሳፍ ሰጠውች በግጥሟ ቱማታ::
አንዷ በዚያው በሞያዋ ከመድረክ ላይ ወጥታ
ታዳሚ እጅ ነስታ ማማዋን ቃኝታ
ባለሥልጣኑንም ባለኮከቡንም ግራ ቀኝን አይታ

እናንት የእፍኝት ልጆች እንዳለው መጥምቁ
እሷም አለች ንቁ
ነውሩንም፤ሃጢአትንም፤ግፉንም ሁሉንም ግዜንም እወቁ
በዚህ ንግግሯ ከፊል ተሳለቁ ከፊል አደነቁ
ታማኝ አባታቸው ምንኛ ታደለ!
ምንኛ ይደሰት አጎምርቶ ሲያየው የዘራው አዝመራ ዘሩ እንደበቀለ::

እንዲህ ነው ካሳደጉ አይቀር ከወለዱ
ያስታውቃል ቡቃያው አፍላው ሆነ ግንዱ
በል ታማኝ በልጆችህ እወቅበት ተደሰት
አዜብ ጌታቸውን ስጣት አበልጅነት
ትሁን ለልጆችህ የጡት እናት
እናንተም ልጆቿ እወቋት
እሷም ደስ ይበላት
ሕዝብም እልል እልል ይበል በያለበት

በሁሉም አርከበ በር በዚህ ከቀጠለ
ተንሳኤው ቅርብ ነው እሩቅም አይደለ
ታበጽእ የሚለው ይባል ሀሴ ሉያ በመላው ኢትዮጵያ!
በመላው ኢትዮጵያ አያናዝጊ!

አማረ አፈለ ብሻው መልዕክት ሳጥን ቁጥር!
P.O.BOX 492 SEATTLE.WA 98111.
U.S.A.